2ኛ ዕትም



# የርኅሩኅ ፍቅር

ሙሉ በሙሉ እውነተኛ ታሪክ

በተክሉ ጥላሁን

የብዙዎችን ጉዳይ የሚፈትሽ፣ በቀላሉ የማይረሳ፣ አሳዛኝና ልብ ሰቃይ ...

# የጭን ቁስል

## ሙሉ በሙሉ እውነተኛ ታሪክ

በተክሉ ጥላሁን

የብዙዎችን ጓዳ የሚፈትሽ፣ በቀላሱ የማይደረሳ አሳዛኝና ልብ ሰቃይ ታሪክ

Scanned by CamScanner

1. የጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሴቶች በሙሉ፤

እና

2. ለውድ አያቴ እመ መንበረ አሥራት
መታሰቢያ ይሁንልኝ፤



Scanned by CamScanner

# እውነታ

የዚህ መፅሀፍ አብዛኛው መረጃ ከባለታሪኳ ሰናይት ብርሃኑ ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ከቅርብ ወዳጆቿና ዐምባ ከተሰኘው መፅሄት ከተሰባሰቡ መረጃዎች ተውጣጥቶ ተቀናብሮ የተዘጋጀ ነው።

አንዳንድ ገፀ-ባህሪያት በተለይም በበጎ ጎን ያልተገለፁትን በፈጠራ ስም የተካኋቸው ሲሆን በዚህ መፅሀፍ ውስጥ የተገለፁት ሀሳቦች ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ እንዲሁም ግለሰባዊ አመለካከቶች በሙሉ ከፀሃፊው የመነጩ አለመሆናቸውንና ባለታሪኳ ከራሷ የሕይወት ተሞክሮ በመነሳት የገለፀቻቸው መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

በመሆኑም ባለታሪኳ የመጨረሻውን የመፅሀፉን ረቂቅ አንብባ ሙሉ በሙሉ የራሷ እውነተኛ ታሪክ መሆኑን ገልፃ በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ፈርማበታለች።

ፀሐፊው

ተክሉ ጥላሁን



Scanned by CamScanner

ክፍል አንድ:- ዐምባ 13
ክፍለ ሁለት:- ውጥንቅጥ 89
ክፍል ሶስት:- ትዳር 165
ክፍል አራት:- ቡና ቤትና ከዚያም 249



Scanned by CamScanner

## የባስታሪኳ መልዕክት

ሁሌም አዕምሮዬ ውስጥ የሚመላለስ አንድ ነገር ነበር *ሰው ከስሜት ብቻ ነው ወይ የሚማረው?* የሚል ጥያቄ:: ታሪኬን የነገርኳቸው ብዙ ሰዎች ፊልም ሊሆን እንደሚችል ነገሩኝ:: ከዛ ጊዜ በኋላ በበኩሌ ላደርገው የሚገባኝን አስተዋፅኦ ፍለጋ ባዘንኩ:: የእኔን የውድቀት ታሪክ ለሌሎች ከማካፈል የዘለለ ነገር አልታየኝም::

ምናልባት ይሄ መፅሐፍ በሌሎች እህቶቼ ላይ የተፈፀሙ ጥቃቶችን ለአደባባይ ለማውጣት ምክንያት ይሆናል... ምናልባት ጥቂት ሰዎች የእኔን መሳይ ስህተት እንዳይፈፅሙ ይረዳቸዋል... ምናልባት ጥቂት ወንዶች በሴቶች ላይ የሚፈፅሙትን ጥቃት እንዲያቆሙ ይረዳ ይሆናል... ብዙ ምናልባቶች:: እናም የተጠራቀሙት ብዙ ምናልባቶች ይህን መፅሀፍ ወለዱ::

በተለይ ሴት እህቶቼ መፅሀፉን አንብባችሁ እንድታዝኑብኝ፣ አንገታችሁን ደፍታችሁ ከንፈራችሁን እየመጠጣችሁ እንድታለቅሱልኝና እንድታለቅሱብኝ፣ ጣታችሁን እንድትጠቁሙብኝ አልፈልግም:: ይልቅ ፈጠን በሉና ተማሩብኝ:: እኔ ማንነትን ፍለጋ ስጓዝ የደረሱብኝ ፈተናዎች



Scanned by CamScanner

ሁሉ በብዙ እህቶቼ ላይ የደረሱና የሚደርሱ ናቸው:: በህይወት ውስጥ የሚገጥሟችሁን መሰናክሎች በድል እንድታሸንፉ ነው ታሪኬን፣ ገበናዬን ለአደባባይ ማውጣቴ:: ዛሬ ላይ ሆኜ ከእናቴ ማህፀን ስወጣ ጀምሮ አንድ ሀይል ፅፎ ያዘጋጀውን ተውኔት እየወደቅኩና እየተነሳሁ መጫወት በመቻሌ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ::

መፅሀፉን እጅግ በሚገርም ልብ-ሰቀላና አስደናቂ አቀራረብ ፅፎ የእኔ ታሪክ እንዲህ አጓጊ ነው እንዴ? እስክል ድረስ በግርምት ውስጥ ለከተተኝ *ደራሲ ተከሉ ጥባሁን* የማመሰግንበት አንዳች ቃል እንደሌለኝ ለመግለፅ እወዳለሁ::

በችግሮቼ ሁሉ ከጎኔ በመሆን ብርታት ለሆነኝ አትላንታ ለሚኖረው *ሸዋንግዛው ተረፈ* እንዲሁም ታሪኬን በቅርበት በማወቅ ድጋፋቸው ላልተለየኝ *ቴዎድሮስ ኃብተማርያም፣ ቤተልሄም በቀለ* እና በችግሮቼ ሁሉ ድጋፋችሁ ብርታት ለሆነኝ ሁሉ ጥልቅ የሆነ ልባዊ ምስጋናዬን የምገልፅላችሁ እግዚአብሔር ሀሳባችሁን እንዲሞላላችሁ በመመኘት ነው::

ሰናይት ብርሃኑ



Scanned by CamScanner

# ቅድመ ታሪክ

ዜናውን ስንሰማ ሁላችንም ደነገጥን:: እኔ ግን መብረቅ የመቱኝ ያህል ቀጥ፣ ሰጥ ብዬ ነበር የደረቅኩት:: ሰው ድንገት ቤት ንብረትህን፣ ዘመድ አዝማድህን አለፍ ሲልም ራስህን ጥለህ በማታውቃት ባዕድ ዓለም ላይ ብቻህን ትተዋለህ ቢባል የሚሰማው ስሜት ምን ሊሆን ይችላል? ከየት እንደመጣሁ የማላውቀው አንሶ... ወደ መጣሽበት ተመለሺ... ዐምባው ከዚህ በኋላ ሊያስተናግድሽ አይፈልግም... ስባል እንዴት መብረቅ የመታኝ ያህል አልደነግጥ?

ያኔ ነው *በሽንቅርት ባደ ጅሮ ደገፉ* የሚለው ብሂል የገባኝ:: ከእናትና አባቴ አልፎ ለስም እንኳን የሁለትና ሶስት ቤት ዘመዴን የማላውቅና በውሸት አለም ውስጥ እየኖርኩ መሆኑ የተገለጠልኝ ወቅት ላይ ቢያንስ መንግስት እንኳን ቤተሰቤ ይሆናል ብዬ ልፅናናበት እንዳልችል ዐምባው ሊበተን መሆኑን ስሰማ እንዴት በእንቅርት ላይ... አይሆንብኝ?

ማንነቱን የማያውቅና ምን መሆን እንዳለበት ውሉ የጠፋው የእኔ አይነት ሰው እርግጠኛ ነኝ መጀመሪያ የሚያደርገው ማን መሆኑን ማወቅ ነው:: ማንነት ምን ከመሆን ይበልጣልና:: እኔም ያደረግኩት ይህንኑ ነበር:: ያሳደገኝ ህፃናት ዐምባ ስለእኔ ያለውን ፋይል እንዲያሳየኝ ጠይቄ ተፈቀደልኝ:: ፋይሉ የያዘው ግን ለማንነቴ እምብዛም ጠቀሜታ የሌላቸውን ትርኪምርኪ ነገሮች ነበር:: *ሕፃን ሙሉጎጃም ብርሀኑ ከቀጨኔ*

ህፃናት ማሳደጊያ መጣች ብሎ ስለምወዳቸው ነገሮችና ባህርያቶቼ ይዘረዝራል። ቢያንስ ከየት እንደመጣሁ የሚገልፅ ፍንጭ አለኝና እዛ ብሄድ እድል በቀኜ እንደምትጠብቀኝ አምኜ ገሰገስኩ።

ቀጨኔ ህፃናት ማሳደጊያ በረዣዥም ዛፎች በተከበበ ጊቢ ሴት ልጆች ብቻ የሚያድጉበት ቦታ ነው። እንደገባሁ ተሰብስበው ከቆሙት ሞግዚቶች አንዷ ትኩር ብላ ስታየኝ ቆየችና እየጮኸች "ልጄ... ራሷ ልጄ!" አለች። ወዴት እያመለከተች እንደሆነ ለማወቅ ስገላመጥ ከኔ ሌላ ማንም የለም። ደነገጥኩ። *ስንት ዓመት ስታመምበት የነበረው፣ ስንት ጊዜ ስሰቃይበት የነበረው እናትን መፈለግ ደሄን ያህል ቀላል ኖሯል?* ብዬ አሰብኩ። ይሁንና ለረዥም ዓመታት በስመ እናትና አባት የተሰጡኝ አሳዳጊዎች ወይ እንደልጃቸው አልተቀበሉኝ ወይ ቤተሰቦቼን ቀደም ብዬ እንዳፈላልግ በቂ ፍንጭ አልሰጡኝ... *እነሱ ናቸው... ህይወቴን የጭን ቁስል ያደረጉት እነሱ ናቸው!!* በዚህ ሰዓት ስላለፈ ነገር ማሰቡ ትርጉም አልነበረውም። *እንኳን እናቴን ለገኘኋት* "እንዴ? አታዩም... አይኗን ተመልከቱ ራሷ ናት!" ስትል አጠገቧ ያሉት እንድትረጋጋ ሲያደርጓት አንድ ክፍል ውስጥ ሆና ታለቅስ ጀመር። አብረዋት ከነበሩት ሴቶች አንዷ "ስምሽ ማነው?" አለችኝ። ስሜን ስነግራት አንድ ክፍል ውስጥ ሆና የምታለቅሰው ሴትዮ "አላልኳችሁም?" ስትል ሮጣ መጥታ ተጠመጠመችብኝ።

ሰውነቴ ሲንቀጠቀጥ... የእናት ፍቅርን ማግኘት ልቤን ሲሰውረው... እንደገና ተምጦ የመወለድ ያህል ሀሴት ውስጥ ሲከተኝ ያለውን ስሜት ማጣጣሙ ራሱ ልዩ ህይወት ሆነልኝ። በስሜት ማዕበል ውስጥ እየተንሳፈፍኩ ቢሆንም የተጠመጠምኩባትን እናቴን መጠየቅ ያለብኝ አንድ ከንካኝ ጥያቄ ውስጤን ሠብሳት ሲጀምር ቀስ ብዬ አነሳሁት።

"እናቴ ነሽ እንዴ?"

ምክንያቱም እቅፏ ውስጥ ሆኜ አስብ የነበረው *እንዴት ከቀጨኒ ህፃናት ማሳደጊያ ወደ ዐምባው ሰላክ ዝም ትባለች? እዚሁ ለጠገቧ ለታሳድገኝ ትችል ለለነበር ወይ?* የሚለውን ጥያቄ ነበር::

"ውይ!" አለች ወ/ሮ መሰሉ- የተጠመጠምኩባት ሴት:: ረዘም ያለ ቁመት ያላት ብትሆንም ሞላ ባለው ሰውነቷ አማካይነት መካከለኛ ነው የምትመስለው:: የቀይ ዳማ ስትሆን ወገብ ላይ ያዝ በሚያደርግ ላስቲክ የተሰፋና ከታች ሽንሽን የሆነ ቀሚስ ከነጠላ ጋር ለብሳለች:: "ውይ! እናትሽ መጥታ አትጠይቅሽም እንዴ?" አለችኝ:: ደሜ በቅፅበት ሲንተከተክ ይታወቀኛል:: ብቻ ከእቅፏ ተመንጭቄ ወጥቼ ጥያት ወደ ማህደር ክፍሉ አመራሁ::

የማህደር ክፍሉን ሰራተኛ ፋይሌን ለማየት እንደምፈልግና እንዲተባበረኝ ስጠይቀው "ክልክል ነው" ሲል ደረቀብኝ:: ብዙ ታዳጊዎች የቤተሰቦቻቸውን ታሪክ ለማወቅ ፈልገው ፋይል ባዩ ጊዜ የታመሙ እንዳሉ ሰምቻለሁ:: መከልከሉም ከዚህ የተነሳ ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው:: አስታውሳለሁ አንድ ታዳጊ የቤተሰቦቿን ፋይል ስትመለከት ቤተሰቡ በሙሉ በእሳት አደጋ እንዳለቀና ሰዎች ተሯሩጠው እና ተቀባብለው ካዳኗት በኋላ ህፃናት ዐምባ መግባቷን አንብባ በመታመሟ ጳውሎስ ሆስፒታል ተኝታ ስትሰቃይ ከቆየች በኋላ ለሞት ተዳርጋለች:: እንዲህ ያሉ አስደንጋጭ ክስተቶች ስላሉ እንቢታው በመጠኑም ቢሆን ተቀባይነት ያለው ምክንያት ሊሆን ቢችልም ለእኔ ግን ያለውን ዕውነታ አውቆ መገላገሉ ትልቅ እረፍት ነበርና ልመናዬን ቀጠልኩበት::

"እባክህ? በኔ ቦታ ሆነህ እየው እስቲ... እናትና አባትህን፣ ዘር ማንዘርህን ሳታውቅ መኖር አይከብድህም?"

"እና ምን አድርግ ትይኛለሽ?"



ሞገስ

Scanned by CamScanner

"ፋይሌን አሳየኝ!"

"ክልክል ነው አልኩሽ'ኮ"

"እናስ? በቃ ማንነቴን ሳላውቅ ልሙት? ራሴን ሄጄ ላጥፋ? ምናለ ባንተ ላይ የሆነ ያህል ብታስበው? ቀናነቱ ካለህ'ኮ ምንም ማለት አይደለም:: እባክህ... በፈጠረህ አምላክ?" ላለቅስ ደረስኩ::

ፊቴን በትኩረት አጠናውና "እሺ ለማንኛውም..." አለኝ::

ከልመናዬ ብዛት ተሰላችቶ ዐምባ ማደጌን የሚገልፅ ወረቀት ካመጣሁ ሊያሳየኝ እንደሚችል ነግሮኝ ወጣሁ:: ግቢውን ለቅቄ ከወጣሁና ዝዋይ ተመልሼ ከሄድኩ በኋላ ግን ለምን ወ/ሮ መስሉን *እናትሽ መጥታ ስትጠይቅሽም እንዴ?* ብላ የጠየቀችኝ ጥያቄ ላይ ትኩረት አድርጌ ስለ እናቴ የምታውቀው ነገር ካለ እንዳልጠየቅኳት አስቤ ተበሳጨሁ:: ከዐምባው የተፃፈልኝን ወረቀት ይዤ ስመለስ ግን ሁለት ተስፋ ይዤ ነበር::

እንደገባሁ ወ/ሮ መስሉ ከስራ ውጪ መሆኗን ሰምቼ አንደኛውን ተስፋዬን ውሃ እንደበላው በማሰብ በተለይ ተመዝግቦ ያለውን መረጃ ለማየት እንደጓጓሁ ወደ ማህደር ክፍሉ አመራሁ::

የተሰጠኝን ፋይል እጄ ላይ ሳደርገው የዓለምን ምስጢር ሁሉ ገልጬ የምመለከትበት ያህል ነበር የተሰማኝ:: *ስሁን ከፍቼ በማይበተ ቀፅበተ ከዮተ እንደመጣሁና ማን እንደሆንኩ ስውቃስሁ* ስል አሰብኩና በፈገግታ ተሞልቼ ከፈትኩት:: አራት ጥቁር ያለ የህፃን ልጅ ፎቶ ተደርድሯል- የእኔው ነው:: ፋይሉ ላይ የተፃፈውን ደጋግሜ እያነበብኩ ፊቴ እንደ ጥቁር ዳመና ይጋገር ጀመር:: ፋይሉ ላይ የሰፈረው እንዲህ የሚል ነበር:-

*ህፃን ሰናይት ከፎቶዋ በቀር ማስረጃ የላትም!!*

# ክፍል አንድ

# ዐምባ



Scanned by CamScanner

# -1-

በሁለት ሺ አራት መቶ ሄክታር (105 ጋሻ) መሬት ላይ ከአብያታ ሐይቅ፣ ከሌንጫ ተራራና ከሻላ ሐይቅ በስተምዕራብ የአላባን ተራራ ተንተርሶ፣ ከዚሁ ተራራ መንጭቶ በስተሰሜንና በስተምስራቅ እያካለለው ወደ ደቡብ ዞሮ ሻላ ሐይቅ በሚገባው በጂዶ ወንዝ የታጠረው *ሀምባ* የአርሲን ሐይቆችና ቡታጅራን እንዲሁም የሶዶን ተራሮች ማማተር በሚቻልበት *ሥፍራ* ላይ እንደ አረንጓዴ ስጋጃ ተነጥፎ ይገኛል- የቀድሞው የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሕፃናት ዐምባ የአሁኑ አላጌ ግብርና ቴክኒክ እና *ሙያ* ኮሌጅ::

*ሀም-ባ* በቁሙ ሲታይ ሕዝብ ያለበት የሚለውን ፍቺ ይይዛል:: ይኸውም *ሀም* በዕብራይስጥ ሕዝብ ሲሆን *ባ* በግዕዝ *ያለበት* ማለት ነው:: በሌላ ትርጉሙ ደግሞ ሰው ቀድሞ ለመንደር የሚመርጠው ተራራማ ስፍራን ስለነበር ተራራ የሚለውን ትርጓሜ እንደሚይዝ የደስታ ተክለወልድ መዝገበ *ቃላት* ያስነብባል::

የቀድሞ ሰዎች እነዚህን ከፍተኛ *ሥፍራዎች* ይመርጡ የነበረው ራሳቸውን ከወራሪ ጠላት ለመከላከል አመቺ ሆኖ ስለሚያገኙት ነበር:: በተራራ ላይ የሚገኙ የሕዝብ መኖሪያዎች ወይም መንደሮች

ለማስተዳደር የሚሾመው ሰውም *ሀምባ ራስ* በኋላም *ባለ ሀምባ ራስ* ተብሎ ሲጠራ ኖሯል::

እንዲያውም ዐምባ በግዕዝ *ሀገር* ይባላል:: ምናልባትም ይህ የሆነው ለተራራው የቀድሞ ሰው ሀገሩ ያቺው የሚኖርባት ዐምባ ሆና ስለምትታየውና ከዚያ ከሚታየው አድማስ አልፎ ያለውን ያገር ክፍል ካገሩ አይቆጥር ስለነበር ይመስለኛል::

ቀድሞ አንድ አካባቢ ለመኖሪያ የሚመረጥበት አንድ ትልቅ መለኪያ ጠላትን ለመከላከል በተፈጥሮ የምሽግነት ጠባይ፣ *ገዥ* መሬትነት ያለው ስለነበር የዐምባ የመጀመሪያ ትርጉም ተራራ ወይም በተራራማ ሥፍራ የሚገኙ መንደሮች መሆኑ አያስደንቅም::

እርግጥ በስተኋላ ደገኞች ኢትዮጵያውያንም በረባዳ፣ በሸለቆና በሜዳ የሰሯቸው መንደሮች ዐምባ መባላቸው አልቀረምና ዛሬ ዐምባ መንደር ወይም የመንደሮች የወል ስም ሆኖ ይገኛል::

በመሬት ጥናት ሊቃውንት እንደሚነገረው የአብያታ፣ የሻላ፣ የላንጋኖና የዝዋይ ሐይቆች በአንድ ወቅት አንድ ሰፊ ሐይቅ በነበሩበት ጊዜ ደሴት የነበሩበት ቦታዎች ዛሬ አልፎ አልፎ የሚታዩ የአላጌና የአካባቢዋ ኮረብቶች ሆነው ይገኛሉ:: ረጅም ዕድሜ ያላቸው የግራር፣ የሾላና የዋርካ ዛፎች ዐምባውን ተጨማሪ ውበት አጎናፅፈውታል:: በጂዶ ወንዝ ረግረጋማ ሸለቆዎች ለምለሙ ፊላ እጅብ ብሎ ይታያል::

ከአብያታና ከሻላ ሐይቅ እየመጡ በአላጌ ደን ውስጥ የሚንሸራሸሩትን



Scanned by CamScanner

የተለመደ ነው:: ክርክር፣ ልዩ፣ ልዩ አዕዋፍ ጣዕመ ዜማ መስማት የተለመደ ነው:: ክርክር፣ ቀበሮ፣ ጥንቸል፣ አነር፣ አቦሸማኔ፣ አጋዘን፣ ሽለምጥማጥና ሌሎችም አራዊቶች ቀኑ በታውን ለምሽት በሚለቅበት ወቅት ከየጫካው ይወጣሉ:: በጨለማ ጊዜም የመኪና ወይም የእጅ ባትሪ እያበራ የሚሄድ ተጓዥ ከተለያዩ የአራዊት ዐይኖች ጋር ይገጣጠማል:: እናም ዐምባውን አስደናቂ የሚያደርገው አራዊትና ሰዎች ሳይፈራሩ የሚኖሩበት ቦታ መሆኑ ጭምር ነው:: ሁሌም ታዲያ እኔን የሚያስገርመኝ ነገር ቢኖር የዐምባው በአጭር ጊዜ መመስረት ነው:: አጃኢብ ያሰኛል!

የመጀመሪያው የህፃናት ዐምባ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲቋቋም የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የነበረው ጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ በትዕዛዙ መሰረት ሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ትዕዛዙን በመቀበል አግባብነት ላላቸው የመንግስት ድርጅቶች መመሪያውን አስተላለፈና በተደረገው ጥናት በስምጥ ሸለቆ፣ በሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ በአላባ ቆሊቶ ወረዳ፣ ከአባያታና ከሻላ ሀይቆች ምዕራብ ወደ ሻላ ሐይቅ በሚገባ ጂዶ በተሰኘ ወንዝ በተከበበ አላጌ በተባለ በደን የተሸፈነ ኮረብታ መያያዣ ላይ የአጥኚው ቡድን ዐይን ዐረፈ::

ቦታውን ተዘዋውሮ ያየው ጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም በሰጠው መመሪያ መሰረት አራት ሺ የሚደርሱ ባለሙያዎችና ሰራተኞች ለስራው ተሰማሩ::

የዐምባው የኮንስትራክሽን ሥራ ከአዲስ አበባ- ሻሸመኔ በሚወስደው

አውራ ጎዳና በ185 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘው ከቡልቡላ ከተማ ወደ ሚቶ የሚያመራውን የበጋ መንገድ፤ ክረምት ከበጋ በሚያገለግልበት መልክ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ትራክተሮችና ቡልዶዘሮች... በመጥረግና በመደልደል ጀመሩት:: ይህም ተጠርጎና በተሻሻለ መልክ ተሠርቶ እንዳበቃ ለዐምባው ሥራ ወደተመረጠው ሥፍራ... ወደ አላጌ የሚገነጠለው 5 ኪሎ ሜትር መንገድ ሥራ ቀጠለ:: በዚህ መንገድ ሥራ ከምንጣሮ ሌላ የጂዶን ወንዝ የሚያቋርጥ 25 ሜትር ድልድይ ተሠራ:: ይህ ድልድይ አላጌን ሐፍረተ ስበቷን፣ ድንግል መሬትነቷን፣ ክብረልማቷን፣ ብብቷን ከፍታ የሕፃናት ጎፃን-- የሕፃናት አቃፊ ብብትና ማጎፀን እንድትሆን አደረጋት:: ከመመረጥና ከመታጨት አልፋ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም አህጉር የመጀመሪያው አዲስ ዓይነት ዐምባ ለመሆን የሚያበቃትን ሁሉ ለመቀበል በሯን ወለል አድርጋ ከፈተች::

የዐምባው ፕሮጀክት አፈፃፀም ጥናት ከመንገዱ ሥራ ጎን በጥቂት ወራት ውስጥ ተከናወነ:: የዘማቹ ባለሙያና ሠራተኛ ድንኳን መንገድ ጠራጊውን ትራክተርና ቡልዶዘር እየተከተለ በደጀንነት ወደ አላጌ ተጠጋ:: ጂዶን ተሻግሮ አላጌን አስገብሮ ጥርብ ድንጋይ፣ ኖራ፣ ሲሚንቶ፣ አሸዋ፣ ቆርቆሮ፣ ምስማርና ሌላውም ለሕንፃ ሥራ አስፈላጊ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ መሣሪያ ወደዚያ ይጋዝ ጀመር:: ለሕንፃዎች ግንባታ 600 ሄክታር (15 ጋሻ)፣ ለእርሻ 1ሺ ሄክታር (25 ጋሻ)፣ ለአትክልት፣ ለፍራፍሬና ለመስኖ 600 ሄክታር (15 ጋሻ)፣ ለሰው ሠራሽ ወይም ለአፈር ግድብ ለውስጥ መጋቢ መንገዶችና ለደን ልማት 1ሺ 200



Scanned by CamScanner

ሄክታር (30 ጋሻ) መሬት ተከለለ፣ ተቀየሰ፣ ተሸነሸነ:: ከልደት እስከ 6 ዓመት ዕድሜ ላላቸው 1ሺ 300 ጨቅላ ሕፃናት ሁለት መንደሮች ከ7 ዓመት እስከ 14 ዓመት ለሚሆናቸው 3ሺ 750 አዳጊ ሕፃናት እያንዳንዳቸው 1ሺ 250 ሕፃናት የሚይዙ ሦስት መንደሮች ለመሥራት ታቀደ::

በዕቅዱ መሠረት የታነፁ ሦስት መንደሮች እያንዳንዳቸው ሁለገብ አዳራሽ፣ የመኝታ ህንፃዎች፣ የእናቶችና አባቶች (ሞግዚቶች) መኝታ ክፍሎች፣ የልብስ ማጠቢያ ክፍሎች፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ የትምህርት ቤት ሕንፃዎች፣ ዘመናዊ የንብ ርቢ ጣቢያዎች፣ የዶሮ ርቢ ጣቢያዎች፣ በመስኖ የሚለሙ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎች፣ የየመንደሩ አስተዳዳሪና የሌሎችም የመንደሩ አባላት ቢሮዎች ወዘተ በተፋፋመው የ16 ወራት ዘመቻ ተሠርተውና ተዘጋጅተው ለአገልግሎት በቁ:: ሕፃናቱ በተግባር እየተሳተፉ የሚማሩባቸው ሌሎች ቦታዎችም ተጠናቀቁ:: በበጋው ወራት ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ከጂዶ ወንዝ በመጥለፍ አንድ 700 ሺ ሜትር ኩብ የሚይዝ 20 ሄክታር ኩሬና ወደ ወንዙ የሚገባ የዝናብ ውሃ በመጥለፍ የአፈር ግድቦች ተሰሩ:: የሕፃናቱን የወተት ፍጆታ ለማሟላት የወተት ላም ርቢ ጣቢያ ተቋቋመ:: አንድ የ2ሺ 500 አሳማ ርቢ ጣቢያ ተጠናቀቀ:: ለዐምባው የተማከለ የመሰረተ ልማት አገልግሎት በዚሁ አጭር ጊዜ ውስጥ ተዘረጋ:: አምስቱ መንደሮች እርስ በርሳቸውና ከልዩ ልዩ የልማት ተቋሞች፣ የጠቅላላ አገልግሎትና ከሌሎች ጋር የሚያገናኝ ሃያ ሦስት ኪሎ ሜትር የውስጥ መንገድ ተዘረጋ::



Scanned by CamScanner

በሌላ በኩልም በዚሁ የ16 ወራት ዘመቻ የሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሙያዎች ለሕፃናቱና ለሠራተኛው ሁለት ክሊኒኮች፣ ለዐምባው ሕብረተሰብ የሚያገለግሉ የማዕከላዊ አስተዳደር ቢሮዎች፣ የችርቻሮ ሱቅ፣ የእንግዳ ማረፊያ ቤቶች፣ የሰራተኞች መኖሪያ ቁጠባ ቤቶች፣ የዕደ-ጥበባት ማዕከልና የቤንዚን ማደያ ሠርተው አስረከቡ:: የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ባለሙያዎችም 60 ኪሎሜትር የኤሌክትሪክ መሥመር ከአዳሚ ቱሉ ወደ ዐምባው ከመዘርጋታቸውም በላይ 14 ኪሎ ሜትር የውስጥ ማሠራጫ ዘረጉ:: የመሠረተ ልማቱ ሥራ በዚህ አላበቃም የውሀ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ባለሙያዎችም የዐምባውን ኅብረተሰብ የውሃ ፍላጎት ለማሟላት ስድስት የውሃ ጉድጓዶች አስቆፈሩ:: የምንጭ ውሃ ከ8 ኪሎ ሜትር ርቀት ወደ ዐምባው የሚስብና በየመንደሩም የሚያሠራጭ 14 ኪሎ ሜትር የውሀ ቧንቧ መሥመር ዘረጉ:: እያንዳንዳቸው 100 ሺ ሊትር የሚይዙ ሁለት የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖችም ተከሉ:: የውሀ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ባለሙያዎች ከዚህም በተረፈ በክረምት ወራት የጂዶ ወንዝ ሞልቶ ሲጎርፍ ወደ ዐምባው ሰብሮ እንዳይገባ መከላከያ 4 ኪሎ ሜትር የአፈር ክትር ከተሩ::

በአጭር ጊዜ መጠናቀቁና ትልቅነቱን በተመለከተ የሚወራው እንዳለ ሆኖ ግና ህፃናት ወደ ተቋሙ ተወስደው ቢያድጉ ከቤተሰባቸውና ከማህበረሰቡ በመለየታቸው ምክንያት ሊደርስባቸው ስለሚችለው ተፅዕኖ ባለሙያዎች ሲያቀርቡ የምሰማው አስተያየት እውነትም በወቅቱ በውል የተጤነ እንዳልሆነ ይሰማኛል:: አሁን ሳስበው ያኔ ተቋሙን ለመገንባት የነበረው ሩጫ እነዚህን ጉዳዮች በጥልቀት ለማጤን ባለማስቻሉ እኛ



Scanned by CamScanner

በዐምባው በነበርንበት ጊዜ እንኳን ለምንፈጥራቸው ችግሮች ሁሉ እስተዋፅኦ ያደረገ ይመስለኛል::

እኔም በግዙፍነቱ ብዙ በሚወራለት ዐምባ ውስጥ የገባሁት ነፍስ ሳላውቅ ነበር...

***

መጀመሪያ ወደ ዐምባው የገባሁት እራስ ሆኜ ነው:: እምባው መጠንከር እንዳለብኝ በማመኑ ወደላከኝ ቀጨኔ ህፃናት ማሳደጊያ ይመልሰኛል:: እዛም ለአስር ታዳጊ ህፃናት አንድ ሞግዚት ነበር የሚመደበው:: እና የኔ ሞግዚት ወ/ሮ መሰሉ የምትባል መሀን ሴትዮ ነበረች:: ስለማንነቴ ለማጣራት ስሄድ "ልጄ... ራሷ ልጄ!" ብላ የተጠመጠመችብኝና "እናትሽ መጥታ አትጠይቅሽም ወይ?" ብላ ስትለኝ ገፍቼያት ከሄድኩ በኋላ ተመልሼ ስሄድ ባላገኛትም ከረዥም ጊዜያት በኋላ ነፍሱን ይማርና አለባቸው ተካ ያለብኝን ጭንቀትና ስቃይ ስለሚያውቅ ቤተሰቦቼን በማፈላለጉ ላይ እሱም ተጨመረበትና ወ/ሮ መሰሉን ሲጠይቃት የምታውቀውን ነገረችው::

ወ/ሮ መሰሉ ሞግዚቴ ከመሆኗም በላይ የራሷ ልጅ አድርጋ ልታሳድገኝ ትሻ ነበር:: ያኔም ለክትባት ይዛኝ ስትሄድ ስሜን አታውቀውም ነበር:: ስትጠየቅም ሙሉ ጎጃም ብርሀኑ ብላ ታስመዘግበኛለች:: የአባቴን ስም በባሏ ስም፣ የአያቴን ስም ደግሞ በባሏ ወንድም ስም ነው ያደረገችው:: እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ የእኔ ትልቅ ተስፋ የነበረው በአባቴ ስም ማን



Scanned by CamScanner

መሆኔን አፈላልጋለሁ የሚል ነበር:: ከስሜም በመነሳት ጎጃሜ ነኝ እል ነበር:: አለባቸው ተካ ከወ/ሮ መሰሉ ጋር በስልክ የተነጋገሩትን ይህን ዕውነታ ከነገረኝና ፋይሌ ላይ *ህፃን ሰናይት ከፎቶዋ በቀር ማስረጃ የላትም!!* የሚለውን ካየሁ በኋላ ተስፋዬ ሁሉ ተሟጠጠ:: አንዳንዴ እንዲያውም *ስንደሳር ከመሬት በቅዩ ተገኝሁ ይሆን?* ስል አስባለሁ:: ይሄን እንዳላምን ደግሞ ወ/ሮ መሰሉ እናቷ ወደ ዐምባው ከመሄዷ በፊት ተደብቃ እየመጣች ታያት ነበር ብላ ለአለባቸው ነግራዋለች:: ማን ትሁን፣ ምን ትሁን ትክክለኛ እናቴም ትሁን አትሁን የምታውቀው ነገር ያላት አይመስለኝም:: ይሄንን እንኳን አጥርቼ እንዳላውቅ ከአለቤ ጋር በስልክ ሲያወሩ ከገለፀችለት ነገር በላይ የምታውቀው ነገር እንደሌለና ለማንኛ ውም ቤቷ ብቅ ብሎ ለመጨዋወት ቀጠሮ ይዘው በዕለቱ ሲሄድ የደረሰው ወ/ሮ መሰሉ ስልስት ላይ ነበር::

ሶስት ዓመት ሲሞላኝ ወደ ዐምባው እንድመለስ ተደረግኩ:: ጥቅምት 16 ቀን 1977 ዓ.ም ገባች ነው የሚለው:: ዐምባ ስንገባ ራሳቸው የሚሞሉልን ጊዜ ልክ እንደ ዕድሜያችን ይቆጠርና ልደት የምናከብረውም በገባንበት ቀን ነው:: በተለይ ቤተሰብ መጥቶ የማይጠይቀንን እንዳይሰማንም በማለት ይመስለኛል ለልደታችን ከረሜላ ተገዝቶልን ሽርሽር ተወስደን እንክብካቤ ይደረግልናል:: ያኔም ሞቅ፣ ደመቅ ባለ የደስታ ባህር እንንሳፈፋለን::

ወደ ዐምባው ስገባ መጀመሪያ መስከረም ሁለት የሚባለው መንደር ነው የገባሁት:: *መስከረም ሁለት* እና *ሰብለ ሰብዮት* ተብለው የሚጠሩት መንደሮች የቅድመ መደበኛ ትምህርት መንደሮች ናቸው:: እንዲያውም በተለምዶ

ሁለቱም መንደሮች በአንድነት *ሰብሰ-መስከረም* የሚባሉበትም ጊዜ አለ:: መንደሮቹ ተመሳሳይ ቅርፅና ይዘት ያላቸው ሲሆን እያንዳንዱ የቅድመ መደበኛ ትምህርት መንደር 650 ህፃናት፣ ከ40-41 ሕፃናት በአንድ ክፍል በመያዝ የመኝታና የትምህርት (ትምህርታዊ ጨዋታ) አገልግሎት የሚሰጡ ህንፃዎች አሉት:: መንደሮቹ በአንድ ጊዜ ከ300-400 ህፃናት ማስተናገድ የሚችሉ የምግብ አዳራሾች፣ የቀለብ ፍጆታ የሚከማችባቸው መጋዘኖችም ያሉት ነው:: እንግዲህ ከነዚህ መንደሮች ባንዱ መስከረም ሁለት መንደር ነው ፊደል መቁጠር የጀመርኩት::

አሁን ያለውን የአንድ ሀብታም ግለሰብ ልጅ አያያዝ ከዐምባው ጋር ሳነፃፅረው የዐምባው ይበልጣል:: ስለምንም ነገር አናስብም ነበር:: *እናቴ ማናት? ሰባቴ ማነው? ሰምን ሰጠገቤ የሉም?* የሚባል ነገር የለም:: ጠዋት ስንነሳ ሞግዚቶች ፊታችንን አጥበው፣ ክሬም ቀብተው ወደ ምግብ ቤት አድርሰውን፣ ስንጨርስም መልሰውን ነው... መጫወት፣ መዋኘት የፈለግን እንደሆነ እንክብካቤ ተደርጎልን ነው... ሽንት ቤት ስንገባ እንኳን ሶፍት በእጃችን አንቆርጥም- ተቆርጦ ተሰጥቶን ነው:: ይሄ ጎደለብን ብለን የምናስበው አንዳች ነገር የለም::

ከዚህ የተነሳም ብቻ ሳይሆን በወቅቱ ወደ ውጭ የመውጣት እድልም ያለው በዐምባው በኩል ስለነበርና እንደ አዳሪ ትምህርት ቤትም ስለሚቆጠር ይመስለኛል ቤተሰብ ልጆቹን ለምኖ ነበር ዐምባ የሚያስገባው:: አስታውሳለሁ ከባለስልጣን ዘመድ ልጆችም ዐምባ የሚኖሩ ነበሩ:: እናም ሁላችንም እናትና አባት ነበረን:: ምኑንም ስለማናውቀው በስጋ የወለዱን ይሁኑ አይሁኑ አንጠይቅም:: ክረምት

ላይ ቤተሰቦቻችን ይመጡና ይወስዱናል:: ምናልባትም በደንብ ነፍስ እያወቅን እስከሄድንበት ጊዜ ድረስ አዳሪ ትምህርት ቤት እንዳለን እንጂ የማደጎ ልጆች መሆናችንን አናውቅም::

ለእኔም ዙሪያሽወርቅ ጣሰው የምትባል እናት ነበረችኝ:: ብዙ ግራ ሊያጋቡ የሚችሉ ቤተሰባዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም እንኳን ያኔ ልብ ብዬ በነገሩ ላይ የምጨነቅበት ሁኔታ አልነበረም:: ያለኝ መታወቂያም ላይ የወላጅ ተጠሪ ስም *ዙሪያሽወርቅ ጣሰው* ይላል:: ክፍለ ሀገር- *ሸዋ ሰሡሬጃ የረርና ከረዮ፣* ወረዳ... *ናዝሬተ፣* ከፍተኛ *3፣* ቀበሌ *15፣* የቤት ቁጥር.... ስልክ ቁጥር... የሚል መታወቂያ ወረቀት አለኝ:: ታዲያ ምን ቁርጥ አድርጎኝ ቤተሰብ እንደሌለኝ ማሰብ እችላለሁ? በወቅቱ እረፍቱን ምክንያት አድርጌ ወደ ቤተሰቦቼ ዘንድ የሄድኩ እንደሆነ ተንከባክበው ነበር የሚይዙኝ:: ከስንት አንድ ጊዜ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱኝ ነገሮች ብልጭ ቢሉም ልጅነቴ ላይ ላዩን ብቻ እንድመለከተው ነበር ያደረገኝ:: እነዛ ጥርጣሬ የሚፈነጥቁ ሀሳቦች ተሰባስበው እንደድማሚት እስከፈነዱበት አንድ አሳዛኝ ቀን ድረስ እናትና አባት ያለኝ ሰው ነበርኩ::



Scanned by CamScanner

# -2-

ዐምባ በገባሁ በአመቴ "ይህች ልጅ ቀልጣፋ ትመስላለች" ተባለና ወደ ኦጋዴን መንደር ተዛውሬ አንደኛ ክፍል ትምህርት ጀመርኩ:: ዘርዓይ ድረስና ኦጋዴን መንደር ከ1-8ኛ ክፍል ትምህርት የምንወስድበት ነው:: ኦጋዴን መንደር ገብቼ ትምህርት መማር ብጀምርም በትምህርቴ ያን ያህል ጎበዝ አልነበርኩም:: ትምህርት እጠላ ነበር:: በዛ ላይ በጣም ስለምታመም ብዙ ጊዜ የመምህራኖችና የብሎክ ሀላፊዎች መወያያ እሆናለሁ::

"ይህች ልጅ የስለት ልጅ ትሆን እንዴ?" አንዱ መምህሬ::

"እእ! ሰላሳ ጊዜ ትታመማለች አይደል?" ሌላኛው::

"እረ እንደው ጣጣዋ በዝቷል" ከብሎክ ሀላፊዎች አንዱ::

"ምን'ኮ የማያማት ነገር የለም:: እኔ እስከማውቀው ድረስ የስለት ልጆች ናቸው ጣጣ የሚያበዙት:: ከዛ ተነስቼ'ኮ ነው ትሆን ወይ ያልኩት" የመጀመሪያው መምህር::

"እረ ባክህ..." የብሎክ ሀላፊው:: "እረ ባክህ የስለት ልጅ ብትሆን ኖሮ



Scanned by CamScanner

እናቷ ወልዳ አትጥላትም..."

*ለናቷ ወለዳ ለተጥላትም?* ስለ እኔ እንደሚያወሩ ገብቶኛል:: *ግን የእኔ ለናት ወለዳ ጥላኛለች ለንዴ? ለለጣለችኝም:: በየክረምቱ ሁሉ ለሄድና ለጠይቃታለሁ ለይደለ?* አንደኛ እኔ ልጅ ነኝ፣ ሁለተኛ ዙሪያሽወርቅ የምትባል እናት አለችኝ፤ በዚያ ላይ የስለት ልጅ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም:: የሚባለውን አዕምሮዬ ውስጥ መዝግቤ ከማስቀመጥ በዘለለ ለራሴ ያቀረብኩት ጥያቄ አልነበረም::

በትምህርቴ ጎበዝ አልሁን እንጂ ጥሩ የመያዝ ችሎታ እንዳለኝ ይመሰክርልኛል:: ይሁንና በትምህርት ገበታ ከምገኝበት ቀናት ባልተናነሰ በህመምና በጣጣ የማሳልፈውም ጊዜ ያንኑ ያህል ነው:: "ጭንቀት አለባት" ይላሉ ስለኔ ሲያወሩ:: *ምንድነው የሚያስጨንቀኝ?* እኔን ለጭንቀትና ህመም የዳረገኝ የማላውቀው አንዳች ምክንያት አለ ማለት ነው? አለበለዚያማ ስለሚያስጨንቀኝ ነገር እውቀት ሊኖረኝ በተገባ ነበር:: ብቻ ግን እግሬ ስለሚቆስልና የተለያዩ ከጭንቀት ጋር የተያያዙ በሽታዎች ስለሚጎበኙኝ ሽርሽር እንኳን ከተማሪዎች ጋር ስንሄድ ያማታል እየተባልኩ በአምቡላንስ ነው የምሄደው:: የምመገበው ከሌሎቹ የተለየ ያውም ቢሮ ውስጥ ለብቻዬ ተቆልፎብኝና እየተደበደብኩ ነው::

ምሳችንን ከበላን በኋላ ሁልጊዜ የቀን እንቅልፍ አለን:: ደወል ሲደወል ያኔ በቀጥታ አልጋችን ላይ መገኘት አለብን:: እንዳናወራም አንደኛችን በግርጌ ሌላኛችን በራስጌ ሆነን በደረታችን ነው የምንተኛው:: ብንገላበጥ እንኳ አልጋችን ብረቱ ፍርግርግ ስለሆነ ይጮህል:: ያኔም ተቆጣጣሪዎች

መጥተው ይገርፉናል:: እኔ ደግሞ እንቅልፍ ስለሌለኝ ተኙ የሚለው ደወል ሲሰማ ወደ ጫካው ውስጥ፣ ቆሻሻ መጣያ ቦታ ምናምን ሰወር ብዬ አምፖል ካገኘሁ እሱን በመያዝ ስለ ፋኖስ በሰማሁት ተረት መሰረት "አንተ ፋኖስ እኔና ቤተሰቦቼን ጠብቅ፣ አስማተኛው ፋኖስ እኔና ጓደኞቼን ጥሩ ቤት አኑረን፣ ቤተሰቦቼን ለመርዳት አብቃኝ" እያልኩ ፋኖሱ ተዐምር እንዲፈጥርልኝ እለምነዋለሁ:: ስጨርስም ሁሉም ተማሪዎች ከእንቅልፋቸው የሚነቁበትን ጊዜ ገምቼ እመለሳለሁ:: ከሞግዚቶቻችን አንዷ ታገኘኝና:-

"የት ሄደሽ ነው አንቺ?" ብላ ትጮህብኛለች::

"እ...ኔ.... እንቅልፍ እንቢ ብሎኝ..."

"እኮ ምናባሽ ቢቆርጥሽ?" ወዲያው መገረፍ እጀምራለሁ:: አባባ ከበደ አልማዝ በምትባለው አለንጋ አንድ ሁለት ጊዜ ሸንቆጥ ሲያረጉኝ ውስጤ ስፍስፍ ይላል::

"ነግሬሻለሁ ሙሉጎጃም... ይሄ ብቸኝነት መውደድ፣ አልመገብም ማለትና እዛ ቆሻሻ ቦታ መሄድ ቢቀርብሽ ይሻላል::"

ዝም ብዬ አለቅሳለሁ::

"ሰምተሸኛል የምልሽን?" አዎ ስል ራሴን እነቀንቃለሁ:: ሁሌ የሆነ ጥፋት ስሰራ ወይ ሞግዚቶች፣ ወይ የብሎክ ሀላፊዎች አልያም ባለ አልማዝ አለንጋዋ ባለቤት አባባ ከበደ ያገኙኛል::

"ይህቺ ልጅ ምን ይሻላታል?" ይላሉ ትንሽ ከሌሎቹ ልጆች ለየት ስላለ ባህርዬ ሲያወሩ:: የሆነ ብቸኝነት መውደዴ፣ ጭንቀታምና ታማሚ መሆኔ የምን ምልክት እንደሆነ ባይገባኝም የእኔ እጣ ፈንታ ይመስል ሙጥኝ ብለውብኝ ነው ያሳደጉኝ::

***

ኦጋዴን መንደር እያለሁ የተነሳው አመፅ ከምወደው አባቴ ጋር እንድተዋወቅ ያደረገኝ ይመስለኛል:: አንዳንዴ ግን *ለባቴን የሚመስለኝ እንደኔ ጠቆር ለባለ ይሆን?* ብዬ አስባለሁ:: ጠቆር ያሉ ሰዎችን ባየሁ ቁጥር የመበርገግ መንፈሱ የተፈጠረብኝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን አይቀርም- አባቴ ኮሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያምን ካየሁ::

አመፁ ፓስታው ስጎ የለውም በሚል ነው የተነሳው:: በተለይ እኔ ፓስታው ለምን የስጋ ስጎ እንደማይኖረው በደንብ አውቃለሁ:: ተማሪው አመፅ የቀሰቀሰው ጥርጣሬ ስላለው ይመስለኛል:: የኛ ኦጋዴን መንደር ደግሞ *እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲሁም ጤዛ ነሽ* እንዲሉ በረባሽነቱ ቁጥር አንድ ስለነበር ይፈራል::

ምግብ ቤት ውስጥ እያለን አንዱ ተማሪ ሹካውን ከሳህኑ ጋር አጋጨው "ቋ!" አለ:: ወዲያው ደጋግሞ "ቋ! ቋ! ቋ!" አደረገው:: አጠገቡ ያሉትም በተለይ ወንዶቹ ተቀብለው አስተጋቡለት:: "ቋ! ቋ! ቋ!" ቀስ እያለ በምግብ ቤቱ ውስጥ ያለነው በሙሉ ሹካችንን ከማይካ ሳህኑ ጋር ስናጋጨው አዳራሹን ቀጥቃጮች የሞሉበት ቦታ አስመሰልነው::

ሰራተኞች "ምንድነው? ምንድነው እሱ?" እያሉ ከውስጥ መውጣት ጀመሩ:: የሰራተኞቹ ቁጣና ጥያቄ ሳያስደነግጠን ቀጠልንበት:: ንዴታቸውን ለመግለፅና ጠንከር ያለ ትዕዛዝ ለማስተላለፍ ወደ ወንዶቹ ሲጠጉ ሳህኑን እያነሱ ያልተበላውን ፓስታ ሰራተኞቹ ፊት ላይ ደፉት:: ወዲያውም አዳራሹ ብጥብጥ አለ:: ሳህኑ ከወዲያ ወዲህ እየተሽከረከረ ሰራተኛውን፣ ሲስትም ታዳጊውን እየመታ ያ-ትንሽ ችግር ሀይለኛ ፀብ ወለደ:: ብጥብጡ አየል ሲልም የግቢው ጥበቃዎች ለማረጋጋት ገቡና ሶስት ታዳጊዎችን በጥይት ገደሉ:: የተባለው ግን ታዳጊዎቹ ጠመንጃ ሊነጥቁ ሲሉ ተተኮሰባቸው ነው:: ወዲያውም ዘርዓይ ድረስ እና መንግስቱ ኃይለማርያም መንደር ድረስ ተስፋፋና ጠንካራ አመፅ ሆነ:: ተማሪዎች ደብተራቸውን እየቀደዱ በየመንደሩ በታተኑት:: በየክፍሉና መረጃ ያለባቸው ቦታዎች በመሄድ ፋይሎችን አቃጠሉ:: አመፁ በሀይል ተቀጣጠለ::

አስታውሳለሁ አመፁ የተነሳው እሁድ ቀን ነበር:: የመንደራችን አመፁን አነሳሽ ወንዶች በየክፍላችን እየገቡ፣ መስኮትና በር እየሰበሩ:-

"አንድሽ ነገ ትምህርት ቤት እገባለሁ ብትይ ጉድሽ ይፈላል!" አሉን::

"ሁላችሁም ምን እንደምታደርጉ በደንብ ስሙ!" አለን አንድ የኔ ብጤ ጠቆር ያለ ደልዳላ ሰውነት ያለው አመፅ ወዳድ ታዳጊ:-

"በየሰራተኞቹ ቤት፣ በየሞግዚቶቹ ቤት ትሄዳላችሁ:: እነሱ ስለሆኑ ለኛ የሚዘጋጀውን ቀለብ ለቤታቸው እየወሰዱ የሚበድሉን ቤታቸው ያለውን

ነገር አውድማችሁ ነው መምጣት ያለባችሁ:: ሰምታችኋል?"

ወንዶቹ እጃቸው ላይ ወይም በሚስጥር ኪሳቸው ውስጥ ጨቤና የሆነ ነገር ስለማያጡ ትዕዛዛቸውን ወዲያው ነበር የተቀበልነው:: ወደ ምግዚቶች ቤት በመሄድም በርበሬውን፣ ስኳሩን፣ ዘይቱን... ብቻ ያገኘ ነውን ቀማነን፣ አድፋፋን፣ ዘረፍን:: ለማድፋፋት ስንቻኮል በፈሰሱ ዘይቶች ተንሸራተው ይወድቁ የነበሩትን ልጆች ማየት ራሱ አስደስቶኝ ስፈነድቅ ነበር:: ያኔ ታዲያ አንድ ቀን እንኳ የተቆጣችንን ምግዚት ሳይቀር በዚህ ፅድ እንጨት እያሳደድን እግር እግሯን መጠብጠቡ፣ በአልጋ ልብስ እያፈንን መግረፉ አስፈነጠዘን:: መንደሮች ሁሉ ቀውጢ በመሆናቸው ብዙ ምግዚቶች በየጓሮው፣ በየአሳቻ ስፍራውና በየዛፉ ላይ ነበር ያደሩት:: ትዝ ይለኛል አባት ጦር የሆኑ አባባ ከበደ የሚባሉ ምግብ ቤት እኛን አሰልፈው የሚወስዱ አንድ ሰው ነበሩ:: በቀላሉ በመላጣቸው እንዳይለዩ ጭንቅላታቸው ላይ ፎጣ ጠምጥመው ነበር የተደበቁት:: ምክንያቱም:-

*♪እኔ ምንቸገረኝ ፀሀይ ባትወጣ*

*ታበራልኛለች የከቤ መላጣ...♪* እያልን እንዘፍንባቸው ነበርና::

አቤት! አቶ ከበደ የሚይዟት አልማዝ የምትባለው ጎማ እንዴት ሀይለኛ ነች! ሁለት አባት ጦር ቢኖሩንም አቶ ከበደ ግን አልማዝ በተባለች ጎማቸው ታዋቂነትን ያተረፉ በመሆናቸው በጣም ነው የምንፈራቸው:: እኔማ በየአጋጣሚው ስለሚሸነቁጡኝ በጣም ነው የምጠላቸው:: አባት

ጦር አቶ ከበደ ልጅ በልጅነቱ ካልተቆነጠጠ የሚል ስሜት ይኑራቸው እንጂ ሩህሩህ አባት ነበሩ:: የምግብ ሰዓት ላይ ሲደወል ሰልፍ እንይዝና አንድ አባት ጦር ከፊት፣ አንድ ከኋላ፣ ሞግዚቶች ጎንና ጎን አጅበው ነው የሚወስዱን:: እና ደውሏን ሳንሰማ ዘግየት ካልን "ዋ! አልማዝን እንዳልጠራ!" ሲሉን ተንጋግተን መሰለፍ ነው:: ጥናት ላይ እንቅልፍ ሊወስደን ቢሞክር፣ የሆነ ነገር ብናጠፋ ቶሎ የምናስበው አልማዝን ነው:: እሳቸውም ያኔ በቀላሉ የሚለዩበትን ነገር በፎጣ መጠምጠማቸው ትልቅ ብልህነት ነበር- አልማዝን የቀመሰ ሁሉ ቢያገኛቸው ዱቄት ነበራ የሚያደርጋቸው::

አመፁ ለሶስት ቀናት በመቀጠሉና መረጋጋት ባለመፈጠሩ ቴኳንዶ የሰለጠኑ ወታደሮች እንዲያረጋጉ ተላኩና አመፅ አነሱ የተባሉት ልጆች በሙሉ ተያዙ:: ያም ሆኖ ግን ትምህርት ሊጀመር ባለመቻሉ የመንግስት ባለስልጣን መጥቶ ለማረጋጋት ቢሞክርም አልቻለም:: ጠንካራ፣ ጠንካራ ቃል ነበር የምናሰማው:: "የወንድሞቻችን ደም ይመለስ!" ብለን ጮህን:: እኔማ ልጅ ስለነበርኩ ምኑንም አላውቀው:: ሲጮህ መጮህ፣ ሲለቀስ መቀበል ነበር ስራዬ:: "እኛ አባታችን እንጂ አጎታችን እንዲያናግረን አንፈልግም" አልን:: የኛ አባት አባባ መንግስቱ ኃይለማርያም ነዋ!

ወዲያው አባባ መንግስቱ ኃይለማርያም "ልጆቼ ምን ሆኑ?" ሲል ሊያናግረን መጣ:: የሚገርመኝ ነገሩ እኛን ሊያናግረን ሲመጣ አንድም ሰራተኛና ወታደር አዳራሹ ውስጥ እንዲኖር ያለመፍቀዱ ነው:: ወታደሮች ካሉ እንኳን ከውጭ ይሆናሉ እንጂ የኛን ነፃነት የመረበሽ መብቱ የላቸውም::

በየመንደራችን መለስተኛ አዳራሾች ቢኖሩም ሁላችንንም አካቶ የሚይዘው ትልቁ አዳራሽ ሁለገብ የሚባለውና ዘርዓይ ድረስ መንደር ያለው ነው:: ሁላችንም ታዳጊዎች ለስብሰባ ተጠራንና አዳራሹ ከአፍ እስከገደፉ ጢም ብሎ ሞላ::

"ምን ሆናችሁ ነው አመፁ የተነሳው?" ሲል አባባ መንግስቱ ጠየቀን:: ሁላችንም ልንናገር የምንፈልገው ነገር ቢኖርም ፍርሀት ዝም አሰባለን::

"ንገሩኝ! ምን ሆናችሁ ነው? ሰራተኛ የሚባል አዳራሹ ውስጥ የለ... ለምን ትፈራላችሁ?" ወዲያው በርካታ ታዳጊዎች እየተነሱ መናገር ጀመሩ::

"ደበደቡን!"

"ጓደኛዬን በጥይት መትተው ገደሉት"

"ምግባችን ይስተካከል ባልን ወንድሞቻችንን በጥይት መቱብን"

እጃቸውን እያነሱ ሲፈቀድላቸው የሚናገሩት ያንኑ ሀሳብ በመደጋገም ነው::

"እሺ አሁን ምን እንዲደረግላችሁ ትፈልጋላችሁ?"

"አቶ ሽመልስ አዱኛ ይቀየሩልን!"

"ይሄማ ወፍራም ብልግና ነው" አለ አባባ መንግስቱ ሀሳቡን

እየተቃወመ:: በመሰረቱ አቶ ሽመልስ አዱኛን በስም ነው እንጂ የምናውቃቸው ከኛ ችግር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አልነበራቸውም:: አዲስ አበባ ያለው የዐምባ መከታተያ ፅ/ቤት በበላይነት እንደሚሰሩ ግን ሰምተናል::

"እሺ... አምሳለ ግዛው ትቀየርልን!" የታወቀች ሞግዚት ናት::

"ወፍራም ብልግና" አለ መንግስቱ:: ያልሆነ ነገር ሲነሳ ይህቺን አባባል መድገም ይወዳል:: ታዳጊ ምንም ነገር ሲጠየቅ የተሟላ መልስ የማይሰጥ ከሆነ ደስ አይለውም:: አንገት ማወዛወዝና ራስ መነቅነቅ መልስ አይሆንም:: "ልጆቼን ስነ-ስርዓት አስተምሯቸው!" ሲል ነው የሚቆጣው::

"ሌላስ? ሌላ ማን ይቀየርላችሁ?"

"ወንድሞቻችንን የገደሉት በሙሉ" ወንድሟ የሞተባት አለም ባዘዘው የምትባል ልጅ ተነስታ እያለቀሰች ስታወራ አባባ መንግስቱ ላይ ያለው የሀዘን ገፅታ አይረሳኝም::

"ወንድሜን በጥይት ደብድበው ገደሉት!..." ለቅሶ ቀደማት:: ያለብንንም፣ የሌለብንንም ችግር ዘረዘርንለት:: የግቢውን ሰራተኛ ስም ሁሉ እያነሳን "እገሌ ይቀየር፣ እገሊት ትቀየር" አልን:: እዛው አዳራሹ ውስጥ እያለን ሰራተኞቹን በሙሉ አስገብቶ የወታደሮች ሀላፊ የሆነውና ሙሀመድ የምንለውን... ተኩሶ ልጆቹን የገደለውን ወደ እስር ቤት፣ ሌሎቹን ወታደሮች ምድረ ግቢ ብለን ወደምንጠራው (ሳር ማጨድ)፣ ዳቦ ቤት...



Scanned by CamScanner

እያደረገ ደለደላቸው:: "ልጆቼን ዳቦ አጉርሱልኝ ባልኩ ጥይት ታጎርሷቸዋላችሁ?" እያለ ሲያለቅስ ታዳጊው ሁሉ "አባታችን አለቀሰ፣ አባታችን አለቀሰ" በማለት ሲቀበለው እኔም አምርሬ ነበር ያለቀስኩት:: ሁላችንንም የወለደን አባባ መንግስቱ ኃይለማርያም ነው ብዬ አምኜ ነበርና::

***

ዐምባ የሚገቡ ልጆች ለአብዮቱ ህልውና ሲሉ ቤተሰቦቻቸው የተሰውባቸው ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ያለሰብሳቢና ረዳት የቀሩ መሆን አለባቸው የሚል መስፈርት ቢኖርም የባለስልጣንና ቤተሰቦቻቸው በህይወት ያሉም ልጆች የገቡበት አጋጣሚ ነበር:: እናም ዐምባው ውስጥ ካሉን ሞግዚቶች ውጪ እናትና አባት ለሌለን ልክ እንደ እውነተኛ አባታችንና እናታችን ጥሩ ትወና የሚተውኑ ሰዎች ተዘጋጅተውልናል:: የዚህን እንከን አልባ ትወና ሚስጢር ምክንያት እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አላውቀውም ነበር::

አሳዳጊ አባቴ ብዙ ጊዜ ስለማይመቸው ወታደሮችን ልኮ ነበር በወታደር መኪና እረፍት ወደ ቤተሰቦቼ ቤት የምሄደው:: ባመቸው ጊዜ ግን እሱም መጥቶ ይወስደኛል:: ቤት ስሄድ በረብሻ ነው የሚጠብቁኝ:: የባጥ የቆጡን ያስቀባጥሩኛል፣ ይላፉኛል.... ይቃለዱኛል::

ታዲያ ሁልጊዜም ግራ የሚገባኝ የነበረው የዐምባ ሰዎች የሆኑት የአቶ ንጉሴና ወ/ሪት ኢትዮጵያ ወደኛ ቤት መምጣት ነው:: ናዝሬት ባለው ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ተብሎ በሚጠራው የዐምባው ቅርጫፍ ውስጥ

የሚሰሩ ሲሆን ዕምባ ሲመላለሱ እናውቃቸዋለን:: ለሰላምታ ብቻ የሚመጡ ከሆነ በር ላይ ሆነው ነው ሰላም ብለውን የሚሄዱት:: መክሰስ ላይ እነሱ እንደሚመጡ የማውቀው አዲስ ልብስ ተገዝቶልኝ ሽክ እንድል ከተደረገ ብቻ ነው:: አዲስ ልብስ በምለብስበት ወቅት ይመጡና ውስጥ ድረስ ዘልቀው ይገባሉ:: አቶ ንጉሴ በጣም ረዥምና ቀይ ሲሆን ፊቱ ላይ ፈንጣጣ ነገር ትናንሽ ጠባሳዎች ጥሎበታል:: ሲስቅ ፊቱ የተጨማደደ ይምሰል እንጂ የአባትነት ባህርይና አሳሳቅ ነው ያለው:: ኮትና ሱሪ በቲሸርት መልበስ ያዘወትራል:: እጁ ላይ ሁሌም መፅሀፍ አይጠፋም:: እነሱ ውስጥ ድረስ ዘለቁ ማለት ራት ይቀርብና ጨዋታ ይኖራል ማለት ነው::

"እንዴት ነው ለመደች? ከልጆቹስ ጋር ትጫወታለች?" ይላል አቶ ንጉሴ::

"እነሱ'ኮ ከቤተሰብ ተለይተው ስለሚያድጉ ብቸኝነት ያጠቃቸዋል" ትላለች ወ/ት ኢትዮጵያ:: ፈገግታዋን የምትቆጥብ፣ ጉንጯ ላይ የሚሰረጉድ ነገር ያለባት ፀይም የሚያምር ከለር ያላትና አጭር ግን ሞላ ብሎ አይን የሚገባ ሰውነት ያላት ናት:: የጨርቅ ሱሪ መልበስ ታዘወትራለች:: በልጅነት አዕምሯችን ስለምናውቃት ነው መሰለኝ ኢትዮጵያ አገር ማለት እሷ ነው የምትመስለን::

"አዬዬ... አሁንማ ለምዷ... ሙያ እየተማረች ነው:: ቡና ሁሉ ታፈላልኝ ጀምራለች::" ትላለች ዙሪያሽወርቅ::

"ሙያ መልመድ አለባት" ኢትዮጵያ::

"ብቻ ዐምባ ቶሎ ካልተመለስኩ እያለች ታስቸግራለች"

"የልጅ ነገር ሆኖ ጨዋታ ፍለጋ ነው:: መዝለል፣ መጨፈር ነው ስራቸው::" ራቱ ሲያበቃ አንድ ወረቀት ለዙሪያሽወርቅ ይሰጣትና የሚሏትን ነገር ከሞላች በኋላ በፖስታ የታሸገ ነገር ይሰጧታል:: በፖስታ የምትቀበለው ነገር ምን እንደሆነ እያሰብኩ ከመብሰልሰል ውጭ ለጥያቄዎቼ መልስ አላገኘሁም:: እርግጠኛ ነኝ ጥያቄዎቹ ተመልሰውልኝ ቢሆን ኖሮ ገና በጊዜ መንቃት በቻልኩ ነበር::

* * *

መጠሪያ ስሜ ሙሉ ጎጃም ስለነበር ዙሪያሽወርቅ ቤት ውስጥ አቆላምጠው ሊጠሩኝ ሲፈልጉ "ጎጂ!" ነበር የሚሉኝ:: ይመስለኛል አባቴ ይሄንን ስም አልወደደውም:: የሆነ የበዐል ሥነ-ሥርዓትም የነበረ ይመስለኛል:: ብቻ የቀይ ጥለት ያለው በጊዜው ፋሽን የሆነ የሀገር ባህል ልብስ አባቴ ሲያለብሰኝ የተሰማኝ ደስታ የተለየ ነበር:: ዐምባ ስሄድ ጓደኞቼን የማጓጓበት አንድ ልዩ ነገር አለኝ ማለት ነው:: በተለይ የሀገር ባህል ልብስ ዐምባ ውስጥ ያልተለመደ በመሆኑ ለረዥም ጊዜ መነጋገሪያና የሰው ዓይን ሁሉ ማረፊያ እንደምሆን አውቄዋለሁ:: ቀድሞውንም ወደ ዐምባ ስመለስ የሚታሰርልኝና ይዤው የምሄደው ምግብ የተለየ በመሆኑ "የሀብታም ልጅ ናት" ነው የምባለው:: አሁን ይሄ ሲጨመር ደግሞ አዳሚ የእኔ አይነት እናትና አባት ስለሌላቸው ቅናት እርር፣ ድብንና

ኩርምት ሲያደርጋቸው ታየኝ::

"ከዚህ በኋላ!" አለ አባቴ የቀረበው ዳቦ ላይ ያለውን ቢላ እያየ:: ቀይ፣ ሲበዛ ልዝብ ፀባይ ያለው፣ ችምችም ብለው ያደጉት ፂሞቹ በከፊል ፊቱን የሸፈኑበት ለግላጋና ብዙ ጊዜ ሰማያዊ የኢሰፓ ኮት የማይለየው ነው:: ጥሬ ስጋና ወይን የአባቴ መገለጫዎች ናቸው:: "ከዚህ በኋላ አንድ ሰው ጎጂ ብሎ እንዳይጠራት!" ሲል ወረቀት ቀዳድዶ የሆነ ነገር ፃፈና በእጣ መልክ ጠቅልሎ በእጆቹ መዳፍ በማድረግ እጣዎቹን መትቶ ለአያቴ አንዱን እንድታነሳ ነገራት:: አያቴ ያነሳችው ስም በሚገርም ሁኔታ ሰናይት የሚል ነበር:: ምክንያቱ ሊገባኝ ባይችልም የፀደቀውና መጠሪያዬ እንዲሆን የተወሰነው ፀሀይ የሚለው ነው::

አያቴ ወ/ሮ ዘነበች በጣም ነው የምትወደኝ:: የዙሪያሽወርቅ እናት አትመስልም:: በጣም ፍቅር የምታውቅ ሴት ናት:: ሁሌ ክረምት ላይ ለእረፍት የሄድኩ እንደሆነ ከአጠገቧ እንድለይ አትፈቅድልኝም:: መኝታዬ ራሱ ከሷው ጋር ነው:: አንድ ጊዜ በጠና ታማ አይኗም ተከልሎ እኔ ብቻ እንዳጎርሳት ትፈልግ ነበር:: ህመሙ ጠንቶባት ውጪ ነፍስ፣ ግቢ ነፍስ ውስጥ እያለች ዙሪያሽወርቅን ጥሪያትና ነይ ብላኝ ጠርቼያት አጠገቧ ቆምኩ:: ያኔም ለዙሪያሽ:-

"አደራ የፀሐይን ነገር... የወለድሻቸው እንኳ እንደሷ አይጮሁልሽም!" ብላት ትንሽ ቆይታ በሞት ተነጠቀች::

* * *

በልጅነትሽ ረባሽ ነበርሽ ይሉኛል:: ጨዋታ እወዳለሁ:: በተለይ ሌባና ፖሊስ እና ፔፕሲ በጣም ነው የሚያስደስቱኝ:: ራቁቴን ሆኜ መሮጥና ገደል ውስጥ መደበቅ ደስ ይለኛል:: ያኔ ጡት የሚባል እንዲህ ጎልቶ የሚታይ ነገር የለኝም:: ቢኖርም ሴቶች ብቻ ስለሆንን ማንም ግድ የለውም:: እኔ ታማሚ ናት ስለምባል ምንም ነገር ማፅዳት አይጠበቅብኝም:: ህፃናቱን በምክር ማሳደግ የሚል ፅኑ መርህ ቢኖርም እንደኔ ምክር የማይገባውና ረባሽ ከተገኘ ሳይገረፍ አያድርም:: ሌሎችም ያጠፉ ካሉ ተራ በተራ አዳራሽ ውስጥ እየገባን ስለምንገረፍ ዱላው ቢያምም እንኳ መፅናኛ አለን::

"እከሊት!" ስም ይጠራል::

"አ-ቤ-ት!" ዱላ የፈራ መልስ::

"ነይ ግቢ!" ከዛ "ፊትሽን ወደ ግድግዳ" ይባላል:: ፊታችንን ወደ ግድግዳው እናዞራለን:: "ቀሚስሽን ሰብስቢ... በደንብ ቂጥሽን ወጥሪ" ከዛ ዱላው ቂጣችን ላይ ይዘንባል:: ያጠፋነው ብዙ ታዳጊዎች ከሆንን የማይቀርልንን ግርፍ ለመቀበል ራሳችንን እናዘጋጃለን:: እናም ዱላውን ለመቋቋም ወፍራም ልብሶችን ደራርበን እንለብሳለን:: ዱላው ሲያርፍብን እንደሌላው ጊዜ አንንገበገብም:: ይልቁንም ዱላው ባረፈብን ቁጥር እንስቃለን::

"ደ'ሞ ትስቃለች እንዴ? ጥርስሽ ይርገፍ!" ሀይላቸውን ሁሉ ያወርዱብናል:: መከራው ያለው ያጠፋሁት እኔ ብቻ ስሆን ነው:: ቀስ ብለው ወደ አንድ ቢሮ ይጠሩኛል:: "ነይ ሙሉጎጃም!" ወደ ቢሮው ስገባ



Scanned by CamScanner

ይቆለፍብኝና "ቂጥሽን አዙሪ!" እባላለሁ::

ዛፕ! በተለይ እቴቴ ቡዝዬ የምትባል ሞግዚታችን ስትጋረፍ ጨካኝ ናት:: ጥቁርና ወፍራም ስትሆን መጥረጊያ፣ እንጨት... ብቻ ያገኘ ችውን ታዳጊ ላይ ማዝነብ ያስደስታታል:: የብሎኩ ሰው ሁሉ በጣም ነው የሚፈራት:: መብራት የጠፋ ዕለት የሁሉም ታዳጊ የሽር መነሺያ እሷ ናት:: በበት እንደተመታች፣ ሽንት እንደተደፋባትና በሽውሻዋ ፅድ እግሯን እንደተጠበሰች ኖረቻት:: ሁለተኛው ገራፊያችን አባባ ከበደ ናቸው:: በአልማዝ አለንጋ ይገሽልጡናል::

"አባብዬ ስሞትልዎት፣ በእናትዎት... በልጅዎት... ልጅ የሎትም? አባብዬ ነፍሴ ተቃጠለ... አባብዬ... ኧረ በጌታ... ኧረ በተሰቀለው... አባብ ቂጤ ተላጠ..." የልመና መዐት ለጉድ ይኸጎደጎዳል:: እሳቸው ታዲያ መብራት የጠፋ ቀን ባትሪ አብርተውና ጥቁር ጎማ ይዘው ስለሚዞሩ ከድብቅ ስድብና፣ የስም ጥሪ በቀር ዱላ አያገኛቸውም::

እኔ ደግሞ የሙዚቃና ድራማ ተሰጥኦው ነበረኝ:: ለመጀመሪያ ጊዜ እናት ሆኜ እንድሰራ አምስት ገፅ የድራማ ፅሁፍ ተሰጥቶኝ በአንድ ሳምንት በቃሌ ሸምድጄ ሰርቼዋለሁ:: ይመስለኛል ቶሎ የመያዝ ችሎታ ስላለኝ ድራማ ስራ ላይ እመረጥ ነበር:: በየመንደራችን ባለን ብሎክ የየራሳችን አዳራሽ አለን:: በዛ አዳራሽም ሁሌ አርብ አርብ እየተሰበሰብን የሳምንቱን የፀጉር ፋሽን፣ የምናደርገውን ሪቫን አይነት፣ የምንለብሰውን ዩኒፎርም እጅ እያወጣን እንጠቁምና በድምፅ ብልጫ ይመረጣል:: ይሄም እንዳለቀ ድራማ ይቅረብ ተብሎ እናቀርባለን::



Scanned by CamScanner

የኛ ቡድን ታዲያ በጓደኛዬ ስም የብርቄ ቡድን ተብሎ ነው የሚጠራው:: የሆነ ነገር ጠፋ ከተባለ 'የብርቄ ቡድን ነው' ይባላል:: በዚህም ምክንያት እየተጠራን ልባችን እስኪጠፋ እንንገረፋለን:: የዚያኑም ያህል ደግሞ ድራማ ለማቅረብ የመጀመሪያ የምንሆነው የብርቄ ቡድኖች ነን:: ቡድናችን ሰባት አባላት አሉት:: ሙዚቃ ይጀመር ሲባል አንደኛ የብርቄ ቡድን ነው:: ለነገሩ በረባሽነትም የማያውቀን የለም:: ሁሉም ውስጥ የመጀመሪያ ለመሆን እኛም ፍላጎቱ አለን መሰለኝ *ደማሪ ሰማኝ ከፋፋሱ ዕብለጥ ደባል* እንደሚባለው ሁሉም ነገር ውስጥ እንደ እርጎ ዝምብ ጥልቅ ብለን ፈጠን ለመውጣት እንጥራለን:: ውጤቱ ታዲያ መገረፍ ነው:: ምንም እንኳን ዐምባ ውስጥ ድራማ መስራት፣ ሙዚቃ ላይ መሳተፍ ዱርዬ ቢያስብልም ሊገባኝ ባልቻለ ምክንያት እሳብበት ስለነበር ዱርዬ ነው የምባለው::

በድራማ ክበብና በመንፈሳዊ የቤተክርስትያን ክበብ ውስጥ እንድወክላቸው የሚሰጡኝ ገፀ-ባህርያት ብዙ ጊዜ እናትና የኔቢጤነትን ነው:: በተለይ የኔቢጤና አሳዛኝ እናት መሆን የእኔም ተሰጥኦ ነው:: ግርም የሚለኝ ልክ እንደ እኔ ህይወት ምስቅልቅል ያሉና አሳዛኝ ገፀ-ባህርያትን መወከሌ ነው:: *ሰው በሰቡ ስንዳሰበው ስንዲሁ ነው* የሚል ጥቅስ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ አንብቤያለሁ ልበል?

***

አባባ መንግስቱ እንደሚመጣ ከታወቀ ወይም ሄሊኮፕተር በሰማይ ላይ ከተሽከረከረ ክፍል ውስጥ እየተማርን እንኳ ቢሆን በቶሎ እንለቀቃለን::

በሚያስገርም ፍጥነት ምግዚቶቹ ልብሳችንን ይቀይሩልናል:: አንድ ዓይነት ልብስ ከአንድ አይነት ሪቫን ጋር አልብሰው ፊታችን የቅቤ ቅል ይመስል እስኪያብረቀርቅ ድረስ ክሬም ይቀቡናል:: በጭንቅላታችን ፎረፎር የሚታይም ከሆነ ቅባት በአናታችን ይፈስልናል:: በሰልፍ ተደርገን ቀይ ኮረኮንች በፈሰሰበት መንገድ ላይ ከወንዶቹ ትይዩ ያቆሙናል:: የምንዘምረው ይነገረንና በተጠንቀቅ እንጠባበቃለን:: አባባ መንግስቱ ሲመጣ ደስ እያለው፣ በፈገግታ ተጥለቅልቆ በመሀላችን ሲያልፍ:-

*♪ አባባ መንግስቱ አባታችን*

*የሁላችን ተስፋ መመኪያችን* እያልን መዝሙሩን ከጫፍ እስከ ጫፍ እየተቀባበልን እንለዋለን::

*አባባ መንግስቱ- ችብ ችብ*

*የኛ መሪ- ችብ ችብ*

*ታግሎ አታጋይ- ችብ ችብ*

*ድሀ አብሳሪ - ችብ ችብ*

*ህፃናቱን የሚወደው- ችብ ችብ*

*ተንከባክቦ የሚይዘው- ችብ ችብ*

*በሶሻሊስት ስርስት- ችብ ችብ*

*ስሳድገን የኛ ስባት- ችብ ችብ♫*

በእልህ፣ በጩኸት፣ በደስታ ያለማቋረጥ እስክንጨበጥ ድረስ እየደጋገምን እንዘምራለን:: ከዛም ሰብሰብ ያደርገንና ዐምባ የሚመጡ እንግዶች ሁሉ የሚወዱትን መዝሙር እንድንዘምር ያደርገናል::

*♫ስባባ የወደቀበት ብረሀ ሰባማ*

*ስባባ ያቀሰመው ቀይ የድብ ስርማ*

*የነፃነት ዳገና የምስራች ነገሯብ*

*የዳገና ሰጅ ዳገና ተጋዳይ ተከቷብ♫*

እኛም ይቺን፣ ይቺን ስለለመድን ሄሊኮፕተር ሲያልፍ ካየን ልብሳችንን አውልቀን እናውለበልባለን:: ብዙ ጊዜ የሚያደርገው ዛሬ ኦጋዴን ሰፈር ሄሊኮፕተሩ አርፎ ከሆነ ብዙ መኪናዎች ይመጡና ከኦጋዴን መንደር ጀምሮ ሁሉንም ይጎበኛል:: በሚቀጥለው ሲመጣ ደግሞ ዘርአይ ድረስ መንደር ያርፍና እንዲሁ ሁሉንም መንደሮች በመኪና እየተዟዟረ ይጎበኛ ል:: ለእኔ የአባባ መንግስቱ አስደናቂ ባህርይ አድርጌ የማየው ሳይታሰብ የሚያደርገውን ድብቅ ጉብኝት ነው::

መቼም የዐምባ ሰራተኛ መሆን ጥቅሙ ጥሩ እንደነበር ይሰማኛል:: በተለይ ምግብ ቤት ውስጥ የሚሰሩ ፕሮግራማችንን በተለያዩ መንገዶች



Scanned by CamScanner

በመለወጥ የተካኑበት ነው የሚመስሉት:: በመሰረቱ የሳምንቱ የምግብ ፕሮግራማችን በየብሎካችን ተፅፎ ተለጥፏል:: ይሁንና ዛሬ ፕሮግራማችን ስጋ ሆኖ ሳለ ፓስታ በማብላት የሚሸውዱን ቀናት አሉ:: መቼም የማንሸወድበት ፕሮግራም የአሳማ ሥጋ የምንመገብበትን ቀን ነው:: አሳማው ሲጠበስ ገና ሽታው በያለንበት መልዕክቱን ያስተላልፋል:: አሞሮች ሁሉ ማንዣበብ ይጀምሯሉ:: ያኔ የአሳማ ቀን መሆኗን እንረሳትም::

እኔ ያማታል ተብዬ ቢሮ ውስጥ እየተወሰድኩ በልዩ እንክብካቤ ስለምመገብ ምግብ ቤት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆኑና የስጋ ፕሮግራሙን በሌላ ምግብ በመስራት፣ የፓስታውን የስጋ ስጎ በቲማቲም ብቻ በማዘጋጀት ለራሳቸው እንደሚከፋፈሉ ጠንቅቄ አውቃለሁ:: ዐምባ አሳማ ማርቢያው፣ ከብት ማደለቢያው ብቻ ሁሉ ነገር የተሟላበት ይሄ ጎደለው የማይባል ስለሆነ ከዐምባው ተርፎ ለሽያጭ ሁሉ ስለሚቀርብ ችግር የሚባለው ቋንቋ የማይታሰብ ነበር::

ሰራተኞች የሚሰሩበት ቦታ እኛ እንድንጠጋ አያደርጉንም:: አንድም ሚስጥራቸውን እንዳናውቅ፤ በሌላም በኩል አንዲት ታዳጊ ከሰራተኛ ጋር ከታየች "እንጀራ አስጋግረሻት ነው ወይም እንዲህ አሰርተሻት ነው" ተብላ ከደሞዟ ትቀጣ ስለነበር ነው:: ያም ሆኖ ግን ጥቂት ከሰራተኞች ጋር የምንግባባውን ቱታ እያለበሱ "ዶሮ እረዱ!" ይሉና ይወስዱናል:: ዶሮ የሚታረደው ታዲያ "ኢትዮጵያ ትቅደም!" እየተባለ ነው::



Scanned by CamScanner

ብዙ ጊዜ የምግብ ፕሮግራማችን መዛባት አለመዛባቱን ለማጣራት አባባ መንግስቱ ሳይታሰብ ይመጣል:: አስታውሳለሁ "መንግስቱ ነኝ ሁላችሁም ከየብሎካችሁ ውጡ" ብሎ እሱ ራሱ አሰርቶ አስመግቦን የሄደበትም ጊዜ አለ:: ከዚህም የተነሳ ይመስለኛል ሁልግዜም የችግራችን ፈቺና አባታችን መንግስቱ ነው ብለን የምናምነው:: የሆነች አሳዳጊ አስቀየመችን ካልን ይመጣል::

"ችግራችሁ ምንድነው?" ሲለን

"እከሊት ትቀየርልን" እንላለን::

"ለምን?" ስንባል

"ስለመታችን" ይሄን ስንነግረው በደሞዝ ቢቀጣት እንደማይገባን ስለሚያውቅ ይመስለኛል "እከሊት!" ተብላ ትጠራና ፊት ለፊታችን "ከነገ ጀምሮ ሽንት ቤት እንድታፀጂ" ትባላለች:: ደሞዟ'ኮ አይነካም:: ብቻ እኛ ተቀጥታ እንዳየናት እንድናውቅ ነው:: እንደኔ፣ እንደኔ የሆነ ያስብልናል የሚለው ቃል ብቻ የሚገልፀው አይመስለኝም:: ይሄ ስሜት ደግሞ የእኔ ስሜት ብቻ አይመስለኝም:: የዐምባ ልጆች ሁሉ አባት ነበር:: ምንም እንኳን ቤተሰቦቼን እንዳውቅ መንግስቱ ባይረዳኝም እንደልጁ አንድ ነገር ሳይጎድልብኝ ነው ያሳደገኝ:: በእሱ እግር የተተካው ስርዐት ዐምባውን በሌላ ተቋም ቀይሮ ህይወቴ ፍፁም የመከራ ቋት እንዲሆን እስካደረገው ድረስ መልካም ህይወት ነበረኝ::

* * *

እያደግኩ ስሄድና በደንብ ነገሮችን ማመዛዘን ስጀምር የዛኑ ያህል በተለያዩ ጭንቀቶችና ህመሞች እየተሰቃየሁ ትምህርቴን በአግባቡ መከታተል ተቸገርኩ:: ደግነቱ ለእኔ የተመቸኝ በዐምባ ህይወታችን ውስጥ ዘርፈ ብዙ የኩረጃ ስልት ባለቤት መሆናችን ነው:: የመጀመሪያው ዘዴ ሲነቃብን ወደሌላኛው ስልት እንሸጋገራለን:: መኮረጁ ራሱ ሳይንቲስት የሆንን ያህል ያኮራናል:: እንዴ! ራሱን የቻለ ብቃት ይጠይቃላ! ፈተና በሚሰጥበት ወቅት ሁሉ እንደምንኮራረጅ ስለሚታወቅ ጥብቅ ቁጥጥር ነው የሚደረገው:: ስድስት የሚደርሱ መምህራን በክፍሉ ይመደባሉ:: ኮራጅና ረባሽ ተማሪዎች ተነጥለው የበለጠ ቁጥጥር ያለበት ላይብረሪ ውስጥ ይወሰዳሉ፤ ጎበዝና አስኮራጅ ተማሪዎች በፊተኞቹ የአይን ወጥመድ ውስጥ ይወድቃሉ:: ታዲያ ይሄንን ሁሉ አልፎ መኮራረጅ መቻል በኩራት ቢወጥር ስህተት ያስብላል?

ክፍሎቻችን መደዳ የተሰሩ ናቸው:: ከኩረጃ ስልታችን አንዱ ኤሌትሪክ የሚቀበርበትን ቱቦ ፈልፍሎ ማዘጋጀት ነው:: ቱቦው ተፈልፍሎ ከተዘጋጀ በኋላ ቀጭን ሽቦ በማይለይ መንገድ ይደረግበታል:: የሽቦው ጫፍ የሚቀመጥበትን ቦታ ሁሉም ተማሪ ያውቀዋል:: ልክ ፈተና በሚጀመርበት ሰዓት ሁላችንም ተደፍተን ተግቶ እንደሚሰራ ተማሪ ጎበዝ ተማሪዎች ጨርሰው እስኪወጡ እንጠብቃለን:: ሁሌም አስኮራጆች ቶሎ ጨርሰው የመውጣት ግዴታ አለባቸው:: ያንን ካላደረጉ ከፈተና በኋላ ለሚደርስባቸው ነገር ሁሉ ተዘጋጅተዋል ማለት ነው:: ይሄን መድፈር ስለሚሳናቸው በቶሎ ይወጡና በውጭ በኩል ባለው ትቦ መልሱን ግጥም አድርገው ፅፈው በሽቦው ያስሩታል:: ወዲያውም ሶስት አራት ተማሪዎች ይሆኑና ራቅ ብለው በመሄድ ትልቅ ዛፍ ላይ

ወጥተው እንዲህ እያሉ ይዘፍናሉ::

*♪ሳበው ስሀ... ስሀ...ሳበው...*

*ወዷት ነው መንገዱ*

*ስንደርስበታበን ስኛም በመውደዱ*

*ሳበው ስሀ... ስሀ...ሳበው...♪*

ወዲያውኑ እነድምፃዊት የሺመቤት ዱባለን እያመሰገንን የክፍሉ ተማሪ ሁሉ ግጥም አድርገን እየሰራነው ለግሬድ ሳይቀር በመምህራኖቹ ላይ ራስ ምታት ሆነንባቸው ቁጭ እንላለን::

ይሄ በሸቦ መልስ አድርጎ መሳቡ ሲነቃ ወደ ሌላው እናመራለን:: መብራት ሲጠፋ የሚያገለግል የብረት ደወል አለ አይደል? በሱ ደግሞ መልስ እናገኛለን:: ጎበዝ ተማሪዎች ጨርሰው እንደወጡ በደውሉ የመጀመሪያውን 'ኪውታ' ያሰሙናል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ኪው ካለ ተዘጋጁ ማለት ነው:: ያኔ ሁላችንም ጠላቷን ለማጥቃት እንደተዘጋጀች ድንቢጥ ፈጥጠንና ጆሯችንን በተጠንቀቅ አዘጋጅተን እንጠብቃለን:: የመጀመሪያው ደውል ሁለት ጊዜ 'ኪው ኪው' ካለ መልሱ 'ቢ' ነው ማለት ነው:: ሶስቴ ሲሆን 'ሲ' እያለ እንደምርጫው ሁኔታ ይቀጥላል:: ትንሽ ችግሩ ከምርጫ ውጪ ደረቅና እውነት ውሸት ከመጣ ነው:: ያም ሆኖ ግን ብዙ የምርጫ ጥያቄ ስለሚቀርብ መውደቅ የማይታሰብ ነው:: ይህቺ የደውሏ ኩረጃ 'በጠበጠች' በሚል ነው የታገደችው እንጂ ማንም

አስተማሪ አልነቃባትም ነበር::

ብቻ የኩረጃ ስልታችንን ልክ እንደጦር ውጊያ ስትራቴጂ በጥበብ ነበር የምንነድፈው:: አንዱ ሲነቃ በአንዱ እንለውጠዋለን:: የፈተና ጊዜ ሲደርስ ቀደም ተብሎ ስልቱ ይነደፋል:: ግቢው ውስጥ እርግብ የሚያረቡ ልጆች ስላሉ እርግቦቹ እግር ላይ መልሱ ይታሰርና በበሩ ይለቀቃሉ:: እርግቦቹም ቀጥታ ወደ ለመዷቸው ልጆች በርረው ያርፋሉ:: ያኔ በዘዴ የታሰረ ወረቀታቸው ይፈታና መልሱ ለጉድ ይገለበጣል:: ይሄም ሲነቃ ቅጠል ላይ መልስ ጽፎ ንፋስ ወደ ክፍሉ ያስገባው ይመስል መስኮት ስር ላሉ ልጆች መላክ፣ ሆነ ብሎ ሴቶች ላይ አይጥ በመልቀቅ በሚፈጠረው ሽብር መልስ በማቀበል ታዋቂነትን አትርፈን ቁጭ አልን:: ከዛ በኋላ ለሚመጡ አስተማሪዎች ሁሉ ሁለት ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸው ጀመር- ኩረጃ ላይ ስለማትችሏቸው አትድከሙና ቅፅል ስም እንደሚወጣላችሁ ጠብቁ የሚል::

ስም ሊወጣላችሁ ስለሚችል 'አክት' አታድርጉ ቢባሉም በሳምንቱ ይረሱታል:: እኛም ታዲያ 'ስም ያጣ ዐምባ ይምጣ' እንደተባለልን ሁሉ ዳቦ ሳይቆረስ ስሙን ሰይመን ለረዥም ጊዜ እንዝናናበታለን:: ኧረ እንደውም ዝናውን የሰሙ መምህራኖች ቀድመው አደራ ማለት ሁሉ ያበዛሉ:: አሁን አንዱ ሳሙኤል የተባለ መምህራችን ሲገባ አንገቱ ይንቀጠቀጥ ነበርና ፎቦት ተባለ:: የኬሚስትሪ መምህራችን በልዩ ዲዛይን የተሰራ ይመስል ፀጉራቸው ጥግ፣ ጥግ ላይ ሸበት ስለነበር ጥግ ጥጉን የሚል ስም ሰጠናቸው:: ከሁሉም የሚጥመኝ ስም ቶ ፊስ የምንላቸው መምህር ስያሜ ነው:: አንቱም ለማለት፣ አንተም ለማለት የሚያስቸግር

ፊት ስላላቸው ነው- ቱ ፌስ ያልናቸው:: በተለይ የሂሳብ መምህራችን በዘመኑ በጣም ፋሽን የሆነ ልብስ፣ የሚንቀጠቀጥ ጥቁር ሱሪና ቀይ ቢትልስ አድርጎ ክረምት እረፍቱን ጨርሶ ሲመጣ *ሰምፒስቢን* አልነውና አበደ- "ታዲያ እኛ እንዴት ሆነን እንቅረብ?" ሲል::

እኔ ስም ማውጣቱ ላይ ንቁ ተሳታፊ ባልሆንም ፍሬሽና ስለወጣው ስም የማያውቁ ካሉ "ከቲቸር ጥግ፣ ጥጉ ቸክ ይዘሽ ነይ!" ብዬ አንዷን በመላክ "ቲቸር ጥግ ጥጉ" ባለችበት ቅፅበት ማጀቢያ የሆነ ቀጭን ለቅሶ ስትለቅ መስማትና ኩረጃ ላይ መሳተፍ ተሰጥዎቼ ነበሩ:: አንድ ጊዜ ግን ስኮርጅ ተይዤ ለብቻዬ አንድ ክፍል ተዘግቶብኝ እንድፈተን ተደረግኩ:: ያኔ ማን ለትምህርት ግድ ይሰጠው ነበር? አንደኛ ልጅ ነኝ፤ ሌላው ደግሞ ኑሮዬና ሞቴ እዛው ዐምባ በምቾት እንደሚሆን እንጂ እንዴት ኑሮ *በራሷ ዛቢያ ለሽከርከሬ የማይሆን ህይወት ውስጥ ልተከተኝ ተችባለች ብዬ ማሰብ እችባለሁ?* የሆነው ሆኖ ግን ስኮርጅ ተይዤ አንድ ክፍል ውስጥ ሲዘጋብኝ "ኡኡኡ!" ብዬ ጮህኩ:: "አይ ይቺ ልጅ ሴጣን አለባት" ተብሎ አባ ሚካኤል የሚባሉ አባት ተጠሩና ብቻቸውን መጥተው ሲያዩኝ "አባ መልስ ፈልጌ ነው" አልኳቸው:: ወዲያው ትንሽ ቆይተው ፀበል ይዘው ሲመጡ በገርጋጋ ቀሚሳቸው እጄታ ውስጥ ከተማሪዎቹ ያገኙትን መልስ ይዘውልኝ ነበር የመጡት::

# -3-

በህይወታችን ውስጥ እንደዱብ ዕዳ የተከሰተው ለውጥ እኔን ጨምሮ የብዙዎቻችንን ዕጣ ፋንታ እንቆቅልሽ ያደርገዋል ብለን ለማሰብ የሚያስችል ብስለት አልነበረንም:: ይሁንና ሻዕቢያ ተንኮለኛና ጠብ አጫሪ በመሆኗ በጥይት እንዳትመታን ጥንቃቄ መውሰድ እንዳለብን ተነግሮን አልጋ ላይ መተኛታችንን ትተን አልጋችን ስር መሬት ላይ ፍራሽ በማንጠፍ እንድንተኛ እንመከር ነበር:: ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ጥፍራቸው የሾለ፣ ጥርሳቸው የገጠጠ፣ ፀጉራቸው የተንጨባረረ የእኔ ቢጤ ጥቁር የሆኑ በአጭር አማርኛ ጭራቅ አድርገን እንድንስላቸው የተደረጉት 'ወያኔዎች' እኛጋ ይመጣሉ ብለን በእውናችንም ይሁን በህልማችን አላሰብንም::

በበነጋው ሰኞ ቀን ላይ ቁርስ ለመብላት ወደ አዳራሹ ስናመራ በፍርሀት ነበር:: ይሁንና ያየናቸው ሰዎች ፀጉራቸውን አሳድገው ጃርት ከመምሰላቸው ውጪ አንዳችም 'የጭራቅ' ነገር ሳናይባቸው ስንቀር ተገረምን:: ወደ ምግብ አዳራሹ ልንገባ ስንል የዐምባው ሀላፊዎች ቀስ ብለው የኛን የኦጋዴን መንደር ኗሪ ታዳጊዎችን በተለይ በረባሽነታቸው የሚታወቁትን የወንዶቹን ብሎክ ቁጥር አምስትና የኛን የሴቶቹን ብሎክ ቁጥር ሁለት ታዳጊዎች እየነጠሉ "እንዳትረብሹ ይሄው ተመልከቱት!"

ሲሶ እንደሌሎቹ መንደሮች የአባባ መንግስቱ ፎቶ ያለመቃጠሉንና ማታ ለሚመጡ ባለስልጣኖች ሲባል የምግብ ቤቱን ግድግዳ የሚሞላው ምስል መነሳቱን አሳዩን:: ገብተን እንቁላል ጥብሳችንን ይዘን ለመመገብ እንደተቀመጥን የአዳራሹ ጭር ማለት መንፈሳችንን ረበሸው:: ሁላችንም እንዳጎነበስን እንቁላሉን ንክች ሳናደርግ በለቅሶ ተዋጥን:: ቀደም ብሎ በተሰጣቸው ትዕዛዝ ዐምባ ያሉት አስተዳደሮች ሁሉም ቦታ ያሉት የአባባ መንግስቱ ኃይለማርያም ፎቶዎችን ሰብስበው አቃጥለዋቸው የኛን የኦጋዴንን መንደር አናስነካም ብለናቸው ትተውት ነበር::

ወያኔዎች በየክፍላችን ይመጣሉ ሲባል ፀሎት ያዝን:: "እግዚያብሄር አባታችን ሆይ... ጭራቅ ሆነው ከሚመጡት ሰውረን:: የወያኔዎችን እግር ቀልጥምልን:: እኛን የመንግስቱን ልጆች ጠብቀን::" ድንገት ከኦጋዴን መንደር የመጀመሪያው ብሎክ ሀይለኛ ጩኸት ተሰማ::

"በቃ እግዚአብሔር ፀሎታችንን አልሰማም ማለት ነው"

"ኡኡኡ!" ጩኸቱ አየሩን ሞላው:: ጭራቆቹ ገብተዋል ማለት ነው ብለን እኛም ጩኸቱን ተቀብለን አስተጋባነው:: *በቃ በጭራቆቹ ልንበላ ነው!* ወዲያው የኛ ብሎክ ተንኳኳና ተከፈተ:: ሁላችንም የሚመጣውን ነገር ፈርተን አልጋ ስር ተደብቀን ነበር::

"ናይ እናንተ አትወጡ እንዴ?" ዝም::

"የሚነካችሁ እዚ የለም ከአልጋው ስር ውጡ!" ዝም:: ሲሰለቻቸው ትተውን ሄዱ:: ፍርሀት እንደወባ ያንዘረዝረን ስለነበር ደፍረን ወጥተን



Scanned by CamScanner

ጭራቆቹን ለማየት ወኔ አልነበረንም::

ወደ የትምህርት ቤታችን ስንሄድ ይሄን ከአምስት መቶ ብር በላይ ደሞዝተኛ የሚለብሰው የሚባለውን ደማቁን ሰማያዊ ዩኒፎርም በነጭ ሸሚዝና ቆብ መሰል ኮፍያ ጋር በስፒል ከተያያዘች አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራ አድርገን ነጭ ካልሲ በጥቁር ሰንደል ቆዳ ጫማ ነበር የተጫማነው::

ወዲያው ወያኔዎቹ አስቁመውን እኛ የምንላችሁን መፈክር ካላላችሁ አታልፉም አሉንና "እኛ ጭቁኖች!" በሉ አሉን:: እኛም በነሱ ቋንቋ እያሾፍን "እኛ ጭቁኖች" አልን::

"ነፃ ወጥተናል!" በሉ::

"ነፃ ወጥተናል"

"በድጋሚ እኛ ጭቁኖች በሉ"

"ኡፍ!" ብለን ስንመናጨቅ አሳለፉን::

ምንም እንኳን ከወያኔዎቹ ጋር ለመግባባት ብዙ ጊዜ ባይፈጅብንም በጣም ተጠራጥረውን በርቀት ነበር የሚቆጣጠሩን:: "እንዳትቀርቧቸው ፖለቲከኛ ናቸው" ተብለው ስለነበር ለነሱ ወደተሰጣቸው ክፍል እንድንጠጋ ፊት አይሰጡንም:: እኛ ግን 'ጭራቅ' ያለመሆናቸውን ስንለይ ልጅነታችን ቶሎ ወዳጅ መሆን ላይ ጣለንና ተቀራረብናቸው:: ያኔ ትንሿ ድቡልቡል ማስቲካ የመጣችበት ወቅት ነበርና "እንኩ!"

ስንላቸው "መጀመሪያ ቅመሱትና" እያሉን ግማሹን በልተን ነበር የምንሰጣቸው:: ለነሱ የሚቀርበውን ምግብ ከመብላታቸው በፊት ሶስት አራት ታዳጊ ቀምሶ ነው የሚሰየሙበት:: ያም ሆኖ ግን ከነሱ ጋር ለመግባባት ያገደን ነገር አልነበረም::

*ሲህስዴግ ሆነ ቅብርፕሴ ዐከ እንደ ሰባባ መንግስቱ ኃይለማርያም ቢሆንዐን ሰባታችን ነው ብሰን ቢሳውንስ ሰመቀበሰ ምን ያገደናል?* አስገራሚው ነገር ግን ለውጡ ያልተጠበቀና የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ያለው መሆኑ ነበር::

*ያ- ጡት ያሰው* ብለን ስም ያወጣንለት ለአንድ ታዳጊ ሽክም የሚሆንበት ትልቅ ዳቦ በግማሽ ተለወጠ:: አራት እንቁላል ቅቅል ከሻይና ዳቦ ጋር እንዳልተሰጠን ያ ፕሮግራም ቀረና የተቆረጠ ደረቅ እንጀራ በሻይ አማምገን እንድንበላ ይሰጠን ጀመር:: እንቅፋት ሲመታን እንኳን "በሞትኩት ልጄን!" እንዳልተባልን በበሽታ መረፍረፍ፣ ሀኪም ቤትም ስንሄድ በጀት የለም እየተባልን መማቀቅ ውስጥ ገባን:: ፊትኮ ምርጥ ምርጡን ለህፃናት ስለሚባል አንድ አስተዳደር ሰራተኛ ታሞ ከታዳጊም የታመመ ካለ መጀመሪያ ታዳጊው ታክሞ ሲያበቃ ነበር አስተዳደር ሰራኛው የሚታከመው:: ኧረ ምን ይሄ ብቻ አንዳችን ለሌላችን ሁሉ እንታከም ነበር::

በአባባ መንግስቱ ጊዜ እንኳንስ ህክምና ልንቸገር ከሶቭየት ህብረት የሚመጣልንን በአንዴ ሦስትና አራት አይነት ከለር የሚያወጣ ኮልጌት እንደልብ እየተሰጠን ለሰራተኞች አስር ብር ሂሳብ እንሸጠው ነበር:: የሸጥንበትን ብር ማታ ከቆጠራ በኋላ ክፍላችንን ዘግተን መብራት

በማጥፋት ሻማ ብቻ እናበራና በቆርቆሮ በሰራነው ማንደጃ ቡናችንን አፍልተን ነጩ እስኪወጣ እስከ አስራስድስተኛ እየጠጣን ወሬያችንን ስንቀድ እናድራለን።

"የመንግስት ልጆች ምልክታቸው እንዲህ ነው" እስኪባል ድረስ ክሊኒክ እየሄድን "በናትህ እቁባይ አሞኛል... አምፕሲሊን ከሰጠኸኝ ይሻለኛል" እያልን መድሀኒት እየወሰድን ለሰራተኞች ሁሉ እንሸጠው ነበር። ሰራተኞች የሚዝናኑበት ክበብ መግባት ለታዳጊ ስለማይፈቀድ ተሸሎክሉከን እንደትልቅ ሰው መስለንና ፊታችን ላይ በጥላሸት መስመር ሰርተን እንገባና ምግብ አዝዘን በገንዘቡ እንበላበታለን። ከሁሉም ደስ የሚለው ለጓደኞቻችን መታከማችን ነው። አንድ ጊዜ ጓደኛዬ ያማታል። "ብርድ፣ ብርድ ብሎኛል ታከሚልኝ" ስትለኝ እሺ ብዬ ክሊኒክ ሄድኩ።

"ምንሽን ነው ያመመሽ?" አለኝ ዶ/ር እቁባይ።

"ብርድ ነዋ!"

"እንዴት ነው የሚያደርግሽ?"

"በቃ ብርድ ብርድ ይለኛል" ልክ ጓደኛዬ እንዳለችኝ ነገርኩት። ቶሎ መድሀኒት አዝዞልኝ ተቀብዬ ለመውጣት ጓጉቻለሁ።

"ብርድ ብርድ ብቻ?"

"አዎ ብርድ ብርድ ብቻ!"



Scanned by CamScanner

"ብርድ መጥፎ በሽታ መሆኑን ታውቂያለሽ?"

"አዎ ዶ/ር እቁባይ... መድሀኒቱን ስታዝልኝ ይሻለኛል"

"የብርድማ መድሀኒት በዓለም ላይ የለም::"

"እ?"

"አዎ:: ነይ!" እጄን ይዞ ልብሴን እንዳወልቅ አደረገና ይሄን የእብድ ዱላ የሚያክል መርፌ ሲሸጥብኝ ሳላውቀው ብርድ ብርድ አለኝ:: ምልክቱን ይዞ ሄዶ ለጓደኛና ሰራተኛ መታከም፣ መድሀኒት እየተቀበሉ መሸጥ የተለመደ ነበር- ለእኔ አልተሳካልኝም እንጂ:: አንድ ታዳጊ ታሚል ከተባለ አንቡላንስ መንደሩን ቀውጢ ሲያደርገው ነበር የሚውለው:: ሁኔታዎች ተለውጠው ኢህአዴግ ሲገባ ግን የመድሀኒት በጆትም ጠፍቶ ቁጭ አለ::

እንዲያ በዓል የመጣ እንደሆነ አስራ አምስት እና ሀያ ዓይነት ብፌ በየመንደራችን ተዘጋጅቶልን፣ በቂጠማና ጌጣጌጥ ሽብርቅ ብሎ፣ መኝታ ክፍላችን ሳይቀር በበዓሌ ድምቀት ተሸቆጥቁጦ፣ የበላነውን ያህል በልተን የቻልነውን ያህል ወደ መኝታ ክፍላችን ይዘን እንዳልሄድን፣ እንቅልፋችንን ስንጨርስ ኬክ፣ ዳቦ፣ ብርቱካንና ለስላሳውን የበዐሉ ዕለት ጀምሮ እስካለቀ ድረስ ለሶስትና አራት ቀናት እስኪሰለቸን እንዳልበላን ነገሮች ሲለዋወጡ የሚቀርብልን ሽሮ ሲጠለል አሸዋና አሸክት ምስሩ ላይ እየተገኙ ልዩነቱን እስክናማርረው ድረስ ቀጠለ::



Scanned by CamScanner

# -4-

በ1988 ዓ.ም. ክረምት ላይ ወደ ቤተሰቦቼ ቤት ለዕረፍት ለመሄድ "ባህርዳር ነው የምሄደው እናቴ ለስራ ወደ እዚያ ተቀይራለች" ብዬ ዘጠና ዘጠኝ ብር ተቀበልኩ:: አባቴ ደርግ ከወደቀ በኋላ በመታሰሩ እንደበፊቱ ክረምት ላይ ከቻለ እሱ መጥቶ አልያም የወታደር መኪና ተልኮልኝ ታጅቤ መሄዴ ስለቀረ ከዐምባው የመሳፈሪያ ብር እየተቀበልኩ ነበር በትራንስፖርት የምሄደው:: ቤተሰቦቻችን ካሉበት ሳይነቃነቁ "ባህርዳር ወይም ገለመሌ" ሄደዋል እያልን ጠቀም ያለ ብር መቀበልና ከትራንስፖርት የሚተርፈንን ለራሳችን ማድረግ ልምዳችን ስለሆነ ነው እኔም እናቴ ባህርዳር ለስራ ተቀይራለች ብዬ ዘጠና ዘጠኝ ብር የተቀበልኩት::

የእኛ ቤት 15 ቀበሌ በተለምዶ አንደኛ መንገድ በመባል የሚታወቀው አካባቢ ነው:: የግቢያችን በር አጠገብ ትልቅ የሚሊያ ዛፍ አለ:: በእርሱ ስር ጊንጧ አለ:: እሱን አልፎ የዝገት መከላከያ ቀለም የተቀባው የዋናው በር መግቢያ ሲከፈት ፊት ለፊት በቆዳ የተሰሩ የባህል የሶፋ ወንበሮች በጠረጴዛው መሀል ማለፊያ መንገድ በመተው በስተግራ ተሰይመዋል:: በስተቀኝ በኮምፖርሳቶ የተከፈለ አስጎንብሶ የሚያስገባ በር ያለው የሽቀጣ ሸቀጥ ሱቅ አለ:: ከሱቁ ጀርባ በውስጥ በኩል



Scanned by CamScanner

ዙሪያሽወርቅ ሀያ አራት ሰዓት የምትቀመጥበት ፍራሽ ተነጥፏል። በግራ በኩል በቁጥር ያልተሟላ ሶፋ ተቀምጧል። በቀኝ በኩል ቴሌቭዥን ከዴክ ጋር አለ። እዛው አጠገብ የድሮ ሬዲዮ ከነሻተሩ ተገትሯል። ሳሎኑን አልፎ ወደጓዳ የእያቴ መኝታ ቤት ይገኛል። በኮሪደሩ በኩል ቀጭን መንገድ ላይ ኮንትሮል ብፌ ግድግዳውን ተጣብቆ ቆሟል። በስተቀኝ የዙሪያሽወርቅ ባለቤት መኝታ ክፍል አለ። ባሏ ከሌለ ብቻዋን እዚህ መኝታ ክፍል አታድርም። እዛው ሳሎን የተነጠፈ ፍራሿ ላይ ነው ውላ የምታነጋው።

ቤት ስገባ የተደረገልኝ አቀባበል ከወትሮው የቀዘቀዘ ነው። ሌላው ቢቀር እንኳን ቡና ተፈልቶ ነበር የሚጠብቀኝ። አሁን ግን ቡናውም የሚናፈቅ ሆኖ ቤቱ የሞት ድባብ የሰፈነበት መስሏል። ዙሪያሽወርቅ አስምና ኩላሊት ስለሚያማት ተኝታለች። የተኛችው ሳሎን ፍራሽ አንጥፋ ነው። ሰላም ብያት ገባሁና ሰውነቴን ታጠብኩ። የቤቱ መንፈስ ግን አልተመቸኝም። ወይም ደግሞ የእኔ መንፈስ አንዳች ነገር ሊፈጥር እንደሚችል ገብቶት ፍርሀት ውስጥ ከቶኛል ማለት ነው- ብቻ በጣም ተረብሼያለሁ።

ያም ሆኖ ግን የእኔ መንፈስ ችግር ብቻ ነው እንዳልልም እናቴ ዙሪያሽወርቅ በሙሉ አይኗ ልታየኝ አለመፈለጓን በግልፅ ማየት ቻልኩ።

ዙሪያሽወርቅ ጣሰው ከልጅነቷ ጀምሮ ቆንጆ ለመሆኗ ቀይ የፊት ገፅታዋ ይመሰክራል። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ስለሚባል እንጂ ከቤተሰቡ እኔ ብቻ ነኝ አፍሪካዊ ጠቆር ያለ ቀለም ያለኝ። ዙሪያሽወርቅ የፊቷ ቆዳ



Scanned by CamScanner

አይኗ ስር ሽብሽብ ብሏል:: አይኗ ትላልቅ ሆኖ ብዙ ጊዜ ጥቁር ሻሽ ፀጉሯ ላይ አይጠፋም:: ሽበት የለበሰው ሉጫ ፀጉሯ በሻሽ መሸፈኑ ያሳዝናል:: የምትወደው ልብስ ጥቁርና ቡናማ ቀሚስ ነው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በእናቷ ሞት ምክንያት ጥቁር ጥለት ያለው ነጠላ ታዘወትራለች:: ቁጣ የሚባል ነገር ከአንደበቷ አይወጣም:: ንግግሯ ሁሉ ረጋ፣ ቀስ ብላ ነው:: ንግግሯ ሲያምም የዚያኑ ያህል ቀስ እያለ ነው:: ፍራሿ ላይ ሆና ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ስታዝ ብትውል ደስ ይላታል:: ስራም ካላት እዛው ፍራሿ ላይ ሆና ነው የምትሰራው:: እኔ ወደናዝሬት በሄድኩ ቁጥር እግሯ ስር ቁጭ ብዬ እያሻሸሁላት ወሬ እንሰልቅ ነበር::

ዛሬ ግን ይሄ ሁሉ የለም:: የዙሪያሽወርቅ ፊት ሰው አያቀርብም::

በበነጋው ከምሳ በኋላ ልታወራኝ እንደምትፈልግ ነግራኝ ፍራሿ ላይ ቁጭ አልኩኝ:: ትንፋሿ እየተቆራረጠ፣ ለማውራት የምትፈልገው ነገር እየቸገራት መንተባተቧን በደግ አልተረጎምኩትም:: ብቻ እንደምንም አምጣ ቃሉን ተፋችው:: *ለካ ሁለት ቃላት የሰውን ልጅ ህይወት የመከራ ቋት ውስጥ መከተት ይችላሉና? ለካ ሁለት ቃላት ብቻ ማንነትን ለዕም ያለ ውሀ ለበባ ቀውስ ውስጥ ለመጨመር ብቃቱ ለላቸውና?* ሰማይና ምድሩ ዞረብኝ:: ያለችኝን ሁለት ቃላት ደግሜ ሳስታውሳቸው ውስጤ መቃጠል ይጀምራል:: ሰውነቴ ያልተለመደ ትኩሳት ይተፋል:: ራስ ምታቴ ይጨምራል:: እና በምድር ላይ እንደሳር የበቀልኩ ብቸኛ የሰው ፍጡር የሆንኩ ያህል ይሰማኛል::

"እናትሽ አይደለሁም!" ነበር ያለችኝ::

ደረቅ ጡቷን አጥብታ ያሳደገችኝ፣ በእቅፏ አድርጋ ያስተኛችኝ፣ ጠረኗን እንድለምደው ለጋስ የሆነችልኝና "ዙሪያሽ ትሙት!" ብዬ የምምልባት እናቴ "እናትሽ አይደለሁም!" ስትለኝ ምን ሊሰማኝ ይችላል? ታሪኩን ሁሉ ዘርዝራ ነገረችኝ:: ሀሳቧን ስትደመድምም ሌላ መርዶ አከለችበት:-

"በጊዜ መጠጊያሽን ፈልጊ!"

በሀይል እያቅለሸለሸኝ ትኩሳትና ራስ ምታት ያለማቋረጥ ወጥረው ያዙኝ:: ስትነግረኝ በድን ሆኜ ነው የሰማኋት:: ምንም የቃላት ጋጋታ አላበዛችም:: አጭር፣ አጭር እያደረገች ስትነግረኝ እንባዬ ኮለል ብሎ እየወረደ ጡቴ ውስጥ ሲንጠባጠብ ይታወቀኛል:: *የማን ልጅ ነኝ? ማነው በዚህ ስሰም ባይ ያለኝ?*

እኔ በደንብ አልገባኝም እንጂ ፊትም ጀምሮ ዐምባ እያለሁ በእናቴ ስም ስምል "የት ያለችሽን እናት?" እባል ነበር:: መታወቂያዬ ላይ የወላጅ ተጠሪ በሚለው ቦታ የእሷ ስም የሰፈረ መሆኑና "እናቴ" ብዬ ስሄድ "ልጄ!" ብላ ትቀበለኝ ስለነበር እንዴት ይሄን አይነት መርዶ ልጠብቅ እችላለሁ? በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የተነገረኝን ብሰማም ማስተዋል አለመቻሌ ቀድሜ መዘጋጀት እንዳልችልና የተጣለብኝን የመከራ ቀንበር መሸከም ባለመቻል ጎብጬ እንድቀር አደረገኝ::

እናቴን ዙሪያሽወርቅን እንዳልረግማት ወኔው አጠረኝ:: ፊትም ጀምሮ ልለምዳት እንዳልቻልኩ፣ አልቃሻ እንደነበርኩ ትነግረኝ የነበረው ቅድመ

ጥቆማ መሆኑን ማወቅ ነበረብኝ:: የእናቴ የልጅ ልጆች ሲያስቀይሙኝ ለምን ክፉ እንደሚናገሩኝና "የመጣሁበት የማይታወቅ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚነግሩኝን በደንብ ማኘክ ይገባኝ ነበር:: ያኔ ግን ልጅነቱም ስላለና እሷም የሚናገሩኝን ሁሉ ትከላከልልኝ ስለነበር ጥቂት ጊዜ ነገሩን አምሰልስዬ ጨዋታ ሳገኝ ከመርሳት በዘለለ የተጨነቅኩበት ጉዳይ አልነበረም:: ብዙ ነገሮችን አድርጌ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ልጋፈጠው የከበደኝን መሪር ዜና ለመቀበል ባላዳገተኝ::

*"የስለተ ልጅ ናት"*

*"ስመደች ደቺ ልጅ?"*

*"ልጅ ስያስሽ'ኮ ለልቃሻ ነበርሽ:: ለናቴን ተደኝ ነበር"*

*"የት ያለችሽን ለናት?"*

ብቻ "በጊዜ መጠጊያሽን ፈልጊ" ስትለኝ እንባዬ ዝርግፍ፣ ዝርግፍ እያለ አስቸገረኝ:: የት ነው የኔ መጠጊያ? ምንስ ብዬ ነው ለምን እንደምታባርረኝ የምጠይቃት? የማደርገው እንደጠፋኝ ስታውቅ ተነስታ ከአይኔ ተሰወረች:: ሶስት ቀን ሙሉ ምግብ አልበላ፣ ብቻዬን ክፍሌ ውስጥ ዘግቼ እየየውን አስነካሁት:: ሶስተኛው ቀን ላይ "እንግዳ ስለሚመጣብኝ ቤቱን ለቀሽልኝ ውጪ!" አለችኝ::

እግሯ ላይ ወድቄ ለመንኳት:: የት መሄድ እችላለሁ? ወደ ዐምባ አልመለስ ክረምቱን ቤተሰቦቻቸውን ሊጠይቁ ላልሄዱ ልጆች ነው በጀት ተመድቦ ሁሉ ነገር የሚዘጋጀው:: በዛ ላይ እናቴ ጋ ብዬ መጥቼ ተመልሼ ብሄድ "የት ያለችሽን እናት?" ሲሉ ስምልባት እንዳልተሳለቁብኝ ተባርሬ መሄዴን ሲያውቁ ዘለዓለም መቀለጃቸው ልሆን ነው:: ዐምባ

ውስጥ ወሬ እንደወረርሽኝ የሚተላለፍና ትንሽ ከመደበኛው አኗኗር ወጣ ብሎ የሚታይ፣ ሙዚቃና ድራማ ክበብ የተሳተፈ ባለጌ ተደርጎ በጓደኞቹ ዘንድ የሚታይበት ሁኔታ ነው ያለው:: አንድ አጉል ነገር እንድናደርግ ከተጋበዝን እንኳን እንቢ ስንል ጓደኛዬ ትቆጣኛለች ነው የምንለው::

አሁን አሁን ሳስበው ወላጆቼ ዐምባ ሳለሁ ክረምት ላይ ለእረፍት ናዝሬት ይወስዱኝ የነበረው ሰብዓዊ ስሜት ተሰምቷቸው ሳይሆን ለስርዓቱ የነበራቸውን ታማኝነት ለማረጋገጥ ከነበራቸው ፍላጎት ነበር:: ዙሪያሽወርቅ እናትሽን ፈልጊ ስትለኝ የተረዳሁት በየክረምቱ ትንከባከብ የነበረው ባሏ ያገለግል የነበረውን ስርዓት እንጂ ከየት መጤነቷ የማይታወቅ... እኔን እንዳልነበር ነው::

እግሯ ላይ ወድቄ እየተንሰቀሰቅኩ "ዙሪያሽዬ በናትሽ! ያጠፋሁት ካለ ይቅር በይኝ... ይህችን ክረምት ብቻ እንኳን ልቆይ? ስሞትልሽ ሁለተኛ ድርሽ አልልም... ይህችን ክረምት ብቻ!" ብዬ ብለምናትም አንድ ጊዜ ተናግሬያለሁ በሚል ጥላኝ ሄደች:: ምንም እንግዳ እንደማይመጣባት፣ ቢመጣባትም እንኳ ረዥም አመታት ካሳደገችኝ ልጇ በልጠውና ቦታ ጠቧት እንደማትቸገር ቢገባኝም ከዚህ በኋላ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እናቴ እንዳልሆነች፣ ልጇ እንዳልሆንኩ አውቄያለሁና እንዳለችው ዕጣዬ የለገሰኝን መጠጊያ በጊዜ መፈለግ አለብኝ...



Scanned by CamScanner

# -5-

ነጭ መሀሉ ላይ ክፍተት ያለው ጫማ፣ ስምንት ቅድ ቀሚስ፣ ቲሸርት ለብሼ የዙሪያሽወርቅን አንድ ነጠላ ከላይ ደርቤ ነው በአራተኛው ቀን ቤቱን ለቅቄ የወጣሁት:: ወዴት መሄድ እንዳለብኝ እርግጠኛ ባልሆንም እንኳ ጥልቅ ሀሳብ ውስጥ ሆኜ ዝም ብዬ መራመዴን ወድጄው ነበር:: ትንሽ እንደራቅኩ ከትራንስፖርት የተረፈኝን ብር ይዤው ስለነበር ሰልባጅ ሹራብ ገዝቼ ለበስኩ:: ወደ ዐምባ መመለሱ እንደሆነ የማይታሰብ መሆኑን ባልበሰለ አዕምሮዬ አገናዝቤ አምኜበታሁ:: ማንም ቤተሰቦቹ ቤት ለዕረፍት የሄደ ታዳጊ መስከረም ላይ አዲስ ልብስ ለብሶ ግቢው ውስጥ መነጋገሪያ መሆን ትልቁ ነገሩ ነው:: *እሱን ሳሳሚሳ እንዴት እሄዳለሁ? እንዴት ዐምባ ውስጥ መጠቋቆሚያና መቀለጃ እሆናለሁ?* ከአስተዳደሩ ጀምሮ "ለምን መጣሽ?" ተብዬ እጠየቃለሁ:: አልዋሽ ነገር ዐምባው ከቤተሰቦቼ ጋር ግንኙነት እንዳለው አውቃለሁ:: ድንገት ግን አዕምሮዬ ውስጥ የሆነ ሀሳብ ብልጭ አለ... *ለእናቴ በፖስታ እየተደረገ ይሰጣት የነበረው ነገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቀረው ለምንድነው?* ያም ሆነ ይህ ግን ዐምባ መመለስ በብዙ ሁኔታዎች የማይሞከር በመሆኑ እግሬ ወደመራኝ መንጎዱን የብልህ ዕርምጃ ያህል ተቀበልኩት::

ቀጥታ ያመራሁት ናዝሬት ውስጥ ወዳለችው ማርያም ቤተክርስቲያን

ነው:: ሰማዩ እንደእኔ ፊት ተከፍቶ እያጉረመረመ ነው:: ሰው ውር ውር ሲል እያየሁ ውስጤ ተረበሸ:: ሰው ማየት አስጠላኝ:: አዕምሮዬ ቆርቆሮ ውስጥ እንዳለ ብረት "እናትሽ አይደለሁም!" እና "በጊዜ መጠጊያሽን ፈልጊ" የሚሉትን ቃላት ከወዲያ ወዲህ እያጋጨ ረብሻ አድርጎ አሰማኝ:: የቤተክርስትያኗን ቅጥር ግቢ አልፌ መግቢያው በር ላይ ተንበርክኬ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: *ለሴት ልጅ መፅናኛዋ ስንባዋ ለይደለ?* ለቅሶዬን ተከትሎ ደጋግሞ ፍንጥር የሚለው መብረቅ የቁጣ ምልክት መሰለኝ:: እዛው ቤተክርስትያኗ ውስጥ ሳላዝን ጨለማ ሊነግስ መጣሁ ማለት በመጀመሩ የት ላድር እንደምችል ሀሳብ ገባኝ:: ባወጣና ባወርድም አንድስ እንኳ መፍትሄ አልመጣልኝም- እዛው ቤተክርስትያኗ ውስጥ ከማደር ውጪ::

መቼም ማንም ከነበረበት ሻል ያለ የኑሮ ደረጃ ሲወርድ ዝቅ ያለውን መጠየፍና ሊለምደው መገዳደሩ አይቀርም:: በተለይ በመንግስት እጅ ተሸሞንሙኜ ላደግኩት ለእኔ አፈር እፍ ብሎ መተኛትን የመሰለ ታላቅ ሞት ያለ አይመስለኝም:: ብቻ ያለኝን አማራጭ ለመጠቀም መሬቱን እፍ ብዬ ከመተኛት ይልቅ ካርቶኖችን ፈላልጎ እንደው አለ አይደል ጎዝጎዝ አድርጎ መተኛቱ ምቾትና ክብር ይሰጣል ብዬ አደረግኩት:: አካባቢው የሚያድሩ የጎዳና ተዳዳሪዎች ግን እያዩኝ ይሳሳቁ ነበር:: እርግጠኛ ነኝ "እስክትለምደው ነው ባክህ!" እየተባባሉ እንደሚሆን::

ጠዋት ስነቃ ሰውነቴ ደቅቋል:: ያለሁበትን ቦታ ስለየው በራሴ አፈርኩ:: እንዲህ ያለው ነገር አሪፍ ህልም ብቻ ሆኖ ቢቀር ተመኘሁ- ግን አይደለም:: እንደገና ለቅሶ መጣብኝ:: ከዛ በኋላ ጠጠር በወጋኝ ቁጥር

ማልቀስ፣ ብሶቴን በዕንባ መግለፁን የሰርክ ተግባሬ አደረኩት::

ኑሮዬ ጎዳና ላይ መሆኑን አምኖ ለመቀበል እንኳን በቂ ማሰቢያ ጊዜ ሳልወስድ ነው ኑሮውን የጀምርኩት:: ወይ ጎዳና? እንደ እኔ አይነት ሀብታም ከሆኑ በሀምሳ ሳንቲም መልኩና ቅርፁ ያልለየ ጎመን በዳቦ ቀርድዶ መዋል ይቻላል:: ግን ለእኔ ቅንጡዋ እንዴት ይበላልኝ? እናቴ የሚቀርብላት ምግብ ላይ አይደለም ፀጉር ተገኝቶበት ይቅርና ፀጉር የሚለው ቃል ከተሰማት እንኳን በእጇ ለመንካት እንደምትፀየፍ ስለማይና ዐምባም ፅዱ ነገር መመገብ ስለለመድኩ ቆሸሽ ያለውን ውሀና ጎመን በዳቦ መልመድ ከባድ ሆነብኝ::

*እናቴ ማንናት? ከየት ነው የተገኘሁት?* ጥቁር ከመሆኔ የተነሳ አንቺ ኢትዮጵያዊ አትመስይም የሚሉኝን ሰዎች እያሰብኩ የምን ሀገር ዜጋ ነኝ የሚለውን ማምሰልሰል የሰርክ ተግባሬ ሆነ:: በመጠኑም ቢሆን ቤተክርስትያን ግቢ መጠለሌ ተስፋ ሰጠኝ እንጂ በዕርግጥም አብድ ነበር:: ያም ሆኖ ግን ለእፍታው ከዚህ ሁሉ ስቃይ ራሴን ባጠፋ ጥሩ ሀሳብ መሆኑን አምሰለሰልኩት:: ሞት ግን አስፈራኝ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ማንና ምን መሆኔን ሳላውቅ መሞቱ አልመች አለኝ:: *ለሚ ሙሉ ጎደም ለናትና ለባተሽን ለፈባዐገሽ ማገኘት ለለብሽ!* አልኩ ለራሴ:: ሰው እንዴት ከየት እንደመጣ ሳያውቅ ወዴት እንደሚሄድ ወደማያውቅበት ዓለም ለመሸጋገር ይመኛል? *ለይሆንም!*

"ለመሆኑ ከየት የመጣሽ ልዕልት ነሽ?" ዝም

"እንዱ ኢፐ አድርጎ በቀይ አሰናበተሽ እንዴ?"

ራሳቸው እያወሩ ራሳቸው ይሳሳቃሉ:: ለአይነት እንኳ አንድም ሥነ ምግባር ያለው የጎዳና ተዳዳሪ የለም:: *እኔም ለቀይ እንደነሱ እሆን ይሆን?*

"ይመስለኛል ፎንቃ ሳስያዛት ጎረምሳ ከቤት ብር ስትሞጨልፍ ተይዛ ነው" አንዱ::

"እየነገርኩህ... ደህና አድርጎ ሰደቃዋን አሳይቷት ነው እንጂ" ሌላኛው::

"ግን የምን መንጠባረር ነው እኛን የምትጠየፊው?"

"ቆይ ዝም በላት ደህና አድርጌ ልቧ እስኪጠፋ..." መልስም አልሰጣቸው:: እንደውም እያደር የነሱንም ተረብ ሆነ የብርድና ውርጩን ስቃይ እየለመድኩት *ተንሸ ቀን ነው* እያልኩ ራሴን አሳመንኩት::

የያዝኩት ብር እየተመናመነ ሲሄድ ሀሳብ ገባኝ:: የፍስለታ ፆምን ለመያዝ ከመጡት ሰዎች እየተጠጋሁ የሚበላ እየለመንኩና መኝታ እየተጋራሁ ትንሽ ቀኑን ገፋሁት::

ይሁንና እያደር ሀሳቤ ሁሉ ለእኔ ለራሴ አልገባ ይለኝ ጀመር:: *ገንዘቡን በሙሉ ከጨረስኩት በምኔ ነው ሰብስ ገዝቼ በምባ ልገባ የምችለው?* ስል ራሴን ጠየቅኩት:: የግድ የተሻለ አማራጭ መፈለግ እንዳለብኝ ወሰንኩ:: ለሱ ደግሞ አዲስ አበባ ከመሄድ የበለጠ ጥሩ ነገር አልታይ አለኝ:: በስጋ የማይወልደኝ አሳዳጊ አባቴ ያስተዋወቀኝ የሱ ዘመዶች አዲስ አበባ ስላሉ ትንሽ ቀን እነሱ ዘንድ ባርፍና ለትምህርት ቤቴ የሚሆን ነገር ባገኝ ብዬ በማሰብ አምስት ብር በመክፈል ከናዝሬት ተሳፍሬ ወደ አዲስ



Scanned by CamScanner

አበባ ገሰገስኩ::

እንዳንዴ ወደ ዐምባ ልንገባ ስንል ወደ አዲስ አበባ ሄደን ጓደኞቻችን ቤት ወይም ለገሀር በመሰባሰብ ከብዙ ጓደኞቼ ጋር በመሆን ነበር ወደ ዐምባው የምንሄደው:: አሁንም ዐምባ መግቢያችን ቀን ገና ቢሆንም እንኳን ልጠይቃት ብዬ ጓደኛዬ እጅጋየሁ ቤት አመራሁ:: *ስሷን ሰላም ብያት ወደ ሰባቴ ዘመዶቼ ጋ ብደውል ይሻላል* ብዬ ብማሰብ:: የሷ ቤተሰቦች ቤት ጨርቆስ ነበር:: ቤታቸውን በደምብ ስለማውቀው እሷ ጋ ስሄድ ልጠይቃት የሄድኩ መስሏት እቅፍ አድርጋ ስማኝ አድረሽ ሂጂ ስትል ለመነችኝ:: ጥያቄውን በለስ የቀናኝ ያህል ነው በደስታ የተቀበልኩት:: ያን ዕለት እሷ ጋ አድሬ ሁለተኛውን ቀን ስደግም ግን እህቷ የእንጀራ አባታቸው እንደተቆጣ ስትነግረኝ "እደሪ ስላለችኝ ነው::" ብዬ ነገሩን በመሸፋፈን "በቃ እሄዳለሁ... ደህና እደሩ!" ብዬ ሚስጥሬን አፍኜ ተሰናብቻቸው ወጣሁ:: ወዴት እንደምሄድ ግራ ገባኝ:: እርግጥ ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ ስመጣ ገና የአባቴን ቤተሰቦች ለመጠየቅ ብዬ ቢሆንም ያገኘሁት አጋጣሚ ጥሩ ተስማምቶኝ ስለነበር ምንም ሳልጨነቅ እንደምቆይ ሀሳብ ይዤ ነበር:: አሁንም የትኛው ዘመድ ቤት መሄድ እንዳለብኝ ለማሰብ በ1 ብር ከሀምሳ ሳንቲም የገዛኋትን የማርያም ስዕል ይዤ ጨርቆስ ሀዲዱ ላይ ተቀምጬ አለቅስ ጀመር::

## -6-

እዛው ጨርቆስ ሀዲዱ አጠገብ ቁጭ ባልኩበት ዕንባዬ ከዝናቡና ንፍጤ ጋ ወደ አፌ እስኪገባ ድረስ ቀጥዬ ወዴት መሄድ እንዳለብኝ እያሰብኩ እያለ ነው የዙሪያሽወርቅ ልጆች አክስቴ የሚሏት ዘመድ ቤት ቦሌ አካባቢ መኖሩንና ስልክ ቁጥራቸውን አስታውሼ ለመደወል የተነሳሁት:: "አዲስ አበባ መጥቼ ልጠይቃችሁ ፈልጌ ቤታችሁ ጠፋብኝ..." ብዬ ስልኩን ላነሳው ዘመዳችን ነገርኩት:: "ቦሌ ፒኮክ መናፈሻ ብለሽ ነይና እዛ ውረጂ!" ብሎ መንገዱን በደንብ ገለፀልኝ:: በስንት እንክርት ፒኮክ ስደርስ ዘመዳችን ተቀበለኝ::

ቤት ስገባ ግን ዙሪያሽወርቅ ጋ ሲመጡ እንደምሆነው ነፃ ሆኜ አብሬያቸው ለመጫወት አልቻልኩም:: ሰምተው ሊሆን ይችላል ብዬ በማሰብ በነገሬ ላይ ሁሉ ቁጥብ ሆንኩ:: ሁለት ቀናት እነሱ ጋ ካደርኩ በኋላ "ክረምቱን እዚህ ከምትቀመጪ ስራ ጀመሪ" ሲሉኝ "እሺ" አልኩ:: የአክስቴ ልጅ ተኮላም ስራ አስገባት ተብሎ ቦታውን ሊያሳየኝ ወሰደኝ:: ተኮላ የአራተኛ ዓመት የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነው:: ዘበኛ ሰፈር ወደሚባለው ሰፈር ትንሽ ልብስ በፌስታል ይዤ ሄድኩ:: ይዞኝ የሄደው ሰው ቤት መሆኑንና የተገኘልኝ ስራ የቤት ሰራተኝነት እንደሆነ ሳውቅ ደነገጥኩ:: *ምን ስራ ለችባለሁ?*

"ስራ ትችያለሽ?" አሉኝ ቀጣሪዎቼ::

"አዎ!" ማረፊያ እስካገኝሁ ድረስ ምን ማለት እችላለሁ?

"እንጀራ መጋገር ትችያለሽ?"

"አይ እንጀራ መጋገር እንኳን አልችልም:: እሳት ሲነካኝ ስለሚነስረኝ..." ስል ከአፌ ነጥቀው:- "አይ ግድ የለም... እስክትለምጂው ነው!" አሉኝ:: የቤት ሰራተኛ ቀጣሪዎች መጀመሪያ ጥሩ ፊት አሳይተው እየቆዩ መከራ እንደሚያመጡ ያወቅኩት ከዛ በኋላ ነበር::

ስለብር አላወራሁ፣ ስራ እንደማልችልና ዐምባ አሞላቅቆ ያሳደገኝ መሆኑን አልተናገርኩ ብቻ "እሺ" ብዬ ገባሁ:: የመኝታ ክፍሌን ሲያሳዩኝ ደስ አለኝ:: *የዐምባ ልጆች እንዳያዩኝ እንጂ ደሂስ ምንም አይደደስም::* እንደገባሁ ያገር ልብስና ጋቢ አጠብኩና ስጨርስ ቤቱ በሰም እንዴት መወልወል እንዳለበት አሳይተውኝ መወልወል ጀመርኩ:: ትንሽ እየሰራሁ ሳለሁ አቅም እያጠረኝ ሄደ:: *ምንድነው ችግሬ?* መቼም ኢህአዴግ ከገባ ጀምሮ ክፍላችንንና ልብሳችንን ማፅዳት የኛ ስራ ስለሆነ በመጠኑም ቢሆን ለምጄዋለሁ:: አሁን ግን ለምን አቅም እንዳጠረኝ ባልገባኝ ሁኔታ ራሴን ስቼ ወደቅኩ:: ርሀብ ቢኖርብኝም ያን ያህል አጥወልውሎ ለመጣል የሚያደርስ አልመሰለኝም ነበር:: ቤቱ ውስጥ የነበሩ ሁለት ሴቶች "ምን ሆነሽ ነው?" ሲሉ ደጋግፈው አነሱኝ:: በጣም ሲያስመልሰኝም አይተው ***ርሀብ ይሆናል*** በሚል አስበው ይመስለኛል ድንች ሰጥተውኝ በላሁ::

ጋቢና ጅንስ ማጠብ፣ የነሱ ፍላጎት የሆነ ምግብ ማዘጋጀትና እንደባለሙያ

መምሰል የተራራ ያህል ገዝፎ እየተፈታተነኝ እያለ አንድ ቀን የቤቱ ልጆች "ወርቅ ጠፋን!" ብለው ይጯጯሁ ጀመር:: ወዲያው የነሱ ጩኸት ሳይበርድ አድርሳት ተብሎ የተላከው የዩኒቨርስቲ ተማሪው ተከላ መጣ:: ሳየው ገና ደነገጥኩ:: የመጣበት ምክንያትም ግልፅ ሆነልኝ:: *ሌባ ሆኛለሁ ማለት ነው?* ውስጤ የፌዝ ሳቅ ሲያስተጋባ ይታወቀኛል::

"ሌላ ማን ሊወስደው ይችላል?"

"ምን አይነቷን የለየላት ሌባ ነው ያመጣህልን?" ተንጫጩ:: ሶስት የደረሱ ሴቶች፣ ሁለት ህፃን ሴቶች፣ ከሴቶቹ መለስ ያሉ ሁለት ወንዶች... ቤቱ ተቃጠለ:: በተለይ ትላልቆቹ እየተቀባባሉ ሲናገሩ በፍርሀት አይን አይናቸውን አይ ነበር:: "እኔ አልወሰድኩትም!" ለማለት ፋታ አላገኘ ሁም:: ልብሴ ያለበትን ፌስታል አውጥተው እያራገፉ ወርቁን ይፈልጉት ጀመር:: የሚሆነውን ከመጠበቅ ውጪ የማደርገው ስላልነበረኝ መፈጠሬን ጥላቻ ውስጤ ምሬት እየረጨ ነበር:: "ወደዛ ይዘሀት ሂድ!" ሲሉት ተንደርድሮ መጥቶ አሰሪዎቹ በተሰበሰቡበት በጥፊ ደረገመብኝ:: እንባዬ እየተዝረበረበ እጄን አፈፍ አድርጎ እየጎተተ ይዞኝ እየወጣ "ይቺ ዙሪያሽወርቅ ናት ማንንም ለቃቅማ አምጥታ እንዲህ ጉድ የምታደርገን!" ሲል አጉረመረመ:: የሰራሁበትን የሳምንት ሂሳብ ሳልቀበል ሌባ ተብዬ ከመሸኘቴ በላይ ውስጥን የሚያቃጥል ንግግር ከአክስቴ ልጅ ተብዬው ስሰማ አመመኝ:: እየጎተተ ሲወስደኝ *ዕስ ነህ ዙሪያሽወርቅ ናት ስኒንም ለዚህ ጉድ የዳረገችኝ::* ስል እያሰብኩ እንዳመፀኛ ፍየል እየተጎተትኩ ሄድኩ::

ይዞኝ የሄደው የማላውቀው ቤትና ሰፈር ነው:: ከዛው ከዘበኛ ሰፈር ብዙ

አይርቅም:: ውስጥ ለውስጥ ስለወሰደኝ ትክክለኛውን ቦታ አላወቅኩትም:: እኔ የምጠብቀው ቦሌ ወዳለው ቤት ይዞኝ እንደሚሄድ ነበር:: ዝናብ እየደበደበንና ጭቃ እያላቆጥን ስንሄድ "ወዴት ነው የምትወስደኝ?" ብዬ ስጠይቀው ለጉድ ገላምጦ ጎተተኝ:: አንድ የግቢ በር እንኳን ወደ ሌለው ቤት ወስዶኝ ሲያንኳኳ ተከፈተለት:: አሁን እንግዲህ ለመደብደብም፣ ለመግደልም መብት ያለው እሱ ነውና የሚደርስብኝን በፀጋ ለመቀበል ራሴን ከማዘጋጀት የዘለለ የማደርገው አንዳች ነገር አልነበረም:: *ግን ለምንድነው ሴባ ሁሉ እንዲደበድብ የሚሆነው? ማለቴ ሴባን ሴባ ማሰት ያስተምረው ይሆን? የሴብነቱን ምክንያት መርምሮ ውጤት ላይ ያደረሰውን ችግር እንዲፈታ መርዳት እንጂ?* የኔ አጉል መመራመር ትርጉም አልነበረውም:: ይዞኝ ወደገባበት ቤት እግሬን አስገባሁ::

"እህቴ ናት ያልኩህ ልጅ ናት ተዋወቃት!" አለው ቤቱ ውስጥ የነበረውን ልጅ:: ተዋወቀኝና ሻይ ቡና በይም ሳይለኝ ጥሎኝ ወጣ:: ልክ የተዋወቀኝ ልጅ እግር ወጣ እንዳለ ተኮላ በሩን ቀረቀረው:: *በቃ ቀጥቅጦ ሊገለኝ ነው::* ፍርሀት መንቀጥቀጥ ለቀቀብኝ:: በሩ ተዘግቶ የሚወርድብኝን ዱላ ብጠብቅም- አልነበረም:: ድንገት ድንፋታ ቅልቅል የሆነው አስገምጋሚ ድምፅ ግን ሌላ ተንኮል እንደተሸረበብኝ አመለከተኝ:: የቤቱ በር የራሱን የእንጨት መልክ የያዘና ምንም ቫርኒሽ ሆነ ቀለም ያላረፈበት ነው:: አንድ አልጋ፣ ትንሽ ኮመዲኖ፣ በመጋረጃ የተከለለ በጣም ትንሽ ለመታጠቢያ ያህል የምታገለግል ጓዳ ያለው ነው:: ቤቱ ውስጥ የተነጠፈው ምንጣፍና የግድግዳው ውሃ ሰማያዊ ቀለም ቤቱን አደብዝዘውታል:: የካልሲና የወንደላጤ ጠረን ክፍሉን ስለሞላው ርብሽ የሚያደርግ ስሜት

ይፈጥራል፡፡

"የምልሽን ተግባራዊ ማድረግ ከቻልሽ ከኛ ጋር እዚሁ ቆይተሽ ወደ ዐምባ በሰላም መመለስ ትችያለሽ!" ደስታም ሆነ ሀዘን ምንም ስሜት አልተፈጠረብኝም፡፡ ሀሳቡን ማስጨረስ ስለነበረብኝ ያልገባኝን ነገር እንዲያብራራልኝ በፀጥታ ጠበቅኩት፡፡

"በይ በሀሳቤ ከተስማማሽ አውልቂ!" አለኝ፡፡

"ምንድን ነው የማወልቀው?"

"ልብስሽን፡፡"

"ምን ልታደርግ?"

"አሳይሻለሁ!" ተጠጋኝ፡፡

"ኡኡኡ!" እዬዬን አቀለጥኩት፡፡ *ልብስሽን ለውልቂ?* በህይወት ዘመኔ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ያለ አስደንጋጭ ጥያቄ ቀረበልኝ፡፡ ሳስበው ድንግል ነኝ፡፡ ግን ምን አይነት ምክንያት ስለወሲብ እንዳስብ ያደርገኛ ልና ሳምሰለስለው እከርማለሁ? እንደው እንደዘበት ቀሚስ ተወልቆ የሚፈፀም ተራ ጉዳይ ነው እንዴ? ምነው እስከዛሬ ድረስ ዐምባው ያሉ ሰዎች አላስተማሩንም? ነው ወይስ አጠገቤ ቆሞ "አውልቂ!" እንደሚለኝ እንደ ተከላ ያለ ዕውቀት እንዲኖረኝ ዩኒቨርስቲ መድረስ አለብኝ? *ሳይሆን ለይቀርም!*

ጨኸቴ ምንም አልረዳኝም። ቤቱ ራሱ የተመረጠው ለዚህ ዓላማ ተብሎ ሳይሆን አይቀርም። ብጮህ፣ ባቀልጠው እሱ ግድ ሳይሰጠው ግዳይ እንደጣለ አንበሳ አጠገቤ እየተንጎማለለ *ጉድሽን ስያስዙ* የሚል መሰለኝ። ጨኸቴ ዋጋ ሲያጣብኝ ልመና ጀመርኩ። "በናትህ... እናት የለህም?" *ወይ ጉዴ! ለንዳሰቸው'ኮ ለሳምሬ ለውቃለሁ።* የታቦታት መዐት፣ የልመና ዶፍ ባወርድበት ትርጉም ለሌለው ነገር አፌን መክፈቴ አበሳጨው መሰለኝ አፌ ውስጥ ጨርቅ አድርጎ ፀጥ አሰኘኝ። በፍቃዴ ልብሴን እንደማላወላልቅ ሲገባው እሱ ገባበት። ታገልኩ። የምችለውን ያህል ታገልኩ። ግን ትግሌ በዕድል የታጀበ አልነበረም። ዙሪያሽወርቅ *ደታደሱታፀ ለንጂ ሰደታገሱተም* የምትለው አባባል ውስጤ ሲያቃጭል ተስፋ ቆረጥኩ። የውስጥ ሱሪዬን ለመቅደድ ሲታገል እጄን የያዘ እጁን ነፃ ሲያደርገው አፌ ውስጥ የጠቀጠቀውን ጨርቅ ስቤ አወጣሁትና። ቁና ቁና እየተነፈስኩ ዝቅ ብዬ ስመለከት የውስጥ ሱሪዬን ተቀድዶ መውደቅ አየሁ።

በትግል ላሸንፈው እንደማልችል ሲገባኝ የልመና መዝገበ ቃላት የሆንኩ ያህል በሰባት ቤቱና በአርባ አራቱ ታቦት ሳይቀር ለመንኩት። ብቻ ስሜቱን ሊያረካ ሲጣደፍ አዕምሮዬ ውስጥ በድንገት የተከሰተውን ሀሳብ ሳላውቀው ተፋሁት። "ኤድስ አለብኝ ተኮላ!" ከሰውነቴ ጋር የተጣበቀ ሰውነቱ ብርግግ ሲል ታወቀኝ። ንዴቱን ለመግለፅ ጊዜም ሳይወስድ ቦክስ ቅልቅል ጥፊ ደረገመብኝ።

በወቅቱ ኤድስ የሚለው ቃል የራሱ የሆነ የሚያስፈራ ግርማ ነበረው። ጥቅጥቅ ባለ ፂሙ ላይ ፀይምና ደልዳላ ቁመቱ ጋር ሲታይ ያምራል·

ተኮላ:: አሁን ግን በሰማው ነገር ሲናደድ ትላልቅ አይኖቹ ተጉረጥርጠው አስጠላ:: ከወገቡ በታች ባለው ራቁት ገላና ከሚያስፈራው ዘንዶ ጋር ሳየው ሊያስመልሰኝ ደረሰ:: አዘውትሮ ምላሱን ማኘክ እንደሚወደው አሁንም እንደዚያው እያደረገ በተለመደ ተብታባ አንደበቱ:-

"እንዲህ... እንዲህ... እነሳስተሸኝማ አትቀሪም... አትቀሪም!" ሲል እሱ እንዲደረግለት የሚፈልገውን ነገር ነገረኝ:: ለልምዴ አይደለም ለሀሳቤ እንኳ እንግዳ የሆነውን ይህንን ችግር የምቋቋምበት መላ አልነበረኝም:: ኧረ ምን የምቋቋምበት... የሚፈልገውን የማድረግ ችሎታው እንኳ የለኝም::

"የታመቀ ስሜቴን... ስ... ስ... ሜቴን ማርገብ ነው የምፈልገው" አለኝ ልበል? ቋንቋውን በጨዋ ደንብ ላስቀምጠው እንጂ ያለኝ ለመስማት የሚዘገንን ነበር::

"ስለዚህ በእጅሽ እንትን... እንትን አድርጊልኝ..." እንቢ ብዬ ቁጣዬን ገለፅኩ:: ጩኸቴን አሰማሁ፣ ትግሌን ቀጠልኩ::

"ተ... ተ... ተተ... ተይው በቃ! በጀርባ ዙሪና አደርጋለሁ" ኡኡ ብዬ ስጮህ መታኝ:: ምንም የተሟጠጠ እንኳ ተስፋ የሌለኝ መሆኑን አመንኩ:: ብጮህ የሚደርስልኝ ከሌለ፣ የውስጥ ሱሪዬና ቀሚሴ የተቀደደና የወለቀ ከሆነና ተኮላ ካለበት የስሜት ውጥረት ካልተነፈሰ የማይመለስ ከሆነ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ? ጥያቄው ደግሞ ወይ የሚፈልገውን ላደርግለት ይገባል ወይም የሚፈልገውን ሲያደርግብኝ ይችላል:: መወሰን ነበረብኝ::



Scanned by CamScanner

"ምራቅሽን እጅሽ ላይ ትፊ!"

እንዳለኝ አደረግኩ።

"ላዩ ላይ ቀ... ቀ... ቀቀ... ቀቢና አሻሺ፣ ምቺው!" ታገልኩ። ምንም ለውጥ አልነበረም። ብቻ እየቀጠቀጠኝ "በደንብ!" ሲል ይጮህብኝ ነበር። እንቢ ሲለው ሳሙና ቀብቶ መጣና በድጋሚ እንደበፊቱ እንዳደርግ ጠፈጠፈኝ። የሚፈልገውን አደረግኩለት። ብቻ ፊቴ ላይ የሆነ ነገር ጩር እያለ ሞቅ ያለ ፈሳሽ ሲሞላው ይታወቀኛል። እያለከለከ ዝልፍልፍ ብሎ አልጋው ላይ ተሰተረ። *ለካ ይሀን ያህል ቀባል ነበር?* ስል አሰብኩ። ቢያንስ ድንግል እንደሆንኩ ነው የምቆየው። ቢያንስ ዕምባ ስገባ በር ላይ ሽንት ምርመራ ተደርጎልኝ አርግዛለች ተብዬ አልባረርም። እንዴ እግዚአብሔር በስንቱ ሊቀጣኝ ይገባል? ይመስገን። ክብሬን ጥዬ ክብር ካተረፍኩ ምናለ?

"ሂጂ ታጠቢ!" ሲል ጮኸብኝ።

የሚዘገንነውን ነገር ከፊቴ ላይ አፀዳሁት። አይኔ በዕንባ ብዛት አብጦ የተላቆጠ በርበሬ መስሏል። ፌስታል ውስጥ ያለውን አንድ የውስጥ ሱሪ አውጥቼ በማድረግ ቀሚሴን ለበስኩ። ከዚያ በኋላ ለሚፈልገው ነገር ሁሉ ምቹ እንደማልሆንለት ሲገባው "ወደኛ ቤት ይዤሽ እሄዳለሁ!" አለኝ። "አንድ ስላደረግነው ነገር ብታወሪ ሬሳ ነው የማደርግሽ!" ሲል አስጠነቀቀኝና ይዞኝ ወደ ቤት ሄደ።

"ምን ሆና አመጣሀት?" ሲሉ ጠየቁት ቤት ያሉት።

"ስርቃ!" አላቸው:: ሽምቅቅ አልኩ *የሚሰርቁ ሰዎች ሌባ ሲባሉ ምን ያህል ይሸማቀቁ ይሆን?* አይጥሉኝ... ውጪ የራስሽ ጉዳይ አይሉኝ ነገር ይሉኝታ ያዛቸው፣ በቃ ኑሪ አይሉኝ ምቾት ያልተሰማቸው መሰሉኝ:: የሆነች አንዲት ክፍል ውስጥ ፍራሽ ነገር ሰጥተውኝ አንጥፌ ተኛሁ:: ምንም ግን መረጋጋት አልተሰማኝም:: ሌባ እንዴት መረጋጋት ሊሰማው ይችላል? መስረቁ እያባነነ ጤና ይነሳዋል:: እኔ ደግሞ መባሌ የሌባ ያህል ውስጤ ሰላም ነሳኝ:: ራሴን ተጠራጠርኩት *ምናልባት እንደው ከደረሱብኝ ፈጣንና ከማይታመኑ ለውጦችና ክስተቶች ጋር የተነሳ የማደርገውን ሳላውቅ በመቅረቴ ሰርቄ ይሆን እንዴ?* በራሴ ሀሳብ ሳቅ አፈነኝ:: *ምናለ ሰርቄ ሌባ በተባልኩ?* ስል ሀሳብ ገባኝ::

እዛው ግቢ ውስጥ ያለ ተሾመ የተባለ ተከራይ ሁኔታዬን አይቶ አሳዝኜው ይሁን ወይም የሰማው ነገር ኖሮ ምክንያቱን ባላውቀውም የተራረፈውን ምግብ ይሰጠኝ ስለነበር ብዙም ያስቸገርኳቸው አልመሰለኝም:: ውስጤ ግን ምቾት ስለነፈገኝ ሄጄ ላስቸግራት ወደማልፈልገው ጓደኛዬ ብርቄ ጋ ሄድኩኝ:: ለብርቄ እናት ጥሩዬና ለራሷ ለብርቄ ከእናቴ ዙሪያሽወርቅ ጋ ትንሽ ተጋጭቼ ነው የመጣሁት ብዬ የደረሰብኝን አጫወትኳቸው:: በፍፁም ግን እናት እና አባት አልባ፣ የመጣሁበት የማይታወቅ መሆኔን አልነገርኳቸውም:: እኔ ውስጥ የሚቀበር ፈንጂ ብቻ እንዲሆን ነው የፈቀድኩት:: *የታመቀ ፈንጂ!*

የጓደኛዬ ብርቄ እናት ጥሩዬ በጣም አዘነች:: ዐምባ እስከምንገባ ድረስ እሷ ቤት ብቆይ ችግር እንደሌለውና ዐምባ ስንገባም ልብስ ልትገዛልኝ እንደምትችል ነገረችኝ:: ደስ አለኝ:: ቢያንስ የቀሩኝ ቀናት እስኪያልቁ

ማረፊያ ማግኘቴ ትልቅ ነገር ነበር:: የዐምባ ልጆች ታሪካችን ደግሞ መስከረም 3 ትምህርት ቤት ቢጀመርም ዘግይተን በሃያ አካባቢ ስለሆነ ዐምባ የምንገባው ሊደርሱብኝ ከሚችሉ በርካታ ችግሮች ሁሉ ነውና የታደገችኝ በደስታ ውስጥ ብገኝ አይደንቅም::

ወደ አክስቶቼ ቤት ሄጄ "ስራ ኮተቤ አካባቢ አግኝቻለሁ::" ብያቸው በላስቲክ ውስጥ ያለኝን ልብስና የማርያም ስዕል ይዤ ልወጣ ስል አክስቴ ሀምሳ ብር ለማንኛውም ብላ ሰጠችኝ:: ሊደፍረኝ የሞከረው ተኮላም ለታክሲ ብሎ ሰላሳ ብር ሰጠኝ:: ብሩን ቀዳድጄ ላዩ ላይ ብበትነው በተደሰትኩ:: ሆኖም ግን መውደቂያዬ የማይታወቅ ሰው ነኝና ለንቀት ቦታ ልሰጠው እንደማይገባ ራሴን አሳምኜ ብሩን ይዤ ወጣሁ::

ጥሩዬ ቤት በነበርኩባቸው ቀናት ሁሉ አንዳች የጎደለብኝ ነገር ባይኖርም ደስታ ግን በጣም ነበር የራቀኝ:: ሰው ከየት እንደመጣ፣ ለሱ መገኘት ምክንያት የሆኑትን ሰዎች እስካላወቀ ድረስ እውነተኛ ደስታ ከየት ያመጣል? ማልቀስ፣ እንቅልፍ ማጣት፣ የመመገብ ስሜት መጥፋት በነገሮች ላይ ቁጥብ መሆን... የቅርብ ጓደኞቼ ሆነው አረፉት:: ያም ሆኖ ግን ዐምባ ስገባ ከመቼውም በላይ አምሮብኝና ወፍሬ በመግባቴ ተገረምኩ:: *ሰውን ግን በስጋው መገመት እንዴት ይከብዳል?*

## -7-

*እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲሁም ጤዛ ነሽ* ነው የሚባለው? ባሰብኝ:: ሀሳብ ሰቀቀን ውስጥ ከተተኝ:: ዕለት በዕለት መታመም ስራዬ ሆነ:: ጤነኛ ሆኜ የዋልኩ ቀን እኔ እራሴ እደነግጥ ጀመር:: ክፍል ከምገባበት ቀን የማልገባበት ባሰ:: ለመኖር፣ ለራሱ ለህይወት ትርጉም አጣሁለት:: ለካ መኖር ማለት የመኖርን ምክንያት ማወቅ ነው:: ራሴን ለማጥፋት ወኔ ካነሰኝ የመኖሬ ምክንያት ሊያሳውቀኝ የፈለገው ነገር አለው ማለት ነው:: አለበለዚያ ምን ሊያስጨንቀኝ ይችላል? ራሴን እንደሳር የበቀልኩ አድርጌ እስከተቀበልኩት ድረስ መሞትና መኖር ምን የተለያየ ስሜት የሚሰጥ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል? ልጁ አያለቅስ፣ የተባዛ ዘሬ አይጨነቅ... ጣጣ ፈንጣጣ የለብኝ:: ለመሞት ምንድነው ወኔቢስ ያደረገኝ?

ይመስለኛል. ከህፃንነቴም ጀምሮ ህመምተኛ የነበርኩት ለይቼ ላውቀው ያልቻልኩት አንዳች ምክንያት ስላለ ነው:: አሁን ግን ግልፅ ሆኖልኛል:: ቢሆንልኝም ቅሉ ለመኖሬ ምክንያት የሚሆነኝ በቂ ነገር አልነበረም:: ለመሞትም ድፍረት አልነበረኝም:: መወሰን ሲያቅተኝ ደግሞ በዘፈቀደ መኖር ጀመርኩ:: መማር ምኔ ነው? ስለነገ ማሰብ ምን ይጠቅመኛል? ሰው ትናንትና ከሌለው ነገ እንዴት ሊኖረው ይችላል? ዛሬን ኖሮ ነገ



Scanned by CamScanner

ጥሎት ለሚያልፈው ለራሱ ቀንና ለመጪው ነገ መሠረት እንዲሆነው ማድረግ ይችላል:: ያኔ ዛሬን ልወቀውና ለነገ መኖሬ ምክንያት ልፍጠር ብዬ ዐምባው ስለ እኔ ያለውን ፋይል እንዲያሳየኝ ብጨቀጭቅ ሰሚ አጣሁ:: ከዘፈቀደ ኑሮዬ ሊገታኝ የቻለ ታሪክ ጠፋ::

አስተማሪው ሲያስተምር ክፍል ውስጥ የአፋር የመሰለ መፋቂያ ይዤ ቤተሰቦቼ በምናቤ እኔ ከጥርሴ ጋር እየታገልኩ ስለማላውቃቸው እየፈጠርኩ በሀሳብ እምስልስሎሽ ውስጥ መዳከር ተግባሬ ሆነ::

"እማዬ?"

"ወዬ ልጄ!"

"አባቴ ማን ነው?"

"ለምን ጠየቅሽኝ?"

"ለማወቅ ነዋ:: ለምን ወልደሽ ጣልሽኝ?"

"ላሳድግሽ አልቻልኩም"

"አባዬ ምን ይመስላል?"

"ጠቆር ብሎ ሴኔጋላዊ ይመስላል"

"አንቺም እኮ ጥቁር ነሽ"

"አዎ!"

"ግን እማዬ ለምን በመንፈሴ ብቻ ትመጪያለሽ?"

"መንፈስ ነኝ!"

"እና ልገልሽ አልችልም ማለት ነው?"

"አዎ ልጄ... ልትገይኝ አትችይም::"

ራሴ በምፈጥረው ዓለም እየዳከርኩ ሌላ ስብዕና ውስጤ የፈጠርኩ ያህል ርብሽ ማለት አበዛሁ:: ብዙ ጊዜ ራሴን ሀሳብ ውስጥ የማገኘው መፋቂያ አፌ ውስጥ ሲገባ ነው:: አንድ አማርኛ መምህራችንማ "ይሄን ስንዝር የሚያክል መፋቂያዋን መዘዘችው!" እያለ በተማሪ ያስሾፍብኝ፣ ልቤ እስኪጠፋ በቀበቶ ይገርፈኝ ነበር:: የተማሪ መተረቻ፣ የአስተዳደር መጠቋቆሚያ ብሆንም ግድ አልሰጠኝም:: ፈተና ላይ ቀርቤ አስተማሪ ገና አሰራሩን አብራርቶ ሳይጨርስ እኔ ፈተናውን አስረክቤ እወጣለሁ:: ነገ ተስፋ የሌለው ሰው የዛሬ መበላሸቱ ለምን ይቆጨዋል? እርግጠኛ ነኝ ማንም ግን "ልክ አይደለሽም... ትምህርትሽን በደንብ መከታተልና ራስሽን ማረጋጋት ነበረብሽ!" ብሎ ሊፈርድብኝ እንደሚቋምጥ:: የመኖር ትርጉሙን ሊያስረዳኝ እስካልቻለ ድረስ ምክሩ ለእኔ ምንም ነው- መኖር አስጠልቶኛል!

አንዴ ወባ አለብሽ፣ አንዴ ጭንቀት ነው፣ አንዴ ምንትሴ፣ አንዴ

ቅብርጥሴ እየተባልኩ የጉልኮስ ቀበኛ ሆንኩ። አንዴማ ዘጠኝ ጉልኮስ ተከታትሎ ተሰጥቶኝ እጄ ከመደንዘዙ የተነሳ ፈፅሞ አልንቀሳቀስ ሲል አስረኛውን በጣጥሼ ፖፖ ውስጥ አደረግኩት። በዚህ አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ነው ዐምባው ሊበተን ይችላል የሚል ጭምጭምታ የሰማሁት። *በስንቅርት ባይ ጀር ደገፍ* ነው የሚባለው ተረቱ? አስታውሳለሁ የዐምባውን መበተን አስመልክቶ ኃላፊውን ስናናግራቸው "አርፋችሁ ተማሩ ማነው እንዲህ እያለ የሚያወራው? እናንተ ወፍ ናችሁ እንዴ የምትበተኑት?" ብለው ነበር ያረጋጉን። ሰማንያ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት የዕረፍት ጊዜ ሲደርስ ግን ከወትሮው በተለየ መልኩ ፎርም ያስሞሉን ጀመር።

## -8-

ሰማንያ ዘጠኝ ዓ.ም. ክረምትን እዛው ዐምባ ነው ያሳለፍኩት:: ባለፈው ዓመት ክረምት ላይ የቀመስኳትን መከራ እኔ ነኝና የማውቃት የታባቴ ሄጄ አሳልፋለሁ? አርፌ ዐምባዬ መከተት እንጂ:: ደ'ሞ አባት እንዳለው ሰው አባቴን እሰድባለሁ እንዴ? ብቻ ጉዴን ደብቆ የያዘው ዐምባ ውስጥ እያለሁ ኖሬ ብቀበርም ግድ በማይሰጠኝ ሁኔታ ከጥቂት ታዳጊዎች ጋር እዛው ቀረሁ::

ሁልጊዜም የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስርጭት ካለ ቋንቋውን አወቅነውም አላወቅነውም ተከፍቶ ማየታችን የተለመደ ነው:: ብዙ ጊዜ 'ትሽ' የሚለውን ድምፅ እስክንሰማ አይናችንን እንደተከልን እንቀራለን:: እንደተለመደው ሁሉ ዛሬም አይናችንን ተክለን እየተመለከትን እያለ ነው የብዙዎቻችንን ህይወት የሚለውጥ አንድ ማስታወቂያ የተላለፈው:: ሁላችንም ደነገጥን!

ድንጋጤው ግን እኔ ላይ ባሰ:: መብረቅ ድባቅ የመታኝ ያህል ነው ኩምሽሽ ያልኩት:: ለመጀመሪያ ጊዜ ድንጋጤ አቅል እንደሚያሳጣ፣ ሩህ እንደሚያስት ተረዳሁት:: *ለምንድነው ሀይወት እንዲህ መጥፎ ካባዋን*



Scanned by CamScanner

የኔ ብጤ ብዙዎች የካባው ተቋዳሽ ሊሆኑ ሲያበሰብሱኝ ያስችሉ? ሌሎች የኔ ብጤ ብዙዎች የካባው ተቋዳሽ ሊሆኑ ቢችሉም እንኳ እኔ የማውቀው የራሴን ብቻ ነበር:: የጠረጠርነው ነገር ባልጠበቅነውና ባልገመትነው መንገድ አስደንጋጭ ሆኖ ሲመጣ እንዴት ነው መቀበል የሚቻለው?

*ለሲተዮጵያ ህፃናት ዐምባ ነዋሪዎች በሙሉ:: ከዚህ (?) ቀን ጀምሮ ታዳጊዎችን ከቤተሰብ ጋር የምናገናኝ መሆኑን እየገለፅን ታዳጊዎቹ በዐምባው ውስጥ በነበሩቸው ቆይታ ከቤተሰብ ርቀው ስላደጉ ከሰው መቀሳቀስ ስቅቷቸው ባህርያቸው ተለውጧል:: ያለፈው የደርግ መንግስት ባደረሰባቸው ተፅዕኖ በርካታ ህፃናት የስዕምሮ ዝግመት የደረሰባቸው ሲሆን ሌሎቹም ለረዥም ጊዜ በዐምባው በመቆየታቸው ከማህበረሰቡ የተለየ ለይነት ችግር እየታየባቸው ነው:: ስለዚህም የክረምቱን ወራት ከቤተሰብ ጋር ለማሳለፍ በየቤተሰብ የሔዳችሁ ተማሪዎች ባሳችሁበት ወረዳና ቀበሌ የወሳጅ ተጠሪ እየያዛችሁ እንድትመዘገቡ::* የሚል መንፈስ ያለው ማስታወቂያ ነበር በቴሌቪዝን የተላለፈው::

ከዐምባው መፍረስ በኋላ ያለው ምክንያት ለእኔ ምን ስሜት ይሰጠኛል? ሁሉም ለክረምቱ ዕረፍት ቤተሰቦቻቸው ዘንድ ስለሄዱ በጣም ጥቂት ታዳጊዎች ብቻ ነበር የቀረነው:: ለጉድ ተላቀስነው:: ቤታችን ሲፈርስ፣ ቤተሰባችን ዳግመኛ ሊገናኝ በማይችልበት ሁኔታ የሚበተን መሆኑን ስንሰማ ምንድነው ሊፈጠርብን የሚችለው? በተለይ እኔን ከየትኞቹ ቤተቦቼ ነው መንግስት ሊያገናኘኝ የሚችለው? በእውነት እናትና አባቴ በህይወት ኖረው በየትኛውም አለም ሆነው ልገናኛቸው ከቻልኩ እድለኛ



Scanned by CamScanner

ነኝና የዐምባው መበተን የዓለም መጨረሻ አይሆንብኝም:: አለበለዚያ ግን ነው- የህይወቴ መጨረሻ እየተቃረበ::

ከአስተዳደር እስከታዳጊ፣ ከወታደር እስከ ዘብ እዬዬ ሆነ:: ሬሳ የሚወጣበት ግቢ መሰለ:: ኢህአዴጎቹ ከኛ ጋር ተላምደዋል፣ ግቢው ውስጥ ያሉት ወልደዋል... ህይወት በዐምባው ተሳስራ ነበር:: የዐምባው መበተን የታዳጊው ሀዘን ብቻ አልነበረም:: ታዳጊው ላይ ግን የከፋ ነበርና ምሬቱ፣ ሀዘኑ፣ የመለየት ዳዋ የሚፈጥረው ቅስም መሰበር ሁሉ በግልፅ እየታየ አስቀያሚ በሆነ ስሜት ውስጥ ያስዋኝ ነበር::

በሚገርም ሁኔታ ከዚያን ዕለት በኋላ በቴሌቪዥን የሚቀርበው ዘፈን ሁሉ የሀዘን፣ የእሮሮ፣ የመለየት ዳዋ የተመላበት ሆነ:: ፎርም አዘጋጅተን ዐምባው ውስጥ ያለነው አድራሻ መለዋወጥ ጀመርን:: እኔ ግን እዚህ እገኝበታለሁ የምለው አድራሻ ስላልነበረኝ "ፖሊስ ፕሮግራም ላይ ታገኙኛላችሁ!" ነበር የምለው:: መቼም በወንጀል ተሰማርቼ ወይም ጎዳና ላይ ወጥቼ ካልተገኘሁ ሙያ የለኝ በሙያዬ ተቀጥሬ አልገኝ፣ ዘመድ የለኝ አንዱ ቤት አልጠጋ... ማረፊያ ጎጆ ያጣች ወፍ ነኝና የምበርበትና የማርፍበት ስለማይታወቅ አድራሻ መስጠት አልቻልኩም::

*የዐምባው ዳኛ* የሚለውና የኤፍሬም *ታምሩ ስንዴት ነሽ ሀገሬ* የሚለው 'እንዴት ነሽ ዐምባዬ' በሚለው እየተተካ ዘፈኑን አስነካነው:: ያለንን ዕቃ እየሸጥን ፊልም እየሞላን በጊቢው ውስጥ እየተዟዟርን ይሄንን ፎቶ ተቀጨቀጭነው:: በረንዳ እያፀዳን፣ ሽንት ቤት እያጠብን፣ ገላችንን



Scanned by CamScanner

እየታጠብን፣ ምግብ እየበላን፣ ፎቶ መነሳት፣ ከወንዶቹ ጋር አሸሸ ገዳሜ ማለቱን ተያያዝነው::

ዜናው በተላለፈ በአራተኛው ቀን ይመስለኛል በሁለገብ አዳራሽ የዕራት ግብዣ የተጠራነው:: የግብዣው ዓላማ ባይገባንም ጤናማ እንዳልሆነ መገመት ግን አላዳገተንም:: ራቱ ካበቃ በኋላ ግጥምና አንዳንድ ቀልድ እንድናቀርብ ብንጋበዝም ማንም ቀልድ ሊመጣለት አልቻለም:: ምናለ ዕሮሮና ሙሾ ተብሎ ቢሆን? አዳራሹን የዓለም ፍፃሜ መድረክ አድርገነው ቁጭ ባልን?! እኔ የመግጠም ተሰጥኦው ስለነበረኝ፣ ድራማና ሙዚቃ ክበብ እንዲሁም ሚኒሚዲያ ውስጥ እሰራ ስለነበር ግጥም እንዳቀርብ በመጋበዜ 'እንባ እንባ ይለኛል' የሚል ግጥም አቀረብኩ:: ሌሎች መምህራኖችም ያቀረቡ ነበሩ::

*እንባ እንባ ይለኛል*
*መለየት ከብዶኛል*
*ግን እንባ ከየት ለባቱ*
*እልልታ ነው ቤቱ!*
*ሳቅ ሳቅም ይለኛል ሳቅ ባይስቅ ጥርሴ*
*በመለየት ሀሳብ ተወንቃብኝ ነፍሴ*
*እልልታ በጆሮ እንባ ባይኔ ሲፈስ*
*ሆዴ እየተከፋ ጥርሴ በሳቅ ሲፈርስ*
*መለየት ከደስታ ውስጤ ሲተራመስ*



Scanned by CamScanner

*የሚይዘው ስጦታ ሲበተን ሀሳቤ*
*ፀሎት ስደረስች ሀጢያተኛ ልቤ*
*የፍቅር ተምሳሌት የጌቶቹ ጌታ*
*ውድ ጓደኞቼን ሁናችው መከታ*
*ጠብቀህ ካኖርከን በፍቅር በደስታ*
*ስባክህ ስትሰየን የማታ የማታ*
*ስብሮ ኑሯችንን ስታርገው ትዝታ።*

ግጥሙን ሳልጨርስ በፊት ለቅሶ ተጀመረና አቋረጥኩት፡፡ አባባ መንግስቱ ከወጣ በኋላ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ልዩ ብፌ ያለው ራት የተጋበዝነው፡፡ ለዛ ነው የተሰማኝን ከፊል ደስታና የመለየት ስሜቱን ቀላቅዬ ግጥሜ ላይ ያሰፈርኩት፡፡ ለቅሶ ሲበዛ ግጥም መቅረቡ ተተወና የፎቶ ፕሮግራም ተጀመረ፡፡ ዓላማው ሽኝት መሆኑ ገባን፡፡ መቼ እንደምንሸኝ ግን የምናውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ፕሮግራሙ ተጠናቅቆ ወደ ክፍላችን ስናመራ የሁላችንም አልጋ ተነስቷል፡፡ ችፑድ ብቻ ነው የቀረው፡፡ ለካ እኛ እራት ላይ እያለን መኪኖች ገብተው መኝታችን በሙሉ ተነስቶ ተጭኗል፡፡ ችቡዱ ላይ ሰውነታችንን አሳርፈን ወሬ ማውራት ጀመርን፡፡

በበነጋው ማታ ላይ በሁለት መኪኖች ጥቂት ወንዶች ተጭነው ተወሰዱ፡፡ ይህንን አውቀን ስለነበር በማግስቱ ሁላችንም ተጭነን ላለመወሰድ ከክፍላችን አንወጣም ብለን እንቢ አልን፡፡ የማናውቃቸው ወታደር ልብስ የለበሱ ስብሰባ እንድናደርግ ውጡ አሉን፡፡ ራት ልንመገብ

የምንሄድበት መንገድ ዳር ያለች ዛፍ ስር ተሰበሰብን። የዐምባው ጠባቂዎች የነበሩት በሙሉ ከኛ ጋር በጣም ስለተላመዱ እነሱ ላይ ደፍረን መሳሪያ አንደግንም ብለው ቀድመው ሸሽተው ነበር። አሁን የመጡት ግን የማናውቃቸው እንግዶች ናቸው።

ለስብሰባው የወጣነው ሴቶች ብቻ ነበርን። ወንዶቹ ጨቤና መከላከያ የሆኑ ነገሮችን አዘጋጅተው "እስቲ ወንድ የሆነ ያስወጣናል!" ሲሉ አምፀው ነበር። ቀደም ሲል አንድ መኪና ሙሉ ወታደር ዐምባ መግባቱን እናውቅ ስለነበር ምናልባትም መንግስት ካምፕ ሊያደርገው አስቦ ይሆናል የሚል ግምት ነበር። "እናቃጥለዋለን እንጂ ካምፕ አይሆናትም!" ሲሉ ወንዶቹ ዙሪያውን ጎማ አድርገውበት ነበር። ይሁንና ሙሉ በሙሉ በወታደር ተከበቡና ነገሩ በቀላሉ እልባት እንደማያገኝ ስለተሰማን እኛ ሴቶቹ እየተንጫጫን "በቃ ይወጣሉ!" ብለን ነገሩን ለማብረድ ሞከርን። ወዲያውም ተከብበው እንዲውጡ ተደረገ።

የዓለም ህዝብ ሬሳ የሚሸኝ መሰለ!

የአባባ መንግስቱን ፎቶ ይዘን ተላቀስን። ሰራተኞች፣ መምህራኖች፣ አባቶች ጥግ ጥጉን ሆነው እንባ ተራጩ። ወታደሮች ዙሪያችንን መሳሪያ ደግነውብን ወደ መኪናው እንወጣ ጀመር። ከዐምባ እየተጫኘን እየተወሰድን ቡልቡላ ላይ እንደምንተው ያወቁ የዝዋይ ገዳም አባቶች አባ ሚካኤልን ጨምሮ መጡ። መኪኖቹ ላይ ስንወጣ ዘፈኑ፣ ለቅሶው፣ ጩኸቱ፣ ልመናው ትርምስምስ ያለ ከተማ መሰለ። መምህራኖችና

ሰራተኞች መኪናው ላይ እየተደፉ ዋይ፣ ዋይ ሲሉ ሙሾ... ወንዶቹ ታዳጊዎች እልህ እየገነፈለባቸው:-

*ተገፋን፣ ተገፋን ዘንድሮ ጭራሽ ተገፋን*

*የሰሁኑ ደባስ ብሰን ብሰን ከገደና ወጣን*

ሴቶቹ ዐምባ ደህና ሁኚ የሚለውን ዘፈን... ቀውጢ:: ማንም ግን በዚያ ሰዓት አባባ መንግስቱ ኃይለማርያምን ለቅፅበት ከአዕምሮው ማውጣት የቻለ አልነበረም:: ሁላችንም የተመካከርን ይመስል በአንድ ጊዜ የምንወደውን መዝሙር ማንቆርቆር ጀምርን::

*መንግስቱ ሰባታችን*

*የሁላችን ተስፋ መመኪያችን*

*እኛ ታዳጊዎች ተነስተናል*

*የድሉ ባለቤት ሆነናል::*

እንደዕውነቱ ግን ድል አጥተን ቡልቡላ ላይ ልንበተን ነው:: ይሁንና አባባ መንግስቱ ሲመጣ የምንዘምረውና አሁን ላለንበት ዕድገት ያበቃን እሱ ነውና ቤታችንን ስንለቅ እንባ እየተራጨን ይሄን ከመዘመር የበለጠ ምን ምስጋና አለን?

ከዝዋይ ገዳም የመጡት ቄሶችና አባቶች የመኪኖቹን ሹፌሮች ያውቋቸው ስለነበር መስቀሎቻቸውን አውጥተው እየተንበረከኩ ሳይቀር "ቡልቡላ ላይ አትጣሏቸው:: እባካችሁ ዝዋይ ገዳም አራግፏቸው!"

ሲሉ ለመኗቸው:: ልመናቸው ከንቱ አልቀረም:: ቀጥታ ተወስደን የተዘረገፍነው ከገዳሙ ነበር:: ሁላችንም ዐምባው ውስጥ ባለን ፋይል መሰረት አሳዳጊዎቻችን ትግራይ ቢሆኑ ቤተሰቦቻችንን ለመፈለግ መሄድ ያለብን እዛ ነበር- ምክንያቱም ወደዛ እንድንሄድ ነዋ ገንዘቡ የተሰጠን:: "ኧረ እኔ ትግራይ ዘመድ ወይም ቤተሰብ የለኝም!" የሚሉ ቢኖሩም "ፋይልሽ ላይ ተፅፏል ሄደሽ ፈልጊ!" ነበር መልሱ:: አዲስ አበባና ናዝሬት ለምንሄደው ሰላሳ፣ ሰላሳ ብር ብቻ ተሰጠን::



Scanned by CamScanner

# -9-

ያን ዕለት ዝዋይ ገዳም ውስጥ አደርንና በጠዋት በየመስመራችን መኪና ይዘን ዕድላችን ያደለንን ለመቋደስ ተጓዝን:: ምን ማድረግ እንዳለብኝና የት ማረፍ እንደምችል የጠራ ምስል ሳልይዝ ነው ወደናዝሬት ያመራሁት:: ሙልጭ ብዬ በተስፋ ማጣት ማዕበል ተንገዋለልኩ:: ማዕበሉ ሲፈልግ ሲደፍቀኝ፣ ሲፈልግ ከላይ ሲያንሳፍፈኝ... ብቻ ያሻውን ሲያደርገኝ መብቱ ነበረው:: ባዶ ነኛ- ዕጣ ፈንታዬን ማለም ያልቻልኩ ባዶ!

ውስጤ ግን ዙሪያሽወርቅ ስለእናቴ የምታውቀው ነገር ካለ ሄጄ እንድጠይቃት ገፋፋኝ:: ምናልባትም ማረፊያ ፍለጋ የፈጠርኩት ሰበብ ሊሆን ይችላል እንጂ በበኩሏ ምንም የምታውቀው ነገር እንደሌለ ሳላውቀው ቀርቼ አልነበረም:: ይሁንና ናዝሬት ወርጄ ወደ ዙሪያሽወርቅ ቤት የሚወስደውን መንገድ ተያያዝኩት:: ወደ ቤቱ ስቃረብ ግን ልቤ መምታት ጀመረ:: ፍርሀት ሊያጥወለውለኝ ቃጣው:: *ገብቼ ምንድነው የማደርገው? ምንስ ነው የምላት?* ልመልሳቸው ያልቻልኳቸው ጥያቄዎች ውስጤ ጭንቀት ፈጠሩ:: *በጊዜ ማረፊያሽን ፈልጊ!* ሌላኛው ተተካ *እናትሽ ሰይደብሁም!* ምንም እንደማታውቅና ቤተሰቦቼን በማፈላለግ ልትረዳኝ እንደማትችል እያመንኩ እንዲያ ብላ የሸኘችኝ አሳዳጊ እናቴ ቤት

መግባቱ ፍርሀት ለቀቀብኝ::

ወዲያው አካባቢው ያሉ ሰዎች እንዳያዩኝ እየተጣደፍኩ ዙሪያሽወርቅ ቤት መግባቱን ትቼ ወደ ናዝሬት ማርያም በሚወስደው መንገድ ታጥፌ የሶምሶማ ሩጫ ውስጥ ገባሁ:: ወደ ማርያም ስሄድ ዙሪያሽወርቅ ቤት የተዋወቅኳት ሽዋፀሀይ የምትባል ጓደኛዬን አገኘኋትና ከሷ ጋር አትለፋኝ የሚባለው ምግብ ቤታቸው ሄድን:: እናቷ ወ/ሮ ሙሉነሽ ሲያዩኝ ጮኸው ሳሙኝ:: "እናትሽ ጋ ደረስሽ ወይ?" አሉኝ:: እንደተጣላን አውቀዋል:: "ግቢ!" አሉኝ እኔ ግን ዙሪያሽወርቅ ቤት መግባቱን ስላልፈለግኩ እንቢ አልኳቸው:: እነሱ ጋ አደርኩና በበነጋው ብር አዋጥተው ሰጡኝ:: እሱን ይዤ ወደ ማርያም ቤተክርስትያን ሳዘግም ወንድማገኝ የተባለውን የዐምባ ልጅ አገኘሁ:: እቤት ካልሄድን ብሎ ይዞኝ ሄደ:: በእውነት በጥሩ ሁኔታ ሶስት ቀናት እሱ ጋ ቆየሁ:: ያኔ የዐምባ ልጆች ፍቅራችን እንደዛሬው የደበዘዘ አልነበረም::

እሱ ጋ ሶስት ቀናት ከቆየሁ በኋላ ተሰናብቼው ወጣሁ:: ወዴት እየሄድኩ እንደሆነ እርግጠኛ ባልሆንም ከእኔ ፈቃድ ውጪ ግን አዕምሮዬ በመዘገበው ቦታ ለመድረስ እግሮቼን እያዘዛቸው ነው:: እኔ እንግዲህ ታሪክ የሌለኝ ሰው ነኝ የት መሄጃ ይኖረኛል? አይታወቅም! ከየት ነው የመጣሁት? እሱም አይታወቅም! የማን ልጅ ነኝ? አይታወቅም! የት ነው አድራሻዬ? አይታወቅም:: ምንም የሚታወቅ ነገር በሌለኝ ሰዓት ስለማይታወቀው ታሪኬ ላምሰለስል ስል ብቻ እያዘገምኩ ነው:: ወዴት? አላውቀውም!



Scanned by CamScanner

# ክፍል ሁለት

# ውጥንቅጥ



Scanned by CamScanner

# -10-

ሁለት ምርጫዎች ብቻ አሉኝ::

ሁለቱም መጥፎዎች ከሆኑ የሚወዳደሩት ከመጥፎነታቸው ጋር ብቻ ነው- ጥሩ ነገር የላቸውማ:: ድንገት ከሁለቱ አንዱን ለይቼ ከመረጥኩ መጥፎነቱ እንዳለ ሆኖ እንኳን የመጥፎ ጥሩ ይሆናል:: ህይወት ለእኔ ሺ ጊዜ መጥፎ ብትሆንም ጥሩነቷን ፈልጌ መጥፎ ጎኗን ለመቀነስ ያለኝ ህልም እንዳለ ነው:: አሁን ግን ከሁለቱ መጥፎ ምርጫዎች አንዱን የተሻለ መጥፎ መምረጥ አለብኝ::

ወይ ሴተኛ አዳሪ መሆን አልያም ጎዳና ላይ መኖር::

የድንግልናዬ ነገር አላሳሰበኝም:: ሰው ክብሩ ኖሮ ህልውናው ቢጠፋ ምንድነው ጥቅሙ? ድንግልናዬን አጥቼ ራሴን ካተረፍኩ ምን ይገደኛል? ይሁን እንጂ ጠንካራ እምነት አልነበረኝም:: ከወንድ ጋር ተኝቼ እንዳለማወቄ የማንም ስሜት መርኪያ መሆኑን እንደመጨረሻ አማራጭ ያዝኩት- ጎዳና ላይ መኖር የተሻለ መጥፎ መሆኑን ተቀብዬ:: *ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል* አይደል የሚባለው? ጎዳና ቢያንስ የጥቂት ቀናት ቤቴ አልነበር?

ቀጥታ ወደ ናዝሬት ማርያም ቤተክርስቲያን አመራሁ:: ቤተክርስትያኗን የግንቡ አጥር በደንብ ከልሏታል:: የዝገት መከላከያ ቀለም የተቀባውን ዋናውን የቤተክርስትያን አጥር አልፌ ወደ ውስጥ ዘለቅኩ:: ሲሚንቶ ሊሾ የተደረገው መንገድ ላይ ስደርስ እንደተቀሩት ምዕመናን ጫማዬን አውልቄ ወደ መቅደሱ ዘለቅኩ:: ቤተክርስትያኗ ፊት፣ ለፊት በሚገኘው በረንዳ ላይ የእንጨት ቀለም ተቀብቶ ባለ አንድ ትልቅ የበር እንጨት በኩል ወደ መቅደሱ ያስገባል:: የቤተክርስትያኗ ጣራ በመቅደሱ ውስጥ ሲበራ ስዕሉ ወደታች ስለሚያንፀባርቅ ለቤተክርስትያኗ ውበት ሆኗል:: በቀይ መጋረጃ የተሸፈነው የካህናት ማስቀደሻ መቅደስ ከምዕመናን መቆሚያ ከፍ ብሎ የተሰራ ሲሆን ስርዓተ ቅዳሴው እዚያው ላይ ይፈፀማል:: እሱን አለፍ ብሎ ካህናት ብቻ ሊገቡበት የሚፈቀድበት ቦታ በውሀ ሰማያዊ መጋረጃ ተከልሎ በትንሹ ክፍት ሆኗል:: እዛ ውስጥ የእመቤቴ እና የልጇ የክርስቶስ ስዕል ተደራርቦ በደረጃ ተቀምጧል:: ዘው ብዬ ወደዚሁ ቦታ በማምራት ድንግል ማርያም ብትሰማኝም፣ ባትሰማኝም ግድ በማይሰጠኝ ሁኔታ ተደፍቼ እያለቀስኩ ነገርኳት:: የሚበቃኝን ያህል ነግሬያት ዝም ስትለኝ ከመቅደሱ ወጥቼ ወደ ግቢው አመራሁ::

ራሴን ለማሳመን ምክንያት ስላላስፈለገኝ ያለምንም ጭንቀት ነው አፈር 'እፍ' ብዬ የተኛሁት:: ምርጫ ከሌለኝ የተመረጠልኝን መጠቀም ብቻ ነው:: ያን ዕለት ጀምሮ ግን የጎዳና ተዳዳሪዎቹ አላስቀምጥ አሉኝ:: ያባርሩኝ፣ ይሰድቡኝና ያስፈራሩኝ ጀመር:: ጎዳናም ላይ ሰው ያስፈልጋል:: ተመልሼ እንደምመጣ እርግጠኛ አልነበርኩም እንጂ አንዱን ጉብል በደንብ አግባብቼ አቃቅፌ ባድር ለዛሬ ውለታ በሰራልኝ::

ይህን የሚያደርግ ወኔ ግን የለኝም:: ሊኖረኝም አይችል:: ጎዳና ላይ ስወጣ የመጀመሪያዬ ስላልሆነ የሚደርሱብኝን ዛቻዎችና ማስፈራሪያዎች ለመመከት የሚያስችል ፅናት ነበረኝ::

"ዛሬ ከኔ ጋር ብታድሪ መሬቱን ሁሉ ለግዛትሽ እሰጥሽ ነበር!" ይለኛል አንዱ ቡቱቷም የኔ ቢጤ::

"ባሪቾ... ነፍሴ... ብርድልብሴ... ልተኛሽ አድርጌሽ ትራሴ!" ሌላኛው ይቀጥላል::

"ኩራቷ ደ'ሞ... ብጣሻም!" አንዱ ወጠምሻና ፊቱ የተተለተለ የጎዳና ተዳዳሪ::

"እረ በናታችሁ ትንሽ ቀን ጠብቋት ኩራቷ ሞቷ ይሆናል..." ሌላኛው የጎዳና ተዳዳሪ- ቀጫጫና ነገረኛ::

እውነትም ቀስ እያለ ኩራቴ ሞቴ መሆን ጀመረ:: የምበላው፣ የምለብሰው፣ የምልስ የምቀምሰው ተቸገርኩ:: እኔ እራሴ ይታወቀኛል... ቀስ እያለ የነበረኝ ርዝራዥ ሞራል ሲላሽቅ:: ሰው ተስፋ ከሌለው ምን ሞራል ይኖረዋል?

አንድ ቀን ቤተክርስትያኗ ግቢ ውስጥ ካርቶን ሰብስቤ አንጥፌ ኩርምት ብዬ ከተኛሁበት ጠዋት ስነሳ ራሴን ላስቲክ ለብሼ አገኘሁት:: *በቃ እየተቀበሉኝ... ጎዳና ተዳዳሪዎቹ እየወደዱኝ ነው ማለት ነው?* ብዬ ራሴን ጠየቅኩት:: ከዛ ጊዜ በኋላ ከስር ካርቶን፣ ከላይ ያንን ላስቲክ እየለበስኩ



Scanned by CamScanner

ነው የምተኛው:: ትልቁ ችግሬ ምግብ ሆነ:: ርሀብ እየጠናብኝ ሄደ::

ጎዳና ላይ ያሉት ልጆች ሲጋራ ሲያጨሱ፣ የተራረፉ ቢራዎች ሲጠጡ፣ ጫት ሲቅሙ ሳይ እገረምና ይሄን ባህርያቸውን እንዲያቆሙ ልመክራቸው እዳዳስሁ:: እየቆየ ግን የእኔ ምክር ከንቱ መሆኑን ተረዳሁት::

"ባሪቾ... ቅመሽው እስቲ?" አለኝ ቾምቤ የምንለው የጎዳና ላይ ወጠምሻ

"ወዲያ ውሰድልኝ!"

"ልትሞቺ'ኮ ነው:: አንድ ጊዜ... አንዴ ሳብ ብታደርጊው ርሀቡን ድራሹን ያጠፋዋል"

"እኔ አጭሼ አላውቅም" ተቃወምኩት::

"እናቴ አይደለችም እኔንም ያስተማረችኝ::"

"በናትህ ቾምቤ..."

"አበዛሽው እሺ... ሲጋራ ማጊ እንቢ፣ ቤንዚል አሽትቺ እንቢ፣ ወስጄ ጠቅ ላድርግሽ እንቢ እናትሽ እንቢ ብለው ነው እንዴ ለአባትሽ..."

"አፍህን ዝጋ! ክፍት አፍ!"

"ነይ ግቢበታ!" ማዛጋት ጀመረ::

"ክፍሉ ጠባብ ነው" አልኩት- እነሱን ካልመሰልኩ ጠላቶቹ እንደሚሆኑ አውቄዋለሁ::

"ያንቺ የታችኛው ክፍልስ?..."

ሲጋራውን መነተፍኩትና ወደ ከንፈሬ ወስጄ በሀይል ስምገው እሱም በስሜት አፉን ከፍቶ ቀረ:: ወዲያው ያለማቋረጥ ሲያስለኝ ሳቁን ለቀቀው::

"ድገሚበት! አንዴ ሳቢው!" ዝም አልኩት::

"በይ እንጂ... እሾህን በጉጠት ነው የሚሉት ሼባዎች?"

"እሾህን በሾህ"

"ተየት ነው... ተመንዜው ነው የመጣሽው?" ሳቅኩ::

"በይ ሳቢና ስጭኝ!" ይግረመው ብዬ በጣም ደጋግሜ እየሳብኩ፣ እየሳልኩ ልቤን ላፈነዳት ደረስኩ:: እውነትም የርሀብ ስሜቴ ድራሹ ጠፋ:: ሲጋራ ማጨሱ በራሱ የርሀብ ስሜትን ይቀንሳል:: ጫቱ ምግብን ትዝታ ብቻ ያደርጋል... እና ከጎዳና ላይ ልጆች በጣም ባልቀራረብም እነሱ የሚያደርጉትን እያደረግኩ እስትንፋሴን ለማቆየት ትግል ውስጥ ገባሁ::

በተለይ ሲጋራው ተመቸኝ:: ከምግብ ይልቅ አሳድጄ የምለቃቅመው ወረቀትና ሲጋራ ሆነ:: ወረቀቱ ግጥም ለመፃፊያ... ሲጋራው ደግሞ ርሀቤን አስታግሶ ለማሰብ ረዳኝ:: ሲጋራ ስይዝ በደንብ ማሰብ እችላለሁ...



Scanned by CamScanner

ሳብ... ብ... ብ... አደርገውና የታመቀ ሀሳቤን የያዘውን ጭስ በስልት አስወጣውና ተመልሼ ሀሳብ ውስጥ እሞጀራለሁ:: እንደገና በረዥሙ ስቤ በረዥሙ አስወጣለሁ... ሰላም!

አንድ ሰው ነገርን መጥፎ ነው ብሎ የሚያስበው በግዴታም ሆነ በውዴታ ከህይወቱ ጋር ስላላለማመደው ነው ብዬ አመንኩ:: መጥፎ የሚመስሉኝ ነገሮች ሁሉ ጥሩ ናቸው ብዬ እውነታነታቸውን እስከማፀድቅ ድረስ ከራሴ ጋር አዋሀድኳቸው:: የጎዳና ህይወቱን ኖርኩበት:: ርሀቡን ተራብኩት:: ልለምን ስሞክር "አንቺ ሰርተሽ አትበይም?" እየተባልኩ ፊት ብነሳም፤ የጎዳና ተዳዳሪዎቹ ራሳቸው "ለሷ አትስጧት... ሌባ ነች... ለማኝ አይደለችም ሌባ ነች" እያሉ እድሌን ሊዘጉት ሞከሩ:: እኔ ግን አልሞት ባይ ተጋዳይነቴን ቀጠልኩ::

አንዳንድ ረዥም ዓመት ጎዳና ላይ የመኖር ልምድ ያላቸው ልጆች የቻሉትን ያህል ይረዱኝ ነበር:: ሲጋራ ሲገዙ ቆርጠው "እንኪ ባርኞ፣ ግንባር ጌጡ!" እያሉ ይሰጡኛል:: አንድ ዕብድ በድንጋይ መሀል ግንባሬን በስቶት ቁስል ስላለብኝ ነው ግንባር ጌጡ የሚሉኝ:: የጎዳና ላይ መከራ ስንቱ ይወራል? እንዲህ እንደዘበት እብድ ፈንክቶኝ፣ እንትን እንትን አድርጎኝ ካልተባለ በቀር የዓለም ጉድ የተከማቸበትን ስፍራ ጥቃቅን ነገር ሁሉ በማውራት ማን ይቆስላል?

ትልቁ ችግር ግን ትቦ ውስጥ ሳይቀር በማደር ግድ የሌላቸው መሆናቸውን የሚያሳዩኝ የጎዳና ተዳዳሪዎች "አንድ ቀን አንዱ ወስዶ ጠቅ ካደረገሽ በኋላ ልጅሽን ስትታቀፊ ብጣሽምነትሽን ታቆሚያለሽ!" የሚሉኝ ነገር

በሁሉም ላይ የሚታይ በመሆኑ ቀኔን የምጠብቅ መሆኔን እያሰብኩ በፍርሀት ውስጥ መኖሬ ነው::

ያለሁበት የጎዳና ህይወት ማብቂያ ቀን አልታይሽ ብሎ አስጨነቀኝ:: እንደሳር በቅዬ ጎዳና ላይ እንደሳር መክሰሙን ስላልፈለግኩት ያልተጨበጠም እንኳ ቢሆን ተስፋ አረገዝኩ:: *ለንድ ቀን ከዚህ ሀይወት እወጣለሁ... በእርግጠኝነት ለንድ ቀን ሰው እሆናለሁ!* ይሁንና ሰው የመሆን ትርጉሙ እንደ ህይወቴ ሁሉ እንቆቅልሽ ይሆንብኝ ጀመር::

# -11-

ለማኝ እንትን ሳይል ከተኛንበት መነሳት አለብን:: ማህሌት ይዘው የሚያስቀድሱ ሰዎች በሌሊት ስለሚመጡና የቤተክርስትያኗ ለማኙ ወደስራው ሲሰማራ ተነስቼ በናዝሬት ጎዳና ላይ እንገላወዳለሁ:: እግረ መንገዴን ሳያልቁ የተጣሉ ሲጋሮችንና በላስቲክ ሆነው የተጣሉ የተራረፉ ጫቶችን እለቃቅማለሁ:: ደፈር ብዬ ልጠይቀው የምችለው ሰው ካገኘሁ "ነፍሱ... አስር ሳንቲም አበድረኝ!" እለዋለሁ:: ሁላችንም በየፊናችን ለምነንም ይሁን መንትፈን ያገኘነውን ይዘን አንድ ላይ እንሰባሰብና ወጭና ወራጁን እየተረብን ፀሀዩ በረድ እስኪል እንቆያለን:: ጀምበር ማዘቅዘቅ ስትጀምርም በየመጠጥ ቤቱ በራፍ ሰካራምን ማጅራት ለመምታት፣ የተራረፈ መጠጥ ለመገልበጥ፣ ድሪያና ስሪያ ለመጥመድ፣ ፈንክቶ ወይ ተፈንክቶ ለመመለስ እንንቀሳቀሳለን:: ዝርፊያ፣ ድሪያና ስሪያው ላይ አልሰማራና መጠጥ አልጠጣ እንጂ እኔም *ምን ካየው ምን ለየው* እንደሚባለው የቡድኑ አባል ተደርጌ ነው የምታየው::

ያም ሆኖ ግን ከአንዳንድ የጎዳና ተዳዳሪዎች ጋር እጅና ጓንት መሆን ተሳነኝ:: በተለይ ጉልበተኛ የሆኑ ወንዶች እንደጥላ እየተከተሉ ሲያጠቁኝ ፈለጉ:: ጎዳና ላይ የወጣች ሴት ብልጠት ተጠቅማ የአንዱ ሚስት

በመሆን ሊደርስባት የሚችለውን ጥቃት ማክሸፍ ካልቻለች የማንም መጫወቻ ልትሆንና ነጋ ጠባ በሰቀቀን ልትኖር ትችላለች:: ይህን ብዙዎች ደጋግመው ነግረውኛል:: ጥቃቱን ፍራቻ ልቤ ካልፈቀደው ሰው ጋር ዝም ብዬ ከምጋደም ጥቃቱን ለመቋቋም መርጬ የተሰጠኝን ዛቻ ንቄ ተውኩት:: አንድ ቀን ጠዋት አብረውኝ የሚያድሩ ጎረምሶች ተሰብስበው ወደተቀመጥኩበት መጡ:: የሆነ፣ ያልሆነ ሀሳብ እያነሱ አንድ ሁለት ጊዜ ለከፉኝ:: ዝምታዬ ቀጥሉ የሚል መስኋቸው ነው መሰለኝ መነካካትና መምታት ሲጀምሩ ግን *ማንም የጎዳና ዱርዬ የሚመታኝ አይደለሁም!* ብዬ ወረድኩባቸው::

"ክብሬን የጠበቅኩ ነኝ ሌላ ሰው ፈልጉ!" አልኳቸው:: ሳቁብኝ:: አሳሳቃቸው ክብር የሚለውን ቃል የት ቦታ እንደሚያውቁት ጠፍቶባቸው በመጨረሻው ሰዓት ያስታወሱት ነው ያስመሰለባቸው:: ድሮስ እንዲህ ያለ ቀሽም ቃል እዛ ቦታ እንዴት ይጠበቃል?

"ለመሆኑ አንቺ ከማን በልጠሽ ነው?" አንደኛው ጎረምሳ::

"ከማንም! ጫፌን ግን አትነኳትም"

"ወደሽ ነው በግድሽ የምትሰጭን?" ሌላኛው ጎረምሳ::

"ስድ! ስድ ነህ! መጀመሪያ እንትንህን ጥረግ!"

"እረ በናትሽ? የማነሽ ሞልቃቃ? እንደኑግ ነው የምለጠልጥሽ!" የመጨረሻው ጎረምሳ::



Scanned by CamScanner

"ወራዳ! እናንተ እንትን ያለባችሁ... ቆሻሾች..." የምችለውን ያህል ተሳድቤ ሮጥኩ:: ተዘጋጅተው እንደመጡ ስለሚያስታውቅባቸው ጥቃት እንዲፈፅሙብኝ እድል ልሰጣቸው አይገባም::

ሀሳብ እያምሰለሰልኩ ስለሮጥኩ እንደሁ እንጃ በቤተክርስትያኗ ጀርባ ዞሬ ቁርቁራ ሰፈር ስደርስ ያዙኝ:: ዛፍ የበዛበት ጥላማ ሰፈር ነው:: ራቅ ወዳሉ ቦታዎች የሚሰሩ ሰራተኞች ስለሚበዙበትና ሰራተኞቹ ጠዋት ወጥተው ማታ ስለሚገቡ አካባቢው ፀጥ ያለ ነው:: ብቻ ደርሰውብኝ ሲይዙኝ አቅሜ የቻለውን ያህል "ኡኡኡ!" ብዬ በጩኸት አቀለጥኩት:: ትግሌን ቀጠልኩ:: አንድ ሰው ደርሶ ካላስጣለኝ ለሶስት ሊጫወቱብኝ እንደቆረጡ ያስታውቃሉ:: ድንገት ግን ባልጠበቅኩት ሁኔታ ዝገት ያለው ጩቤ ወደ ሆዴ ተላከ:: ሶስት ጊዜ ጩቤው ሆዴ ላይ አረፈ:: በተሰነዘረ ቁጥር ለመሸሽ ስሞክር፣ ሆዴ ላይ ሲደርስ፣ ስሞክር ሲደርስ... አራተኛው ላይ እጄን ሰንዝሬ ሆዴን ላድን ስጥር ጩቤው ራሱ እጄ ላይ ተሰካ::

አንዲት ሴትዮ ጩኸቴን ሰምታ እንደ እብድ እየከነፈች ስትመጣ ጥለውኝ ጠፉ:: እጄ ላይ ያለውን ጩቤ ለመንቀል እየታገልኩ ዝልፍልፍ ብዬ ከመሬቱ ላይ ወደቅኩ:: ሴትየዋ ሮጣ አጠገቤ ስትደርስ እየጮኸች አፋፍሳ አነሳችኝ:: ሆዴ ላይ የተወጋሁትን እርስት አድርጌው የሚደማ እጄን ለማስታመም ስሞክር ደግፋ ወደ ቤተክርስትያኗ ወሰደችኝ:: ቤተክርስትያኗ ውስጥ ባለው ቧንቧ እጄ ላይ ያለውን ደም ታጠብኩት:: ሴትየዋ ቡና ለምና አመጣችና ሶስት ቦታ ሆዴ ላይና አንድ ቦታ እጄ ላይ በተወጋሁበት ደሙን ጠራርጋ ቡናውን ደመደመችልኝ:: ሆዴ ላይ

ያሉት የተወጋሁባቸው ቦታዎች ነጭ ስብ የመሰለ ነገር ከማሳየታቸው ውጪ ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር አልነበረም:: የእጄ ግን መቋቋም ያልቻልኩትን ህመም እየመገበ በስቃይ ውስጥ ከተተኝ::

ነገሩን በቸልታ መመልከት እንደሌለብኝና ወዲያውኑ ለፖሊስ እንዳሳውቅ ቢጎተጉቱኝም እኔ ግን ለጊዜው የተፈጠረብኝ ድንጋጤ በርሮ ከህመሙ ጋር ብቻ ስለቀረሁ ክስ ለመመስረት ፍላጎቱ አልነበረኝም:: *ለምንድነው ወደ ሆዴ ጩቤውን ሲሰነዝረው ሽሽት የያዝኩት?* ስል ተቆጨሁ:: አጋጣሚው ይህችን ለእኔ የመከራ ቋት የሆነች አለም ለመገላገል መፍትሄ ነበር:: በራሴ ተናደድኩ:: *ለሁንስ ማናባቱ ራሴን እንዳባጠፋ ይከለክለኛል?* ማንም! እስከዛሬ እንዲህ ያለው ድንቅ ሀሳብ ሊከሰትልኝ ያልቻለው እኔ ቀሽም በመሆኔ መሆኑን ለራሴ እየነገርኩት እያለ አንድ አባት ሆዴ በጨርቅ እየታሰረልኝ መሆኑን አይተው ወደኔ መጡ:: አጠገቤ ከመድረሳቸው በፊት ዛሬ፣ ያውም አሁኑኑ ራሴን እንደማጠፋ መሀላ ያዝኩ::

# -12-

አጠገቤ የቆሙት አባት ፊታቸው እንግዳ አልሆነብኝም:: *እዚሁ ሲገቡና ሲወጡ አይቻቸው ይሆናል* ስል አሰብኩ:: *ቁም ነገሩ ግን አወቅኳቸው አላወቅኳቸው ምን ልዩነት ያመጣል? ያው ሆዴ ሲታሰር አባዩ መጥተው በገርምት እያዩኝ ቆሙ... በቃ!* ለራሴ ግሳፄ የመሰለ መልዕክት አስተላለፍኩ::

"ነይ እስቲ ልጄ!" ሲሉ ይዘውኝ መቀመጫ ወዳለበት አመሩ:: *እርግጠኛ ነኝ እግዚአብሄር፣ ማርያም እያሉ የመፅናኛ ቃል ሲመግቡኝ ነው:: ለእዚህ ለመሞት ባለኝ ውሳኔ ላይ ሴጣን ሲሆኑብኝ ነውና በአንዱ ለሞቼ በሲባው ማፍሰስ አለብኝ!* የመጣው ቢመጣ መሞቴ እንደሆነ አይቀር!

"የት ነው የማውቅሽ?" አሉኝ *እሳቸውም ፊቴ አዲስ አለሆነባቸውም ማለት ነው? ግን የት ያውቁኛል? እዚሁ ነዋ!* ይሄንኑ ልነግራቸው ከህመሙ ጋር እየታገልኩ አፌን ሳሾል ቀድመውኝ "ገዳም ትመጪ አልነበር?" አሉኝ:: ወዲያው ትዝታው ተገጠገጠብኝ::

የዐምባ ልጆች የድራማና መዝሙር ቡድን አባላት ዝዋይ ገዳም እየሄድን የምናቀርባቸው መንፈሳዊ ድራማዎች ነበሩ:: ከገዳሙ ጋር ካለን ቅርበትም የተነሳ ጭምር ይመስለኛል 'የአቡነ ጎርጎርዮስ ልጆች' እየተባልን

ነው በገዳሙ አስተዳዳሪ ስም የምንጠራው- የዕምባ ልጆች::

"እና እዚህ ምን ትሰሪያለሽ ልጄ?"

"የት ልሂድ? ምንስ መሄጃ አለኝ? ቤተሰቦቼን አላውቅ!"

"አይይ... ምን በአብዮቱ ምክንያት ቤተሰቦቻቸው የተሰውባቸው አይደሉ እዛ የሚገቡት"

"እና የእኔም ቤተሰቦች ተሰውተዋል ነው የሚሉኝ?" ስል ተገርሜ ፊታቸውን ለማንበብ እየሞከርኩ ጠየቅኳቸው::

"አይ እንደሱስ አይደለም:: የኔን ግምት ነገርኩሽ እንጂ!"

"ልጄ... አሁን ታዲያ ወንዶቹ ተተናኩለውሽ ነው?" የደረሰብኝን ሁሉ ዘርዝሬ ስነግራቸው በጣም አዘኑ:: ሀዘኔታቸው እኔም ውስጥ ተጋባ:: *ለስንቱ ሰቀቀን ሆኜ እዘልቀዋለሁ?*

"ለመሆኑ አባሚካኤል ደህና ናቸው?" አልኳቸው:: አባ ሚካኤል የቤተሰቤ ያህል ነፃ ሆኜ የምቀርባቸው ሰው መሆናቸውን እሳቸውም ያውቃሉ::

"ደህና... ነው..."

"ምነው ቅር አለዎት?"

"ኸረ አላለኝም:: እንደው ጌታ ነፍሳቸውን በገነት ያኑርና አቡነ ጎርጎርዮስ ከሞቱ በኋላ የገዳሙ አያያዝ ስለተበላሸ ለቅቄ ከወጣሁ ሰነባብቻለሁ ብዬ

ነው::"

"ውይ ያሳዝናል..."

"ምን ይደረጋል? ጌታ የሚወደውን ይፈትናል::" ብለው ትንሽ ቆዩና "እንደው ልጄ ባይሆን እንኳ ዳቦ ልግዛልሽ" ብለው እጄን በመያዝ ወስደው ዳቦ ገዙልኝ:: እንደኔ ጎዳና ላይ አልወጡም እንጂ ችግር ላይ እንዳሉ ያስታውቅባቸዋል::

"አይዞሽ... እግዚያብሄር ይረዳሻል" ሲሉ በቻሉ ጊዜ እንደሚጠይቁኝ ነግረው ተሰናበቱኝ::

ራቅ ብለው መሄዳቸውን አየሁና በጨቤ የተጫጫረ ሆዴና ንቅናቄ እንዳይጠዘጥዘኝ አንከርፍፌ የያዝኩት እጄ እየፈጠሩብኝ ያለውን ህመም ተቋቁሜ ወደ አንዱ ሱቅ ሄድኩ::

"ባለሱቅ?"

"እ?"

"ጋዝ ስጠኝ"

"የምን ጋዝ?" አጠያየቁ ግራ አጋባው::

"ጋዝ ነዋ! ስንት ዓይነት ጋዝ አለ?"

"ባለ ስንት?"

"ባለ... ባለ... ባለ... ስንት ነው ያለህ?"

"በለስላሳ ጠርሙስ ከሆነ ዋጋው..."

"እሺ ስጠኝ" ብዙ ቢሆንም ወዲያው ስቃዬን ሳያበዛ እንደሚገለኝ ስለተሰማኝ ብዛቱን አልጠላሁትም::

"የታለ እቃሽ?"

"የምን ዕቃ?"

"እምጪ ልገልብጥልሽ!"

"አልያዝኩም!"

"ምን ትላለች ይቺ? እና በምን ልስጥሽ?"

"ግዴለህም አሁን እሰጥሀለሁ::"

"ምን ላይ ልትገለብጭው?"

"ስጠኝና ምን ላይ ገልብጬ እንደምሰጥህ ታያለህ አይደል?" ሲፈራ ሲቸር ቀድቶ ሰጠኝ:: ተቀብየው ከአይኑ ለዓመል ዞር ብዬ በአንድ ትንፋሽ ግጥም አድርጌ ጠጣሁት:: ቃናው ሁሉ የሆነ ልገልፀው የማልችለው አሙለጭላጭና ጣዕም አልባ ከመሆኑ ውጪ ሆዴ ገብቶ ምንም ነገር ሳይፈጥር እንዲሁ ሰምቶ አደረገኝ:: ጠርሙሱን እየተቀበለኝ ያለው ባለሱቅ አይኑን ከንፈሬ ላይ ተክሎ ቆየና ልሄድ ፊቴን ሳዞር፦

"ከንፈርሽ አመድ መስሏል" አለኝ:: አናደደኝ:: *ምን ሰገባው?* ቫዝሊን ተቀብቼ ብሞት ወይም ሳልቀባ ብሞት ምን ልዩነት ያመጣል? ለማንኛ ውም መንገድ ላይ እንዳልሞት አስቤ እየሮጥኩ ቤተክርስትያኗ ውስጥ ገባሁ::

ስሞት ሰው እንዳያየኝ ብዬ ግንቡ ጥግ ላይ ልጥፍ ብዬ ተቀመጥኩ:: ካሁን፣ ካሁን እሞታለሁ ብዬ ብጓጓም ምንም የተፈጠረ ነገር ጠፋ:: እየቆየ ግን ሆዴ መነፋት ጀመረ:: *ወይኔ ሆዴ ሰብጦ ነው ስንዴ የምሞተው?* ሀሳብ ገባኝ:: እየተከታተለ የሚወጣው የብስናት ግሳት ረበሸኝ:: አይኖቼን ጨፍኜ ለጥቂት ደቂቃዎች ሆዴ እንደዳውላ ተቀብትቶ እንደፊኛ ሲፈነዳ ታየኝ:: ወዲያው ግን ብስናቱ ዘገነነኝና አይኖቼን ገለጥኳቸው:: ሰዓቱ እየገሰገሰ ምሽቱ በብርሀን ላይ የበላይነቱን እየተቀዳጀ ነው:: እንደ ቅድሙ አይኖቼን ስጨፍን ስሞት ይታየኝና በዛው እነጉዳለሁ ብዬ ታገልኩ:: ምንም ለውጥ አለመፈጠሩና ማቅለሽለሽ፣ ሆድ መንፋትና ብስናት ብቻ ማግሳት በመሆኑ ተበሳጨሁ:: *ስንዴት ጋዝ ጠጥቼ ስስሞትም?* አይደለም ጋዝ ሳሙና እንኳ ወደ ሆድ ከገባ ይገላል ብዬ ነው የማስበው:: እምነቴ ግን አልሰራም::

ማቅለሽለሹ ወደ ማስመለስ ሲያሸጋግረኝ *ስሁን በቃ ስሞት ነው!* ብዬ ተዘጋጀሁ:: እግሮቼን ዘርግቼ እጆቼን በማወናጨፍ ልክ ሰው ሲሞት ዝርግትግት ነው ሊል የሚችለው ብዬ በምናቤ በሳልኩት መሰረት እንደዛው ሆንኩ:: እውነታው የተገላቢጦሽ ሆኖ ሞት ሸሸኝ:: ውስጤ ሞት እንደነጎደብኝ ሲሰማው አምርሬ አለቀስኩና በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ "ምናለ ብትተወኝ?" ስል እግዚአብሄር ላይ ጮህኩበት::

## -13-

ሞት እንደሰማይ ራቀኝ::

ህመሙ እየፈጠረብኝ ያለውና ተስፋ መቁረጥ የፀነሰብኝን ስቃይ ቋቅ እስኪለኝ አጣጣምኩት:: የእጄና የሆዱ ቁስል ቀስ እያለ መጠገግ ጀመረ:: ቁስሌ የውሻ ቁስል እንኳን እንዳይሆን የምመገበው ደህና ነገር የለኝም:: ርሀቡና እርዛቱ ሞቴን ቢያስመኙኝም ሞትም ሸሸኝ:: በጨቤ የተወጋ እጄን በደንብ ማከም ባለመቻሌ ይሁን ወይም ዝገቱ የፈጠረብኝ ችግር ብቻ ለጉድ እየለበለበኝ እከኪኝ፣ እከኪኝ ሲለኝ ነካካሁት:: እየቆየ ግን ጥዝጣዜውና ማቃጠሉ ሊያሳብደኝ ደረሰ:: *ህመሜን ሳስታግስ ወይስ ርሀቤን?* ተሰቃየሁ:: *በቃ ሙሉ ጎዳም... በቃ!* ራሴን ገሰፅኩ:: መለመን አለብኝ:: እንደዕውነቱ ከሆነ ሳልለምን ቀርቼ አልነበረም:: ለምዕመናኑ ሁሉ ግልጥ ብሎ የሚታይ ምልክት ስለሌለኝ ከጉዳይም የሚጥፈኝ የለም *ዕውነቱን ነው ሲያሉስ ምልክት የሚወድ ህዝብ ያለው!*

ከአካላችን አንዱ ካልጎደለ የሚሰጠን የለም:: አካላችን ባይጎድል እንኳን ለዕይታ የሚዘገንን ነገር ያለብን መሆኑን ማየት ይፈልጋሉ:: ነግ በኔ እንዳይደርስ በማለት የሚሰጡን ነው የሚመስሉት:: ብዙ የጎዳና ልጆች ይህን ስለሚያውቁ ወይ ሆዳቸው ላይ ቲማቲም በማድረግ፣ አንደኛው

እንደኛውን ሆነ ብሎ ሰውነቱን አክኮ ነጭ በማድረግ አልያም እግር የሚያቆስል ቅጠል አለ በሱ ሰውነትን በመፈቅፈቅና ዕግርን በማቁሰል ሊታይ የሚችል ምልክት ይፈጥራሉ:: ምክንያቱም ለእያንዳንዱ የጎዳና ተዳዳሪ ተስፋው ሰው ነውና:: ዞር ብሎ የሚያያቸው የጠፋ ዕለት ሊባሉ ይደርሳሉ:: አይናቸው እያየ፣ ልቦናቸው እያስተዋለ ትንፋሻቸው ጥልም ብሎ ከሚጠፋ ወንጀል ሰርተው ለዕለቱ ህይወታቸውን ቢታደጓት ይመርጣሉ:: ለመኖር እልህ አስጨራሽ ትግል የሚካሄድበት ስፍራ ነው- ጎዳና::

የተወጋ እጄ ደጋግሞ ሲበላኝ አክከው ስለነበር ፍም እየሆነ ሄደ:: ያኔም አንድ ዘዴ ዘየድኩና ደጋግሜ አከክኩት::

"ምን እያደረግሽ ነው ግንባር ጌጡ?" አለችኝ የሁለት ልጆች እናት የሆነች የጎዳና ተዳዳሪ:: ልጆቹን ከማን እንደወለደቻቸው የምታውቅ አይመስለኝም:: "ወይ ትዝታ! የማንም ሽንት መድፊያ ሆኜ ልቅር?" ትላለች ቁጭት ሲይዛት:: "አንቺ ግን ምን ብትሆኚ ነው ያልነኩሽ?" ትለኝ ነበር:: በዛገ ጩቤ ሊያርዱኝ እንደነበር የሰማች ዕለት ግን ቀርባ "አጉል ህይወትሽን አደጋ ላይ እንዳትጥይ!" አለችኝ:: እሷም እንደ እኔ ዝንቤን አላስነካም ባይ ነበረች:: አምስት ሆነው እኩለ ሌሊት ላይ ከተፈራረቁባት በኋላ ሞራሏ ላሽቀ መሰለኝ ጎኗ መሬቱ ላይ ሲያርፍ ቀድሞ ለሚመጣው ወንድ ሁሉ ጭኗን እየከፈተች ከነገሩ ጋር ተላምዳው ቁጭ አለች::

"እያደማሁት ነው"

"ለምን? ምን ነካሽ ፊነዳሽ እንዴ?"

"ዝም በይ ቆይ"

"እንዴት? ግንባር ጌጡ! ምነው እንዲህ በደም ተከየፍሽ?"

"አሳይሻለሁ አይደል... ተረጋጊ!" እጄ በደንብ ሲደማ ቆሻሻ ጨርቅ አምጥቼ ለበስ አደረግኩትና አስፓልቱ ላይ ቆሜ ለመንኩ::

"ነፍሱ... አስር ሳንቲም በናትህ?"

"እህቴ... እጂ እንዲህ ሲደማ እያየሽ ታልፊኛለሽ?"

"አባባ... በልጅዎት.... መታከሚያ አጥቼ ነው"

"ጎረምሶች ካልደፈርንሽ ሲሉ ወጋጉኝ..."

ትንሽ ብር ሳገኝ እሱን ይዤ ወደ አንድ ሱቅ አመራሁ:: ቴትራሳይክልና የቁስል ፕላስተር ገዝቼ የሚደማውን በመጥረግ አሸግኩት::

ለአንድ ሳምንት ያህል ያለ ሀሳብ ጎመን በዳቦ መግዣ ሳንቲም ማግኘቴን ሳረጋግጥ ልመናውን አቆምኩት:: ለምን የምበላው ብቻ ከሌለኝ እንደምለምን አልገባኝም:: ልጆቹ እንዳሉኝ ትንሽ ሳልበጣጠስ የቀረሁ አልመሰለኝም - ብጣሻም አይደል ያሉኝ?

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ነው ለሶስተኛ ጊዜ ጤናዬን ሊጠይቁኝ ብቅ ያሉት አባ አንድ ዜና ይዘውልኝ የመጡት:: ብዙ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ

ስለሚመላለሱ ዐምባው ከተበተነ በኋላ በየጎዳናው ላይ የህፃናት ዐምባ ጉዳይ አስፈፃሚ ፅ/ቤት እኛ በተለምዶ ሙከታተያ ብለን የምንጠራው ቢሮ እየቀረቡ ኡኡታቸውን አሰምተው ኖሯል:: በዚህም ምክንያት ችግር ላይ ያሉ የዐምባ ልጆችን መመዝገብ ሲጀመር አባ ሄደው አስመዝግበውኝ ነበር የመጡት::

"በይ ነገ ቀጥታ ፅ/ቤቱ መሄድ አለብሽ" አሉኝ::

"ግን'ኮ አባ ዐምባው እንደሆነ ተበትኗል መመዝገቤ ምን ይጠቅመኛል?"

"ማን ያውቃል አንድ መፍትሄ ይኖራቸው ይሆናል::"

"እና ሂጂ ነው የሚሉኝ?"

"አዎ ልጄ!" ሲሉ መሳፈሪያ ብለው ብር ሰጡኝ::

ዳግመኛ ወደ ዐምባ እመለሳለሁ ብዬ አላስብኩም ነበር:: ለትንሽ ሰዓት ካለሁበት መነሳት አቃተኝ:: እንደገና ከሰው ጎራ ልመደብ መሆኑን ማመን ከበደኝ:: *እንደቀሸሽ ከተጣልኩበት ተነስቼ ወደ እናቴ ቤት ዐምባ ልመለስ ነው?* ራሴን ጠየቅኩት:: ውስጤ እውነታውን መቀበል አቅቶት ዋለለብኝ:: *ዐምባ ልገባ ነው::* ውስጤ በተገኘው ዜና ለምን ሊቧርቅ እንዳልቻለ አልገባኝም:: ያም ሆኖ ግን ወደ ዐምባ መሄዱን በመምረጤ ሰልባጅ ሻርፕ፣ ዘመን ያለፈበት ዚኮ ጫማ፣ ሸንሸን ቀሚስ፣ ዩ ኤስ ኤ የሚል ቲሸርት ገዛሁና ልክ ክረምት እረፍቴን ጨርሼ ወደ ዐምባው ስገባ

እንደማደርገው ድምቅ ለማለት ሞከርኩ:: የቆሰለ እጄ ላይ ነጭ ጨርቅ ከመጠምጠሜ በቀር ሙሽራ እንደመሰልኩ ነው አዲስ አበባ መከታተያ ፅ/ቤት የደረስኩት::

ግቢው በዐምባ ልጆች ተጥለቅልቋል:: ገሚሱ የበላይ ጠባቂና ወላጅ ያለው፣ ገሚሱ የሌለው... ከጎዳና ተነስቶ የመጣ... ከቤቱ የመጣ... ተስፋ ያለው... የሌለው ድብልቅልቅ ያለ ስሜት የሚታይበት ሆኗል:: ግን ከዚያ ሁሉ መከራ አልፈን መገናኘታችን በራሱ ፈንጠዝያ ውስጥ ከትቶን እየተላቀስን ተሳሳምን::

ፍቃደኛ ሆነው ከወሰዷቸው ቤተሰቦች ጋር መስማማት ሳይችሉ ቀርተው የተጣሉና ከቤት የወጡ ጥቂቶች፣ ጎዳና ላይ የወደቁና አሳማኝ ችግር ላይ ናቸው የተባልነው ተለየንና ሌሎቹ አሳዳጊዎቻቸው በያሉበት ቀበሌ አመልክተው በየወሩ 60 ብር እንዲቀበሉ ተወስኖ እኛ ያኔውኑ በዐምባው የጭነት መኪና ተጭነን ወደ ዐምባ ተወሰድን:: ዐምባ እንደምኞቴ መቀበሪያዬም ልትሆን ይሆን?

# -14-

የአስራ ዘጠኝ ዘጠና ዓ.ም. ትምህርት ቢጀመርም የዐምባ ህይወት እንደድሮው አልሆነም:: ሁሉ ነገር ቀዝቅዞ መንፈስን ይረብሻል:: ታዳጊው በሙሉ ወጥቶ ጥቂቶች ብቻ ነን የተመለስነው:: ትምህርት ከጀመርን በኋላ ጤና ስለራቀኝም ሊሆን ይችላል የዐምባ ህይወት አልሞቀኝም፣ አልበረደኝምም፤ እንዲያው ለብ ያለ ሆነ::

እጄን ተሻለኝ ብዬ ደስ ደስ ሲለኝ ልክ የዛው አይነት ስሜት ጡቴ ላይ ተከስቶ የማከክ ርሀብ ለቀቀብኝ:: ለጉድ ሲበላኝ ጥፍሬን ሰድጄ ሳክከው ደስ አለኝ:: ማከኩን ራሱ አልጠግበው አልኩ:: ሳከው ከጡቴ ላይ የሆነ እንደ ቆዳ ግልፍፍ እያለ የሚፈረፈር ነጭ ነገር ይወጣል:: ማከኩ ቢያስደስተኝም እየቆየ ግን የፈጠረብኝ የማቃጠል ስሜት አሳሰበኝ:: ከላይ ሳከው ከውስጥ ያለው ለጥቂት ጊዜ የመሻል ስሜት ያሳየኝና ተመልሶ ያመኛል:: ሞዠቅ፣ ሞዠቅ ሳደርገው ነጭ ነገር በጥፍሬ ሙሉ ሞልቶ እየተረፈ ከሁለቱም ጡቶቼ ላይ ረገፈ::

እያደር ህመምና ጭንቀት እየተፈራረቁ የመማር ስሜቴን አጠፉት:: በተለይ ጭንቀቴ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር:: ምን እንደሆነ እንዲያ ያለ ስሜት ውስጥ እየከተተኝ ያለው መለየት አልቻልኩም:: እኛ ራሳችን



Scanned by CamScanner

ለይተን የማናውቀው አንዳች ሀይል በውስጣችን ይኖር ይሆን? ከልጅነቴ ጀምሮ ያለው የጭንቀት ስሜት አንድ ወቅት ላይ የጠፋ መስሎኝ ነበር:: ይሁንና አሁን እንደገና አገርሽቶብኛል:: ምክንያቱን ለመመርመር ስሞክር አሁን ለሚሰማኝ ስሜት ብቻ መልስ አገኛለሁ- ከደረሱብኝ ችግሮች በመነሳት ነው የሚል:: እሺ ልጅ እያለሁስ? መልስ የለም!

ያለሁበት ህይወት ከጎዳና ለየት ያለው የተሻለ ምግብ፣ መኝታና ትምህርት ስላለው ይመስለኛል:: በተረፈ ግን ልክ ጎዳና ላይ እንዳለሁ ያህል ይሰማኛል:: አብዝቼ እጨነቃለሁ፤ ህመም ደጋግሞ ይጎበኘኛል:: ከዛሬ ነገ ነገሮች ተለውጠው መንፈሴ ይስተካከላል፣ የሚያመኝም ይቆማል ብዬ ተስፋ ብገነባም አልሆነም:: ከዚህ መንፈስ ለመሸሽም ግጥም መፃፍ ጀመርኩ:: መንፈሳዊ ድራማ ክበብ መሳተፍ፣ የጋዜጠኝነት ክበብ፣ የሥነ-ፁሁፍ ክበብ፣ ሙዚቃ ክበብ ብቻ አርት፣ አርት የሚሸቱ ክበቦች ሁሉ አባል ሆንኩ:: እንዲህ ያሉ ክበባት መሳተፌ በትንሹም ቢሆን ነፃ አደረገኝ:: ትምህርት የሚሰጥበት ክፍል ስሆን ግን ዝምታ እየበዛ ራሴን ስለማዳምጠውም ነው መሰለኝ በጣም እታመማለሁ::

አንድ ቀን አስተዳደር ቢሮ ተጠርቼ ቀረብኩ::

"ምንድነው ችግርሽ?" ሲል መንግስተ አብ የተባለው አስተዳደር ጠየቀኝ።

"ምንም! መቼ ችግር አለብኝ አልኩ?"

"ትምህርትሽን ለምን አትከታተይም?"

"ኧረ እየተከታተልኩ ነው"

"ብዙ ጊዜ በትምህርት ገበታ ላይ እንደማትገኚ ሪፖርቱ ደርሶኛል::"

"ኧረ እገኛለሁ!"

"አትዋሺ! ስሚ ሙሉ ጎጃም ትምህርትሽን በስርዓት የማትከታተይ ከሆነ እንደምትባረሪ ማወቅ አለብሽ:: ሰምተሸኛል ያልኩሽን?"

እኔም'ኮ መማሩን ጠልቼው አልነበረም:: ግን ማንም ውስጤን ሊረዳልኝ የቻለ የለም:: አስተማሪዎች ሁሉ ሲያገኙኝ አንዳንድ ነገር ጣል ሳያደርጉብኝ አያልፉም::

"አንቺ ልጅ ጉርምስና ነው አይደል?" አለማየሁ ፀጋዬ የሚባል መምህራችን::

ዝም!

"ተናገሪ እንጂ... ጉርምስና ነው አይደል?"

"አይደለም::"

"እና? ትምህርት እያስተወ የሚያንጦለጡል ምን የሚሉት ሰይጣን ነው?"

"እኔ ስለምጨነቅ ነው"

"አየሽ! ያለመማር ጭንቀትን ብቻ ነው የሚፈጥረው"

"እኔ'ኮ ስለሚያመኝም ጭምር ነው"

"ተማሪ! ጉርምስናው ይቅርብሽ። ድራማ፣ ገለመሌ ማለቱን ተይ። ኑሮ እንኳን ዱርዬ ሆነሽ እንዲሁም ጥሩ አይደለም!"

ኑሮ ጥሩ እንዳልሆነ የሚያብራራልኝ ሰው አላስፈለገኝም። እኔ እየኖርኩበት ስለሆነ በተገቢው መንገድ ትርጉም ልሰጠው አልቸገርም። የመምህራኑንና የአስተዳደሩን ማስጠንቃቂያ ተቀብዬ እንዳሉት ከጉርምስናዬ በረድ ለማለት ብዙ ጊዜዬን ትምህርቴ ላይ አተኮርኩ። ክፍል ውስጥ ገብቼ እየተከታተልኩ እያለሁ ከየት መጣ ያላልኩት ጩኸት ከእኔ ወጣ። "ዋይ!..." ብዬ ጮኹኩ። ያስደነገጠኝ ወይም ለጩኸቴ ምክንያት የሆነ አንዳች ክስተት አልነበረም። ጩኸቴን ተከትሎ ልቤ በጣም ታፈነ። እጄ እየተንቀጠቀጠ ከጉልበቴ በታች ነዘረኝ። ወዲያው አፋፍሰው የመምህራን መሰብሰቢያ ክፍል ወሰዱኝና ውሃ እላዬ ላይ እያፈሰሱ አርገበገቡልኝ። ህክምና ከወሰድኩ በኋላ ትንሽ መለስ ይበልልኝ እንጂ መኝታ ክፍላችን ውስጥ ሆኜም ሆነ የትምህርት ክፍል ውስጥ ጩኸቱና ጭንቀቱ እያሰለሱ ይጎበኙኝ ነበር። ልቤን ዛሬ አሞኝ እንደሆነ ባሉት ሁለትና ሶስት ተከታታይ ቀናት ጡቴን ያመኛል። በተለይ የጡቴን ህመም ለማንም ሳልናገር ዝም ብዬ በላስቲክ እያሰርኩ ላስታምመው ነበር የሞከርኩት። እንዲያ ሳደርገው ደግሞ እየቆሰለ አስቸገረኝ። አንድ ቀን አንዲት ተማሪ ሳታውቅ በጨዋታ መሀል በክርኗ ጡቴን መታችው። በጣም አንገበገበኝ። ነፍሴን

ያሳመመቻት ያህል ነው ስቅቅ ያልኩት:: ወዲያው ጡቴ ደማ:: ደሙ ልብሴን ጭምር ሲያበላሸው ግን ግዴን ወደ ክሊኒክ ሄድኩ:: ቁስሉን የሚያደርቅ መድሀኒት ተቀባልኝና ለጊዜው ሻል አለኝ:: ካሉብኝ ችግሮች አንዱ ጭንቀት መሆኑ ተነግሮኝ የመድሀኒት መሞከሪያ ሆንኩ::

"ዛሬ እስቲ ይሄ መድሀኒት ይሞከርላት!"

"ይሄን መድሀኒት ለአንድ ሳምንት ውሰጂና ለውጥ ከሌለው በሌላ እቀይርልሻለሁ::"

"ምን ይሻላል? መድሀኒቱ ሁሉ ሊያድንሽ አልቻለም:: እስቲ ይሄን ሞክሪበት!"

ራሴን የመድሀኒት መሞከሪያ አይጥ አድርጌ አሰቤው ቁጭ አልኩ::

ታዳጊዎች ሁሉ ነገ ምን እንሆን ይሆን? እያሉ ሲጨነቁ ለምን እኔ አብሬያቸው ልጨነቅ እንዳልቻኩ ሀሳብ ገባኝ:: ግድ የለሽ ነበር የሆንኩት:: በደንብ ጊዜ ወስጄ ሳስበው ግን እንዲያ ትምህርት ያስጠላኝና በየክበባቱ የሚያዞረኝ፣ ጭንቀት ሊያፈነዳኝ የደረሰው ለካ ውስጤ ካመነበት ነገር የተነሳ ኖሯል:: መጀመሪያውኑም ወደ ዐምባው የመመለሱ ዜና ያላስፈነጠዘኝ አዕምሮዬ ያመነበት አንድ ነገር ኖሮ ኖሯል:: እኔ ደግሞ የነገ እጣ ፋንታዬን በደንብ አውቄዋለሁ- ጎዳና ላይ ነው የምኖረው:: እዛ ደግሞ ምን ሊደርስብኝ እንደሚችል አውቀዋለሁ:: ከመራብና መታረዝ አንስቶ በዛገ ጩቤ እስከመወጋት ደርሼያለሁ:: ከታዳጊው ጭንቀት እኩል እኔን ያስጨነቀኝ ነገር ቢኖር ነገ ጠዋት ከየትኛው የጎዳና ተዳዳሪ

ጋር አብሬ መተኛት እንዳለብኝ ነው። ሊደርሱብኝ ከሚችሉ ጥቃቶች ሁሉ የሚጠብቀኝ ሰው ያስፈልገኛል። ከዛ ውጭ እናቴ ጋ ሄጄ... ወደፊት በትምህርቴ ገፍቼ... ትዳር መስርቼ ምናምን የሚሉትን እቃ፣ እቃ ጨዋታ ለመጫወት እድሉ እንደሌለኝ እና የነገ እጣ ፋንታዬ ጎዳና እንደሆነ አውቃለሁ። ታዲያ ግድየለሽ ኑሮ ብኖር ጥፋቱ ምኑ ላይ ነው?

እንደሆነ አንድ ግልጥ ያለልኝ ሚስጥር አለ- ዐምባው እንደሚበተን። ምክንያቱም የሰበሰቡን ለስም ነውና!

# -15-

የዝዋይ ከተማ የእግር ኳስ ቡድን ከዐምባ ቡድን ጋር ግጥሚያ ነበረው:: ሁሌም እንዲህ ያሉ ጨዋታዎችና ፕሮግራሞች ሲኖሩ የኛ የጋዜጠኛ ው ቡድን በቀይ መስቀል መኪና ተጭኖ ሄዶ በቀይ መስቀሉ መኪና ነው ተመልሶ የሚመጣው:: ፕሮግራሙን ልቅም አድርገን ተከታትለን ሰኞ፣ ሰኞ የሳምንቱ ክንዋኔዎች የሚለው ፕሮግራም ላይ ዝግጅታችንን እናቀርባለን:: እንደተለመደው ዛሬም የሁለቱን ቡድኖች ጨዋታ እየተከታተልን ሳለ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ብጥብጥ ተነሳ:: ብጥብጡ ሲካረር መከላከያዎች ችግሩን ለማርገብ ይመጡና ተኩሰው ወደ አምስት የሚደርሱ የዐምባ ልጆችን በጥይት ይመታሉ:: ይሄ ነገር በባለስልጣኖች ዘንድ ይሰማና ዶ/ር፣ ነርስ ሳይባል እንዳለ ታፍሶ ዝዋይ እስር ቤት እንዲገባ ትዕዛዝ ይሰጣል:: እኛ ያለነው ቀይ መስቀል መኪና ውስጥ ስለነበር የሚያስታውሰን ጠፍቶ ቀጥታ ዐምባ ገባን::

በበነጋው የኛ ዜና ይጠበቅ ስለነበር ትንትን አድርገን አቀረብነው:: ይሄ እንደፖለቲከኛ አስቆጥሮን ቁጭ አለ:: ይሁንና የብሎክ ሀላፊ ከነበረው አብዱል መጅድ ጋር ትንሽ ተጣልተን ስለነበር ፈቃድ ሳይጠይቁ ዙረት በመሄድ በሚል ታሰርን::

በየመንደሩ ካሉት ጣቢያዎች በአንዱ ውስጥ ነበር ሶስት ሴቶች በአንድ ላይ የታሰርነው:: እስር ቤት ውስጥ ሆነን ታዳጊ ጓደኞቻችን ምግብ ስለሚያመጡልን አልተቸገርንም:: ከጠባቂ ወታደሮቹም ጋር በጣም ስለምንግባባ አጠገባችን በካቴና የታሰረውን ሌባ መጠበቅ ትተው ከኛ ጋር ሲጫወቱ፣ ማስቲካ ሲሰጡን፣ ሽቶ ሲቀቡን፣ በተቆለፈብን ስንዘምርና ስንዘፍን ስለነበር መታሰራችን ብዙም ግድ አልሰጠንም::

የመንደሩ ሀላፊ "ምን አድርገው ነው የታሰሩት?" ተብሎ ሲጠየቅ "ጫት ሲቅሙ ተገኝተው!" ብሎ ተናገረብን:: በመሰረቱ ጫት ሲቅም ዐምባ ውስጥ የተገኘ ልጅ ያለምንም ማወላዳት ዐምባውን ለቆ ይወጣል:: ሁላችንም ከዕረፍት ተመልሰን ወደ ዐምባ ልንገባ ስንል በር ላይ የሚደረግልንን የሽንት ምርመራና ጫት ስንቅም መያዝን አጥብቀን ነው የምንጠነቀቀው- ውጤቱ መባረር ነውና::

ብቻ የቀረበብን ክስ ከዕውነት የራቀና ከብሎክ ሀላፊው ጋ ስለተጋጨን በዛ ብቻ የታሰርን መሆኑን ገልፀን ክሱን ውድቅ ለማድረግ ታገልን:: አጋጣሚም ሆነና አጠገባችን የታሰረው ሌባ አመለጠ:: ሲያመልጥ ጉዳዩን ለማጣራት የመጡት ተወልደ ሐጎስ የተባሉ አስተዳደር እኛ መታሰራችንን አዩ::

"እነዚህ ደግሞ ምን ይሰራሉ እዚህ?"

"ታስረው ነው::"

"እኮ ምን ያህል ጊዜ ሆናቸው?"



Scanned by CamScanner

"ሳምንታቸው ነው"

"ማን መጥቶ ጠይቋቸዋል?"

"ማንም!"

አስተዳደሩ ተናድደው "እንዴት ሴት ልጆችን ይህን ያህል ጊዜ ታስራላችሁ? በአስቸኳይ ይለቀቁ!" ይላሉ:: ሁላችንም ልንፈታ መሆናችንን ሰምተን ደስ አለን::

የፍቺው ዕጣ ግን እኔ ላይ ነጠፈ:: ይባስ ብሎ ሌሎቹ ተፈትተው እኔ ወደዋናው እስር ቤት ተዛወርኩ:: ዋናው እስር ቤት መሬቱ ሲሚንቶ ነው:: እዛ ላይ መተኛት ማለት በብርድ ማለቅ ነው:: በዛ ላይ ብቸኛ እስረኛ ነኝ::

ያማታል እየተባለ ልዩ ምግብ እየታሰረ ቢመጣልኝም ያለሁበት እስር ቤት መጥፎ በመሆኑ በጣም ተጎዳሁ:: ምግብ ይዘውልኝ የሚመጡ ታዳጊዎችን ባየሁ ቁጥር ሆድ እየባሰኝ እዬዬ አልኩ:: በዚያ ላይ የማውቃቸው መከላከያዎች በሌላ ተቀየሩና አዲሶቹ ሰዎች በፈለጉ ጊዜ ወደታሰርኩበት እየመጡ ቃል ስጭን በማለት አስጨነቁኝ::

"ለምን ቃልሽን አትሰጭም?" አለኝ አበበ የሚባለው መርማሪ የታሰርኩበትን ክፍል ከፍቶ ወደ ውጭ እንድወጣ እያደረገኝ:: ሰዓቱ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ተኩል ሆኗል:: በዚህ ሰዓት መውጣት ችግር ነው::

"ነገ ጠዋት እሰጣለሁ"

"እንደሱ ለማለት መብቱ የለሽም:: ነይ ውጪ!" ጥቁር፣ ወፍራምና አይኖቹ ትላልቅ ሆነው የደፈረሰ ደም የያዙ ናቸው::

"እንዴት በዚህ ሰዓት ቃል እሰጣለሁ?"

"ወንጀለኛ ቃል ለመስጠት ጊዜ መምረጥ አይችልም" ሲናገር እንደ አስም በሽተኛ እፍን፣ እፍን ያደርገዋል::

"ወንጀለኛ አይደለሁም::"

"በመሰረቱ ነሽ! እኔ ግን ወንጀለኛ እንዳይደለሽ አድርጌ ላስወጣሽ እችላለሁ::"

"እ?"

"አዎ:: ውለታውን ለመክፈል ራስሽን ካዘጋጀሽ ችግር የለውም"

"ምንድነው ውለታው?" ያልገባኝ መሰልኩ::

"ትወጪልኛለሽ"

"ምን?"

"ምን ያስጮህሻል?" አይኖቹን ሲያጉረጠርጣቸው በጨለማ ውስጥ ያለ ሰይጣን መሰለኝ::

"አላደርገውም!"

"ጥሩ! ቃልሽን ትሰጪኛለሽ እንግዲያው"

"በናትህ! ነገ ጠዋት ቃሌን መስጠት እችላለሁ"



Scanned by CamScanner

"አሁን ነው የሚፈለገው... አሁኑኑ!"

"ኡኡኡ!"

"አንቺ... ምናባሽ ያስጮህሻል?"

"ኡኡኡኡ!"

"አንቺን አይደል እንዴ? ምንሽ ተነካ"

"ኡኡኡኡ!"

"አንቺ ባሪያ!"

"ኡኡኡኡ!"

"ጥሩ ነገ ጠዋት ትሰሚታለሽ!" በሩን ጠርቅሞ ከውጭ በመቆለፍ ጥሎኝ ሄደ:: እፎይ አልኩኝ:: ከዛ በኋላ በየተራ እየተፈራረቁ እኩለ ሌሊት ላይ በመምጣት ሊያስቸግሩኝ ቢሞክሩም በሀይል እየጮህኩ ልከላከላቸው ቻልኩ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን ብርድ በጣም ታመምኩ:: ያለሁበት ጥሩ ያልሆነ ሁኔታም ተደማምሮ ይመስለኛል ጡቴም መልሶ ቆሰለ:: ጭንቀት ባሰብኝ:: ያም ሆኖ ግን የሚተናኮሉኝ መከላከያዎች እንዲያ ታምሜ እንኳ ግድ ማጣታቸው ራሱ ሌላ በሽታ ሆነብኝ::

አለመፈታቴን የሰሙት የመንደሩ ሀላፊና የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራችን አቶ አለማየሁ ፀጋዬ በሞተር ሳይክል ሆነው መጡና አስጠሩኝ:: ሲያዩኝ በጣም ታምሜያለሁ:: ደነገጡ:: እኔም እሳቸውን ሳይ እዬዬዬን አቀለጥኩት:: "እኛ ጋዜጠኛችን እያልን ስንኮራብሽ፣ በሽተኛ ናት እያልን ስንንከባከብሽ እንዴት እንዲህ ረባሽ ትሆኛለሽ?"



Scanned by CamScanner

"እኔ መች ረባሽ ሆንኩ?"

"በይ ነይ አሁን... ሞተሩ ላይ ውጪ!" እሳቸውን ድጋፍ አድርጌ ወጣሁ:: ቀጥታም ክሊኒክ ይዘውኝ ሄዱ:: ትንሽ ህክምና አገኘሁና አገገምኩ:: ሙሉ በሙሉ ባለመዳኔ የሷ ትልቁ በሽታ ጭንቀት ነውና የስነ- ልቦና ባለሙያ ይያት ተብሎ ሳሙኤል ብርሀኑ ወደተባለ የዐምባው የሳይኮሎጂ ባለሙያ ዘንድ ቀረብኩ::

ከሱ ትይዩ ወዳለ ወንበር እያመለከተ "ተቀመጭ" አለኝ:: የተረጋጋና ሰው የማቅረብ ልዩ ተሰጥኦ ያለው ይመስላል::

"ደህና ነሽ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን"

"ቆንጆ ልጅ አይደለሽ እንዴ?"

"ማለት? እንዳመሰግንህ ነው?"

"አይ... አንቺ የጭንቀት ችግር አለብሽ ለማለት ይከብዳል ብዬ ነው"

"ጭንቀት የውስጥ ችግር መስሎኝ::"

"ልክ ነሽ... ውስጣችን ግን በላያችን ይገለጣል::"

ዝም አልኩት:: የባጥ የቆጡን ሲያወራኝ ቆየና ምንም ሳይለኝ አሰናበተኝ:: ሌላ ጊዜ በቀጠረኝ ቀን ሄድኩ:: እንደተለመደው የመግቢያ ጋጋታውን ሲጨርስ ምን እንደሚያስጨንቀኝ ይጠይቀኝ ጀመር::



Scanned by CamScanner

"እኔ ማነኝ?"

"እ?"

"እኔ ማነኝ?" ለጥያቄዬ የሚመልሰው ቸገረው መሰለኝ ዝም አለኝ::

"እኔ ማነኝ? ንገረኝ!" አለቀስኩ:: ዝም ብሎኝ እኔ ማነኝ የሚለውን ፊት ለፊት ባለው ወረቀት ላይ ፅፎ ደጋግሞ ሀሳብ ውስጥ ሆኖ አሰማመረበት:: በተገናኘን ቁጥር የምጠይቀው ጥያቄ ያንኑ ሆነበት:: አንድ ቀንም:-

"ጥያቄውን ተይው!" አለኝ::

"መልሱን አላገኘሁትም!" አልኩት እጆቼን ደረቴ ላይ አጣምሬ::

"አንቺ ሙሉ ጎጃም ብርሀኑ ነሽ:: እኔ ሳሙኤል ብርሀኑ ነኝ:: እኔ'ኮ ወንድምሽ ነኝ::"

ዝም!

"እንቅልፍ ለምን አትተኚም?"

"እንጃ! ለመተኛት ስሞክር ጩኺ፣ ጩኺ ይለኛል::"

"እንዲህ አድርጊ እስቲ... እንቅልፍሽ አልመጣ ሲል ከአንድ እስከ መቶ ቁጠሪ:: በሱ መንገድ ካልወሰደሽ መፅሐፍ አንብቢ"

ከንቱ ሙከራ መሆኑን በሌላኛው ቀን ስነግረው የእንቅልፍ ክኒን አዘዘልኝ:: ለጥቂት ቀናት መተኛት ቻልኩ:: በቀን በቀን መድሀኒቱን ስወስድ ከሰውነቴ ጋር ተዋደደ መሰለኝ እንቅልፍ ሲቸግረኝ ሁለት፣ ሶስቱን



Scanned by CamScanner

እያደረግኩ ዋጥኩ:: አልሰራ አለ::

በሚቀጥለው ጊዜ በእስኩየር ወረቀት የተሰራ ማስታወሻ ሰጥቶኝ የቀን ውሎዬን በሙሉ እየፃፍኩ ቢሮው እንዳቀርብ አዘዘኝ:: በተቻለው መጠን ሞክሮ ሳይሳካ ሲቀር "አንቺ እብድ ነሽ!" ብሎ ድምዳሜ ላይ በመድረስ የትም መንገድ ብቻዬን እንዳልሄድ፣ ቤተክርስትያን ብቻ እንድመላለስ ወይም አንድ ቢሮ ውስጥ ሆኜ ወረቀት እንዳገላብጥ ብቻ እንጂ ትምህርት በደረሰበት እንዳልደርስ አሳገደኝ::

ትምህርትና ብቻዬን ራቅ ያለ መንገድ መሄድን ልከልከል እንጂ ምግብ ቤትና መዝናኛ ክበብ ጎራ የማለት ነፃነት ተሰጥቶኝ ነበር:: አንድ ማክሰኞ ቀንም ከምግብ ቤት ሾርባ በሳህንና ዳቦ ይገፔ ብዙ ጊዜ በምንጠቀምበት አቋራጭ መንገድ ወይም በተለምዶ አይናፋሯ መንገድ ብለን በምንጠራው ቦታ ወደ መኝታ ክፍሌ ሳመራ አሳዳጊ ቤተሰብ የለውም ተብሎ ከኛ ጋ የገባ አንድ ይድነቃቸው የሚባል ልጅ ጠብቆ ያዘኝ:: ይሄ ታዳጊ ጓደኛዬ የሆነችውን ቀኑብሽ የምትባል ልጅ በፍቅር ፈልጎ ጠይቋት እንቢ ብላዋለች:: ለዚህ እንቢታ የእኔም ምክር እንዳለበት ስለተሰማው ደጋግሞ አስጠንቅቆኛል:: አሁንም በዚሁ ጉዳይ ሊነተርከኝ እንደሆነ ገብቶኛል::

"እ? ዛሬም በኔ ላይ ታደባላችሁ?"

"ለምንድነው የምናደባው?" አልፌው ስሄድ በሰላም እያወራኝ ከመንገዱ ወጣ ብለን ጉዞ ጀመርን::

"ምን አንቺ አይደለሽምና ነው እንቢ በይ ያልሻት?"

"ስንት ጊዜ ነው የምነግርህ? በራሷ ጉዳይ የመወሰን መብቱ የሷ ነው"

"ቆይ እኔ ምን ያንሰኛል?"

"ምንም!"

"እኔ ለአንድ አይደለም ለብዙ ሴት መሆን አልችልምና ነው?"

"ማለት?"

"ምን ማለት ትይኛለሽ? አንቺንስ ለማስደሰት ምን ያንሰኛል?"

"አልገባኝም"

"ቆይ እንዲገባሽ ለምን ፓንትሽን ዝቅ አታደርጊውምና አላሳይሽም?" ያለንበት ቦታ ጨለማ ነው::

"ከዛስ?"

"ከዛማ..."

"ምን ልትሆን?" መንገዱን ዘጋብኝ::

"የምሆነውንማ አሳይሻለሁ" እጆቼን ሲይዛቸው የያዝኩትን ሁሉ ጣልኩት::

"እረፍ... ይድነቃቸው እረፍ!" በጣም ታገለኝ:: ልለምነው ብሞክርም ሊሰማኝ አልቻለም:: ትግሉ ሲያይል አሻግሬ በዋናው መንገድ ላይ

ትግሉን ተቋቋምኩት:: ወደኛ የሚያልፉ ወጣቶችን አይቼ እስኪቀርቡን ትግሉን ተቋቋምኩት:: ወደኛ ሲደርሱ ጮኽኩ:: ጩኸቴን ሰምተው ሲመጡልኝ ጥዬው እየሮጥኩ ስሄድ ተከተለኝ:: ጫማዬ መንገድ ላይ ወልቆ በባዶ እግሬ ስለነበር የምሮጠው በቀላሉ ደረሰብኝና የለበስኩትን ሹራብ ያዘው::

ከቆምኩለት ሊደፍረኝ ባይችል እንኳ ሊጎዳኝ እንደሚችል ስላወቅኩ ሩጫዬን ስቀጥል ሹራቤ ተቀድዶ ከላዬ ላይ ተነሳ:: የለበስኩት ረዥም ቀሚስ ወደ ላይ ይሳብ ስለነበር ጎትቼ ጡቴን በመሸፈን ፊልም የምሰራ እስኪመስለኝ ድረስ በባዶ እግሬ ሮጬ አመለጥኩ::

ወዲያው ክስ መመስረት እንዳለብኝ ተነገረኝና ወታደሮቹ በየክፍሉ፣ በየቦታው ይፈልጉት ጀመር:: ከመንደር መንደር እየተሹሎከሎከ በቀላሉ ያለበት ዱካ ሳይታወቅ ሶስት ቀናት ቆየ:: በሶስተኛው ቀን ግን ተያዘ:: በደንብ እሽት አድርገው ከደበደቡት በኋላ እኔ ተጠራሁ:: ከመከላከያዎቹ ጋር በጣም ስለምቀራረብ ነው ይዘውት የጠሩኝ:: "አሁን ውሳኔው ያንቺ ነው ይባረር ወይስ አይባረር?" ተብዬ ተጠየቅኩ:: አንደኛ እንደያዙት ሲፈትሹት ኪሱ ውስጥ የዛገ እሱ የሰራው ጩቤ መገኘቱን ነግረውኛል:: ብዙ ጊዜ ወንዶቹ ማንኪያና ሹካ በመስረቅ ጩቤ እንደሚሰሩ እናውቃለን:: ይሄን ይዞ መገኘቱ በራሱ ያስቀጣዋል- ግን ለመባረር የሚያበቃው አይደለም:: ሌላው ያው በእኔ ላይ የመድፈር ሙከራ አድርጓል::

ተመልሰን ከገባን በኋላ ነው እንጂ ዐምባው ውስጥ መድፈር ምናምን የሚባሉ ወንጀሎች የተበራከቱት በፊት የምንተኛበት ክፍል ከፍቶን

እያደረ እንኳን እንዲህ ያለ ችግር ጎልቶ አይታይም። አስታውሳለሁ አንዲት ልጅ ለአምስት ተደፍራ ደፋሪዎቹ አልተባረሩም። አንዲት ልጅ ደግሞ አንዱ ድንግልናዋን ወስዶ ደፍሯት በታሰረ በሶስተኛው ቀን በመፈታቱ ልታብድ ደርሳ ነበር- ሌላ ወንጀል ሲሰራ ተይዞ በጥይት ተመትቶ ሞተ እንጂ።

የመድፈር ሙከራ ስለፈፀመብኝ ብቻ እንዲባረርም ሆነ እንዲቆይ የመወሰኑ ስልጣን ለእኔ ተሰጥቶኛል።

ያልኩት ነገር ያለማወላወል እንደሚፈፀም ያወቀው ታዳጊ እግሬ ላይ ወድቆ ይለምነኝ ጀመር።

"ወስኚ!" ተባልኩ። "በቅጣት እንልቀቀው ወይስ ይባረር?" ይሄንን እድል እናፍቀው ነበር። በተለይ በወንድ ላይ ውሳኔ መስጠት እንዴት እንደሚያስደስት ያጣጣምኩት ያን እለት ነው።

"ይባረር!" አልኩ።

ተባረረ።



Scanned by CamScanner

# -16-

ውሳኔው እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችንን ያስደነገጠን አይመስለኝም::

ልክ እንዳሰብኩት ዘጠና ዓመተ ምህረትን ስንጨርስ ዐምባው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበትኖ መንደሮቹ ለሌላ አገልግሎት ሊውሉ መሆኑ ተገለፀልንና ቀጨኔና ሚኪሊላንድ የሚባሉ ማሳደጊያዎች ልንዛወር መሆኑ ተነገረን:: አሳዛኙ ነገር ግን የዐምባው መበተን አይደለም- ቀጨኔና ሚኪሊላንድ ሊቀበሉን ፈቃደኛ አለመሆናቸውን መስማታችን እንጂ:: እኔን የገባኝ ነገር ቢኖር አለባብሶ የማረስ ዘዴን እየተጠቀሙ እንደሆነ ነው::

እኔ የደረሰኝ ቀጨኔ ህፃናት ማሳደጊያ ነው:: ምን እኔ ደረሰኝ እላለሁ ሴቶቹ እዛ ነው የሄድነው:: ደግነቱ እንኳን ሚኪሊላንድ አልደረሰኝ ነው ያልኩት:: ስም ማጥፋት አይሁንብኝና እንደሰማነው ሀሜት ከሆነ እዛ ያሉት ወልደው ተዋልደው ስለሚኖሩ እኛን እዛ ማስገባት ማለት መጥፎ ፍርድ ከመፍረድ ያልተናነሰ ነበር:: ያም ሆኖ ቀጨኔ ህፃናት ማሳደጊያ ደርሶኝ ወደዛ ስዛወር ያስደሰተኝ ምንም ነገር አልነበረም::

ማታ ማታ ልብስሽን አወላልቀሽ ጨኺ፣ ብረሪ፣ ብረሪ የሚል ስሜት ይተናነቀኝ ጀመር:: ሌሊት ሽለብ አድርጎኝም የባነንኩ እንደሆነ ጨኺ፣



Scanned by CamScanner

እየበረረኝ ውጪ የሚለው ስሜት በጣም ይታገለኛል:: ይሄን ስሜት ለማሸነፍ ይሁን ወይም አያያዙ ከዐምባ ጋር ስላልተጣጣመልኝ ባላውቅም ግቢው ውስጥ መዋል ስለሚያስጠላኝ ጠዋት ወጥቼ ማታ ነው የምመለሰው::

ድርጅቱ ትንሽ ክሊኒክ ያለው ሲሆን ከፍተኛ ህመም ለሚገጥማቸው ለከፍተኛ ህክምና ሌላ ሆስፒታል እንዲታከሙ ይፅፋል:: እንደ ዐምባ ሁሉ ነገር እዛው አያልቅም:: ትምህርት ቤት ስለሌለው ታዳጊዎቹ በተለያዩ ት/ቤቶች ተምረው ነው የሚመጡት:: ያም ሆኖ ግን እንደልብ መውጣት የሚባለው ነገር የማይታሰብ ነው:: እኔ ነኝ አመፀኛ ሆኜ ጠዋት ወጥቼ ማታ የምመለሰው:: ሁሌም ግን "የት ቆይተሽ ነው?" እየተባልኩ እንድፈርም እደረግ ነበር:: ጭንቅላቴን ስለሚወጋኝና እጅግ ቀፋፊ የሆነ የጭንቀት ስሜት ስላለብኝ ሊያባርሩኝ ቢሞክሩ እንኳ ግድ አልነበረኝም:: ድርጅቱ በጣሊያን መንግስት የሚረዳና ለኛ የሚሆን በጀት የሌለው መሆኑን ስለሰማን የምንባረርበትን ቀን የምንቆጥር እንጂ ኑሮ ለመመስረት ሀሳብ የሚገባን አልነበርንም- በተለይ እኔ::

ማንም ከማሳደጊያው ለመውጣት የፈለገ ምክንያት ዘርዝሮ፣ ወረቀት ተፅፎላት ካልሆነ ዝም ብሎ መውጣት አይችልም:: ከወጣ ግን ማታ ሲገባ የሚዘንብበትን ጥያቄ መመከት መቻል አለበት:: አራተኛ ጊዜ ለምን ሳታስፈቅጂ ወጣሽ ብለው ካስፈረሙኝ በኋላ ኮሚቴ ጋ እንድቀርብ ተደረገ::

ገና ስንገባ ጀምሮ የዐምባ ልጆችን ከቀጨኔ ልጆች እንዳንገጥም ብለው ለይተውን ነበር:: እኛ የዐምባ ልጆች ሌቦች፣ አብዶች፣ ረባሾች ተደርገን

በሁለት ሳምንታችን ስለተፈረጅን፣ ቀጨኔ መቃብሩ ጋ የዐምባ ልጆች መጡ እየተባለ ጨለማን ተገን አድርጎ መድፈር ሲጀመርና እንደፖለቲከኛ ስንቆጠር ነገሩ ምቾት ነሳኝ:: የነሱ ልጆች እንደልብ እየወጡ እኛ እንከለከላለን:: ስለዚህ ትዕዛዙን በመጣስ በአማፂነት እየወጣሁ መድሀኒያለም ቤተክርስትያን መቀመጡን ሰላም እንደማግኘት ቆጠርኩት:: ይሁንና ህግ በመጣስ ተከሰስኩ::

የድርጅቱ የኮሚቴ አባላት ለመቀመጥ የሚያስችላቸውን እድል ያገኙት ከአንዲት ሐና ከምትባል የታዳጊ ኮሚቴ አባል ጋር በመጣላቴ ነበር:: ለምን ህግ እየጣስኩ ወደውጭ እንደምወጣ ሲጠይቁኝ የማቀርብላቸው አጥጋቢ መልስ ስላልነበር ጥጋበኛነቴን ደጋግማ ነገረችኝ:: በዚሁ ታቆማለች ብዬ ዝም አልኳት:: እሷ ግን ልትበርድ አልቻለችም::

"ጥጋበኛ የማደጎ ልጅ!" ብላ ስትሰድበኝ ግን መታገስ አልቻልኩም:: ድንጋይ አንስቼ ግንባሯ ላይ ጠበስኳት:: ደሟ ቡልቅ፣ ቡልቅ ሲል ሳይ ደስ አለኝ:: ወዲያውም ወደ ክፍሌ አምርቼ በጀርባዬ ኿! ብዬ ተኛሁ:: ተከትለውኝ የመጡት ሁሉ ከተኛሁበት አንስተው ሊቦጫጭቁኝ ቢፈልጉም የዐምባ ልጆች በሩ ላይ ዘጉባቸውና "እሷ እንዲህ አይነት ነገር አታውቅም:: የሆነ ነገር ካላለቻት በቀር ሰው ለመምታ አትሞክርም!" ብለው ተከላከሉልኝ:: ወዲያው ጉዳዩ ለድርጅቱ የኮሚቴ አባላት ደረሰና ጥሩወርቅ የተባለችው የኮሚቴ አባል መጥታ ወደስብሰባው ቦታ ወሰደችኝ::

የስብሰባው ክፍል ውስጥ ሁለት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ተቀምጠዋል:: እኔና ጥሩወርቅ ስንጨመር ስድስት ሆንን:: ከክፍሌ የጠራችኝ ጥሩወርቅ



Scanned by CamScanner

"ለምን እንደተጠራሽ አውቀሻል?" አለችኝ።

"አዎ... ስለተጣላሁ አይደል?"

"ብቻ አይደለም!" ካሳሁን የሚባለው የኮሚቴ አባል በንዴት ደንፍቶ ጠረጴዛውን ጓ አደረገው። ስገባ ጀምሮ አስር ጊዜ ሲጋራውን እየመጠጠ ቶሎ፣ ቶሎ ጭ ን ይተፋው ነበር። "የግቢውን ሰላም አውከሸዋል። እናንተ ከመጣችሁ በኋላ ነው ይሄ ጊቢ የታወከው" አነጋገሩ አናደደኝ። ምንም መልስ መስጠት እንደሌለብኝ ተሰምቶኝ ዝም አልኩ። ስብሰባው ላይ አርቲ፣ ቡርቲ ሲበዛብኝ ግን "ግቢውን ለቅቄ መሄድ እፈልጋሁ!" ስል ፈቃድም ሳልጠይቃቸው የስብሰባውን ክፍል ለቅቄ ወደ ክፍሌ አመራሁ።

ወዲያው የዐምባ ልጆች በሙሉ ስብሰባ ተጠርተው ሲሄዱ እኔ ቀረሁ። "ድርጅቱን አለቃለሁ!" ስል እዛ ድርጅት ውስጥ ብዙ ዓመታት የቆየችና ቁርጥ እኔን የምትመስል ፋንቱ መንግስቱ የምትባል ልጅ "ገንዘብ እንዲሰጡሽ ሳትጠይቂ አትልቀቂ!" አለችኝ። ፋንቱ ልክ እንደ እኔ ቤተሰቦቿን በደንብ አታውቅ ስለነበር "እህቴ ሳትሆኚ አትቀሪም።" እያልኩ እላትና ተስፋ አደርግም ሁሉ ነበር- ቤተሰቦቿን አግኝታ ከነሱ ዘር ያልተገኘሁ መሆኔን አስረግጣልኝ ቁጭ አለች እንጂ።

በማግስቱ ጠዋት ወደምሄድበት ሊያደርሰኝ መኪና ተዘጋጀልኝ።

"የት ነው የምትሄጂው?"

"ወደ ናዝሬት"

ካልተሰጠኝ አልለቅም "ነይ ውጪ!" ስባል ግን ስራ ማፈላለጊያ ብር ካልተሰጠኝ አልለቅም አልኩ።

"ይሄ'ኮ የጣሊያን መንግስት የሚረዳው ድርጅት ነው... ለናንተ ደግሞ በጀት አልተያዘላችሁም።" አሉኝ። የድርጅቱ ልጆች ሲወጡ ሶስት ሺ ብር ስራ ማፈላለጊያ ተብሎ ይሰጣቸዋል። ሶስት ሺ ብር ምን ልትሆን እንደምትችል ግን አላውቅም።

"ስራ ማፈላለጊያ ካልሰጣችሁኝ አልወጣም!" አልኩ። አመፅኩ። ከተማከሩ በኋላ ሊሰጡኝ የሚችሉት አንድ ሺ ስድስት መቶ ብር ብቻ መሆኑን አስረግጠው በመግለፅ እሱንም የሚሰጡኝ መጀመሪያ እቃዬን መኪናው ላይ ከጫንኩ ብቻ መሆኑን ነገሩኝ። እዬዬ ብዬ ከዐምባ ልጆች ጋር ተላቅሼና ተሳስሜ እቃዬን ይዤ ወጣሁ። መለየቱ እጅግ ከባድ ቢሆንም እንኳን ያልተፈታ ታሪኬን እስከያዝኩ ድረስ እድሜ ዓለሜን ሳለቅስ እንደምኖር ስለማውቀው እንባዬን እየጠጣሁት ናዝሬት አደረሱኝ።

ናዝሬት የመምጣቴ ምክንያት በውል አልገባ ሲለኝ "ሀሳቤን ለውጫለሁ ዝዋይ አድርሱኝ!" አልኳቸው። በአበል ስለሚንቀሳቀሱ ምንም ሳይከፋቸው በደስታ ዝዋይ አደረሱኝ። ብሩን ሰጥተውኝም ፎርም እያስሞሉ ፎቶ ለጉድ አነሱኝ። እኔን ለመሸኘት ከተመደቡት አንዷ እንድበረታ መከራኝ ወደ ዝዋይ ከመጣችም እንደምትጠይቀኝ ቃል ገብታ አድራሻዋን ሰጥታኝ ተሰናብተውኝ ሄዱ።

እኔም በርካታ ኗሪ ባላት ዝዋይ ከተማ ውስጥ ብቸኝነት ብርድ እየለቀቀብኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ በማሰብ ተገትሬ ቀረሁ።

# -17-

*ስንኳን ደስ ስለሽ ሙሉ ገዳም!* አልኳት የእኔዋን አምሳያ ውስጤ ያለችውን:: እንዴ! ዛሬማ እንደ እኔ ያለ ሀብታም ቢታሰስ እንኳን የት ይገኛል? አንድ ሺ ስድስት መቶ ብር ለአንድ ሺ ስድስት መቶ ቀናት ቁርስ ይሆናል:: እንዲህ የሰላም አየር እየማግኩ ቁርሴን ከበላሁ ሌላ ምን ያስፈልገኛል? ለነገሩ በራሴ ለመቀለድ ሞከርኩ እንጂ ብሯ ትርጉም የሌላት መሆኗን አጥቼው አልነበረም:: እውነታው ይሄ ይሁን እንጂ በህይወት ዘመኔ ሁሉ ቆጥሬው የማላውቀው ብር እጄ ላይ አለ:: ታዲያ ሀብታም ነኝ ማለት ምን ይነሰኝ?

መጀመሪያ ናዝሬት ነው ዘመድ ያለኝ ብያቸው ወደዚያ ሲያደርሱኝ ዝዋይ ይሻለኛል ብዬ ያልኩት በደንብ የማውቃቸው ሁለቱን ከተሞች ብቻ ስለሆነ ነው:: በተለይ ለዐምባ ልጆች ትልቁ ከተማ፣ ትልቁ መዝናኛ ዝዋይ ነው:: ብዙ ምክንያቶች ዝዋይን እንድንረግጥ ስለሚያደርጉንና የኑሮ ርካሽነትም ዝዋይ ስለሚሻል በደንብ እናውቃታለን ብዬ ብል ማጋነን አይሆንብኝም::

ቺርስ ሆቴል በቀን ስድስት ብር አልጋ እየያዝኩ ሁለት ቀናት ቆየሁ::



Scanned by CamScanner

ሀሳቤ ተራም ቢሆን እንኳን ስራ አላጣም የሚል ነበር:: በየቦታው እየዞርኩ ብሞክር የሚያስጠጋኝና ፊት የሚሰጠኝ ጠፋ:: ስራ ማጣት ብቻ ሳይሆን ተስፋም ጭምር ነበር ያጣሁት:: አዝማሚያውን ሳየው ድቅድቅ ጨለማ ብቻ ሆነብኝ:: የሰው ልጅ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በተስፋ መቁረጥ ማዕበል ከመንገላታት ውጪ እድል እንደሌለው ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም::

የሁለተኛው ቀን ምሽት ላይ እንደተለመደው እንቅልፍ ሲያስቸግረኝ ስለህይወቴ ማሰብ ጀመርኩ::

ከአሁን በኋላ ለእኔ ያለሁት እኔ ብቻ መሆኔ ገባኝ:: ዐምባ፣ መንግስት ቅብርጥሴ ብዬ ብል የማመጣው አንዳችም ለውጥ እንደማይኖር ተረዳሁት:: *ስንገዳያው ውሳኔ ላይ መድረስ ስለብኝ!* ስል አሰብኩ::

ህይወት በውሳኔ የተሞላች ናት:: *ውሳኔ ህይወት ነው* አይደል የሚባለው? መኖር ካለብኝ መወሰን ግዴ ነው:: አውቀዋለሁ የዛሬ ውሳኔዬ ለነገ ማንነቴ ወይ በጎ ወይም መጥፎ አሻራ እንደሚኖረው:: እንዳለመታደል ሆኖ ግን መጥፎ አሻራ ያለውን ውሳኔ ነው የመረጥኩት::

ውሳኔዬ ሊያኖረኝ ከቻለ ማድረግ የነበረብኝ ይሄን ብቻ ነው:: እርግጥ እድሜ ዘመኔን አንገቴን ሲያስደፋኝ የማይኖር ሆኖ አይደለም:: ይሁን እንጂ መኖር እስከቻልኩ ድረስ ትርጉሙ ምንም ቢሆን ግድ አይሰጠኝም:: ግን ለምንድነው መኖር አጓጉቶ እንዲህ ያለ ውሳኔ ላይ ሊያደርሰኝ



Scanned by CamScanner

የቻለው? ለምንድነው ራሴን ለማጥፋት ወኔ ያጣሁት? ለምንድንስ ነው አዕምሮ እንዲህ ያለውን አስቀያሚ ውሳኔ ሲያስወስነኝ የሰው ፊት የማያሳየውን የዘላለም ሞት የሚያጎናፅፍ ድንቅ ውሳኔ ባለቤት ሲያደርገኝ ያልቻለው? ማን ነበር እሱ፡-

*ካለመኖር መኖር ሳይሻል ስይቀርም*

*ከመኖር ተስፋ ለለ ካለመኖር ምንም ያለው?*

እኔም የነበረኝ ተስፋ አንድና አንድ ነበር- ሴተኛ አዳሪነት ስራ መጀመር:: ማን ይሆን የመጀመሪያ አብሮኝ የሚተኛኝና ድንግልናዬን የሚወስደው ወንድ? አላውቅም!

# -18-

ቡና ቤት ለመስራት ከተማ መምረጥ ራሱ ትልቅ ጥቅም ያለው መሆኑን ያወቅኩት አሁን ነው:: ያኔ ግን ከዝዋይ ለቅቄ ወደ ናዝሬት ነበር ያመራሁት:: አንደኛ ነገር ዝዋይ ውስጥ በጥቂቱም ቢሆን ስለምታወቅ፣ ሁለተኛ ናዝሬት ላይ ገበያው ሞቅ ያለ መሆኑን ስለማውቅ ነበር ወደናዝሬት የተመለስኩት:: ናዝሬት እንደገባሁ ቀጥታ አስር ቀበሌ ወዳለው ፒኮክ ሆቴል አመራሁ:: ባለቤቱን እንዲያገናኙኝ ጠየቅኩና ቃሉን ከአፌ ለማውጣት እየከበደኝ "መ... መ... ስራት እፈልጋለሁ" አልኳቸው:: ነገሩ የገባቸው ስለሆኑ ገልመጥመጥ ብለው አይተውኝ "ከዚህ በፊት ሰርተሽ ታውቂያለሽ?" አሉኝ:: "አላውቅም" ፈገግ አሉ:: "ጥሩ መጀመር ትችያለሽ..." ሲሉኝ ለስራው የሚሆኑኝን ልብሶች ልገዛ ወጣሁ:: ፀጉሬ በጣም ረዥም ስለነበር አሳጠርኩትና ፍሪዝ ዊግ ተሰራሁ:: ጥብቅ ብላ ቅርፅ የምታሳይ አረንጓዴ ሰረዝ የበዛባት ቦዲ፣ ቡኒ ሰደርያና እግሩ ቤል የሆነ ሰማያዊ ጅንስ ለብሼ ራሴን ሳየው ታጥባ ታጥና ለገበያ የተዘጋጀች ሴት ማለት እኔ ማለት መሆኑን በመስታወቱ ውስጥ አየሁ:: እናም ጨለማን ተገን አድርጌ ስራው ላይ ተሰየምኩ::

ያስፈራል:: ሕይወቱ ያስፈራል:: ለነገሩ ምንም ነገር እስኪለመድ ድረስ መሆኑን አላጣሁትም:: በሚገርም ሁኔታ አዲስ የገባውን ሰው የመለየት

ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ጠጪዎች ናቸው የተሰባሰቡት:: በእኔ ሀሳብ የነበረው ገና አዲስ እንደመሆኔ ቀስ ብለው አለማምደው፣ ከነዕፍረተ ወበቱ ነገሩ በጨዋ ደንብ ይጠናቀቃል ብዬ ነበር የጠበቅኩት:: ይሁንና በቃ እንደዕቃ እንደፈለጉ ብድግ ለማድረግ ሲሞክሩ አስበረገጉኝ::

ሴቶቹ ፊር ኤንድ ላቭሊ ተቀብተው እንደ ፍርኖ ዱቄት ነጥተዋል:: መላ ሰውነታቸው ድብን ተደርጎ ፓራፊን ስለተቀባ በደብዛዛው ብርሀን እንደ እንቁ ያብለጨልጫሉ:: የአብዛኞቹ ጭን እንደብርቱካን ፍልቃጭ ፍም መስሏል:: ዞር ስል አንዱ ጣቶቹን በአንዷ ሴት ብልት መሀል አስገብቶት ፊቷ በርበሬ ሲመስል አየሁ:: እሱን ሸሽቼ ስዞር አንዷ እጇን በአንዱ ዚፕ ውስጥ ዶላዋለች... አይኔን ሌላ ቦታ ሳበር በአጠገቡ እያለፈች ያለችን ሴት ደህና አድርጎ ቂጧ ላይ በጥፊ ሲመታት ተመልክቼ ንዴት ሊያንጨረጭረኝ ሲሞክር እሷ ግን ዞር ብላ እየሳቀች "ይመቻል አይደል?" ስትለው ደንግጬ ወደ ሌላ ቦታ አዞርኩ:: ያኔም አይስክሬም የምትልስ ይመስል አንዷ የአንዱን ተስተናጋጅ ከንፈር ለጉድ ላስ ላስ... ስታደርገው እሱ ስፍስፍ ብሎ በአፉ ሙሉ ሲገባበት ሲል ወደኋላ ሸሸት እያለች እንደገና መለስ እያለች ደርሳ ላስ አድርጋው ስትሸሽ በግርምት ውስጥ ሳለሁ የተከፈተው ሙዚቃ ትዕይንቱን ሁሉ ረባበሸው:: የሲጋራው ሽታ፣ የወንዶቹ፣ ጋን፣ ጋን የሚል የመጠጥ ሽታ... የሴቶቹ ሽሌሻወርና በዛ ላይ የተነሰነሰ ሽቶ ቤቱን ቅርናት... ቅርናት እንዲሸት አድርጎታል:: ብዙም ታዛቢ ሆኜ ሳልቆይ እየደነሱ ያሉ አንዳንድ ወንዶች ቀረብረብ ይሉኝ ጀመር::

ከዕጣ ፈንታው ሊያቋድሱኝ በሞከሩት ላይ ሁሉ እንደፌንጣ እየዘለልኩና

ለጉድ እየደነበርኩ *ማንሰባቱ ነው የሚነካኝ?* አልኩ:: ራሴን ላሳምነው እንጂ ድርጊት ውስጥ ለመግባት ግን የሚያስችል ወኔ አሁንም ድረስ የለኝም:: *ስንዴት ደሆን የምሰምደው?* ብቻ ተቃውሞ በማስማቴ ምክንያት "እሷ ከማን በልጣ ነው?" ተባልኩና የሁሉም ዓይን ማረፊያ ሆንኩ:: ሰዎች በተፈጥሯችን የተከለከለ የማግኘት ልዩ ተሰጥኦ አለን አይደል? "ምናባሽ ያስኮራሻል?" ተብዬ ተሰደብኩ:: ስድቡ ግን አላመመኝም:: አባቴን አላውቀውማ:: ባውቀው ደግሞ "ምናባክ!" ብዬ የምሰድበው አይመስለኝም:: ለዚህ ሁሉ ህይወት ሊዳርገኝ የቻለው እሱም ጭምር ነውና በቂ ማብራሪያ ነው የምጠይቀው:: ከዛ በኋላ ብፋረደው እንኳን ግድ አይሰጠኝም:: *ስሱ ግን ማን ደሆን?*

አጉል አትንኩኝ ባይ ባህርዬን የተመለከቱት የቤቱ ባለቤት አቶ ተፈራ ጠርተው ማስጠንቀቂያ ሰጡኝ:: *ሰምነሽበት ከገባሽ በኋላ ምን ጣጣ ታበዛለሽ?* የሚል አንድምታ ያለው ይመስላል:: ያም ሆነ ይህ አብዝተው ሊጮኹብኝ ቢሞክሩም ውስጤ ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊቀበለው የሚችለው ወንድ ካልገጠመው እንዴት ስንት ዓመት አክብሬ የጠበቅኩትን ድንግልና ዝም ብዬ አስበላዋለሁ? ማንም የማናት ቅንጡ ሊለኝ ይችል ይሆናል- እውነታው ግን ድፍረት ላለማግኘት የማቀርበው የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ አይነት ሰበብ መሆኑን ሊረዳኝ የቻለ ባዘነልኝ::

አንድ ሁለት ቀናት በእንቢታዬ እየፀናሁ የማድረው እዛው ለሴቶች ተብሎ በተዘጋጀው ቤት ውስጥ ነበር:: በለስ ያልቀናቸው ቡና ቤቱ ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች በሙሉ የሚታጎሩበት ክፍል በጣም አስቀያሚ

ነው:: መተኛው የሳር ፍራሽ ሲሆን በአንዷ ክፍል ውስጥ አስራ አምስት ሴቶች ልናድር እንችላለን:: የሴቶቹ ባህርይና ድርጊት ለመግለፅ እንኳ የሚከብድ ነው:: ሴዚቢያን ሴቶች አሉ... ምላሳምና ነገረኛ ሴቶች አሉ... ሀሺሽ ተጠቃሚና ዕፅ ያነደዳቸው ዓይነት አሉ... ገበያ በማጣት ብዛት መከራ እያጣጣሙ ያሉ አሉ... ብቻ የሚያስጠላ ህይወት... ባህርያቸው እንደስራቸው ሽርሙጥ ያለ ነው:: እርግጠኛ ነኝ የወሲብ ፍላጎት ንዳድ ያለባቸው ሴቶች እዚህ እንደማይገቡ:: በቀላሉ ወሲብና ኑሮ ያቅለሸለሻቸው... ቋቅ ያላቸው ግን የህይወትን ድግምግሞሽ ጉዞ እየተሽከረከሩበት ያሉ ናቸው::

በርካታ ቆነጃጅት ቤቱን የሞሉት ቢሆንም ለጥቂት ቀናት የቤቱ ንግስት የሆንኩት እኔ ነበርኩ:: ውበት ኖሮኝ፣ ከወንዶች ጋር አድሬ ወይም እንደሴተኛ አዳሪ አይነት ባህርይ አሳይቼ አይደለም- የነገስኩት በእንቢታዬ በመፅናቴ ነው:: ጥቂት ወንዶች ደጋግመው ሲያስቸግሩኝ የተመለከተ አንድ ሰው በጨዋ ደንብ ጠራኝና ወደሱ ሄድኩ:: ድፍረት የሚፈጥርብኝ ነው እንጂ ያጣሁት ህይወቱንማ ገብቼ ላጣጥመው ወስኜ ብሬን ደመቅመቅ ያሉ ልብሶች ገዝቼበት ጨርሼዋለሁ:: እጄ ላይ ያለው ገንዘብ ሊያወላዳኝ የሚችል አልነበረም:: በዚህ ሁኔታዬ ደግሞ ካንዱ ጋ ካላደርኩ ምሳዬን የምበላበት ሳንቲም እንኳ ላጣ እችላለሁ:: አስታውሳለሁ ዐምባ እያለን ዝዋይ ለሽርሽር ይዘውን እንደወጡ ለሁላችንም ሀምሳ፣ ሀምሳ ሳንቲም ሰጥተውን "በሉ ሂዱ የምትፈልጉትን ዕቃ ሁሉ ግዙ!" ተብለን ገበያ ውስጥ ገብተን ሲሊፐርና ልብስ እየጠየቅን ሀምሳ ሳንቲሙ ሊገዛው የሚችለው ነገር አለመኖሩን አውቀን ነበር

የተመለስነው:: ቁም ነገሩ ግን ገንዘብ ምን እንደሆነና እንዴት መያዝ እንዳለበት ያልተማርኩ በመሆኑ ያለ የሌለ ጨርቅ ስገዛ ነገ የምበላው አጣ ይሆን? ብዬ ማሰብ እንኳን አልቻልኩም::

ወደጠራኝ ሰው ጋ ስቀርብ እጄን ይዞ እያሻሸ እንድቀመጥ ጋበዘኝ:: *እጄን ማሻሸቱ ምንም ለይደለ* ስል አሰብኩ:: "ቢራ አምጭላት!" አላት አንዷን አስተናጋጅ::

"ቢራ አልጠጣም::" አልኩት::

"ኦ! አይሲ... ውስኪ ነው?"

"አልኮል የሚባል አልጠጣም"

"እውነትሽን ነው?" ድምፁ ሹፌት ያዘለ ነው::

"አዎ!" እርግጠኛ ሆኜ ስመልስለት በሹፌቱ ለመቀጠል ያልፈለገ መሰለ::

"ለስላሳስ?"

"ይመቸኛል" ታዘዘልኝና እየጠጣሁ መጫወት ጀመርን:: የብዙ ወንዶች አስቀያሚ ጥያቄ ቀረበልኝ::

"ለምን እዚህ ህይወት ውስጥ ገባሽ?" *ማፈሪያ* አልኩ በልቤ:: *የወንድ ፍላጎት ናላዬን ለዙሮት፣ የወሲብ ጥማት ለሳስቀምጥ ብሉኝ* ልለው አሰብኩ:: እንዴት እንዲህ ያለ ጥያቄ ይጠይቃል? ብቻ ግን ነገርኩት- ማወቅ

ያለበትን ያህል::

"አኬ! ዐምባውን አውቀዋለሁ:: አንድ ጊዜ የሆነ ብጥብጥ ተነስቶ ለማረጋጋት መጥተን ነበር!" ሲለኝ በቅርብ የምንተዋወቅ ያህል ተሰማኝ::

"ለምን ሌላ ስራ አትሰሪም?" ሲል ጠየቀኝ::

"የት አገኛለሁ?" እዚህ ህይወት ውስጥ መቆየት እንደሌለብኝ፣ የእውነት ስራ የመፈለግ ስሜት ካለኝ እሱ የሚሰራበት አዋሽ አርባ ያለው የወታደሮች ካምፕ ውስጥ ስራ ሊያገኝልኝ እንደሚችል ነገረኝ:: ያን ምሽት ምንም ሳናደርግ አምሽተን ተለያየን::

ከበነጋው ጀምሮ አብረን ምሳ መብላት ጀመርን:: እሱ እዛ ሆቴል ስለነበር ያረፈው በቆየባቸው ቀናት ሁሉ አልነኬ የመሆን ባህርዬን በማድነቅ በዚሁ እንድቀጥልና ሌላ ስራ መያዝ እንዳለብኝ እየመከረ ጥቂት ብሮችን እየሰጠ ሲያበረታታኝ ቆየና ወደ አዋሽ አርባ ሊሄድ መሆኑን ነግሮኝ አብረን እንድንሄድና የጠቀሰልኝ የወታደሮች ካምፕ ውስጥ በተላላኪነት ስራ እንደሚያገኝልኝ በመግለፅ ጨቀጨቀኝ:: ምክንያቱ ባልተገለፀልኝ ሁኔታ ሰውየውን አምኜ ተከትየው እንድሄድ የሚያስችል ወኔ አልነበረኝም:: አድራሻውን ተቀብየው እንደምመጣ ነግሬው ተለያየን::

ነገሮች እንዳሰብኳቸው ሳይሆኑ ቀርተው ይሁን ወይም ሌላ በውል ያልተረዳሁት ምክንያት ኖሮ ለይቼ ባላውቀውም በሁለት ምክንያቶች የተነሳ ናዝሬት ውስጥ መስራት እንደማልችል እየተረዳሁት መጣሁ::

አንደኛ አንድ ሁለት የዐምባ ልጆች ቡና ቤት ውስጥ አይተውኛል:: አልፎ ተርፎም በአሳዳጊዎቼ ቤተሰቦች ተከብቤያለሁ:: ሁለተኛ ደፍሬ ከወንድ ጋር የመተኛቱ ስሜት አልመጣልኝም:: ቦታ መቀየሩ ድፍረት ሊፈጥርልኝ ይችላል ብዬ አማራጭ ከተሞችን አሰብኩ:: አዲስ አበባ፣ አዋሳና ጅማ ጥሩ መሆናቸውን ብሰማም ብዙ የዐምባ ልጆች በተጠቀሱት ከተሞች በርካታ ቡና ቤቶች ውስጥ እየሰሩ እንዳሉ ስለሰማሁ ደፍሮ መሄድ አቃተኝ:: መተሀራን ግን በሁለት ምክንያቶች መረጥኳት:: አንደኛ የዐምባ ልጆች ላይኖሩ ይችላሉ በሚልና ካልሆነልኝ እንኳን በዛው አዋሽ አርባ በመሄድ ስራ አስቀጥርሻለሁ ያለኝ ፍቅሩ ሃይሉን ማግኘት እችላለሁ በሚል::

መተሀራ መርቲ ስሄድ በጣም ነው የደነገጥኩት- አራት የዐምባ ልጆችን አገኘሁ:: *የት ምድር ይሆን የዐምባ ልጆች ያልፈሰሱበት? የት ይሆን ዐይናቸውን የማላይበት?* በተለይ እንደእኔ ጨርሶ እንኳን ዘር ማንዘራቸውን የማያውቁ ወይም እያወቁም ተቀባይ ያጡ የተሰማሩት መጥፎ ስራ ላይ ከሆነ ማንነታቸውን ሸምጥጥ አድርገው ከመካድ ወደኋላ አይሉም:: ዝዋይ እያለሁ ሀይቆች ሆቴል ሁለት የዐምባ ሴቶችን አግኝቼ በስማቸው ጠርቼ ላናግራቸው ስል "ተሳስተሻል" ሲሉ ድርቅ ብለውብኛል:: *እኔም አንድ ቀን እንደነሱ አደርግ ይሆን?* መርቲ ላይ ዕዮን ተስፋዬና መታሰቢያ ተስፋዬ የሚባሉ እህትማማቾችን ሳገኛቸው ጮህኩ:: ዕዮን ጋዜጠኝነት ከእኔ ጋ ትሰራ ስለነበር በጣም እንቀራረባለን:: "በይ ነይ እኛ ጋ ትቆያለሽ::" ብላ ይዛኝ ሄደች:: *የምን ቡና ቤት ለስራ ነው የመጣሁት ለለ?* ትንፍሽ ሳልል ሁለት ቀን ቆየሁ:: ይሁን እንጂ ከፍተኛ ሙቀት ያለበት ሀገር ስለነበር

ጡቴ በጣም ታመመ:: ፍቅፍቅ እያለ አሰቃየኝ:: ለፅዮንም ለምን እንደመጣሁ ጫፍ፣ ጫፉን ስነግራት በሁኔታው አዝና መከረችኝ:: "ምን ሲደረግ ነው ቡና ቤት የምትገቢው? እዚሁ ኬክ ቤት ነገር ፈልገንልሽ ትሰሪያለሽ" አለችኝ:: ፅዮን ከእናቷ ጋር ነው የምትኖረው::

*ስራው ቢገኝስ እንዴት ነው የምሰራው?* ጥያቂ የሆነብኝ ነገር ነበር:: ሌሊቱን እንዲችው ካርቶን ሲርገበገብልኝ፣ እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ጭንቀት አዕምሮዬን ወጥሮት ሙቀት ጡቶቼን ሲያፈነዳቸው ደርሶ በመከራ ስማይና ምድሩ ተላቀቀ:: ሙቀት፣ ጭንቀቱና ህመሙ ህይወቴን ሲኦል ያለች አስመሰሏት:: ምንም እንኳን ያስጠጉኝ ሰዎች ተንከባክበው ቢይዙኝም ከህመሜ ልፈወስ ስላልቻልኩና ስራውም ስላልተገኘልኝ *ስበፍ ቢሱ ስበፍ ደገኛስ* የሚለውን ብሂል እውነታነት ላረጋግጥ ወሰንኩ:: እናም አዋሽ አርባ የማውቀው ሰው ስላለ ጠይቄ እመለሳለሁ ብዬ ተነሳሁ:: የነበረኝ የመጨረሻ ምርጫና ተስፋ እሱ ብቻ ነበር:: እዛው ያረፍኩበት ቤት ከነበረች አንዲት ቀልቃላና ከወንዶች ጋር ፈጣን የመግባባት ችሎታ ካላት ልጅ ጋ ተያይዘን ሄድን::

የተሳፈርንበት አውቶቡስ ውስጥ ሆኜ በሀሳብ ማዕበል እየቀዘፍኩ ሳለሁ ህይወቴን የሚለውጥ ክስተት እንደሚጠብቀኝ ቀልቤ ሹክ አለኝ:: ሹክ...

# -19-

አዋሽ አርባ ኬላው ጋ ስንወርድ ከኬላ ጠባቂዎቹ መካከል የዐምባ ልጆች መኖራቸውን አይቼ ደነገጥኩ:: ምሳ በልተን፣ ለስላሳ ጠጥተን እንድንሄድ ሲጠይቁን ካምፑ ከኬላው በጣም ጥቂት ርቀት ያለው በመሆኑ ተመልሰን እንደምንመጣ ነግሬያቸው በእግር ወክ እያደረግን ሄድን::

ካምፑ በር ላይ ስንደርስ ፍቅሩ ሀይሉን ለማናገር እንደመጣሁ ስነግራቸው ጠሩልኝ:: ፍቅሩ ግጥም አድርጎ ሬንጀር የወታደር ልብስ ለብሶ ሳየው በጣም ተገረምኩ:: ምን እንደሚሰራ ጠይቄው ወታደር መሆኑን ሊነግረኝ ስላልፈለገ በዝምታ የማለፉ ምክንያት አሁን ገባኝ:: የመጣው ጠንክር ከሚባል ወታደር ጋር ነበር:: በቃ ወታደሮቹ ሁሉ እኔን ሲያዩ እንግዳ መጣ ብለው ልዩ እንክብካቤ ጀመሩ:: ከሁሉም ጋር "ያልኳችሁ ልጅ እሷ ናት::" እያለ አስተዋወቀኝ:: መስፍን የሚባል መምህራቸው ክፍል አስገቡንና አብዝተው ተንከባከቡን:: ጨዋታ ተጀምሮ በቋንቋቸውና በሁኔታቸው ሲያስቁን ቆዩና "ምሳ እንብላ እንውጣ!" ተባለ:: ካምፑ ውስጥ ካፌና ሬስቶራንት ቢጤ ቢኖርም ነገሩ ሁሉ እንቁላል በዳቦ ዳቦ በምናምን፣ ዳቦ... ዳቦ ብቻ ነው:: ያው ዳቦ በምናምን ተጋበዝን::

ምሳው ካለቀ በኋላ ተዝናንተን እንምጣ ብለው አንድ የጭነት መኪና

እስቋመው ተጭነን ወደ ከተማው ወጣን:: እነሱ ቢራ ሲጠጡ እኛ ለስላሳ እየጠጣን ስንጫወት ቆይተን ወደ መስፍን ክፍል ተመለስን:: ወደ ክፍል ስንመለስ አብራኝ የመጣችው ልጅ ከሌሎች ወታደሮች ጋር ቆማ ስትጫወት ፍቅሩ የካምፑን መዝናኛና የተላላኪዎችን ስራ ወስዶ አሳየኝና "እዚህ ነው አስገባሻለሁ ያልኩሽ::" አለኝ::

"በጣም ጥሩ ነው... ግን ወታደሮቹ አይተናኮሉም?" ስል ጠየቅኩት::

"አይዞሽ የእኔ ዘመድ መሆንሽን ስለሚያውቁ ምንም አያደርጉሽም!" አለኝ:: ያሳየኝ ተላላኪዎች ስራቸውን ለማቀላጠፍ ተፍ፣ ተፍ እያሉ ነበር:: ቢያንስ ነገሮችን እስካስተካክል ድረስ ጥሩ ቦታ ሊሆነኝ እንደሚችል አሰብኩ::

"እሺ በቃ ልሂድ::" አልኩኝ እየተነሳሁ::

"እንዴ የምን ጥድፊያ ነው?"

"ኧረ አልተጣደፍኩም... እየመሸ'ኮ ነው::"

"በቃ ስራሽን ለመጀመር ደግሞ የምን መሸ ነጋ ያስፈልጋል? እዚሁ አይደል የምትኖሪው? ለማንኛውም ስላንቺ በጣም ብዙ ነገር ፍቅሩ ነግሮናል::" አለኝ መስፍን::

"ይሆናል" ስል ለመውጣት ተነሳሁ:: አብራኝ የመጣችውን ልጅ የት ይዘዋት እንደሄዱ ለማወቅ ብትፈለግ፣ ብትታሰስ ጠፋች::



Scanned by CamScanner

"ለማንኛውም ልፈልጋት እስቲ?" ሲል መስፍን ወጣ:: ነገር ግን ጨለማ በሰማይ ላይ እስኪነግስ የገቡበት ጠፋ::

"እንዴ ምነው አንቺ እንዲህ ተጨነቅሽ? ስራውን የምትሰሪው'ኮ እዚሁ ካምፕ እያደርሽ ነው:: ምነው ካውሬ ጋ የምታድሪ አስመሰልሽው?" ሲል ተነስቶ የክፍሉን በር ቆለፈው::

ቆልፎት ግን የተፈጠረ ነገር አልነበረም::

ስናወራ ቆየንና "አንቺ እንግዳ ነሽና አልጋው ላይ ተኚ እኔ መሬት እተኛለሁ" አለኝ:: በጣም መሽቶ ነበር:: አብራኝ የመጣችውን ልጅ ጠንክር የተባለው ጓደኛው ይዟት እንደሚመጣ ነግሮኝ ፍራሽ አንጥፎ ተኛ:: እኔ አልጋው ላይ ተቀምጬ ልጅቷ የት ልትሄድ እንደምትችል እያሰብኩ በጥበቃ ላይ ሳለሁ:-

"በበኩሌ ግን እዚህ ስራ ከገባሽ ወታደሮቹ ላያስቀምጡሽ ይችላሉ ብየ እሰጋለሁ::" አለኝ::

"እንዴ? ቅድም ምን ነበር ያልከኝና አሁን ሀሳብህን ለወጥክ?"

"መለወጤ ሳይሆን እኔ ስለወደድኩሽ እንዲነኩብኝ ስላልፈለግኩ ነው"

ደነገጥኩ:: ጨርሶ ያልጠበቅኩት ነገር ነው:: ለዚህ ሀሳቡ ምን መልስ መስጠት እችላለሁ? ዝም አልኩ::

"ሴክስ እንድናደርግ እፈልጋሁ::" ሲል ድንገት ከፍራሹ እንጣጥ ብሎ

አልጋው ላይ አረፈ::

"ኖ... ፍቅሩ! እኔ ድንግል ነኝ::"

"ኧረ ባክሽ?" በሹፈት::

"ሙት... በናትህ እኔ አምኜህ ነው ዝም ብዬ የተቀመጥኩት::" በእውነት የሚገርመኝ ታላቅ ደደብነቴ ፈፅሞ መጠርጠር የሚባል ያልፈጠረብኝ መሆኔ ነው:: ከማላውቀው ሰው ጋር እየተጫወትኩ ቆይቼ አንድ አልጋ ላይ መተኛት ቢኖርብን አደርገዋለሁ:: እኔ እንደውም መሬት መተኛት አለብኝ ምናምን ማለት ያላሰበውን ሰው ማሳሰብም መስሎ ነው የሚታየኝ::

"የማላውቀሽ መሰለሽ? ሸርሙጣ! ቡና ቤት አይደል ያገኘሁሽ?"

"እና... ቢሆንስ... ልግባ፣ አልግባ እያልኩ እየታገልኩ እያለ አግኝቼህ ተስፋ ስለሰጠኸኝ አይደል ትቼው የመጣሁት?"

"በጣም ጥሩ:: ስራውን አስቀጥርሻለሁ ብዬሻለሁ:: አንቺ ደግሞ ልትቸገሪልኝ ይገባል::"

"አይሆንም ፍቅሩ! በፈጠረህ አምላክ::"

"ይኸው... ኮንዶም እኮ አለ::" ከፍራሹ ስር አወጣ::

"እኔ'ኮ ሌላ ነገር ብዬ አይደለም... ወንድ የሚባል አላውቅም..."



Scanned by CamScanner

በቦክስ ደረገመብኝ:: ብቻ ልቆጣጠረው እስኪያዳግተኝ የዱላ ውርጅብኝ አዘነበብኝ:: ስቅስቅ ብዬ እያለቀስኩ ለመንኩት:: *ከቡና ቤት ሀይወት ያዳነኝን ለምሳሌ እንዳላመሰገንኩት እንዲህ ያለ መከራ ላይ ይጣለኝ?*

ጥረቴና ልመናዬ ከንቱ ሆኑ::

ሁለቱን እጆቼን በሁለቱ ጉልበቶቹ ተጭኖ አላፈናፍን አለኝ:: ወዲያውም በሀይል ብጥስጥስ አድርጎ ፓንቴን አወለቀው:: በአንድ እጁ አንገቴ ላይ ይዞ ከፍራሹ ጋር በማጣበቅ ነፃ በሆነው እጁ ኮንዶሙን አንስቶ በጥርሱ በመታገዝ ቀደደው:: ከዛም እንደሌባ ጣት በተገተረ ብልቱ ላይ አጠለቀውና ወደሰውነቴ ሲያስገባው በጣም ጮህኩ::

"ኡኡኡ!" በሀይል ጮህኩ::

"ዝም በይ አንቺ!" ሊስመኝ ተጠጋ::

"ኡኡኡ!"

"ናይ ዝምበ አንቺ! እናትሽ አፈር የበላች!"

"እባክህ!"

"ምን ያለችው ሸርሙጣ ናት!" ዱላ፣ ስድብና ወሲብ ተደራርበውብኝ ተዝለፈለፍኩ:: ሰው ቢደርስልኝ ብዬ ብጮህም ወታደሮች ባህርያቸው ሆኖ ጨርሶ ሊሰሙኝ አልቻሉም:: ግፊቱ ሲጠነክርብኝ በተሰማኝ ህመመም እየጮህኩ ለመንፈራገጥ ስሞክር በጥፊ መታኝ::

"አውቀሽ... ለማስመሰል ነው አይደል የምትጮኺው?" ዱላው ሲበዛብኝ ህመሙን ለመቋቋም እየሞከርኩ ጩኸቴን እውጠዋለሁ:: ግፊቱ ሲጠክርብኝ ግን መልሼ እጮሀለሁ::

"ምን የማገባሽ መሰለሽ እንዴ? አይዞሽ ድንግል እንዳልሆንሽ አውቃለሁ!" ስድቡን፣ ዱላውንና ግፊቱን መቋቋም ትልቅ ችግር ነበር የሆነብኝ:: የግፊቱ ማየል ጨርሶ ከእኔ አንደበት አወጣዋለሁ ብዬ የማላስበውን ረዥምና ጥልቅ የስቃይ ጩኸት እንዳወጣ አደረገኝ::

ጎንበስ ብሎ ሲመለከት ደም በደም ሆኛለሁ:: ደነገጠ:: ከላዬ ላይ ብድግ እያለ "እኔ'ኮ ድንግል ነኝ ስትይኝ ነው እልህ ያስያዝሽኝ" አለኝ:: ዝም ብሎ አትረመረመና ደም የፈሰሰበትን አንሶላ ሊያጥብ ሳፋ ነገር አመጣ:: እኔ ግን አጠገቤ የተቀመጠ ወረቀት አንስቼ አንሶላ ላይ የፈሰሰ ደሜን በጣቴ እያጠቀስኩ ወረቀቱ ላይ ቀኑን እየፃፍኩት ነበር- ከደናግላን ጎራ የወጣሁበትን ቀን::

አንሶላውን አጥቦ ሲጨርስ እንደገና ግንኙነት ማድረግ እንደሚፈልግ ነገረኝ:: የምችለውን ያህል ተወራጭቼ አጠገቤ እንዳይደርስ ለመከላከል ሞከርኩ:: ተሳደብኩ:: እነዚህ ሁሉ ግን ትርጉም አልነበራቸውም::

የጠየቀኝ ጥያቄ ደግሞ አስደንጋጭ ነበር-

ዱላው ስለጎዳኝና አቅም ስላጠረኝ እንዷ እንደወረቀት ቡጭቅጭቅ ባደርገው ደስ ባለኝ:: በተቻለኝ መጠን ተቃውሞዬን ለመግለፅ ብሞክርም አልተሳካልኝም:: እየደበደበ... እየቀጠቀጠ "አንቺ ሸርሙጣ!" ሲል



Scanned by CamScanner

እየተሳደበ እግሮቼን ከአልጋው ብረት ጋር አሰራቸው:: እውነቱን ለመናገር ግን እግሮቼን ሲያስራቸው ፈፅሞ አላውቅም ነበር:: በመቀመጫዬ በኩል ሀይለኛ ህመም ሲሰማኝ ከገባሁበት አዕምሮ መሳት ነቅቼ ነው ያወቅኩት::

በደረቴ አልጋው ላይ አስተኝቶ እግሮቼን ከብረቱ ጋር ካሰራቸው በኋላ ከሆዴ ዝቅ ብሎ ይዞ በትከሻዬ አልጋውን እንድስም በማድረግ ስቃዩ ልብን በሚሰውር ሁኔታ በኋላ በኩል... ስቃዩን መቋቋም አቅቶኝ እንባዬ እርግፍ፣ እርግፍ እያለ ሳቃስት "በቃ ጨረስኩ... ጨረስኩ" ይለኝ ነበር:: እኔ ግን ነብሴንም ቢጨርሳት ተመኘሁ:: ከኋላ በኩል ሰውነቴ ሲደማ በደንብ ነበር የታወቀኝ:: በመጨረሻ ዝልፍልፍ ብሎ ሲወድቅ ወደ አልጋው ላይ ሰውነቴን ለማሳረፍ እንኳ ተስኖኝ በሰቀቀን አለቅኩ::

እንዴት ልሁን? መገላበጥ አልችል... በጀርባዬ መተኛት አልችል እንዲችው ስቃይ ሲያስምጠኝ ቆየ:: ካለማቋረጥ ከማልቀሴ የተነሳ አይኖቼ አብጠው እንደ እሳት ሲፈጁኝ አነጋኋት:: *ከዚህ በኋላ እዚህ ቤት መቆየት የለብኝም!* ስል የግዴን ተነሳሁ:: እግሬ አልታጠፍና አልዘረጋ ሲለኝ በመከራ ሳብ መለስ፣ እጥፍ ዘርጋ እያደረግኩ ላንቀሳቅሰው ሞከርኩና ተሳካልኝ::

ማስታጠቢያና ውሀ እንዲሰጠኝ ስጠይቀው ፍራሹ ላይ አቀርቅሮ እንደተቀመጠ ያለበትን ቦታ አሳየኝ:: ሳፋ አቅርቤ በቀዝቃዛ ውሀ ከወገቤ በታች ልታጠብ ውሀውን ባፈሰስኩበት ቅፅበት በድንጋጤ ከሳፋው ተስፈንጥሬ ወጣሁ:: እሳት የሆነ ውሀ እላዬ ላይ የደፋሁ ያህል ነው

ጥዝጣዜው ያስፈነጠረኝ:: በጣም ተቃጠልኩ:: በተለይ ውሀ በመቀመጪያዬ በኩል ሲነካኝና ሽንቴን ስሸና የተፈጠሩብኝ ስቃዮች ዘለዓለም የማያልፉ ያህል ተሰሙኝ:: እንባዬ ክንብል፣ ክንብል እያለ ሲያል ውስጥ ያለሁ ያህል ሁሉ ነገሬ እንደ እሳት መንደድ ጀመረ::

ሰውነቴን መሸከም አቅቶኝ፣ እግሮቼን እየጎተትኩ ከክፍሉ ስወጣ ሊሸኝ ኝ ተነሳ:: "እንዳትከተለኝ... አንድ ሰው እንዲጠጋኝ አልፈልግም!" አልኩት:: እየተጎተትኩ ስወጣ አብራኝ የመጣችውን ልጅ ኬላው ጋ አገኘኋት:: ከኋ ጋ የት ነበርሽ? የት አደርሽ? ብዬ የምጨቃጨቅበት አቅም አልነበረኝም:: እንዳመመኝ ነገርኳትና እንደምንም ደግፋ አውቶቡሱ ውስጥ አስገባችኝ:: እንዴት ብዬ ልቀመጥ? ህመሙ ሲበረታብኝና ሊያስቀምጠኝ ሲያስቸግረኝ በአንድ ጎኔ ከፊት ያለውን ወንበር ይዤ ተንጠልጥዬ ለመጓዝ ሞከርኩ:: ውስጤ በጣም ሲረበሽ ቆየና ከቁጥጥሬ ውጪ ሆኖ አስመለሰኝ::

ይሄን ጉድ ለማን አወራዋለሁ? ምንስ ሆንኩ ብዬ? ይነገራልስ? ብቻ እንዳፈንኩት መተሀራ ላይ ደረስን:: እሷ ስትወርድ እኔ በዛው ወደናዝሬት ለመሄድ ፈልጌ ነበር:: የሚያስመልሰኝ ነገር በጣም ሲተናነቀኝና ጡቴንም በሙቀቱ ምክንያት ህመም ሲሰማኝ ከመኪናው መውረድ ጀመርኩ:: ወርጄ ሳልጨርስ ግን የሚያስመልሰኝ ነገር ከፊት ጨር ብሎ በመፍሰስ ቀደመኝ::

# -20-

ናዝሬት እንደደረስኩ ቀጥታ ወደማርያም ቤተክርስቲያን ነበር የገሰገስኩት:: ቤተክርስትያኗ እንደገባሁም አፈሩ ላይ እየተንከባለልኩ እዬዬን አስነካሁት:: አፈሩን እያፈስኩ ሰውነቴን ሁሉ እያበስኩበት "እመቤቴ ማርያም ሆይ በዚህ ላይ ባረግዝ አላሳዝንሽም ወይ?" ብዬ ጠየኳት:: እስከ አሁን የተመሰቃቀለ ህይወቴ ሳያንስ ሌላ ምስቅልቅል ለማስተናገድ የሚያስችል ወኔ እንደሌለኝ ሳውቅ አምርሬ አለቀስኩ:: "እባክሽ እመቤቴ ማርያም ሁሉም ይቅር.... ግን እንዳረግዝ አታድርጊኝ!" ለቅሶው ሲያዝለኝ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ::

ስነቃ ከነህመሜ ነበር የነቃሁት:: በመቀመጫዬ በኩል ልብሴ በደም ርሷል:: *ዮት ሄጄ ምን ሆንኩ በማለት ምን ማውራት ስችባለሁ?* ለራሴ እንኳን ሊያሳምነኝ የሚችል ምክንያት አጣሁ:: ምንም መሄጃ እንደሌለኝ ሳውቅ ራሴን ማስታመም ወይም ራሴን በማጥፋት አሁን ካለው ስቃይ ብቻ ሳይሆን ነገ ሊፈጠር ከሚችለው ስቃይ ጭምር ራሴን ማዳን አለብኝ አልኩ:: ራሴን ለማጥፋት ግን ድፍረት አጣሁ:: እስከመቼ እንደሆነ ባልለየውም ተመልሼ ጉዳና ላይ ማረፌን አወቅኩት:: ገንዘቡን ሁሉ ልብስ ገዝቼበት፣ ለትራንስፖርትና ምግብ አድርጌ ጨርሼዋለሁ:: *ለሁን ሰጄ ባይ በቀረው ገንዘብ ምን ማድረግ ስችባለሁ?* ቡና ቤት ለመስራት

እንዳልጠቀምበት መታከም አለብኝ፣ እንዳልታከም ምን ብዬና በምን ያህል ብር መታከም እንደምችል ግራ ሲገባኝ እመቤቴ ማርያም እንዳደረገች ታድርገኝ ብዬ ወሰንኩ::

ምንቴንም ቀበጧ ስኔ ነኝ:: ስል ራሴን መውቀስ ጀመርኩ:: ከማን ጋር እየተጋጨሁ እንደሆነ ባይገባኝም ቅሉ ውስጤ ግን በርካታ ሙሉ ጉጃሞች ወይም የማላውቃቸው ሰዎች ያሉ ይመስል ይሞግቱኝ ያዙ::

"ምኑን አውቀሽው ነው... ጥሩ ሰው ነው ብለሽ አይደል የሄድሽው?" አንደኛው::

"ጥፋቱ ያንቺ ነው... ወንድ ነይ ሲልሽ የምትሄጂው ያለጥቅም አንቺን ሊረዳሽ እንደማይችል ሳይገባሽ ቀርቶ ነው?" ሁለተኛው ሃሳብ::

"በገዛ እጅሽ ያመጣሽው ጣጣ ነው::" ሦስተኛው ሃሳብ::

"ለጥፋቱ ሁለታችሁም አስተዋጽኦ አላችሁ" አራተኛው:: ሁሉም የየራሳቸው መልክና ቅርጽ ይዘው ሃሳብ የሚቀባበሉ ያህል ታዩኝ:: ሁኔታው ሲያስፈራኝ ግን በሃይል ጮህኩ:: ቤተክርስትያኑ ውስጥ ያሉ ሰዎች በግርምት እስኪያዩኝ ጮህኩና አይኔን ጨፍኜ ስገልጠው እልም ብለው ጠፉ::

* * *

እያደር ህመሙ ሲጠናብኝ ምንም ምግብ መብላት አቆመኩ:: ሳልበላ ከዋልኩ መፀዳጃ ቦታ ላይ የማስወጣው ስለማይኖር በመቀጫዬ በኩል

ያለውን ህመም ለመንከባከብ ሞከርኩ:: ይሁን እንጂ ርሃቡ ቀን አልሰጥ እያለኝ የበላሁ እለት መፀዳጃ ቦታ ስቀመጥ የማየውን የከፋ ስቃይ እኔና እግዚአብሄር ብቻ ነን የምናውቀው:: ከላይ ጡቴን... ከሥር... በዛ ላይ ጭንቀት.... ያም ሆኖ ግን የጐዳና ላይ ህይወት ከነችግሩ ለእኔ የተሻለ ነበር:: ጎዳና ላይ ያሉ ልጆች በተለይ ከዚህ በፊት ሁለቴም ስመጣ የነበሩት አዝማሚያዬ አስፈርቷቸውና ሦስት ጊዜ ከጠራት የጎዳና ሃድራ ሰፍሮባታል ማለት ነው ብለው ከቤተክርስቲያኑ ግንብ ጋር አያይዘው ትንሽ የላስቲክ ቤት ሰሩልኝ::

# -21-

ለሁለት ዓመታት የናዝሬትን ጎዳና ተኛሁበት:: ህይወቱን ለምጄው ኑሮዬ የሚፈፀመው እዛው ነው ብዬ ባመንኩበት ሰዓት አንድ ዘላለም የሚባል ሰው በጎዳና ተዳዳሪዎች ላይ ፕሮግራም ለመስራት መጥቶ ስዘፍን ካየኝ በኋላ ከአለባቸው ተካ ጋር አገናኝሻለሁ ከቻልሽ አዲስ አበባ ነይ ብሎ ስልክ ቁጥሩን ሰጠኝ:: ነገሩን ሳውጠነጥነው የጎዳና፣ የጎዳና እንደብርቅ የሚታየው አዲስ አበባ ጎዳና ላይ ብከትም ይሻላል ብዬ ለመሄድ ልቤን አነሳሳሁት:: ዘላለም ወደ አዲስ አበባ ከመጣሽ ከአለባቸው ጋር አገናኝሻለሁ ነው እንጂ ያለኝ ሌላ ያደረገልኝ ነገር ስላልነበር ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ የትራንስፖርት ገንዘብ ማግኘት ችግር ሆነብኝ::

ውስጤ ሃሳቡ እየተተራመሰ የትራንስፖርት ማግኛ መንገዱን እያውጠነጠንኩ እያለ "ነገ ኢየሱስ ስለሚነግስ መሄድ አለብን" ተባለ:: ጥቂት ገንዘብና በተለይም ደግሞ ምግብ እንደልብ እንደሚገኝ እርግጠኞች ነበርን:: እኔ ግን በተለየ መንገድ ለትራንስፖርት የሚሆነውን ገንዘብ ማግኘት እንዳለብኝ ተሰማኝ::

ኢየሱስ ቤተክርስቲያን እስክንደርስ ድረስ በምን መንገድ ገንዘቡን ማግኘ

ት እንዳለብኝ ሳምሰለስል ሁለት አማራጮች ነበሩ አእምሮዬ ውስጥ የተከሰቱልኝ መስረቅ ወይም መለመን:: መለመን ካለብኝ የሆነ ተአምር እንዲፈጠር ጭምር ፀልዬ ካልሆነ የአምስት ሰው ፊት አይቼ የሚገኘው ሃምሳ ሣንቲም ብቻ ነበር:: በዚህ ዓይነት እንዴት ነው የምፈልገውን ያህል የማገኘው? መስረቁ በጣም ጥሩና ቀልጣፋው መንገድ ነው:: ግን እንዲያ ላደርግበት የሚያስችል ድፍረትና ህሊና አልነበረኝም:: *ቀደም ሲል ለአእምሮዬ መስረቅ ለቋራጩ የገንዘብ ማግኛ መንገድ መሆኑን ነግሬው ቢሆን ኖሮ ባላዋረደኝ ነበር* ስል አሰብኩ:: ስለዚህ መለመን ሊኖርብኝ ነው ማለት ነው:: ግን እንዴት?

በተመሳሳይ ሁኔታ ታቦት ሲወጣ ለምኜ ነበር:: "እራበኝ!" ስል:-

"ነይ ለእኔ ቀስ ብለሽ በጆሮዬ ሹክ በይኝ..."

"ውይ የኔ ቆንጆ.... እኔ ለምን ሌላውን ነገር አልመግብሽም? አንቺን የመሰለች ልጅ ይለምናል? ምነው የሚሰረቅ ጠፋ እንዴ?" እያሉ ሲቀልዱብኝ ነበር:: ከጉዳና ተዳዳሪዎቹ በተሻለ ንጽህናም የምጠብቅ ስለሆንኩ ልምናዬ ሊሰማና ዕድለኛ ልሆን አልቻልኩም ነበር:: በተደጋጋሚ ያየሁት ነገር ቢኖር ናዝሬት ማርያም ቤተክርስቲያን በር ላይ አንዲት አይነስውር ሴት ስትለምን የሚሰጣት ገንዘብ ከፍተኛ መሆኑን ነው:: *በምስክነት የሚያምን ህዝብ* የሚለው ትዝ አለኝ::

ቤተክርስትያኑ እንደደረስን በቤተክርስትያኑ ጀርባ ዞርኩና አፈሩን አፍሼ ጭቃ እንዲሆን እጄ መዳፍ ላይ በማድረግ በደንብ አላቆጥኩት:: በደንብ መላቆጡን ሳይ ደፍሬ ዓይኔ ላይ ቀባሁት:: ጭቃ ራሱ የሚያቃጥል

መሆኑን ያወቅኩት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው:: በደንብ እስኪደርቅ ድረስ ዓይኔን እንደጨፈንኩ ቆየሁ:: ሲደርቅም ከላይ ያለውን ሳራግፈው በእጄ የምነካው ዓይኔን ብቻ ሆነ:: ጭቃው ጠቆር ያለ ስለነበር ማየት ባልችልም ከኔ ቀለም ጋር በጥሩ ሁኔታ የተመሳሰለ ይመስለኛል::

ዋናውን መንገድ ይዤ ስሄድ ብዙ ሰዎች መስመሬን እየሳትኩ እንዳለሁ በመጠቆም ትክክለኛውን አቅጣጫ ያስይዙኝ ጀመር:: *የተዋጣለት ዓይነስውር መስያለሁ ማለት ነው::* ስል አሰብኩና ድምጼን ሞራርጄ ልመና ጀመርኩ::

*እንባ ከብሰለ፣ ከብሰለ የልጆች ጨዋታ*
*ብርሃኔ ጠፋቶ ሰርቼ እንዳልበላ*
*ለሰሞቼ ለለዓይነ ብርሃን... ለለ ሙሉ ለካላተ ብላቸሁ*
*ለያያቸሁ እንዳታልፉኝ...*

እያልኩ ድምጼን በቅላፄ ለቀቅኩት:: አንዳንድ ሰዎች ከንፈራቸውን በመምጠጥ እጄ ላይ ፍራንኮች መበተን ሲጀምሩ ያቺ ሞዴል የሆነችኝ ዓይነሥውር ትዝ አለችኝ:: ሞራል ጨመርኩ::

*ባሌለ ምን ሲሆን ነው ልጆቼለ ምን ይብሉ*
*ለኔን ሲጠብቁ ዳቦ፣ ዳቦ እያሉ::*

ውስጤ ግን በሳቅ እየታፈነ ነበር:: በተለይ ባሌን ለምኚ ሳበላው ታየኝ:: *ለፈር ይብላ!* አልኩ በውስጤ:: *ወንድ! መርዝ!*

*ለሰሞቼ ለለ ዓይነ ብርሃን...*

ሳንቲሞቹ መርገፍ ሲጀምሩና የሁሉም ሰው ቀልብ እኔ ላይ ሆኖ "ስታሳዝን... ደግሞ የምታምር ልጅ" ሲሉ "ዞር በይ ካጠገባችን" ያሉኝ የኔ-ቢጤዎችና የጉዳና ላይ ተዳዳሪዎች በሙሉ ሲመሩኝ ፈልገው ጠጋ፣ ጠጋ ማለት አበዙ:: ዐምባ ውስጥ ሳለሁና ዓይነ ሥውር ስትለምን የሰማኋቸውን ሁሉ እያልኩ ልመናዬን አጧጧፍኩት::

*ጓደኞቹ ሁሉ ሄዱ ገጠር ለስርሻ*
*እኔ ብቻ ቀረሁ የሰው መጨረሻ*

"እረ ይቺ ልጅ የማታመጣው ነገር የለም:: ሠርተሽ አትበይም እንዴ?"

"እረ እግዚአብሄር እንዳይሰጥሽ!"

"እውር አድርጎ ያስቀርሽ"

ቅናት እርር ድብን አደረጋቸው:: እንደሆነ ያቺን ዕለት ሃብታም ሆኜ ነው የምውለው... ምን ያመጧታል?

*እናንተ የምታዩኝ እኔ የማላያችሁ*
*በብርሃን ለምሳለ ስርዱኝ ለባላችሁ*

ያገኘሁትን ገንዘብ እንደምንም በዳበሳ ቆጠርኩት:: ለማመን እስኪቸግረኝ ድረስ ደጋግሜ ቆጠርኩት- ሀምሳ ብር ነው:: ይህን በአይኔ በብረቱ አይቼ ካላረጋገጥኩ በግምትና ዳበሳ ቆጠራ አላምንም ብዬ አይኖቼን ለመግለጥ በጣም ታገልኩ:: ድርቅ! እንቢ አለኝ::

# -22-

ረዥም ቀሚስ፣ ነጭ ቲሸርትና ነጠላ ጫማ አድርጌ ነበር አዲስ አበባ የገባሁት:: ማንም ጉዳና ተዳዳሪ ናት ብሎ ማሰብ በማይችልበት ሁኔታ ሽክ በልክ ብያለሁ:: እጄ ላይ ጥቂት ገንዘብ ብቻ ቢሆንም ያለው ውስጤ ግን የጉዳና ላይ ስቃይ በቃ የተባለ ያህል ፊቴን ብርሃን አጉናጽፎታል:: ምናልባትም ዐምባው መበተኑን ካወቅኩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ይመስለኛ ል ደስታ የሰፈነብኝ:: ምንም እንኳን የጡቴ ህመም ጨርሶ ባይድንም፣ ምንም እንኳን ብዙ ስለማልመገብ ሽንት ቤት መቀመጡ ስለማይበዛብኝ በመቀመጫዬ በኩል ያለው ህመም ጨርሶ ባይጠፋም እግዚአብሄር ይመስገን ዛሬ የአዲስ አበባን አየር እየማግኩ በመሆኑ ውስጤ ዕረፍት ሰፍኖበታል:: በተለይ የዙሪያሽወርቅ ዘመዶች ጎዳና ላይ ሳያዩኝ ወደ አዲስ አበባ መሄድ መቻሌ ውስጤን በአሸናፊነት ደስታ አጥለቀለቀው:: እርግጥ አንድ ሁለት ሰዎች ያገኙኝ ቢሆንም ጎዳና ላይ እንዳለሁ ሳይሆን ቤተክርስትያን እንደምሳለም በማሰብ ነበር ሰላም ብለውኛ የነበረው:: ዐምባ እያለሁ ሁለት ወር ለክረምት እረፍት ብቻ ስለምመጣ ከዙሪያሽወርቅ ቅርብ ዘመዶች በቀር የሚያውቀኝ እምብዛም ሰው አልነበረም::

ጠዋት ላይ አዲስ አበባ እንደገባሁ የህዝብ ሥልክ ተጠቅሜ ዘላለም ጋ ደወልኩ:: መምጣቴን ስነግረው ቤቱ ኮተቤ ጋ መሆኑን ነግሮኝ ምልክት ሰጠኝ:: በሚገርም ሁኔታ የዐምባ ጓደኛዬ እነብርቄ ሰፈር ነበርና አገኘ ኋት:: በጣም ደንግጣ "ከዝዋይ መምጣትሽን ለምን አልነገርሽኝም?" እሷ የምታወቀው ዝዋይ መሆኔን ነው "ብዙ ደብዳቤ ጽፌልሽ ተመላሽ ሆኖብኛል... ምን ሆነሽ ነው ለመሆኑ?" ስትል ጠየቀችኝ:: እናቷ ጥሩነሽም ስታየኝ ጥምጥም ብላብኝ የት እንደጠፋሁ በጥያቄ ወጥረው ያዙኝ:: አማራጭ ስላልነበረኝ ጉዳና ላይ እንደነበርኩ ነገርኳቸው:: በጩቤ መወጋቴንም አሳየኋቸው:: ነገሩን አምነው እንዲቀበሉኝ እንጂ የቆየ ትዝታ መሆኑን አጥቼው አልነበረም::

ስለሁሉም ነገር ሳጫውታቸው ስለመደፈሬ ግን ትንፍሽ አላልኩላቸውም:: እስከአሁን የሚያወቁት ነገር የለም:: ያለሁበት ህይወት ያንን ለማውራት ፈሪ አደረገኝ:: ጥላዬን እየፈራሁ እንድቆይ ስላደረገኝ ነው ቢያንስ ለጓደኛዬ ብርቄ እንኳን እውነታውን ያልነገርኳት:: ብትሸሸኝስ? ማለቴ ያን ጊዜ በጣም ከስቼ እያለሁ ስለ ኤድስ ያለው ምስል ደግሞ ግነት የሞላበት ነበር:: ማንም መደፈሬን የሰማ ቫይረሱ በደሜ ውስጥ አለ ብሎ ቢያስብ ምኑ ያስደንቃል?

ዘላለምን በአካል አገኘሁት:: አለባቸው ተካ ጋ የሚሰሩ እሱ የሚግባባቸው ሰዎች ስለነበሩ "ሂጂና ዘላለም ልጅነኝ ነው ብለሽ አነጋግሪያቸው::" ብሎኝ ቴሌ መድሃኒያለም ወርጄ ቦሌ ኢንተርናሽናል አጠገብ ሞላ ህንፃ

2ኛ ፎቅ ላይ ቢሮውን እንደማገኘው ምልክት ሰጠኝና ብርቄን አስከትያት ሄድኩ።

ቢሮው ስደርስም ፀሐፊዋ ቀጠሮ ከሌለሽ ማነጋገር አትችይም ብላ አላስገባ አለችኝ። እኔ ቀጥታ ከአለባቸው ተካ ጋር ስላልነበረ በሥልክ የተነጋገርኩት ቀጥተኛ ቀጠሮ ተይዞልኝ እንደነበር ለማወቅ ተቸገርኩ። ይሁንና ካላገኘሁት አልሄድም ብዬ ሳስቸግር ሥልክ ደዋውላ ዘሪሁን ቢሮ እንድገባ ተደረገ። ከሱ ጋር ካወራን በኋላ አለባቸው መጣ። ተዋወቅንና በኋላ ችግሬ ምን እንደሆነ ጠይቆኝ ማወራት ጀመርን።

"መጀመሪያ ቤተሰቦቼን ማግኘት እፈልጋለሁ" አልኩት።

"አታውቂያቸውም እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ። ሁኔታውን ሁሉ እያጫወትኩት ስቅ ስቅ ብዬ አለቀስኩ።

"አሁን ለምንድነው የምታለቅሺው? እስከ አሁን ኖረሽ የለም ወይ?" አለኝ

"ቢሆንስ?"

"ቤተሰብ አወቁ፣ አላወቁ ምን የተለየ ተዐምር አለው?" እምባዬን መቆጣጠር እንዳቃተኝ ሲያይ ጌቱና አሻግሬን ጠርቷቸው እንደሚመለስ በመንገር ይዞኝ ወጣ። አንድ አረንጓዴ መኪና ውስጥ አስገብቶኝ ወደ

አንድ ቦታ ሄድን:: "ከቤተሰቦችሽ ውጭ ያለብሽን ችግር ንገሪኝ" አለኝ:: ስለጡቴ መታመም ስነግረው ደንግጦ ወዲያውኑ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሚያውቀው ኤልያስ የሚባል ዶክተር ጋ ደውሎ አወራና ሌላ ቀን ሲባል ሁለት መቶ ብር ሰጥቶኝ እንድደውልለት ነግሮኝ ተለያየን::

እነብርቄ ቤት ስገባ ብርቄ የለችም:: ለካ እዛው ትቻት ኖሯልና የመጣሁት? በኋላ ለእናቷና ለብርቄ የሆነውን ሁሉ ስነግራቸው ደስ አላቸው:: በእውነት ለእኔም ትልቅ ደስታ ነበር::

ከአለባቸው ጋር በመሆን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄጄ ተመረመርኩና መተኛትና ኦፕራሲዮን መደረግ እንዳለብኝ ተነግሮኝ ቀጠሮ ተሰጠኝ:: ከኦፕራሲዮኑ በፊት ግን ከጡቴ ላይ ደም ተወስዶ መታየት እንዳለበት ተወስኖ በህይወቴ ሙሉ አይቼው በማላውቀው ዓይነት ዱላ የሚያክል ስሪንጅ ሊወስዱ ሲል 'ኡኡ' ብዬ ለያዥ ለገራዥ በማስቸገሬ በበነጋው ተቀጠርኩ:: የመጀመሪያው ቀን ደም ሊወስዱ የሞከሩት ተለማማጅ ዶክተሮች ነበሩ:: ዛሬ ዋናው ዶክተር ቀርቦ በስንት መከራ ምርመራው ተደረገልኝ::

ኦፕራሲዮን ልሆን እንደተኛሁ ገና ሳልቀደድ በፊት በሃይል ታመምኩ:: ትንፋሽ አጥሮኝ ፀጥ አልኩ:: እምባ ብቻ ከዓይኔ ይወርዳል እንጂ ድርቅ ነበር ያልኩት:: አንድ ነርስ ይሁን ዶክተር ባላውቅም መርፌ ከወጋኝ ከረዥም ደቂቃዎች በኋላ ነፍስ መዝራቴ ተነገረኝ:: እንዲያውም ዶክተሩ



Scanned by CamScanner

"ይቺ ልጅ በጣም ጭንቀት ላይ ስለሆነች ጥብቅ ክትትል ቢደረግባት ጥሩ ነው:: እያሳሳቀች ሳታውቁት እጃችሁ ላይ እንዳትጠፋ!" ሲል አስጠነቀቃቸው:: ኦፕራሲዮን ለመደረግ ከተኛሁበት ጊዜ አንስቶ አለባቸው እየመጣ ይጠይቀኝ ነበር:: ኦፕራሲዮንም እንድሆን ሃላፊነቱን ወስዶ የፈረመልኝ እሱ ነው:: ማን ቤተሰብ አለኝና ይፈርምልኝ?

በመጨረሻ ኦፕራሲዮን ክፍል ገብቼ ዝግጅት ተደርጐ ልቀደድ ስል አንድ ዶክተር ሲበር መጥቶ የኦፕሬሽን ክፍሉን ቀውጢ አደረገው:: "አይዞሽ አይዞሽ እሺ እሙዬ..." አለኝ:: አለባቸው ቤተሰብ እንደሌለኝ ስለነገራቸው ሊያጽናናኝ ፈልጐ ነው ብዬ አሰብኩ:: ይሁንና "ኦፕራሲዮን መደረግ የለባትም!" አላቸው:: ለአለባቸውም "ይቺን ልጅ አሁን ብንቀዳት ምንም ለውጥ አናመጣም ደም ተቋጥሮበት የነበረው ጡቷ መርፌ ሲነካው የተቋጠረው ደም ፈርሷል" አለው:: መድሃኒት ተሰጠኝና ኦፕራሲዮን መሆኔ ቀረ::

ኮተቤ እነብርቄ ጋ እያለሁ ከአለቤ ጋ ብዙ ጊዜ እንገናኝ ነበር:: ሃሳቤ ምን እንደሆነ ጠይቆኝ ነገርኩት:: አላምን ብሎ እንድዘፍንለት አደረገኝ:: ሰምቶም ሲጨርስ "ይሄንን ጥረት ይዘሽ ተስፋ እንዳትቆርጪ!" አለኝ:: በየጊዜው በሚችለው አቅም ሁሉ ይረዳኝ ነበር:: እኔ ግን ሥራ ባለማግኘቴና ዝም ብዬ እየተረዳሁ መቆየት እንደሌለብኝ ተሰምቶኝ ወደዝዋይ ሄጄ ብሞክር እንደሚሻለኝ አመንኩ:: ይህንኑ ለአለቤ ሳጫውተው "ጥሩ

ነው በራሴ መሥራት መቻል አለብኝ ብለሽ ከወሰንሽ::" ብሎ ብር ሰጠኝ:: ያንን ይገፔ ኑሮዬን ዝዋይ ላይ ከማድረጌ በፊት ነው ከየት እንደተገኘሁና ማን ዐምባ ውስጥ እንዳስገባኝ ለማወቅ ዐምባ ሄጄ ስጠይቅ ወደቀጨኔ ህፃናት ማሳደጊያ የመሩኝና ወደዛ ስሄድ "ህፃን ሰናይት ከልጅነቷ ፎቶ በቀር ማስረጃ የላትም" የሚለውን ፋይል ማየት ችዬ ስሜ ሙሉጉጃም አለመሆኑን ያወቅኩትና ቢያንስ እንኳን ፋይሉ ላይ ባለ ስሜ ልጠራ ብዬ ስሜን ከሙሉጉጃም ወደ ሰናይት የለወጥኩት::



Scanned by CamScanner

# ክፍል ሶስት
# ትዳር



Scanned by CamScanner

## -23-

ዝዋይ እንደሄድኩ አንድ ዘለቀ የሚባል ሰው አገኘሁ። የእናቱ ስም እልፍነሽ ነው። ከአሳዳጊ እናቴ ጋር ምን ዓይነት ዝምድና እንዳላቸው ባላውቅም እንደዘመድ የተዋወቅነው ናዝሬት ነው። አሁን ከእናቱ ጋር ዝዋይ ኑሮውን የመሠረተ ሲሆን በልብስ ሰፊነት ነው የሚተዳደረው። እነሱ ጋ ሄጄ አረፍኩ። ሲያዩኝ ገና በደስታ ነበር የቀረቡኝ። አቀባበላቸውም ሌላ ነገር ነበር። ለጥቂት ቀናት አንቀባሮ የሚያቆይ ገንዘብም ይዤ ስለነበር "ምን ይሰራልሽ፣ ምን በላሽ" እየተባልኩ ቆየሁ።

ወዲያውም ሐረር ቢራ ማከፋፈያ ሥራ አገኘሁና በወር 240 ብር እየተከፈለኝ ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ማታ 2 ሰዓት እሰራ ጀመር። በእውነቱ ለእኔ ድንቅ ሥራ ነበር። ከጐዳና ህይወት ወጥቼ ተቀጥሬ እየሰራሁ መሆኑን ማመን ከበደኝ። ስንቱ ጐዳና ላይ እንደሚቀር፣ ስንቱ ጐዳና ላይ ወልዶ፣ ተዋልዶ ህይወትን እዛው እንደሚመሰርት፣ ስንቱ በገባበት የቡና ቤት ሥራ በዛው እንደሚቀልጥ አውቀዋለሁና ከዛ ሁሉ በአጋጣሚዎች ተጠብቄ ራሷን በመቻል ላይ ያለች ሴት በመሆኔ ደስታዬ ወደር አጣ። ምንም እንኳን ከየት መጥነቴ እና የማንነቴ ጥያቄ እልባት አጥተው እረፍት እየነሱኝ ቢሆንም እንኳ አንዳንዴ ህመምን ችሎ መደሰትም ትልቅነት ነውና ደስ አለኝ።



Scanned by CamScanner

ዘለቀ ቤት ስኖር ምሳዬን እየቋጠርኩ ነበር ሥራ ቦታ የምመገበው:: እያደር ግን በመካከላችን የተፈጠረው ስሜት እኔን ደስ ሳያሰኘኝ ሲቀር ምሳ መቋጠሩን ተወኩት:: ሲርበኝ አቡወለድ ገዝቼ እየበላሁ ሥራዬን ቀጠልኩ::

አንድ ቀንም ሞጆ ከተማ ውስጥ የምትኖር የዙሪያሽወርቅ እህት ባል በምን መንገድ ያለሁበትን ቦታ አውቆ እንደመጣ ባይገባኝም መልዕክት ይዞልኝ መጣ:: "የዙሪያሽወርቅ ልጅ አይደለሽ?" ሲለኝ እርግጠኝነት በጐደለው ሁኔታ ራሴን ነቅንቄ ስጨርስ አንድ ደብዳቤ ሰጠኝ:: ደብዳቤው እየፈለጉኝ እንደሆነና ቤት እንድመጣ የሚገልጽ ነው:: ይሁንና የራሷ የዙሪያሽወርቅ እጅ ጽሁፍ አይደለም:: እንደገናም ስለሷ የሚገልጽ ነገር የለውም:: "እመጣለሁ በልልኝ" ብዬ ነገር አለሙን ረሳሁት:: ምንም እንኳን ዙሪያሽወርቅ ልጄ አይደለሽምና በጊዜ መውደቂያሽን አዘጋጂ ባለችኝ ሳይ ያለኝ ቅሬታ የደበዘዘ ቢሆንም ከቤቷ ካስወጣችኝ በኋላ ግን ለበርካታ መከራዎችና ስቃዮች መዳረጌን መርሳት የሚችል መልካም መንፈስ አልነበረኝም:: እናም ለመሄድ ጨርሶም ፍላጐት አጣሁ::

ወዲያው ግን ያለሁበት ዘለቀና እናቱ ፊት እየነሱኝ፣ ቅርበታቸው እየቀነሰና ፀባያቸው ጨርሶ እየተለወጠ መጣ:: ሁኔታቸውን እንደማስጠንቀቂያ እየተመለከትኩት እያለ ቤቱን ለቅቄ እንድወጣና የራሴን እንድከራይ መከሩኝ:: የማገኘው ደሞዝ ከኪራይ አልፎ ከወር ወር እንደምንም ሊያቆየኝ የሚችል ነበርና ምንም ሳላንገራግር አመስግኜያቸው የሚከራይ ቤት መፈለግ ጀመርኩ::

አንድ ክፍል ቤት በሃያ ሰባት ብር ተከራየሁ:: ቤቷ ጥሩ ነበረች:: ይሁን

እንጂ የስፈሩ ጉረምሶች መግቢያ መውጫ አሳጡኝ:: ሥራ ቦታ ላይ ባለቤቱና ልጆቹ ማታ እየመጡ የሚጠጡ ሰዎችን በአግባቡ ማስተናገድ እንዳለብኝ እየነገሩኝ ሌት ተቀን ይጨቀጭቁኛል:: የጠጪዎቹን ፍላጉት እንዳላሟላ መንገድ ላይ ዱርዬዎች ይለክፉኛል... በተለይ አንድ ትራፊክ ፖሊስ መተንፈሻ እስካጣ ድረስ መከራ ሆነብኝ... ይሄም ሁሉ እየሆነ ግን ማንም ሰው ሊገጥመው የሚችለው ዕጣ እንደሆነ በማመን ተቋቁሜው ነበር:: ነገሩ ግን እየባሰ ሲሄድ የተከራየሁበት ቤት ጉን ያለ ጫማ ቤት የሚሰሩ ልጆችን ቀስ ብዬ በመቀራረብ እንዲሸኙኝ ማድረግ ጀመርኩ:: ለሚያስቸግሩኝም ሁሉ አንዱን "ባሌ ነው!" እያልኩ እያስተዋወቅኩ እንዲያው ለጥቂት ነገሩን ለማቀዝቀዝ ሞከርኩ:: በዚህ ሰዓት ላይ ደግሞ ባሌ ነው ካልኩት ልጅ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለን ሲረዱ ጠንካራ ዛቻና ዱላ ያቀምሱኝ ገቡ:: ያኔም ቤት መቀየር እንዳለብኝ አምኜ አንገት ማስገቢያ ብቻ ያላት ቤት በ18 ብር ተከራየሁ:: ችግሩ ግን እዚህም ሊተወኝ አልቻለም:: እንደገና ቤት መቀየሩ ትንሽ ጊዜም ቢሆን ትንፋሽ ይሰጠኛልና ጫማ ለሚሰራው ጓደኛዬ ሌላ ቤት እንዲፈልግልኝ ነገርኩት::

ይሄን ባልኩት በአጭር ጊዜ ውስጥ አንድ ቤት እንዳገኘልኝ ነገረኝና ሄጄ አየሁት:: ጥሩ ቤት ስለነበር እዛ ገባሁ:: ውሎ ሲያድር ግን ልጁ እዛ ግቢ ውስጥ ደጋግሞ መታየቱ ግራ ገባኝ:: ለካንስ ከቤተሰቦቹ ውርስ ያገኘው ቤት ውስጥ ኖሯል ያከራየኝ:: ለምን በግልጽ ሊነግረኝ እንዳልቻለ አልገባኝም:: ለቅቄ እንዳልወጣ ለራሴም ሆነ ለሱ የማቀርበው ቅንጣት ታክል አሳማኝ ምክንያት የለኝም:: እንዳልቆይ የሱን ቤት እንዳከራየኝ ሊነግረኝ ያልቻለበት ምክንያት ጥርጣሬ ውስጥ ጥሎኛል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ "ጥሩ ሚስት አመጣህ::" እያሉ ሲሉት እሰማ ጀመር::



Scanned by CamScanner

ግቢው ሰፊ ስለሆነ በርካታ ተከራዮች ያሉበት ግቢ ነው፡፡ እዚያ ውስጥ ደግሞ ወሬ ለማግኘት ከባድ አይደለም፡፡

ቀስ በቀስ ከሱ ጋር ያለን ቅርበት እያደገና እየተመነደገ ሄደ፡፡ አንዳችም ክፉ አሳቢነት ስላላየሁበት ጥርጣሬዬ ቀስ እያለ በራሱ መንገድ ተሸረሸረ፡፡ በደንብ መግባባት ጀመርን፡፡ በየመንገዱ ላይ አላሳልፍ ለሚሉኝ ሁሉ መከታ ሆነና ቁጭ አለ፡፡ እኔም ተንፈስ አልኩ፡፡ በጣም ጫን ብለው ለመጡብኝ ሁሉ "ባለቤቴ ነው፡፡" እያልኩ ኩምሽሽ ሳደርጋቸው ቆየሁ፡፡ በመሠረቱ እሱም እንደ ባለቤት መተወን ጀምሮ ነበር፡፡ ሥራዬ የራሱ ችግር ቢኖረውም ድንገት በተፈጠረብኝ ህመም ምክንያት ላቋርጠው ከመቻሌ ውጪ ጥሩ ነበር፡፡ በየደቂቃው የማያቋርጥ ነስር ተገተገኝ፤ የወር አባባዬ ሦስትና አራት ወር ያህል ያለማቋረጥ እየፈሰሰ አስቸገረኝ፡፡ ጣጣዬ በራሱ መንገድ በህይወቴ ላይ መሰናክል ሲሆን እኔም ራሴ *የሰለተ ዕጅ ስሆን ስንዴ?* ስል ለማሰብ ተገደድኩ፡፡ ህክምና ማዕከል ሄጄ ስመረመር ከጭንቀት የተነሳ ችግሮቹ እየተፈጠሩብኝ እንደሆነ ተነገረኝ፡፡ እንደ እውነቱ ቤተሰቦቼን ከማፈላለግ ስሜት በዘለለ ሌት ተቀን የምጨነቅበት ጉዳይ ባለመኖሩ የህመሜ ምክንያት ምናልባትም እኔም ከማውቀው በላይ ጥልቅ ስሜት ይኖረው ይሆናል ስል አሰብኩ፡፡

ህመሙ ከቁጥጥሬ ውጪ ሲሆን ህክምና ለመውሰድ ስል አቋረጥኩት፡፡ ህመሜ ጭንቀት መሆኑ ስለተነገረኝ መፍትሄው መጨነቁን ማቆም እንደሆነ ስለገባኝ ትንሽ ዕረፍት ወስጄ ያለማቋረጥ እየወረደ የሚያስቸግረኝን የወር አበባ ለማስቆም ህክምና ለመውሰድ ወሰንኩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ቤት ውስጥ መዋል እንደጀመርኩ ነው አከራዬ የፍቅር ጓደኛው እንድሆን ጥያቄ ያቀረበልኝ፡፡

# -24-

የሰጠኝ ውዳሴ ማርያም ነበር::

ውዳሴ ማርያም የደረሰው ማንም ሰው መንፈሳዊነትን እንጂ አለማዊ ፍቅርን የሚጠብቅበት ምንም ምክንያት አይኖረውም:: እናም እኔም አልጠበኩም ነበር:: ድንገት ግን ውዳሴ ማርያሙን ሰጥቶኝ ዞር ሲል ስነካካው የሚቆረቁር ነገር አለው:: ከፈትኩት::

ውስጡ ወረቀት አለ- በዕርሳስ የተፃፈበት መልዕክት የያዘ:: መልዕክቱ ካየኝ ጊዜ ጀምሮ ለእኔ ያለው አመለካከት እንደተለወጠ የሚገልፅ ነው:: ውስጡ ሌላም ነገር ነበር- ማስቲካ:: የማስቲካውን ሽፋን አነሳሁት:: የተለያዩ ምስሎች የሚይዘውና ልባሱን እጅ ላይ ሲያደርጉት ቅርፅ የሚያወጣው ነው:: ሽፋኑን ልጬ እጄ ላይ ስለጥፈው የልብ ቅርፅና I love you የሚል ሲወጣ ለምን እንደሆነ እንጃ ደነገጥኩ::

በአጭሩ የፍቅር ጥያቄ ሆነ::

መልሴ ግን ምን መሆን እንዳለበት ሊገባኝ አልቻለም ነበር:: በጣም ተግባብተናል:: መግባባታችን ደግሞ እንድንናበብ አድርጎናል:: ለጊዜው እንቢም ሆነ እሺ ብዬ መመለስ ቢከብደኝ ዝም አልኩ:: ዝምታዬ



Scanned by CamScanner

ከተቃውሞ ይልቅ ቀስ እያለ ወደተግባር ውስጥ ከተተን።

እያደር እራሴን በቤቢ እንክብካቤ ውስጥ ወድቆ አገኘው ጀመር። ስደክም ብርታቴ ሆነ። ጨርሶ ደከመኝ የሚለውን ቃል ከአንደበቴ እንዳወጣ አይፈቅድልኝም። እንክብካቤው ገዛኝ። የፈሰሰ ውሀ ሳላቀና እሱ ሁሉን አድርጎ ቢያኖረኝ፣ ፍቅሬ በባርነት ግዞት ከትቶት ዘላለሙን ሲያገለግለኝ ቢኖር መርጦ ደፋ ቀና እያለ እጁ ውስጥ ከተተኝ። ልብስ ሳጥብ ከደረሰ እኔን አሳርፎ ይሰየምበታል። ቁጭ ብዬ ፈዝዤ ሳየው አረፋ የተመታውን ውሀ እየረጨ ግቢ ለግቢ ሲያሮጠኝ ይውላል። ወጥ ስሰራ ከደረሰ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ይተካልኛል። እናም ወጡ ተሰርቶ ሳያልቅ በቅምሻ እዛው ላይ እንጨርሰዋለን። እኔ ምግብ ላቅርብ ያልኩ እንደሆነ እሱ ሳር ገዝቶ፣ ጎዝጉዞ ቡና በማፍላት ብዙ ወንዶች ሲያደርጉት የሚከብዳቸውን በማድረግ አጋርነቱን አሳየኝ። የዝዋይን ሀይቅ በጀልባ ተንሳፈፍንበት... በነፋሻው አየር የሆድ፣ የሆዳችንን አወራንበት ፍቅር አስፈጭተን፣ አቡክተንና ጋግረን ገመጥንበት... እንክብካቤው የፍቅሩ እስረኛ አደረገኝ።

እኔም እያደር እሱን በእንክብካቤዬ ውስጥ ከተትኩት። ስራ ስለሌለው ከጓደኞቹ አንሶ እንዲታይብኝ አልፈልግም ነበር። እጄ ላይ ሳንቲም ባይኖር እንኳ ልብሴን እየሸጥኩ ጭምር እንዲለብስ... እንዲያጌጥልኝ ማድረግ ተግባሬ ሆነ። ፍቅራችን ደምቆ እንደፓውዛ ሲያበራ ውስጤ ከቤቢ የተሻለ ዓለም እንደማይኖር አምኖ ተቀበለና ልቤ በፍቅር ከዳኝ። ብከዳው እግዜር ይክዳኝ ብዬ ማህላዬን ጓደኞቼ ፊት ዘረገፍኩት።

እርስ በርስ መናበብ መቻላችን የቃላት መንደርደሪያ ኮተቱን ወዲያ አራግፌን ጥለን በተግባር እንድንገላለፀው ረዳን:: ይሄኔ ነው ቤቢ አልጋ መጋራት ፍቅራችንን ከማፅናቱም በላይ ለዘላለሙ የሚያቆራኘው መሆኑን በመግለፅ የመተኛታችን ጉዳይ ፈጣን ውሳኔ እንዲያገኝ ሲል ሀሳቡን የነገረኝ:: ፈፅሞ ግን ልቀበለው ፈቃደኛ አልሆንኩም:: "ድንግል ነኝ::" አልኩት:: ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈፀም እንደማልችል አስረግጬ በመንገር:: "በምን ሂሳብ ነው ድንግል ልትሆኚ የምትችይው?" የሚል ጥያቄ ሊነሳብኝ እንደሚችል የማውቀው ቢሆንም እንኳን ሳልወድና ሳልፈቅድ ድንግልናዬ ቢወሰድም አዕምሮዬና መንፈሴ ግን ድንግል እንደሆንኩ ነው የሚያምነው:: እናም ድንግል እንደሆንኩ ስናገር ምላሴ ላይ ድንቅፍ የሚል ቃል ሳይኖር፣ ቅንጣት ፍርሀት ሽው ሳይልብኝ በልበ ሙሉነት ነበር::

ዘዋይ ገዳም ካሉት አባሚካኤል ጋ ደጋግመን እንገናኝ ስለነበር የተከራየሁትን ቤት አሳይቻቸው እንደዘመድ እየመጡ የሚጠይቁኝ እሳቸው ብቻ ነበሩ:: የቤቢን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ስላለብኝ አባ እንዲጠመቅ እንዲያደርጉትና የክርስትና ስም እንዲወጣለት ማድረግ ነበረብኝ:: ምክንያቱም ለዕምነት ግድ የነበረው ሰው አልነበረምና:: እኔ ደግሞ ዘላቂነቱ ባልታየኝ ነገር ውስጥ ገብቼ በጣም በትንሹ መስመር እየያዘ ያለ ህይወቴን ማመሰቃቀል አልፈለግኩም:: እናም እንዲጠመቅ አደረግኩ:: አብሬው መተኛት ካለብኝ ባሌ መሆኑን አውቄ መሆን አለበት:: ነገ ስለመፋታት በማላስብበት ሁኔታ ትዳር ለመመስረት የተክሊል ጋብቻ ማድረግ ብቸኛው አማራጭ መሆኑን ነው የተረዳሁት::



Scanned by CamScanner

ለዚህ አቋሜ ደግሞ አባ ተጨማሪ ብርታት ሆነውኛል። ቤቢን በጥቂቱ ያውቁት ስለነበር ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብኝ ሹክ ብለውኛል። በህይወቴ ሙሉ ሲገርመኝ የሚኖረው ምርቃት ግን የቤቢ አያት ሲሞቱ ሲሉ የመረቁኝ ነው።

አባታችን ሆይን እንኳን አጥርቶ የማያውቀውን ቤቢ ክርስትና ካስነሳሁት በኋላ ቤተክርስትያን እንዲመላለስ በመጎትጎቴና አንዳንዴም ይገፎው በመሄዶ የቤተክርስትያን አዘውታሪ ሆኖ ትንሽ ጠንከር ያለ ህመም ውስጥ የዋሉ ጊዜ በነፍስ ይድረስልኝ ብለው ሲያስጠሩት ቤተክርስትያን ሲሳለም መሄዱ ተነገራቸው። በሰሙትም ተገርመው ማን ይህን ልብ መግዛት እንዳስተማረው ሲጠይቁ እኔ መሆኔ ተገለፀላቸው። ያኒም "መሽኚያሽ ይባረክ!" ሲሉ ለወራት መገረምና መመራመር ውስጥ የከተተኝን ምርቃት አስታቀፉኝ።

የቢራ ማከፋፈያ ስራዬን ከለቀቅኩ በኋላ የጤናዬ ሁኔታ መስተካከል ሲጀምር በዛው በተከራየሁበት ቤት መስኮት በኩል ሱቅ ከፍቼ ችርቻሮ ንግድ ጀመርኩ። አለባቸው ተካ ለበዐል እያለ ይልክልኝ የነበረውና እኔም ባጠራቀምኩት ትንሽ ገንዘብ አማካይነት ሱቁን አቋቁሚ ማስቲውካም፣ ሲጋራውም፣ ስኳሩንም እያልኩ ደህና መንቀሳቀስ ያዝኩ።

በዛ ላይ ኒያላ ኢንሹራንስ ይሰራ ከነበረው አቶ ሰለሞን ጋር ተዋውቀን ስለነበር አንድ ጊዜ ሱቅ መክፈቴን ሲያውቅ አዲስ አበባ ድረስ ጠርቶኝ ለሱቄ የሚሆኑ ዕቃዎችን ገዝቼ እንድሄድና ስመለስ ከነትርፉ ይገፎ እንድመጣ ቃል በማስገባት ገንዘብ ሰጠኝ። እንደተባልኩትም ከነትርፉ

ይዤ ስመለስ ግን በደስታ እቅፍ አድርጎኝ በሙሉ ገንዘቡን እንድጠቀምበት በማድረጉ ወፌ ቆመች ለመባል በቃሁ::

ኑሮዬን ለማሻሻል እያደረግኩ ያለሁትን ደፋ ቀና ለመገምገም ግቢ ቁጭ ብዬ ፀሀይ እየሞቅኩ እያለ ክፍት በነበረው በር ወጪና ወራጁ ይታየኝ ነበር:: በአጋጣሚም ካቀረቀርኩበት ቀና ስል ሚካኤል በበሩ ሲያልፍ አይቼው አይኔን ተጠራጠርኩት:: *የወደፊ ልጅ ሚካኤል ምን ያደርግ እዚህ መጣ?* ስል አስብኩና ሮጬ ጠራሁት::

በግርምት ሲያየኝ ቆየና "የዙሪያሽወርቅ ልጅ ነሽ?" አለኝ::

"አዎ::" አልኩት:: ጥምጥም ብሎብኝ እየየውን ለቀቀው::

"ምን ልታደርግ መጣህ?" ስል እንዲገባ ጋበዝኩት::

"እዚህ ዝዋይ ያለው መከላከያ ጋራዥ ተመድቤ መምጣቴ ነው" ሲል አጫወተኝ:: "ምን ሆነሽ ነው ባለፈው ያገኘሁሽ ጊዜ ቤተሰብ ሙሉ ሲጠብቅሽ ሳትመጪ የቀረሽው?" ሲል አጠናኝ:: ምናልባት ዙሪያሽወርቅ ጋ መሄድ አለመሄዴን ለማወቅ ይመስላል አትኩሮ ማየቱ::

"ምን መቼ ይመቻል ብለህ ነው?" ስል ላድበሰብስበት ሞከርኩ:: መሄድ፣ ዙሪያሽወርቅን ሰላም ማለት እንዳለብኝ ቤተሰብ በሙሉ እኔን ፍለጋ ዝዋይ ድረስ መጥተው እንዳጡኝ ነገረኝ::

"መንገድ ላይ ነው የምገኘው እንጂ እንዴት አድራሻዬን ሳያውቁ መጡ?" ብዬ ስጠይቀው የሚመልስልኝ ነገር አልነበረውም:: ጭቅጭቁ ሲሰለቸኝ

ግን "ሄጄ ዙሪያሽወርቅን እጠይቃታለሁ::" ብዬ ቃል ገባሁለት:: ለመጀመሪያ ጊዜ በነቤቢ ቤተሰብ ውስጥ ወንድም ያለኝ ሰው መሆኔን ለማሳየት ሞከርኩ:: ያም ሆኖ ግን ዙሪያሽወርቅ ውጪ ብላ ሜዳ ላይ ከጣለችኝ በኋላ እንዲህ አጥብቃ ልትፈልገኝ የቻለችበት ምክንያት ምን እንደሆ ለማወቅ ጓጓሁ::

* * *

አሁንማ ወደ ትዳሩ ጎራ ልገባ ነው... አሁንማ ሌላውም የሚኖረውን የአነስተኛ ህብረተሰብ ክፍል ኑሮ እየተንጧቸሁበት ነው... አሁንማ ህይወቴ እየተለወጠ ነው:: ስለዚህ ዙሪያሽወርቅ ለምን እንደምትፈልገኝ ማወቅና ያለሁበትን ትንሽ ቦታ ማሳየት እንዳለብኝ በማሰብ ጉዞዬን ወደናዝሬት አደረግኩ::

ናዝሬት ደርሼ ከመኪና ከወረድኩ በኋላ ጋሪ ስይዝ ያየኋቸውና ያዩኝ ቤተዘመዶች ነበሩ:: ቀጥታ ወደ ዙሪያሽወርቅ ቤት አምርቼ ወደ ግቢው ስገባ ጨርሶ አይቻት የማላውቅ አንዲት ልጅ አገኘሁና በጥርጣሬ "የዙሪያሽወርቅ ቤት አይደል?" ስል ጠየቅኳት- ግራ ተጋብቼ:: "ነው" ስትል ፈገግ ብላ ተቀበለችኝ:: ፈገግታዋ ወይ እንደምታውቀኝ ወይም ስለ እኔ እንደሰማች የሚገልፅ ፈገግታ ነው:: ቤቱ ሬሳ የወጣበት ይመስል ጭር ብሏል:: "ማንም የለም እንዴ?" ስላት ቡቹ እንዳለ ነገረችኝ- የዙሪያሽወርቅ ልጅ:: ጥሪው ብያት ቤቱን በግርምት ማየት ጀመርኩ:: ቲቪው የለ... ሶፋው...

እይታዬን ሳልጨርስ ቡቹ መጣና ተንደርድሮ እየተጠመጠብኝ "ወይኔ

እማማ... ወይኔ ዙሪያሽወርቅ... እንደናፈቀችሽ" ብሎ ማልቀስ ሲጀምር ገብታችሁ እንድታጅቡ ተብለው በተጠንቀቅ የተዘጋጁ ይመስል መላው ጎረቤትና ዘመድ አዝማድ ነጠላቸውን አዘቅዝቀው በመምጣት ለቅሶውን አጅበው ያስነኩት ጀመር- የዙሪያሽወርቅን ሞት እርም እንዳወጣ።

ዝም!

ለቅሶ የለ... ሀዘን የለ... የተለየ ስሜት የለ... ብቻ እነሱ ደረት ሲደቁና በርቺ ስንዷ ሕርምሽን ሰውጪ የሚሉ ሲመስሉ እኔ ግን በግዴለሽነት ለቅሷቸውን እስኪጨርሱ ጠበቅኳቸው።

"ይቺ ልጅ ቂም ይዛለች!" ተባለ። እንደተባለው ግን ቂም አልያዝኩም። ቂም ያለበቀለ የከሸፈ ቀፊታ ብቻ ነው ብዬ የማምን ነኝ። እንባ የሚባል ጠብ እንደማይለኝ ሲገባቸው ተስፋ ቆርጠው በተውት በጥቂት ቀናት ውስጥ ዙሪያሽወርቅ ከቤቷ እንዳባረረችኝ ሰምቶ ከሷ ጋር የተጣለው ወንድሜ አበራ ቤት ውስጥ አለመኖሩን ስረዳ የት ሄደ ብዬ ብጠይቅ እሱም መሞቱን በግዴለሽነት አረዱኝ። ጨርሶ ባልጠበቁትና ባልገመቱት ሁኔታ ፍቅፍቅ ብዬ ልሞት ደረስኩ። ማን አቁሚ ይበለኝ? ለማስ ልረታ? አስነካሁት። ድክምክምና ዛል ብዬ እስክወድቅ አለቀስኩ።

# -25-

ከቤቢ ጋር ጥልቅ ፍቅር ውስጥ ስለነበርን የሰርጌን ቀን ለእኔ የህይወቴ ድንቅ ምዕራፍ የሚከፈትበት ጊዜ ያህል ነው የናፈቅኩት፡፡ አንዳንድ ጊዜ ተዐምራትን ለመፍጠር የሚቋምጥ ወኔ አለን... አንዳንድ ጊዜ ሊገጥመን የሚችለውን ደስታ በማሰብ ሀሴት ውስጥ ሆነን የምንገምተው የነገ ብሩህ ተስፋ አለን... አንዳንዱን ጊዜ ዛሬ ልናገኝ የተመኘነው ደስታ ዘላለማዊ እንዲሆን ፈልገን ዕድሜ ዘመናችን በለውጥ ውስጥ የሚጥለቀለቅ ያህል የደስታችን ሁሉ መጀመሪያ እናደርገዋለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንዳንዱን ቀን አንዳንድ አምልኮ እናደርግበታለን- የሰርጌ ቀን የደስታዎች ሁሉ መጀመሪያ እንደሚሆን ዕምነቱ አለኝና፡፡

*ለካ እግዚአብሄር ዕንባን የሚያብስበት ድንቅ ችሎታና ሰፊ መዳፍ ለሰውና?* ስል አሰብኩ- የሰርጌ ዕለት፡፡ ዛሬ ቤተሰቤን ሳላውቅ ቤተሰቦቻቸውን የሚያውቁ ልጆች ባለቤት ወደምሆንበት ጎዳና ልገባ ነው... ከምወደው፣ ከምጨነቅለት ሰው ጋር ትዳር በሚሉት ወርቃማ ሰንሰለት ልታሰር ነው... አቤት እንዴት ደስ ይላል? ከጎዳና ትቢያ ላይ ተነስቼ ዛሬ እንደካባ የምጎናፀፈውን አዲስ ህይወት በደስታ ላጣጥም ነው...

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ነው ዐምባ ውስጥ ያለው ሚካኤል ቤተክርስትያን



Scanned by CamScanner

የገባነው:: ሌሊቱ ሲነጋ ቀኑ ህዳር 12 ዕለቱም ዕረቡ ስለሚሆን የተክሊል ጋብቻው እስከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ይቆይ ስለነበር ቤተክርስትያኑ ውስጥ ሆነን እየቆየ የሚተናነቀኝን ስሜት እንቅልፍ ከማጣት እና መጠን ያለፈ ጉጉት ጋር አያይዤው ቆጭ አልኩ::

ኅዳር ሚካኤል ለዐምባ ሚካኤል ልዩ ቀን ነው:: በተለይ የእኔ የሰርግ ቀንም ስለሆነ እንደሁ እንጃ በጣም የሚያምር ሌሊት ሆነ:: ከቤተክርስትያኑ በስተሰሜን ካለው የእንግዶች ማረፊያ አቅጣጫ የተቀመጥነውን ሙሽሮች ያጀቡ ወጣቶች የያዙት ጧፍ የለሊቱን ግርማ ሰብሮታል:: የሚዜና አጃቢዎቹ ዝማሬ ቤተክርስትያኑ ውስጥ ከሚዘመረው ለየት ብሎ ጎልቶ ተሰማኝ:: ሁለቱንም ጎራዎች ሰማኋቸው:: በቤተክርስትያኑ ውስጥ "ለረድአትየ ነአ ሰፌሀከ ክንፍ ረደኤ ምንዱባን ሚካኤል" ሲባል በሌላ በኩል ደግሞ "ካህናት ተንሰሁ ለተናብቦ እዘይብለ ንሴብሆ" ተባለ::

ወዲያውም በጧፉ ብርሀን እየተመራን ሰብአ-ሰገልን መስለን አውደ ምህረቱ ላይ ደረስን:: አውደ ምህረቱን አልፈን ቅኔ ማህሌቱ ስንደርስ በቤተርክርስትያኑ ውስጥ የነበሩት ምዕመን የሚዜዎቹን ዝማሬ ሲቀበሏቸው ቤተክርስትያኗ በእልልታና በጭብጨባ ደመቀች:: ቅኔ ማህሌቱን አልፈን ቅዱሳን ደርሰን የተክሊል ፀሎት እስኪጀመር ካህናቱ፣ ሊቃውንቱ ቅኔ እያመሳጠሩ ከዜማ ጋር እያዋሀዱ የአፎሚያን፣ የሳራንና የሌሎች ቅዱሳንን ታሪክ ተረኩት::

እየቆየ ግን ጨንራዬ ይነድ ጀመር:: ምንም እንኳን ሰዓቱ እየገሰገሰ ቢሄድም የርሀብ ስሜትና ማጥወልወሉ በጣም ተፈታተነኝ:: አባ

ሚካኤልን ቢያንስ ፀበል እንኳ ብጠጣ ብዬ ባማክራቸው አይሆንም አሉኝ:: ህመሙ ግን ከዐቅሜ በላይ በመሆኑ እዛው መቅደሱ ውስጥ አስመለስኩ:: አየር እንዳገኝ እያርገበገቡልኝ በተቻለ መጠን ስነ ስርዓቱ እስኪጠናቀቅ ችግሩን እንድቋቋመው ያበረቱኝ ያዙ::

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ከቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ሲፀለይበት የነበረው የስርአተ ጋብቻ ንዋያተ ቅዱስ ካባው፣ አክሊሉ ወጥቶ ፊት ለፊታችን ካለው ጠረጴዛ ላይ ተቀመጠ:: ከቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የሀመረብርሀን ገዳም አበምኔት ብቅ አሉ:: የእለቱን የፀሎት ስርዓት በስመአብ ብለው ጀመሩት:: መፅሀፈ ተክሊል በካህናት እየተነበበ ስርዓቱ ተጀመረ:: ከፊታችን የተቀመጡት ንዋያተ ቅዱሳት ተባረኩ:: እጃችንን እንድንዘረጋ ተደርጎ ቅብዐ ሜሮን በእጃችን ፈሰሰ:: እኔ ለቤቢ፣ ቤቢ ለእኔ ቀለበት ተደራረግን:: በካህናት ስርዓት ፈፃሚነት ቅድሚያ ካባውን በመቀጠል አክሊሉን በራሳችን ላይ ጫኑልን:: ያኔም እልልታና ጭብጨባው ቀለጠ::

አጣች ነጣች፣ አመማት ከፋት ብዬ ላልለያት... ላልለየው ተባብለን ቃለመሀላችንን በእግዚአብሔር መንበር ፊት አኖርን:: አሁን ሁሉ ነገር ፍፃሜ የሚያገኝበት ላይ ደረሰና ጋብቻችንን ካህናቱ በፀሎት አተሙት:: በእጣኑ ጢስ ወደ መንበረ ፀባኦት ወደስላሴ ፊት አሳረጉት::

የቤተክርስትያኑ ስነ-ስርዐት ከተጠናቀቀ በኋላ በእኔ በኩል ሙሉ ወጪዬን ችሎ የደገሰልኝ ቤተክርስትያኑ ስለነበር እዛው ዐምባ ውስጥ ነበር የቆየነው:: ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲዘመር እኔ ግን ህመም ውስጥ ስለነበርኩ ራሴን መቆጣጠር እያቃተኝ አስር ጊዜ ስደፋ ቀይቼ በመከራ እንቅልፍ



Scanned by CamScanner

ሸለብ አደረገኝ:: የዐምባ ልጆች በሁለት ሙሉ ካቻማሌ መኪና ተጭነው በመምጣት ስርጌን ያደመቁት ቢሆንም ደስታውን አብሬያቸው ከመካፈል ይልቅ እኔ ሙሽሪት ባይተዋር ነበር የሆንኩት::

በማግስቱ ሁላችንም በሁለቱ መኪኖች ተጭነን ወደ ዝዋይ ስንመለስ ዝዋይ መዳረሻ ላይ የመልስ ካባችንን ቀይረን ለበስንና ወደ ቤት አመራን:: ቀደም ብዬ በግና ፍየል በማሳረድ አልጫና ቀይ ወጥ ለእንግዶች እንዲዘጋጅ አስደርጌ ስለነበር የዐምባ ልጆች በሙሉ ቤት እንዲገቡ አደረግኩ:: ወደ ቤት ስንገባ ግን የጠበቀን የሚገርም ነገር ነበር:: የቤቢ ቤተሰቦች ግጥም አድርገው ብፌ አዘጋጅተው አገኘናቸው:: ስንገባ ቤቢ ቤተሰቦቹን ሲስም ውስጤ ገነፈለ:: አንድ እንኳን የስጋ ዘመዴ የለም:: እንዴት ብዬ እየመጣ የሚያፍነኝን ሳግ ልቋቋመው? እንዴት ብዬ የሚገነፍል ስሜቴን ልግታው? ቻበርቻቻው፣ ሁካታ ደስታው፣ ዘፈን ጭፈራው እንኳን ሳይገቱኝ እንዲችው የቤተሰብ እጦት ሰቀቀን ይዞ በሃሳብ እያናወዘ ሳግ በተባለ ማጀቢያ መረበሼን አከፋው::

ታገልኩ:: ስሜቴን ልቆጣጠረው... እንዳሰብኩት የደስታዬ ቀን ነው ብዬ ራሴን በማሳመን ብችል ልሆነው፣ ባልችል እንኳን ላስመስለው ስል ታገልኩት:: በሚያሳዝን ሁኔታ ግን በልቤ ያሰብኩትን ሳልሆን ቀረሁ:: ሀዘኔንና ሳጌን የተመለከቱት እነሚኪ ምክንያቱ ስለገባቸው ገብቼ እንድተኛ አደረጉ::

አልጋው ላይ ተደፍቼ እንኳ መሪር ለቅሶና ሳጌን ልቆጣጠረው ብሞክር እንቢ አለኝ:: ያኔ ነው አንድ ምስጢር እንደ መብረቅ ስንጣሪ ብልጭ

ብሎ የተገለጠልኝ:: ትዳሬ ሳንካ እንደሚገጥመው!

* * *

እርስት ያደረግኩት ነገር ሲመጣ ድንጋጤ ብርክ ለቀቀብኝ:: *ለካ ወሲብ መፈፀም ለሰበተና? ሳላውቀው ቀርቼ አይደለም:: ግን ምንድነው እንዲህ ፍፁም ደናግል የሆንኩ ያህል የልብ ልብ የፈጠረብኝ?* ለሀሳቤ መልስ አልነበረኝም:: ከእኔ ዕውቀት በላይ የሆነ አንዳች ምስጢር አለ::

ብር አምባር ሰበረልዎ... ጀግናው ልጅዎ ተብሎ ተዘፈነም፣ አልተዘፈነ ከባሌ ጋ መተኛት ግዴታ እንዳለብኝ ማስታወስ ነበረብኝ:: እኔ መከላከያ አጥሬን በማበጀት እስከዛሬ ቆይቻለሁ:: ዛሬ ግን አጥሩን በገዛ እጄ አፍርሼዋለሁና ወደሚፈልገው ቤተ መቅደስ ሰተት ብሎ ይገባ ዘንድ እክል ልፈጥርበት ስለማልችል ፈቀድኩለት::

በፍፁም!

በምንም ነገር እርግጠኛ ለመሆን ጥቂት ጊዜያት የሚያስፈልገኝ በመሆኑ ግንኙነቱ ያለ ኮንዶም መሆን እንደማይችል ሽንጤን ገትሬ ተከራከርኩ:: ማንም ባል በሰርጉ ማግስትና ድንግልና ሊወስድ በቋመጠበት ሰዓት በኮንዶም ነው ልትገናኘኝ የምትችለው የሚባል ማዕቀብ ሲጣልበት በብዙ መልኩ ቅሬታ ሊፈጠርበት ቢችል የሚደንቅ አይሆንም:: ቤቢም ከነቅሬታው ነበር ኮንዶም ሊጠቀም የፈቀደው::

ሁለታችንም መለመላችንን ቀርተን እንሳሳም ጀመር:: ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ አይነት እንግዳ ስሜት ተፈራረቀብኝ:: ግንኙነት



Scanned by CamScanner

ማድረግ ሲጀምር ግን ነፍሴ ተመንጥቃ የተወሰደች ያህል ከፉኛ ህመም ብልቴ ጋ ተሰማኝ:: ግንባሬን አኮሳትሬ፣ ፊቴን አጨፍግጌና አይኔን ጨፍኜ ግፊቱን ልቋቋመው ሞከርኩ:: ህመሙ ግን ያልተጠበቀ ህመም ቀሰቀሰብኝ:: ትናንትናን... የተረሳውን ቀን አስታወሰኝ::

...በጣም እያመመኝ ፍቅሩ ኃይሉ እላዬ ላይ ሆኖ በሀይለኛ የስሜት ሲቃ ውስጥ ነው:: ሲሻው ራሱ ፍቅሩን... ሲሻው አንዳች አይነት መልክና ቅርፁ የሰው የመሰለ አውሬ በጭካኔ ተሞልቶ እላዬ ላይ የሚወራጭ መሰለኝ:: ህመሙ ልክ ፍቅሩ አስገድዶ የደፈረኝ ጊዜ ያለውን አይነት ሆኖ ቁጭ አለ:: ጬኸት... ልክ ከፍቅሩ ጋር እንደነበረው አይነት አሰቃቂ ጬኸት እያወጣሁ እላዬ ላይ ያለውን አውሬ መሳይ ፍቅሩ የተባለ ሰው አሽቀንጥሬ ለመጣል ሀይሌን ላሰባስብ ስል ሁሉም ነገር ጡዘቱ የሚበርድበት መጨረሻው ደረጃ ላይ ደረሰና ተጠናቀቀ::

ቀስ እያለ ቤቢ ከላዬ ላይ ሲነሳ አየሁት:: የተጠቀመበት ኮንዶም ላይ ደም አለ:: ጎንበስ ብዬ ስመለከት በጭኖቼ መካከል በጣም ትንሽ ደም አየሁ:: አንዲት ሴት ድንግልናዋ በተወሰደ በሶስተኛው ቀን ግንኙነት ካላደረገች ሌላ ጊዜ ሊያማት ይችላል... ሊገጥም ይችላል እየተባለ የሚናፈሰውን ፀረ- ሳይንስ ሀሳብ ለማመን ተገደድኩ:: ታዲያ ምን ተዐምር ደም እንዲፈስኝ ሊያደርግ ቻለ? እምላለሁ አንድም ቀን ቤቢ ድንግል ሆና አላገኘኋትም ሲል ሰምቼ አላውቅም:: እስካሁን በሱ ቤት ድንግልናዬን የወሰደው እሱ ነው::

ያን- ዕለት... በጭኖቼ መሀልና የተጠቀመበት ኮንዶም ላይ ያለውን ደም ያየሁ ጊዜ ግን ቤቢን አምርሬ ጠላሁት- ፍቅሩን መሰሎኝ::



Scanned by CamScanner

## -26-

ማን ነበር እሱ እቴ- ሀደወተ ትምህርት ቤተ ናተ ይል የነበረው? ያውም ከስህተት በማስተማር የተሞላች ድንቅ ትምህርት ቤት ጭምር እንጂ:: ትዳር የደስታ ሁሉ ጥግ የተከማቸበት፣ ሰላምና ፍቅር የሚዘፈንበት፣ ሀሴት የሚደለቅበት ይመስለኝ ስለነበር ነው ዘላለም ልለየው በማልችልበት ጠንካራ የወርቅ ካቴና እንድንጠፈር የፈቀድኩት:: ቀስ በቀስ ግን ትዳር ማለት አንድ ሚሊየን ራስ ምታቶችን መቋቋም መቻል መሆኑን መማር ስችል ለአባባሉ ተማረኩ:: ለዚህ ኖሯል ለካ ብዙ ሰዎች ትዳርን ጥንብ እርኩሱን ሲያወጡት የኖሩት?

ያለንበት ግቢ ስምንት ቤቶች ያሉትና ቤቢ ከቤተሰቦቹ የወረሰው ነው:: ሁለት እህቶቹ የሚኖሩት ትልቁ ቤት ሲሆን እኔና ቤቢ እኔ ተከራይቼው የገባሁቢት ትንሿ ክፍል ውስጥ ነን:: በርካታ ተከራዮች ግቢው ውስጥ አሉ:: በአጭሩ ኑሯችን የተመሰረተው ከኪራይ በሚገኝ ገቢ ነው:: ይሄ ደግሞ ላይ ላዩን ሲታይ ለጊዜው ጥሩ ቢመስልም እያደር ግን መዘዝ እየያዘ መጣ::

አንደኛ ነገር ሰማቾች ምቾች ናቸው እንደሚባለው እህቶቹ፣ በተለይ ደግሞ ታናሽ እህቱ በትክክል ምች ትሆንብኝ ጀመር:: የእኔ በቤቢ



Scanned by CamScanner

ህይወት ውስጥ መግባት በኑሯቸው ላይ ታላቅ ጫና እንደፈጠረ በሾርኒ እየነገሩ ሴትነትን ሊያስተምሩኝ ሞከሩ። ነገር እንዴት እንደሚያቅልና ራሱን ያራባ አሽሙር ከዚያም ሲያልፍ ሾርኒና ሽሙጥ እንደሚሆን ማየት ቻልኩ። ያማራቸውን በልተው፣ ያሰኛቸውን ጠጥተው፣ የተመኙትን ለብሰው በ'ደስታ' እንዳልኖሩ እኔ መጥቼ ህይወታቸውን ምስቅልቅሉን ያወጣሁት ይመስል እንደወገብ ቅማል ጠምደው ያዙኝ።

በተቻለኝ መጠን ለቤቢም ሆነ ለእነሱ ጥሩ ለመሆን እንደምሞክር ብቻ ነው የማውቀው። ከየት ተነስቼ መጥቼያለሁና የተንኮልና ክፋት ማግ ሳዳውር እኖራለሁ? የነበርኩበት ህይወት አሁን ለምኖረው ትምህርት ካልሆነ ሰው የመሆን ትርጉሙ እንዴት ሊፈታልኝ ይችላል? ብቻ ግን ቀስ እያለ... በጣም ቀስ እያለ "ይህች ልጅ እንዴት ፀባያቸውን ችላ ኖረች?" እየተባለ ሲወራ ሰማሁ። ለካ ጠልቄና ጠንቅቄ የማላውቀው ነገር ቢኖር ቤተሰባቸው ሰላም የሌለው ቤተሰብ መሆኑን ነው። እያደር ግን አወቅኩት። አባትየው ታንቀው እንደሞቱና እርስ በርስ አይጥና ድመት ይመስል መናቆር የሚወዱ መሆናቸውን ተገነዘብኩት። ራሱ ቤቢም እውነታውን ሲያጠራልኝ "እህቶቼ መጥፎ ናቸው... እቃ ከዚህ ቤት እንዳይወጣ..." ይለኝ ጀመር።

በዚህ መሀል እኔ አጣብቂኝ ውስጥ ገባሁ።

ግቢው ውስጥ ያለ ሰው በሙሉ ጠዋት ውሀ ከቀዳ በኋላ ከቆጣሪው በመቆለፍ ቁልፉን መያዝ ያለብኝ እኔ ነበርኩ- ቤቢ ያ እንዲሆን ይፈልጋልና። እህቶቹ ደግሞ "እንዴት በአባታችን ንብረት አንቺ

ታዥያለሽ?" እያሉ የቤት እቃ በመከልከላቸው ላይ ይደነፉብኛል፡፡ ያም ቢሆን ግን "አንድ ዕቃ እንዳትሰጫቸው" ብሎ አስሮኛል፡፡ ለእነሱ እኔ በህይወታቸው ውስጥ በድንገት የተከሰትኩ የእርጎ ዝንብ ሆንኩባቸው፡፡ እንዲያ እንደሚያስቡ ቢገባኝም እኔ ግን አልነበርኩም፡፡ አስር ጊዜ እቃ እንዋስ እያሉ የሚመላለሱበት የቤቢ ኑሮ አንድ ሽቦ አልጋና ተራ ቅራቅንቦዎች ብቻ የነበሩበት ነው፡፡ ትዳር ነውና ቤታችን ቤት እንዲመስል የእኔም አስተዋፅኦ ነበረበት፡፡ የእህቶቹ ስሜት ግን እኔን ከዚያ ቤት እንደዕብድ አብርሮ ለማስወጣት መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡

ሁለት ነገሮች ትዳራችንን እንደጀርመን ግንብ ሲያፈራርሱት የራሳቸውን አደገኛ መደሻ ተጠቅመው ይወቅሩት ያዙ፡፡ እህቶቹ ባንድ በኩል፣ ቤቢ ባንድ በኩል... ትዳር የገሀነም እሳት የሚፈልቅበት ነውና መጥፋት አለበት የሚሉ ይመስል 'ድው፣ ድው' እያደረጉ መሠረቱን ያናጉት ገቡ፡፡

የእህቶቹ የነጋ ጠባ ንትርክ ሳያንሰኝ የቤቢ እኔን አለመረዳት ደግሞ የበለጠ እንድሸሸው አደረገኝ፡፡ መሸሼ በጥላቻ የታሸ ልብ ይዤ አልነበረም፡፡ እኔ ከገመትኩ ያፈነገጠና ጥላሸት የተቀባ ህይወቴን ከማፅዳት ይልቅ እያበለዘ የሚሄድ ሆነ እንጂ፡፡

እናም እጅ እጅ አለኝ፡፡

ወጣትነት... ትኩስነት... ያለመድከም... ዘመን ያመጣው ለውጥ ተጋግዘው ቤቢን ሃያ አራት ሰዓት አልጋ ላይ በድካም ሲዝሉ መዋል የፍቅር መገለጫ መስለውት ቁጭ አሉ፡፡ ሰለቸኝ፡፡ ነጋ ጠባ ያለ እረፍት በወሲብ

ማዕበል ሲንገላቱ መቆየቱ ታከተኝ:: ስሜት የአንድ ወገን እሳት ሆኖ ሌላውን ከማቀጣጠል ይልቅ እየለበለበ መብሰል የቸገረው ገባ ወጣ ጥብስ ካደረገው ምን ጣዕም ይኖረዋል? እኔ በሄደበት ዝም ብሎ እንጣጥ በማለት ሲሰፍር የማየው ከብትን ነው:: ሰው ግን ወሲብ ላይ የሌላውን ስሜት ጠንቅቆ ማንበብ ሳይችል እንደው የከብት የመሰለ ድርጊት የሚፈፅም ከሆነ ፍቅር በየት በኩል ይነግሳል?

አንደኛ ነገር ለወሲብ ያለኝ አመለካከት የተዛባ ነውና በዚያ 'ነፍስን በገነት ግዞት ውስጥ መክተት ነው' ተብሎ በሚባልለት መንኮራኩር ውስጥ ለመምጠቅ ጊዜ ያስፈልገኛል... የተረጋጋና በፍቅር ውስጥ ያለ ወሲብ ለመልመድ ጥላሸት የለበሰ አመለካከቴን መለወጥ ነበረብኝ:: ለዚህ ግን አልታደልኩም:: ወይ ከነገሩ ጋር እስክላመድ አልያም ያለኝን አመለካከት እስክቀይር ድረስ ብዬ ሽሽት ማለት ጀመርኩ:: ሽሽቴ ግን ፍፁም ፍላጎቱን በመቃወም ሳይሆን በመጠኑ ለመቀነስ ስል የወሰድኩት እርምጃ ነበር:: ይሁንና ጥረቴ ግቡን አልመታም:: ለሽሽቴ ስም ያወጣለትና አውቀሽ ነው በሚል ይቃወመኝ ጀመር::

አሞኝ ትኩሳት እንደገሞራ እየተንተከተከብኝ፣ ላብ እንደ ነሐሴ ውሽንፍር ችፍ እያለብኝ እየተመለከተ ተጠግቶ "አይዞሽ" በማለት አንገቴ ስር በመዳሰስ ወዲያው ወሲብ ለማድረግ ይጣደፋል:: "ኧረ አሞኛል እባክህ!" ብዬ ብለምነውም አይሰማኝም:: አንድ ጊዜ ከምጠላው ወሲብ ጋ በተገናኘ ይመስለኛል ማህፀኔ መቁሰል በመጀመሩ በጣም ታመምኩ:: እንዲያ ሆኜ ባለበት ሁኔታ "ወሲብ ካልፈፀምን" ብሎ ታገለኝ:: *እንዴት ሰው የሚወደት ሚስቱ ለጠገቡ ታማ ተኝታ ወሲብ ካላደረግን ብሎ ያስጨንቃታል? ምንም*

*ፍላጎቱና ስሜቱ ሳይኖረኝስ እንዴት ነው ግንኙነት ሳደርግ የምችለው? መተሳሰብና መደማመጥ ከሌለ ፍቅር ምንድነው? ሰው እንዴት ለስሜቱ የሚሞት ስውሬ ይሆናል?*

"ቤቢ… ማህፀኔን አሞኛል'ኮ ነው የምልህ!"

"አውቀሽ ነው… ውሸትሽን"

ፓንት እንኳን ማድረግ እንዳልቻልኩ ጭምር ከፍቼ አሳየሁት:: እንዳዛም ሆኜ ግን ተገናኘኝ:: እሱ የልቡን ሰርቶ ጀርባውን ሰጥቶኝ እንቅልፍ ውስጥ ሲሰምጥ እኔ ግን *ወይኔ እናቴ!* ስል ስቃይ በወለደው እንባና ንፍጥ እየተዝረበረብኩ ነበር::

* * *

ቀጭን፣ የቀይ ዳማ፣ እንደበርካቶች የዝዋይ ታዳጊዎች ጥርሰ ብልዝ፣ ሰፊ ደረት ያለው፣ ጅንስና ሸሚዝ እንዲሁም ቁምጣና ቲሸርት ከከፋይ ጫማ ጋ መልበስ የሚወድ፣ ከርዳዳ ፀጉር ያለውና አዘውትሮ ፓንክ የሚቆረጥ ነው- ቤቢ::

እንደቤቢ ባይሆንም ቀጠንና ዘለግ ያልኩ (1 ሜትር ከሰባ ሶስት ቁመትና 56 ኪሎ ክብደት ያለኝ) ጥቁር ሴት በመሆኔ አንድ ላይ እንድንጣመር ተብሎ በልክ የተሰራን ነው የምንመስለው:: እሱ ፊልም ሲወድ እኔ መፅሀፍ በተለይም ብርቅርቅታን የማንበብ በሽታ የተጠናወተኝ ነኝ:: ደጋግማ የተደፈረችውንና ለእህቶቿ መስዋዕት የሆነችውን የብርቅርቅታዋን ሂላሪ ከነፍሴ ጋር ነው ያዋሀድኳት:: በኪነ-ጥበብ ላይ

ካለን ልዩነት ባሻገር በአብዛኛው ከቤቢ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎት ነው ያለን::

ቤቢን የሚያውቁ ሁሉ በአንድ ቃል እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል የሰው መጨረሻ! እኔም ይህን አጥብቄ አምንበታለሁ:: በጣም ሰላምተኛ ነው:: ሰው አክባሪ፣ ሽቁጥቁጥና ተወዳጅ:: በተለይ ለእኔ ልዩ ሰው የሚያደርገው እንጀራ ጋግሮ፣ ዶሮ ወጥ ሰርቶ ማብላቱ ነው:: ቤቢ ዘፈንና ጭፈራ ነፍሱ የሆነ እንዲሁም ፊልም ወዳድ ነው::

ማንም ስለ ቤቢ ጥሩነት ሊናገር ከሚችለው ያልተናነሰ ኸረ እንዲያውም ከፍ ባለ ሀይል መናገር እችላለሁ:: ልዩነቱ ሁሉም በውጭያዊ ማንነቱ ከሚያውቁት በላቀ እንደሚስትም ውስጡን ጠልቄ የማውቀው መሆኑ ነው:: በጣም ላደንቅለት የሚገባኝ ባህርይው በሰዎች ዘንድ ጥሩ መስሎ የመታየት ችሎታውን ነው:: ሁሉም ጥሩነቱን፣ ሰላምተኛና ሰው አክባሪነቱን ይነግሩኛል:: እኔ ግን ፅናት የቴአትርና ፀረ- ኤድስ ክበብ ውስጥ አባል ሆኜ ሙዚቀኛና ድራማ ሰሪ ስለሆንኩ በሁሉም ዘንድ እንደባለጌ፣ ዋልጌ ነበር የምቆጠረው:: የውዝዋዜ ቡድን መስርቼ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ለህዝብ በማቅረብ ገቢውን ለጎዳና ተዳዳሪዎች የማድረግ ስራዬ ያን ያህል የጥሩነት መገለጫ አልነበረም:: ይልቁኑ ተቅለስልሶ፣ ሰበር ቀንጠስ ብሎ የሚታየው ባለቤቴ ነበር- ጥሩ:: አባሚካኤል በእንግድነት ቤታችን ሲመጡ እግራቸውን አጥቦ በማስተናገድ ሲሄዱ ሙልጭ አድርጎ የሚሳደብ ከሆነ የጥሩነት መለኪያ እውነት እይታ ብቻ መሆን ይችላልን?

የሱ እንግዶች የእኔ፣ የእኔም የሱ እንግዶች ናቸው ብዬ አምናለሁ:: ትዳር የልዩነት ሳይሆን የአንድነትና የውህደት መገለጫ ነውና:: ለዛ ነው ፌሩዝ የተባለችን ሴት ቤት ድረስ ይዟት ሲመጣ አክብሬ ቡና እያፈላሁ፣ ምሳ እየሰራሁ በአግባቡ ስንከባከባት የነበረው:: እርግጥ እንደትዳር አጋር ሀላፊነት አሰብኝና "ይህቺ ልጅ ምንድን ናት?" ብዬ ጠይቄዋለሁ:: "የድሮ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ናት" ሲለኝ ቃሉን ተቀብዬ አመንኩት:: ስለዚህ በልጅነቷ ልቀና የሚያስችለኝ በቂ ምክንያት አልነበረም- ቆንጆ ከመሆኗ በቀር:: በሰው ደ'ሞ ለምን ቆነጀሽ ተብሎ አይቀናም:: እያደር ግን "ምን ያለችዋ ናት ጣውንቷን የምታስተናግድ?" የሚለውን ሀሜት ስሰማ ባሌን እያማገጠችብኝ ሊሆን ይችላል ብዬ በጥርጣሬ ዋለልኩ:: ከሁሉም በፊት ከራሱ ልስማ ብዬ ጠየቅኩት::

"ቤቢ..."

"እ?!"

"አንድ ነገር ልጠይቅህ ነበር"

"ምን ሆንሽ?"

"ሳትዋሽ ንገረኝ... ከፌሩዝ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምንድነው?"

"ምንም"

"እንዴት ምንም?"

"ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?"

"ጣውንቴ እንደሆነች እየተወራ ነው"



Scanned by CamScanner

"ምንም ግንኙነት የለንም" ከቤት ሊወጣ ከተቀመጠበት ተነሳ።

"ትምላለህ?"

"አዎ!"

"እሺ..." ጥሎኝ ወጥቷል።

ከሆሚቱ በቀር ያየሁት ነገር ስላልነበርና ማስረጃም ስላጣሁ ነገሩን በአይነ ቁራኛ ከማየት በዘለለ ፌሩዝ ይባስ ብላ እህቷንም ጭምር እየያዘች ስትመጣ ፊቴ እንዳይጠቁር እየታገልኩ እንከባከባት ነበር። አንድ ቀን የፌሩዝ እህት ብቻዋን መጣች። በጨዋታ ጨዋታ ተነስቶ ፌሩዝ ለአፓረንት ሺፕ ባሌ ብትመደብም አልፈልግም ብላ ዝዋይ የሆነችበትን ምክንያት እንደቀልድ አዋዝቼ ጠየቅኳት።

"ግን ለምንድነው?"

"ለቤቢ ስትል ነዋ... ቤቢዬን'ኮ በጣም ነው የምትወደው..." አለችኝ። ጠልቄ ልገባ ብሞክርም ጥርጣሬ ነገሰባት መሰለኝ ሸፋፈነችብኝ። እኔም ብዙ ላስጨንቃት አልፈለግኩምና ተውኳት። ነገሩ ግን ሆድ ሆዬን በላው። በዚያው ሰሞን ፌሩዝ ምሳ ልትበላ ቤት መጥታ ወደ መፀዳጃ ቤት ስትዞር አንዳች መንፈስ ሹክ አለኝና ምን ለማግኘት እንደፈለግኩ እንኳ ባላሰብኩበት ቅፅበት ደብተሮቿን ገላልጬ መመልከት ጀመርኩ። ደብተሯ ውስጥ ተሸጉጦ ባየሁት ነገር ልቤ ስንጥቅ እስኪል ነበር የደነገጥኩት።



Scanned by CamScanner

# -27-

ዝዋይ ስቴዲየም መስተዳድሩ የሰጠኝ ቢሮ ስለነበር ወደዛ ላመራ ስዘጋጅ ቤት ከተከራዩት አንዷ አስቸኳይ ስልክ እንደምትጠብቅ ነገረችኝ:: እኔ ልወጣ ስለነበር ለቤቢ ታናሽ እህት "ባዩሽን ከተባለ አደራ ጥሪያት" ብዬ ነግሬያት ወጣሁ:: ስመለስ አገር ሰላም ብዬ ቤት ስገባ ባዩሽ መጥታ ጮኸችብኝ:: ለካ የለችም ተብሎ ተዘግቶባት ኖሯል:: "እንዴት አደራ ብዬሽ እንዲህ ጉድ ትሰሪኛለሽ?" ስትለኝ ስንደረደር ወደ እህቴ ሄድኩ:: "ምን ነካሽ?" ስል ጮህኩባት:: "ምነው እኔ ገረድሽ ነኝ እንዴ?" አለችኝ:: ንግግር ያለመቻሏ እንጂ አስባና አልማ የተናገረችው አልነበረም:: እኔ ግን ይህን ለማሰብ ጊዜው አልነበረኝም:: ውስጣቸውን በደንብ አውቀዋለሁ... ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑ ለይቼዋለሁ:: ወንድማቸው ጥሩ እንዳልሆኑ በአንደበቱ ነግሮኛል... እነሱም ለወንድማቸው ፍቅር እንደሌላቸው ተረድቼዋለሁ:: ንዴቴን የተወጣሁ፣ ብሶቴን የዘረገፍኩ መስሎኝ በጣም ተናገርኳት::

"ስልኩ ለዚህ ግልጋሎት ካልዋለ ታዲያ ለምን አስፈለገ?" ስል ጠየቅኳት::

"በወንድሜ ስልክ አንቺ ምን አገባሽ?"

"የወንድምሽ ንብረት ጥቅም ላይ እንዳይውል ከፈለግሽ ለምን አዝለሽው



Scanned by CamScanner

አትዞሪም ታዲያ?"

"ኤዲያ ባክሽ... አናውቅሽምና ነው? ቂጣ'ኮ ነበር የምትበይው:: እሱ ነው ለዚህ ያበቃሽ:: ከመሬት ያነሳሽ እሱ ነው:: ዘረ ቢስ!"

ነገሩን እኔ ሳበርደው እንደምችል ባውቅም ውስጤ የተከማቸ የነገር ስንቅ ነበርና ነደደኝ:: *እንዴት ዘረ-ቢስ ትለኛለች?* ያልወለድኩት አውቄ ያለመሆኑን ልነግራት እንደሚገባኝ አመንኩ::

"አላማ ስላለኝ ነው እንዳንቺ ወልጄ ያለ አባት የማላኖረው... አቅቶኝ መሰለሽ?" አልኳት:: ዮሴፍ የሚባል ያለ ትዳር የወለደችው ልጅ አላት:: ከኔ ጋር በጣም ነው የምንዋደደው:: "እናትህ ማን ናት?" ሲባል "ሰናይት!" ሲል ነው የእኔን ስም የሚጠራው:: ይሄንን በሰማች ቁጥር እናቱ ትቆጣዋለች:: ይህን ያነሳሁት ሆነ ብዬ ልነካት ነበር *መሆን መሰለኝ፣ እንዴ?*

"ማን ስለሱ ጠየቀሽ? አንቺ አለሽ አይደል ከመነሻሽ ጭምር ዘር የሌለሽ!" ስትለኝ የሆንኩት አፌን እንደከፈትኩ በግርምት መቅረት ብቻ ነበር:: ይህንን ታውቃለች ብዬ ፈፅሞ አስቤው አላውቅም:: ብቻ ግን እንደዕብድ ሲያደርገኝ ይታወቀኛል:: ተከራይ ሲሰባሰብ እዬዬ እያልኩ እዛ ቤት እንደማላድር ተናግሬ ፀሀይ ለምትባል ጎረቤታችን ቤቱን አስረክቤ በጓሮ በር በኩል ወጣሁ:: ትንሽ እንደተራመድኩ በትዕዛዝ የተቀመጠ የሚመስል ገመድ መንገድ ላይ አገኘሁና ይዤው ለሰፈራችን ቅርብ ወደ ሆነው ጫካ ገሰገስኩ::



Scanned by CamScanner

ገመዱን ዛፍ ላይ አስሬ አንገቴ ላይ ሳስገባ ሲከተሉኝ የነበሩት ደርሰው ተጯጭኸው ገመዱን ከአንገቴ ውስጥ ፈልቅቀው አወጡት:: ከኛ ግቢ ጎረቤት ያለች ቅድስት የምትባል ልጅ "እንዴት በዚህ እኩለ ሌሊት ትወጫለሽ? ለምን ቤተሰቦቹን ጠርተሽ አታስመክሪያቸውም?" አለችኝ:: የሆነውን ነገር ነገርኳትና እዛ ቤት ማደር እንደማልፈልግ ጭምር አጫውቻት እሷ ቤት ይዛኝ ሄደች:: ሌሊቱን ሁሉ ንዴትና ብስጭት በሽታዬን ቀስቅሰው ሲያሰቃዩኝ፣ የጥርስ ህመም ጀምሮኝም ሲጠዘጥዘኝ ነጋ:: በበነጋው ጠዋት ቤቢ መጣ:: እህቱን ለምን እንዲህ አደረግሽ ብሎ ሳይቆጣት እኔ ላይ ጮኸብኝ "የነሱን መጥፎነት እያወቅሽ ለምን እኔ የሌለሁበት ተናገርሻቸው!" ሲል::

* * *

ትዳር እንዲህ እንደዘበት ዳቦ ተቆረሰ፣ ጨዋታ ፈረሰ የሚባልበት አይደለምና ቁጣውን ተቀብዬ ተመልሼ ወደቤት ገባሁ:: ወደ ቤት ስገባ ግን የጠበቀኝ የሚገርም ነገር ሆኖ ነው:: ታላቅ እህቱ ማደሪያዋን እኛ ቤት አድርጋ ቁጭ ብላለች:: ከእህቶቹ ጋር ጤናማ ግንኙነት እንደሌለኝ እያወቀ የሚፈነዳ ጦር አዘጋጅቶ ጠበቀኝ::

እያደር ነገሮች መጋጋል ጀመሩ:: ከብጥብጥ ውጪ ሰላም ስደት ገባ:: ምንም እንኳን ከመተዳደሪያችን ውስጥ ትልቁን ቦታ የሚይዘው ከኪራይ የሚገኘው ገቢ ቢሆንም ገና ለገና ለዛ ስል ህይወቴን በእንጦርጦስ ውስጥ ከትቼ ማሳለፍ የለብኝም በሚል አንድ መፍትሄ ለመውሰድ ስል አባ ሚካኤልን አግኝቼ ሁሉንም ነገር ዘርዝሬ ነገርኳቸው:: ስቃዬን ጠንቅቀው



Scanned by CamScanner

ተረድተውት ነበርና ቤቢን አግኝተው ማድረግ ያለበትን ነገሩት::

"ትዳር በቤተሰብ ቤት ውስጥ ጥሩ አይደለም:: ልጅቱ እየተጎዳች ነውና በቶሎ ቤት ተከራይታችሁ ኑሯችሁን አስተካክሉ!" ሲሉ ልንወስደው ይገባል ስል ያሳመንኳቸውን ምክንያት አቀረቡለት:: ከችግሮቹ ግንባር ቀደሙ የእህቶቹ ሰላም መንሳት ነውና:: የባሌንስ ችግር እንደራሴ ችግር ልቀበለው እችላለሁ:: የነሱን ግን በምን ሂሳብ ስል? ስለዚህ የአባን ምክር ተቀብሎ ቤት በመቀየሩ ላይ ሲስማማ ደስ አለኝ::

ደስታዬ ግን አብሮኝ አልዘለቀም:: ስምምነት ብቻ ነው የሆነው:: ሰው ፊት የሚደረግ፣ እኔ ዘንድ የሚረሳ ማህላ ነበር- የቤቢ የህይወት ፍልስፍና:: ያለ መታከት አራት ጊዜ ደጋግመው ቤት እንድንቀይር እንዲያግባቡት ነገርኳቸው:: አደረጉት:: አሳዛኙ ነገር ግን ምንም ለውጥ ሊፈጠር አልቻለም::

"ሀሳብህ ምንድነው?" አልኩት ሁኔታው አልጥም ሲለኝ::

"ምንድነው ሀሳቤ?"

"ምን ያህል ከእህቶችህ ጋር መግባባት እንዳልቻልኩ እያየህ አይደል እንዴ?"

"በቃ አትድረሺባቸዋ!"

"እኔ መች ደረስኩባቸው? ታውቃለህ አይደል ችግሩን?"

"እና ምን አድርግ ነው የምትይኝ?"

"ምን አድርግ እልሀለሁ? ለምን በነገሩ ላይ ሁሉ አዲስ ትሆናለህ? አባ ሚካኤል ባለፈው ሳምንት መስቀል አስይዘው እያለቀሱ አስማሉህ... ይኸው በሳምንት ውስጥ ቤት እንቀይራለን ብለህ እስካሁን ቁሉም ዝም፣ መፅሀፉም ዝም ሆነ!"

"የእናት አባቴን ቤት፣ ንብረትና እህቶቼን ጥዬ የትም አልሄድም።"

"ይኼው ነው በቃ መልስህ?"

"አዎ!"

አባን አገኘኋቸው። ከዚያ በኋላ በድጋሚ እንዲጠይቁት፣ አልቅሰው እንዲለምኑት ፈልጌ አልነበረም። እኔ ግራ የገባኝን ጥያቄ እንዲያብራሩልኝ እንጂ።

"አባሚካኤል?"

"አቤት?"

"ከሰውና ከንብረት ማን ይበልጣል?"

ግራ ተጋብተው በሚመረምር አይን ሲያዩኝ ንብረተ ወይም ሰው ብለው በመምረጥ ውስጤ ያለውን ግራ መጋባት እንደማያጠሩት ገባኝ።

"ቀድሞውኑም አይወዳደሩም!" ሲሉ እቅጩን ነገሩኝ።

ከዚያ በኋላ ምንም ሊለወጥ የሚችል ነገር እንደሌለ ገባኝ:: እናም ተራራው ወዳንተ ቢመጣ ካልቻለ ለንተ ወደተራራው ሂድ የሚለውን መርህ መከተል እንዳለብኝ አሰብኩ:: ቤቢ ለውጡ ውስጥ መግባት ካልፈለገ እኔ 'ንብረቱ' እንኳን አይደለሁምና መለወጥ አለብኝ ስል ወሰንኩ:: ውሳኔዬን ተከትለው የመጡት ሁለት ክስተቶች ፅናት ሆኑኝ::

***

የጥርሴ ህመም አንደኛው ክስተት ነበር:: መጠዝጠዙ ሳያንስ ያለማቋረጥ እየደማ ሃይለኛ ስቃይ ውስጥ ከተተኝ:: ህመሙ ለተከታታይ ቀናት ምንም ባደርግበት ሊድን አልቻለም:: አንድ ቀን ሌሊት ላይ ህመሙ ልቋቋመው ያዳገተኝን ስቃይ ሲፈጥርብኝ ሳቃስት የሰማችው የቤቢ እህት ከእንቅልፏ ነቅታ አየችኝና ብስጭት ብላ ተመልሳ ተገላብጣ ተኛ ች:: ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ቤቢ ከአልጋው ተስፈንጥሮ በመነሳት "ምናለ ባትረብሺን... ምናለ ብንተኛበት!" ሲል ጮኸብኝ::

ጩኸቱን ስሰማ ሰውነቴ ሽምቅቅ ሲል ታወቀኝ:: የእህቱ ግድ የለሽ ሆኖ ተገላብጦ መተኛት ሳያንስ የገዛ ባለቤቴ አትረብሽን ሲል ለእህቱና ለራሱ ብቻ ሲያስብ ማየትን የመሰለ ምን የሚያሸማቅቅ ነገር ይኖራል? ሰው'ኮ ከበሽተኛ አጠገብ ማደር የሚጠላው ከጭንቀት ለመዳን ነው:: የኔው ባለቤት ደ'ሞ ጭንቀቱ ለሱና እህቱ እንቅልፍ ማጣት ሆነ...

"እሺ..." ብዬ ከአልጋው ላይ ተነስቼ ወንበሩ ላይ በመቀመጥ ፊቴን ጠረጴዛው ላይ ደፍቼ ህመሙ እየበላኝ እኔ ደግሞ ነገር እየበላሁ ላለመረበሽ ጥንቃቄ በመውሰድ በውስጤ አነባሁ::

ድንገት ግን አዕምሮዬ ውስጥ "ምናለ ባትረብሺን... ምናለ ብንተኛበት!" የሚለው ቃል ደጋግሞ እያቃጨለ የበዛ መከራዬን ሁሉ እየመላለስኩ እንዳየው አስገደደኝ::

*ለምን ማንንም ሰው ወደማልረብሸበት ለሰም ለልሄድም?* ስል ድንገት ሀሳብ እንዳበነነው ሰው ብድግ ብዬ በሩን በመክፈት ወጣሁ:: በራችን ላይ ተበጥሶ የተንጠለጠለውን የልብስ ማስጫ ገመድ ሳብ አድርጌ ቋጠርኩትና አንገቴ ውስጥ አስገብቼ ሸምቀቆውን ባጠብቀውም አፍና ከማስጨነቅ በቀር እስትንፋሴን አልበጥስ አለው:: ነደደኝ:: *ለምንድነው ገመድ ለጣ ፊንታዬ ያልሆነው?*

ገመዱ አላረካ ብሎኝ አይኖቼን ወዲያ ወዲህ ሳቃብዝ ፊት ለፊቴ የኤሌትሪክ ገመድ አየሁ:: *ጎሽ ነገሯ ሁሉ በጥቂት ደቂቃዎች ይጠናቀቃል::* የኤሌትሪክ ገመዱን ሳብ ሳደርገው ብጥስ አለ:: ሽቦውን ጭምድድ ሳደርገው እያንዘረዘረኝ ሄደ:: *ለደዞሸ ለናይት ሁሉም ነገር ለሳም ይሆናል::* ከኋላዬ ከተከራዩት ቤቶች አንዱ ተከፍቶ አንዲት ሴት "ኡኡኡ!" እያለች የቤቢን ስም ስትጠራ ይሰማኛል:: በዚያው ቅፅበትም ቤቢ ወገቤ ላይ ይዞ ለጉድ ሲጎትተኝ ገመዱ ብጥስጥስ ብሎ ግቢው በድቅድቅ ጨለማ ተዋጠ::

* * *

በበነጋው ጎረቤት ሁሉ ተሰብስቦ ቤቢ ተጠርቶ ምክር ተሰጠው:: "ዘመድ ፊት እንዴት ትናገራታለህ? አንተን እያዩ'ኮ ነው እህቶችህ የሚናገሯትና የሚንቋት:: አካልህ ብታጠፋም እንኳ ብቻዋን ነው መናገር ያለብህ!"



Scanned by CamScanner

አሉት:: ምክሩ ግን አትቆጣት ብቻ አልነበረም:: ካቶሊክ ቤተክርስትያን ውስጥ ሙዚቃ እሰራ ስለነበርና አዲስ አበባም ብዙ ጊዜ እየተመላለስኩ ነጠላ ዜማ እየሰራሁ ስለነበር "ታዋቂ ስትሆን ትከዳሀለች" ሲሉም መከሩት:: "ትውለድልህ!"

በዚያ ምስቅልቅል ያለ ህይወታችን ውስጥ ልጅ መውለድ የማይታሰብ ነገር ነበር- ለእኔ:: እኔ ያየሁትን ስቃይ ከአብራኬ የሚወጣ ልጅ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሰው እንዲደርስበት አልፈልግም:: እናም መውለድ ቀልድ ባለመሆኑ ጥረቱን ወደ ስኬት እንዲለውጥ እድል አልሰጠሁትም:: ነገራችን፣ ትዳራችን፣ ህይወታችን ሻከረ::

ይበልጥ እንዲያሻክረው ብቻ ሳይሆን የሚበጠስበት ክረት ላይ እንዲደርስም ያደረገው ሆነ ተብሎ ስልክ እየተደወለ የሚደርሰኝ ማስፈራሪያና ዛቻ ሆነ::

አንድ ቀን ስልክ ጮኸና አነሳሁት::

"የቤቢ ባለቤት ነሽ?" ማንነቷ ያልታወቀ ደዋይ::

"አዎ!"

"ለምን አትለቂልኝም የእኔ እመቤት?"

"ምኑን ነው የምለቅልሽ?"

"ቤቢዬን"

"ይቅርታ፡ የኔ እመቤት..."

"እመቤትሽን ፈልጊ:: የኔን ሰው ልቀቂልኝ..."

"ምን ማለት ነው?"

"እንደመኸገር ከተጣበቅሽበት ተላቀቂ ነዋ!" ሌላ ቀን::

"ቆይ ለመሆኑ ህይወትሽን አትፈልጊያትም እንዴ?" የደዋይ ድምጽ::

"ምን ማለት ነው?"

"ቤቢዬን ለቀቅ... ቅማልሽን ጠበቅ!"

"ለምን ተገናኝተን ፊት ለፊት አንነጋገርም?"

"እሱን ተይውና እንደተባልሽው አድርጊ::"

"በትዳር ውስጥ ገብቶ መበጥበጥ ነውር አይደለ እንዴ?"

"ማን በጠበጠ? አንቺ በሰው ፍቅር ገብተሽ ነገሩን ሁሉ አበላሸሽው እንጂ"

"ይቅርታ ስልኩን ልዘጋው ነው"

"ከመዝጋትሽ በፊት... የአንቺ እያንዳንዷ ነገር በእይታዬ ውስጥ መሆኗን እንድታውቂ"

"ምን?"

"ያስደነግጣል አይደል? ለማመን ከፈለግሽ አሁን የለበስሽውን ፓንትና ጡት ማስያዣ ልነግርሽ እችላለሁ:: ጥቁር ነው አይደል?"

በየጊዜው እየተደወለልኝ ስለተሰራው ምግብ፣ ስለለበስኩት ልብስ... አጠገቤ የሆነ ሰው ብቻ ሊያውቃቸው የሚችሉ ጥቆማዎች እየተሰጡኝ ውስጤ ሲቆስል ቆየ:: መጨረሻው ላይም ማስጠንቀቂያ ተሰጠኝ::

"ቤቢዬ ትናንትና በሰላም ገባ?" ደዋይዋ:: ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ነው የገባው::

"ማን ልበል?"

"ከእኔ ጋር ነበር ያመሸው"

"እና ምን ላድርግሽ?"

"ምንም! የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ልሰጥሽ ነው"

"አልፈታውም:: ለመሆኑ አንቺ ማነሽ?"

"ስሚኝ ልንገርሽ... በነገው ዕለት ቤቱን ለቀሽ ባትወጪ ሬሳሽ ነው የሚወጣው"

ስልኩ ጆሮዬ ላይ ተዘጋና ቁርጥርጥ ያለ አስቀያሚ የስልክ ድምጽ ብቻ ታቅፌ ቀረሁ::



Scanned by CamScanner

## -28-

ከቤቢ ጋር ያለኝን ህይወት አንድ ምዕራፍ ካላበጀሁለት ዘላለሜን መከራዬን ስመክር ልኖር ነው:: እስከ አሁን ያለው የተበላሸ ህይወቴ ያስቃየኝ አንሶ ተጨማሪ የማይድን የጭን ቁስል ሳስታምም መኖር ማለት በገዛ ፈቃዴ ዘላለማዊ እንጦሮጦስ ውስጥ መከርቸም ሆነብኝ:: ደጋግሜ ራሴን ለማጥፋት በጣርኩ ቁጥር ምንም ያህል ደካማነቴን እያጎላሁት ቢሆንም እግዚአብሄር በሞቶቹ ሁሉ እንቅፋት እየፈጠረ ሊያተርፈኝ የቻለው ለመኖሬ አንዳች ምክንያት ቢኖረው ነው ብዬ አመንኩ:: መኖር ካለብኝ ደግሞ መወሰን ግድ ይለኛል:: ህይወት ነውና!

መጀመሪያ ቤተሰብ መምሪያ ሄጄ ተመረመርኩ:: ማህፀኔን የሚያመኝ ምናልባትም የአባላዘር በሽታ ችግር ሊሆን ይችላል ብዬ በመገመቴ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ጨምሮ ሁሉንም አይነት የአባላዘር በሽታዎች ተመረመርኩ:: ሙሉ በሙሉ ከማንኛውም አይነት ችግር ነፃ መሆኔንና ማህፀኔን ለሚያመኝ ነገር ከባለቤቴ ጋር መተሳሰብ እንዳለብን ተነገረኝ:: እኔ የምፈልገው ነፃ መሆኔን ነበርና መተሳሰብ... ገለመሌ ላሉት አንጃ ግራንጃ ግድ የለሽ ሆኜ ከቤት የምወጣበትን መንገድ ለማበጀት አማራጮቼን ሁሉ መፈተሽ ያዝኩ::



Scanned by CamScanner

*ስዩዩም ሲደባ* ነው እንደሚለው ያገሬ ሰው... ተጣልቼ እንኳን ትንሽ ግዜ የማሳልፍበት የእናቴ ቤት ስለሌለ ወይ ጎዳና ላይ መውደቅ አልያም አነስ አደግ የሆነ ስራ አፈላልጌ መግባት የነበሩኝ ምርጫዎች ነበሩ:: አዲስ አበባ እየተመላለስኩ ስራ በማፈላለግ መውደቂያዬን ማበጀት ያዝኩ:: አዲስ አበባ ውስጥ ስራ ማግኘት ከባድ መሆኑን ሳልረዳው ቀርቼ አይደለም:: ቢያንስ ማረፊያ ቦታ ማግኘት በራሱ ለእኔ ማገገሚያ ነውና ዝዋይ እያለሁ እንደነበረኝ አይነት ትንሽ ሱቅ ተቀጥሬ ወይም ሰው ቤት ግርድናም ገብቼ ቢሆን እድሜዬን የማራዘሙን አማራጭ ሽቼ እንጂ ችግሩን ቀድሞውኑም አጥርቼ አውቀዋለሁ:: ልክ እንደነበረው በመሆኑ ስራ ሳላገኝ ለሶስተኛ ጊዜ ወደ ዝዋይ ተመለስኩ:: ወደ ቤት ልገባ ስል አንድ አየለ የሚባል የዐምባ ልጅ አግኝቶኝ እሱ በባሬስታነት የሚሰራበት ሀራ ደንበል ሆቴል በሴተኛ አዳሪነት እየሰራች ያለችውንና ሁለት የጎዳና ተዳዳሪ የሆኑ የዐምባ ልጆችን በምን መንገድ ልንረዳቸው እንደምንችል ሊያማክረኝ እንደፈለገ ነገረኝ:: ጎዳና ላይ ያሉት ሁለት ወንዶች አላሳሰቡኝም:: የልጅቷ ጉዳይ አስጨንቆኝ አብሬው ሄጀ ሳናግራት ስራ በጣም እንደቀዘቀዘና ሞጆ ስለሚሻል እዛ ልትሄድ እንደሆነ ነግራኝ እኔ ከበርካቶች ጎዳናና ቡና ቤት አጣቸው ከሆኑ የዐምባ ልጆች በተለየ እድለኛ እንደሆንኩ ነገረችኝ:: *ሰባሠቀሽ!* ስል በውስጤ ተሳልቄ መልካም ህይወት ተመኘሁላት::

ቤታችን ቁልፍ ስለነበር ከፍቼ ስገባ ውስጡ ያሉት እቃዎች በከፊል ወጥተዋል:: ወጥተው የት ሊደርሱ እንደቻሉ ባይገባኝም ግድ አልነበረኝም:: ሱቁ ከስራ ከተዘጋች በኋላ የእኔ ለጎጂችን ማንኪያ እንኳ አለመግዛት ያሳስበኝ ስለነበር ንብረቴ፣ ንብረትህ ለማለት የሚያስችል

ወኔው አልነበረኝም:: ደግሞስ ከሰው ይልቅ ንብረቱ ለሚበልጥበት ሰው እንዴትስ ነው ስለ ንብረት ልከራከረው የምችለው? ቤቱ ተተረማምሶ ስለ ነበር እንደገባሁ የያዝኩትን እቃ አስቀምጬ ቤቱን ሳፀዳ ሩብ ኪሎ ስኳር መመዘኛ እቃውን እያራገፍኩ እያለ አንድ ነገር ዱብ አለ::

ባለማመን አይነት መጀመሪያ አፍጥጬ፣ ቀጥዬም አይኖቼን ገለጥ፣ ጨፈን በማድረግ አየሁት::

ኮንዶም!

ያውም ጥቅም ላይ የዋለ ኮንዶም::

***

ንዴት ደሜን እያንተከተከው ባለበት ሰዓት ሳይደግስ አይጣላ ሆኖ የቀድሞው የህፃናት ዐምባ አሁን ግን አላጌ የግብርና ኮሌጅ በመሆን እየሰራ ስለነበር እዛ ያለ ሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ውስጥ ክፍት የስራ ቦታ መውጣቱን ሰማሁና ሄጄ ተመዘገብኩ:: ፈተና ተሰጥቶኝ ካለፍኩ በኋላ ስራውን በደንብ እስከማውቀው ድረስ ለሁለት ወራት ቤት ተሰጥቶኝ ያለ ክፍያ ልምድ ማግኘት እንዳለብኝ ተነገረኝ:: *ሁለቷን ሠር ስንደምንም መኖር ስችላለሁ* ስል ወሰንኩና ተመልሼ ለቤቢ ስራ ማግኘቴንና ዐምባው ውስጥ ልሰራ እንደምፈልግ ነገርኩት:: በግዴለሽነት መኪና ላይ አሳፍሮኝ አምስት ሳንቲም እንኳን ለመጠባበቂያ ብሎ ሳይሰጥ አሰናበተኝ::

ዐምባው ገብቼ ስራውን እየተለማመድኩት፣ በችግር የታጠረ ኑሮዬን እየተቋቋምኩትና እዛው ዐምባ የሚሰሩ ልጆችም ድጋፍ እያደረጉልኝ

ስኖር ከቤቢ ደብዳቤ ይደርሰኝ ጀመር፡፡ ደብዳቤዎቹ በሙሉ በእጅጉ ዘግናኝ ናቸው፡፡

"...አንቺ ሸርሙጣ! ከወንድ ጋር ነው የምትኖሪው አይደል?" አንደኛው ደብዳቤው፡፡

"...እርግጠኛ ነኝ የአባላዘር በሽተኛ አድርገሽ እንደምታኖሪኝ..." ሌላኛው...

"...አስደብሽኝ፡፡ በተከበርኩበት ሀገር ወንድ ወደሽ ኮብልለሽ ስሜን አስጠፋሽው..." ድብዳቤዎቹ በደረሱኝ ቁጥር ውስጤን የሚያቆስል አስጨናቂ መንፈስ ይዘው ስለሚመጡ ጨጓራዬን፣ ሲልም ደህና መለስ ያለልኝን የማፈንና የጭንቀት ህመም እየቀሰቀሱ ለህመም ይዳርጉኝ ያዙ፡፡ ይሄ ነገር ተለመደና ሰናይት ታማለች ከተባለ መቼ ደብዳቤ ደርሷት ነው መባል የሰርክ ተግባር ሆነ፡፡

ለሚልክልኝ ደብዳቤ ሁሉ የምመልስለት በተቻለ መጠን ወንድ ተከትዬ ያለመሄዴን የሚገልፅ መሆኑ አበሳጨው መሰለኝ ካልመጣሁ ሲል ፃፈልኝ፡፡ ለጓደኞቼ ሳማክራቸው "ይምጣና ይይሽ" አሉኝ፡፡ ሲመጣም ግሩም የሆነ አቀባበል አደረጉለት፡፡

በበኩሌ እንዳለው ከወንድ ጋር ኮብልዬ ከሆነና ለዚያም ማረጋገጫ ካለው ፈፅሞ ከኔ ጋር ወሲብ ለመፈፀም፣ ሲጀመርም ከዝዋይ ዐምባ ድረስ ሊመጣ አይችልም ብዬ አስባለሁ፡፡ ብቻ የመጣ ዕለት ማታ ግንኙነት እንድናደርግ ጠየቀኝ፡፡

"አይሆንም!" ቀጥተኛ መልስ ሰጠሁት::

"ለምን?"

"ምን ለምን ትለኛህ? ከሽርሙጣ ጋር ምን አቅብጦህ ትተኛለህ?"

"ለማንኛውም ግን ወሲብ እንድናደርግ እፈልጋለሁ"

"አይሆንም! የአባላዘር በሽታ ይይዝሀል::"

"ኮንዶም አለ:: በሱ መጠቀም እንችላለን"

"ትሰማኛለህ ቤቢ... ማድረግ እንኳን ቢኖርብን ተመርምረን ማን የአባላዘር በሽተኛ እንደሆነና እንዳልሆነ አረጋግጠን ነው::"

"በኮንዶም ብናደርግ'ኮ ችግር የለውም"

"በአንገቴ ብታረድ አይሆንም!"

በጥሩ አስተናግደን ከሸኘነው በኋላ ዝዋይ ሲደርስ ለቁጥር ከሚታክቱ ጎረምሶች ጋ ነው የምትኖረው ብሎ የጎረምሶቹ ቅምጥ እንደሆንኩ አስወርቶብኝ ቁጭ አለ::

* * *

መደበኛ የሱቅ ስራዬን እየሰራሁ ሳለ በየሳምንቱ ዐምባው ውስጥ ኮሌጁ በሚያዘጋጃቸው የሥነ-ፅሁፍ ምሽቶች ላይ እካፈል ስለነበርና አንድ ወቅትም ላይ የኮሌጁን ተማሪዎች ሥነ-ፅሁፍ የሚያስተምር ተብሎ

በወጣው ማስታወቂያ ተወዳድሬ አልፌ የማውቃትን ነገር ሳካፍል ያዩኝ ጓደኞቼ የእኔ ህይወት በዐምባው ውስጥ ብቻ ተቀብሮ የጋን ውስጥ መብራት መሆን እንደሌለበት እና አዲስ አበባ ሄጄ ህይወቴን መቀየር እንዳለብኝ መክረው ገንዘብ አዋጥተው ሰጡኝ::

ቀጥታ ወደ ቤቢ ቤት ሄድኩኝ:: ያለኝን ሻንጣና ልብስ አዘገጃጅቼ ወደ አዲስ አበባ ልሄድ እንደሆነ ስነግረው ለማንያችንን ካልቀደድን መሄድ እንደማልችል ነገረኝ::

"ቤትሽን እየጣልሽ አንዴ እዛ፣ አንዴ እዚህ እያለሽ መመላለስ አትችይም" ሲል መመላለሴን ምክንያት አደረገው:: የምመላለስበት ምክንያት ምን እንደሆነ ከመጠየቅና መረዳት ይልቅ ምክንያት አድርጎ ለመፍታት ነው ያቆበቆበው::

"ታዲያ ምን አድርጊ ነው የምትለኝ?" ስል በመገምገም ሁኔታ ጠየቅኩት:: ቤቢ ከመጋባታችን በፊትና በተጋባን ሰሞን መልዐክ የነበረ ሰው ነበር::

"አንቺም ዘመድሽን ጥሪና የኔም ዘመዶች ባሉበት እንቅደደው"

"ራስህ ቀድደው!" አልኩት ሆነ ብሎ ዘመድ እያለ እየነካካኝ እንደሆነ ስለገባኝ::

"እንደሱ የማድረግማ ስልጣን የለኝም"

"ታዲያ ዘመድ እንደሌለኝ እያወቅክ ለምን ትጨቀጭቀኛለህ?"

"አባቴ ጋ እያልሽ አስር ጊዜ የምትመላለሽባቸው አባ ሚካኤልስ?" ሲል



Scanned by CamScanner

ሊዘባበትባቸው ፈለገ::

"እሳቸውን አትናገርብኝ:: እኔ ያንተን ቤተሰቦች አክብሬ ሲያዋርዱኝና ሲሰድቡኝ ችዬ ተቀምጫለሁ:: በሳቸው የመጣ ነገር በዐይኔ የመጣ ነው::"

"እረ? ለምን እንደምትሄጂ የማላውቅ መሰለሽ? ልትሸረሙጪ'ኮ ነው" ሲል በድንገት ርዕሱን ቀየረው::

"እውነት?"

"አዎ! እስከዛሬም ያበላሽኝ የሸረሞጥሽበትን ገንዘብ ነው:: አንቺ መቼም አያልፍልሽ... እከካም ነሽ... እከክሽን ስታኪ ነው የምትኖሪው"

መልስ ሳልሰጠው አጥንቴ ውስጥ ድረስ ዘልቆ የገባውን ልቅ ዘለፋ ለመቋቋም ስታገል ከቁጥጥሬ ውጪ እንባዎቼ ከአይኔ ረገፉ::

"እሺ... ከኔ የምትፈልገው ምንድነው?"

"ስማንያችንን እንድንቀድ"

"እሺ..."

"ስው የታለሽ?"

"ግዴለም ታዛቢ ባለበት በፈቃዴ እቀድልሀለሁ::"

የጋብቻ ካርዳችንን ፍለጋ ቢባዝን የት ያግኘው? ይመስለኛል ለፌሩዝ የሰጣት መሆኑን በማመን ለዘብ አለ::

# -29-

የጋብቻ ምስክር ወረቀቱ እኔ እጅ ላይ እንዳለ የሚያውቅበት ምንም አይነት ክፍተት አልነበረም:: በዝምታው ውስጥ መሸነፉን መቀበሉን ተረዳሁና እሁድ ዕለት ዳግመኛ ሊያገናኘን የሚችል ነገር እንደማይፈጠር በማመን እንደዘበት ትዳሬን ትቼው ወደ አዲስ አበባ አቀናሁ:: የተገነባን ነገር ማፍረስ ከባድ ነበር:: ይሁንና የእኔና የቤቢ ትዳር እለት በዕለት እየተሸረሸረ በመሄዱ ምንም እንኳ ሰማንያችንን ባንቀድም በመለያየት ዳዋ ስንዋጥ ከብቸኝነት ያለፈ ያመመኝ ነገር አልነበረም:: እንዲያውም ዝዋይ ከተማን ለቅቄ ስወጣ የተሰማኝ ዘላለማዊ ነፃነት የተጎናፀፍኩ ያህል ነበር::

አዲስ አበባ ከተማ ስደርስ ግን ውስጤ በፍርሀት ተርበደበደ:: *የት ነው የማርፈው? ዕጣ ፋንታዬስ ምን ይሆናል?* ህይወት በራሷ ዛቢያ እያሽከረከረችኝ ይሁን ወይም የህይወት ምህዋር ሳይገባኝ ቀርቶ እኔ ያለ አግባብ እየተገለባበጥኩባት ምክንያቱ እንደግንቦት ጨረቃ ጥርት ብሎ ባይታየኝም እልም ያለ ግራ መጋባት ውስጥ ነበርኩ:: *ስንት ሴቶች የእኔ አይነት ዕጣ ፈንታ ተቋዳሽ ይሆኑ?* ሴት መሆናቸው ብቻ ለስንት መከራ ዳረጋቸው ይሆን? *ይህች ሰበም... ኮተታም... ይህች ሰበም... ግሳንግሳም... ይህች*

*ለሰም... በሴቶች ላይ ግፍ የሰራች...* ውስጤ የሚተራመሱትን ሀሳቦች መግታት ተሳነኝ:: *ለእኔ ህይወት መበላሸት ማን ይሆን ተጠያቂው? እኔ ሰናይት? የማላውቃቸው ቤተሰቦቼ? መንግስት? ወንዶች? ወይስ ጠቅላላ ማህበረሰቡ?* ልክደው ያልቻልኩት አንድ ሀቅ ሁላችንም የተውኔቱ ባለቤት መሆናችንን ነው:: ሁላችንም! እና ውስጤ *ቀሽም ተውኔት*¡¡ ሲል ተሳለቀ::

*አሁን ወዴት ነው መሄድ ያለብኝ?* አሰብኩ:: ጓደኛዬ ብርቄ ቤት እየተመላለስኩ ማስቸገሩ አልታየኝም:: ሌላ መሄጃ ደግሞ የለኝም *ቤት መከራየት ነው ያለብኝ*:: አንድ ዝዋይ የነበረች ልጅ ናይት ክለብ የምትሰራ ፈረንሳይ አካባቢ ቤት ተከራይታ እንደምትኖርና የዐምባ ልጆችም እዛ እንዳሉ ስለሰማሁ ወደዛ አመራሁ:: ልጅቷን ካገኘኋት የሆነ ነገር ልትረዳኝ እንደምትችል ተስፋ አድርጌ ነበርና:: ፈረንሳይ ሰፈር ስደርስ እንዳሰብኩት የዐምባ ልጆችን አገኘሁና ቤት እንደምፈልግ ነገርኳቸው:: ወዲያው ለደላሎች ነገሩልኝና ፍለጋው ተጧጧፈ:: አዲስ አበባ ውስጥ በትንሽ ብር... ያውም በአንድ ቀን ቤት ማግኘት ከባድ ነበር:: ይሄው ሲነገረኝ ማደሪያ ፍለጋ የት መሄድ እንዳለብኝ ሳውጠነጥን በሚገርም አጋጣሚ ቤት መገኘቱን አበሰሩኝ:: *ውስጤ ከፋት የለም ማለት ነው?* ስል አሰብኩ- ቤት ያገኘሁበት ፍጥነት አስገርሞኝ::

ቤላ ላይ ነበር ቤቱ የተገኘልኝ- የአፈር ቤት:: *ይሁና! ምን አፈር ለፍ ብዬ ጎዳና ላይ አልተኛሁምና ነው? ዝናብና ፀሀይ አልተፈራረቁብኝምና ነው?* አግኝቶ ከማጣትና አጥቶ ከማግኘት የትኛው ይሻላል? ሁለቱም ልምድ ቢሆኑም ቅሉ አግኝቶ፣ የተመቻቸ አልጋ ላይ ተኝቶ ወደ አፈር መውረድ ለሞራልም



Scanned by CamScanner

ሆነ ክብር የማይመች ነገር ይፈጥራል:: ጥያቄው ግን አግኝቶ የማጣትና አጥቶ የማግኘት ብቻ አልነበረም:: ጥያቄው የሚደላ አልጋ ላይ ተኝቶ አዕምሮን በሚቆረቁሩ አስጨናቂ ሀሳቦች ከመሰቃየትና ድብን ተደርጎ በእበት የተለቀለቀ የአፈር ቤት ላይ እየተኙ ስጋን ብቻ ከመጉዳት የትኛው ይሻላል? የሚል ነው::

"ከመቶ ሀያ ብር አልወርድም!" አሉ ቤቱን ሊያከራዩኝ የተስማሙት ሴትዮ- እቴቴ ነው የሚባሉት::

"እቴቴ በጣም ተወደደብኝ..."

"አዬዬ ልጄ! ገባ ስላለ ነው እንጂ ይሄ ቤት ከሁለት መቶ ባውንድ የበለጠ አይከራይምና ነው?"

"አይ... እኔ'ኮ አቅሜም ስለማይችል..."

"ታዲያ ታልቻልሽ ተይዋ!"

"ማለቴ... አሁን አልችልም ለማለት ነው:: ወደፊት ባይሆን እጨምርልዎታለሁ:: አሁን ግን መቶ ብር ያድርጉልኝ"

ተስማሙና ብሩን ከፍዬ ገባሁ::

ይገሬው የመጣሁትን ሻንጣ በቁም ለቀቅኩትና እኔም ሻንጣው ላይ ዘጭ ብዬ ተቀመጥኩ:: ቤቷ ሶስት በሶስት ናት:: ግድግዳዋ እንደነገሩ ግማሽ

ጎኗ ድረስ ኖራ ተቀብቷል:: የቆየ የኖራ ሽታ ግማሽ ጎኗ ከረጠበውና ግማሽ ጎኗ ደርቆ ከተሰነጣጠቀው መሬሬ አፈር ሽታ ጋር ተዋህዷል:: በኖራና እርጥብ አፈር የታወደውን አየር ደጋግሜ እየማግኩና እያስወጣሁ ቁዘማ ውስጥ ሆኜ ትቼው የመጣሁትን ምንዱባን መለስለስ አድርጌ ቃኘሁት:: *ለሁን ነፃ ነኝ ማለት ነው?* ወለሉ ላይ ኧ! ብዬ አይኔን ወደጣራው በመስካት ከት ከት ብዬ ሳቅኩ:: ሳቄ የእውነት ይሁን የውሸት አልለየሁትም:: ውስጤ ግን በመሬቱ የሚያውድ ሽታ ሲቅበጠበጥ ታወቀኝ:: ይወርድ የነበረው እንባ በአንገቴ እያደረገ ወደ ጡቶቼ ሲደርስ በምናቤ ከሰማይ በተላከ ጠበል እየተጠመቅኩ ያለሁ ያህል ተሰማኝ:: *ሶ! ጌታ በምህረቱ ሲጎበኘኝ ነው!*

ሰማዩ መጠለም ሲጀምር ቦርሳዬ ውስጥ ካሉት ልብሶች በቀላሉ አፈር የማይዞሩትን ለይቼ አወጣሁና በደንብ አሳምሬ አነጠፍኳቸው:: በውስጤም *ተወዳዳሪ በሌለው ድንቅ ምቾት ባለው ለፊጋ ላይ ልተኛ ነው::* ስል አሰብኩ:: ጎኔን ጎሳርፌው በተሰማኝ ስሜት *የናጠጠ ሀብታም እንኳን የሕኔን ያህል የተመቻ ለፊጋ ላይ ለተኛም* ስል ውስጤን አሞቅኩት:: አለም ሁሉ ድብልቅልቋ ወጥቶ ቢያድር ግድ አልነበረኝም- በህይወቴ ሙሉ ተኝቸው የማላቀው አይነት ሞት የመሰለ እንቅልፍ ነበርና ጠርጎ የወሰደኝ::

እያደር የምበላው እንደሚጠፋ፣ ኑሮዬ ከቀድሞው የከፋ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም ፍርሀት እንደብርድ ሸው እያለ ሳያንዘረዝረኝ ቀርቶ አልነበረም:: ዳቦና ስኳር ገዝቼ እየገባሁ ስኳሩን በውሀ እየበጠበጥኩ

ዳቦውን እየገመጥኩ አማምግበት ነበር፡፡ ጠዋት ዳቦ በስኳር በተበጠበጠ ውሃ የተመገበ ሰው ቀኑን ሙሉ ርሀብ ትዝ አይለውም- ክብደቱ ይቀንሳል እንጂ፡፡ በዚህ ሁኔታ በህይወቴ ውስጥ ለውጥ እንደማይፈጠር በማመኔ ጠዋት የወጣሁ ማታ ነበር የምገባው- ስራ ፍለጋ፡፡

*ምንድነው ልሰራ የምችለው?* መስራት እችላለሁና አለብኝ ብዬ የማስባቸውን ነገሮች ሁሉ አወጣሁ፣ አወረድኩ፡፡ ማስታወቂያዎችን ለማየት ባዘንኩ፡፡ ስራ ማግኘቱ ግን የማይቻል ሆነ፡፡ ኬክ ቤት- በወር ሰማንያ ብር፡፡ *ምን ሊተሆን ነው?* ቤት ኪራይ አልሸፍንበት፣ ትራንስፖርት አላደርገው ወይ ለቀለብ አይሆነኝ... ብቻ የምይዝ የምጨብጠው ጠፋኝ፡፡ እኔ ኑሮን የማሸነፍ ትግል ውስጥ ግብግብ ገጥሜ ሳለ ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው እንዲሉ ድፍን ዘዋይንና አዲስ አበባን ያዳረሰው ወሬ ዘግይቶ ነበር የደረሰኝ፡፡ ወንድ ወድዳ ነው የኮበለለችው የሚል፡፡

# -30-

ቤቱን ያከራዩኝ እቴቴ በጣም ጥሩ ሰው ናቸው:: ነጋ ጠባ ዳቦና ስኳር ብቻ እየያዝኩ የመግባቴና ተግባቢ ያለመሆኔ ቢያስጨንቃቸው "አንቺ ልጅ ችግርሽ ምንድነው?" ሲሉ ወደ እኔ ቤት ብቅ አሉ:: ምንም የምተኛ በት አለመኖሩና አንድ ሻንጣና ተራ ቅራቅንቦዎች የተሰባሰቡበት ጉሮኖ የመሰለውን ቤት አይተው "ለመሆኑ ምን ላይ ነው የምትተኚው?" ሲሉ ጠየቁኝ:: መልስ ልሰጣቸው ሲዳዳኝ ገና "ቆይ ያለጥቅም'ኮ ያስቀመጥነው አልጋ አለ እሱን..." ሲሉኝ "አይ... እኔ ወገቤን ስለሚያመኝ አልጋ ላይ መተኛት አልችልም" አልኳቸው:: ደነገጡ:: በመሰረቱ አልጋ ቤት ውስጥ እንዲገባ ያልፈለኩት ወገቤን ስለሚያመኝ አልነበረም- ከመቼውም በላይ ጤና ያገኘሁት አሁን ነው ብዬ ስለማስብ አንዳችም ህመም የለኝም:: ይሁንና ድፍን ዝዋይንና ከፊል አዲስ አበባን ያመሰው የቤቢ ወሬ ከእውነታው ጋር እንደሚጋጭ የማሳየት ፍላጎት ነበረኝ:: "ቆይ እንግዳው ማዳበሪያ አለ ልስጥሽ::" ሲሉ ስስ ማዳበሪያ አመጡልኝና አነጠፍኩት:: ልብሶቼ በአፈር ከመበላት ዳኑ እንጂ የተለየ ምቾት አልፈጠረልኝም::

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ነው ቤቢ በጓደኞቹ በኩል አጠያይቆ ስልክ

ቁጥሬን ማግኘት የቻለውና ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጣ የነገረኝ:: መምጣቱን ልቃወመው መብቱ ባይኖረኝም ላገኘው ግን ፍላጎቱ አልነበረኝም:: *ለምን ለገኘዋለሁ?* ትዳራችን እንደሆነ ፈርሷል:: ሰማንያችንን በእጃችን ላይ ባንቀደውም ቅሉ ፍቅር ይዞ የነበረው ልባችን ተቀድዶ የጥላቻ ደም እያፈሰሰ መርዞታል:: እና እሱን ማግኘቴ ምን ፋይዳ አለው? ሀሳቤን እንደጠበቅኩ እንዳልቆይ ያደረገኝ የጓደኞቼ ነጋ ጠባ ውትወታ ነበር:: መቆሚያ መቀመጫ አሳጡኝ:: *ባገኘው ደገባበ* ስል ወሰንኩ- ቀድሞውኑም ያለሁበትን ሁኔታ እንዲያየው እፈልግ ነበርና:: ከጓደኞቼ ጋ መሆኑ ደግሞ የበለጠ ጥሩ ስሜትና ጉጉት ፈጠረብኝ::

"ቤትሽን ማየት እፈልጋለሁ አለኝ ቤቢ- ጓደኞቼ ቤት ሄጄ እንዳገኘሁት::

"ምን ይሰራልሀል?"

"ምንም ይስራልኝ... ማየት ግን እፈልጋለሁ"

"ለምን ያስከበለለሽን ወንድ ማየት እፈልጋለሁ አትለኝም?"

"ልታሳይኝ ትችያለሽ ወይስ አትችይም?"

"አልችልም!" እርግጠኛ ሆንኩበት::

"አላልኳችሁም! ቤቷን ባየው ምን ችግር አለበት?" ጠየቀ:: "ምንም ችግር የለበትም::" ራሱ መልስ ሰጠ:: "እውነታው ግን አንዱን ጎረምሳ ወድዳ መሄዷ ነው" ጓደኞቼ ጭምር እምነት ያሳደሩ መሰለኝ::



Scanned by CamScanner

"ማየቱ ምን ይጠቅምሀል?" ስል ጠየቅኩት::

"ያለሽበትን ሁኔታ ማወቅ እፈልጋለሁ"

"እሺ... ኑ እንሂድ!"

ይመስለኛል አንዱ ጎረምሳ ቤት ተከራይቶና የቤት ዕቃ አሟልቶልኝ ወይም እሱ ራሱ አብሮኝ እየኖረ መሆኑን የሚጠቁም ነገር ለማየት ነበር ራሱን ያሳመነው:: ገና ግቢው ስንገባ ፊቱ ጠቆርቆር ማለት ሲጀምር እያየሁት በውስጤ ፈገግታ ረጨሁ:: እንደእውነቱ በዚያ ሁኔታ ውስጥ መታየቴ ሞት ቢሆንም ለእኔ ግን ትልቅ ድል ያደረግኩት ወንድ ወድጄ ያለመኩብለሌን እንዲያይ ነበር::

"እና..." አልኩ ኮራ ለማለት በሚያስደፍር የበላይነት ስሜት:: "እና... ወንድ ወድጄ ብመጣ አፈር ላይ ነው የምተኛው? ወንድ ፈልጌ ብመጣ በእንዲህ ያለው የአይጥ ጉሮኖ በመሰለ ቤት ውስጥ ነው የምኖረው? እባክህ ቤቢ... ህይወት እያቀረበችልኝ ያለውን ስቃይ የማጣጥመው ሳያንሰኝ ሌላ ስቃይ አትሁንብኝ?..." ቃላቱን ካወጣኋቸው በኋላ ውስጤ ደስ አልተሰኘም- የስቃዬ አንዱ ምንጭ እሱ ነውና::

ድንገት ጨርሶ በዚህ ፍጥነት ይለወጣል ብዬ ባላሰብኩበት ቅፅበት ተወርውሮ እግሬ ላይ ተደፋ:: እዬዬ እያለ አለቀሰ:: ውስጡ ያለው በደል ፈንቅሎት የመጣ ለቅሶ ይሁን ወይም ጓደኞቹ አብረውን ስላሉ ለታይታ ሲል ያደረገው ለይቼ ላስተምጠው ቢከብደኝም ልመናው

አንጀት ይበላ ነበር፡፡

"በቃ ሰኒ... ዳግመኛ አልጎዳሽም፡፡ እ... እንዲህ ያለ ስቃይ ውስጥ ትሆኛ ለሽ ብዬ እንዴት ማሰብ እችላለሁ?" *እንዴተስ ማሰብ ተችሳለህ? ብታስብማ ኖሮ የት ወደቀሽ ተብኝ ነበር* አልኩ በውስጤ፡፡

"ትዳራችን እንደገና እንዲያብብ እናደርገዋለን፡፡ አንቺ ብቻ ይቅር በይኝ" *ስበበህም ቢቢ... ትዳራችን ረግፏል፡፡*

"ሰኒ እባክሽ! በፈጠረሽ አምላክ" *ስባክህ በፈጠረህ ስምባክ ከስግሬ ባይ ተነሳ!*

"ሰኒ..."

"ቤቢ... አይሆንም! የእኔና ያንተ እህል ውሀ አልቋል"

"አላለቀም ሰኒ... አላለቀም!"

"አልቋል!" ቆራጥ በሆነው መልሴ ተበሳጨ፡፡ *ጓደኞቹም ለምን ሲለምናትና ይቅርታ ሲጠይቃት ስተቀበለውም?* ሲሉ እርስ በርሳቸው ትዝብት ተለዋወጡ፡፡ ያቺን ሰዓት ከትክክለኛ ስሜቴ ጋር ብቻዬን ቀረሁ፡፡ ግድ ግን አልሰጠኝም፡፡

"እንቢ ካልሽ የገዛሁልሽን ልብሶች እና የፎቶ አልበሞቹን እወስዳቸዋለሁ" አለኝ፡፡ ነደደኝ፡፡

"ስለቅራቅንቦ እቃዎች ስል ልታረቅህ እንደምችል አስበህ ከሆነ ተሳስተሀል፡፡ ቤቢ ሌላ በሽታ አትሁንብኝ!" ለነገሩ አስፈራራኝ እንጂ

በአንዲት ሻንጣ ያሉትን በጣት የሚቆጠሩ ልብሶችም ሆነ የፎቶ አልበም ሊወስደው አልሞከረም:: ሀብት ንብረት ልካፌል ሳልል ትቼ የወጣሁት እንሶ እንደትልቅ ነገር ቅራቅንበ ሊለቅም ማሰቡ አበሳጨኝ:: በውሳኔዬ ላይ ያለኝ አቋም ጥብቅ መሆኑን ሲያይ አልቅሶ ከመሄድ በዘለለ አስር ሳንቲም ለስኳር መግዣ እንኳ ትሁንሽ ብሎ አልወረወረልኝም::

ቤቢ ካቀረበልኝ የይቅርታ ጥያቄ ጋር ያለሁበትን ሁኔታ እንደማየቱ ለምን ለችግሬ መፍቻ ትንሽ ፍራንክ እንኳን ሊሰጠኝ እንዳልቻለ እየተገረምኩ ሳለ ከዐምባ ስልክ ተደወለልኝና የላክንልሽ እቃ ስላለ ሀያ ሁለት አካባቢ ሄደሽ ተቀበይ ተባልኩ:: ስደርስ በትላልቁ ቢጫ ኩርቱ ፌስታሎች ሙሉ፣ ሙሉ እቃ ግጥም ተደርጎ ታስሮ አገኘሁ:: የእቃውን ምንነት ለማወቅ እንደጓጓሁ ነበር ቤት የደረስኩት:: አልጋ ልብስ፣ ብርድ ልብስ፣ አንሶላ፣ በሶ... ሽሮ... በርበሬ... ዘይት... ብረት ድስት... ትንሽ ባሊ... ለማመን የሚከብድ:: ልክ እንደጎጆ ወጪ ሁሉ አውጥቼ በቤቱ ወለል ላይ በመደርደር እያየኋቸው ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: ባሌ... የአካሌ ክፋይ የምለው ሰው መጥቶ መሬት ላይ እንደምተኛ አይቶ 'ቆረቆረሽ' ያላለኝ ምንም የማላውቃቸው ባዳዎች እንዲህ ሲደርጉ ማየት እንዴት አያስለቅስ?

* * *

ስራ አለማግኘቴ በራሱ ራስ ምታት ይሁንብኝ እንጂ አልሞት ባይ ተጋዳይነቴን አላቆምኩም ነበር:: ሁኔታዎቹ ተስፋ ሲያስቆርጡኝና

አስፈሪ ጨለማ ከፊቴ እየተደገነ ሲታየኝ በዚህ ሁኔታዬ መቀጠል እንደማልችል ይሰማኝ ጀመር:: *ኪስ ቤትም ቢሆን መስራት ስለብኝ* ብዬ አሰብኩ:: ገንዘቡ ለምንም ባይሆን እንኳ አዲስ አበባ በደባልነትም ቤት መከራየት ስለሚቻል የማገኛትን እያብቃቃሁ:-

*ሰመደው፣ ሰመደው ሆዴ*

*ፊዙን ብሳው በዘዴ*

*ሰመደው፣ ሰመደው ሆዴ*

*ኑሮ በዘዴ*

*ኑሮ በሁዳዴ* እያልኩ ለማንጎራጎር ራሴን ማዘጋጀት ላይ እያለሁ በስራ ፍለጋ አማካይነት ከሰዎች መተዋወቅ ችዬ ነበርና ሜጋ የነበረው ኮፒ ራይት ቢሮ ውስጥ ከሚሰራው ታደሰ ወ/ገብርኤል ጋ ተግባባንና እሱ ዘንድ መለስ ቀለስ ስል ቀስ በቀስ ስላለሁበት ሁኔታ አወጋሁት:: ሁኔታዬና የደረሰብኝ ችግር አንጀቱን ቢያላውሰው "በናታችሁ እንርዳት!" ብሎ ከሚያውቃቸው ሰዎች ጋ በመሆን አብረው ቤት ተከራይተው ሲጨርሱ "እቃሽ የት ነው ያለው? ሂጂና አምጪ" አሉኝ:: ምንጣፍ፣ ሁለት የጥጥ ፍራሽ፣ ትራስ... ገዝተውልኝ ነበር:: የሚገርመው ደግሞ የሶስት ወር የቤት ኪራይ ነበር የከፈሉት:: *እግዚአብሄር ያውቀኛል... ያስታውሰኛል ማለት ነው?* ስል ተደመምኩ:: *በየእንቅፋቶቹ ድርባ እንዲህ ያሉ ደግ ሰዎችን የሚያዘጋጅልኝ ለምን ይሆን?* ልመልሰው በከበደኝ ጥያቄ ላይ ይብሱኑ የሚያገዝፈው ድርጊት ነበር ያደረጉት::



Scanned by CamScanner

ቤላ ያለውን የቤት እቃ ሳስገባ አዩትና መጣን ብለው ሄደው ሙሉ የቤት እቃ... ከማንደጃና ከጋዝ መግዣ ጀሪካን ጀምሮ አንድ ሳይቀራቸው ገዝተው መጡና ቤቱን ግጥም አድርገው ሞሉት፡፡ ካርቶን ፓስታ፣ ካርቶን መካሮኒ...

"አይዞሽ ሰኒ... እኛ ወንድሞችሽ እንሆናለን፡፡ አይዞሽ!" እያሉኝ ውሏቸውን እኔ ቤት በማድረግ ዳግም የመወለድ ያህል የህይወትን ብሩህ ገፅታ እንዳይ አረዱኝ፡፡ ይሁንና ሰው ክፉ ነው ብዬ ስለማምን ጥርጣሬ ሊገለኝ ደርሶ ነበር፡፡



Scanned by CamScanner

# -31-

ወሬ እንደሰደድ እሳት ይቀጣጠልና አገር ያጠፋል:: ትንሿ እሳት እንዲያ እንድትገን የሚያደርጋት ደግሞ ንፋስ ነው:: ሰው ንፋስ:: ወሬ ወዳድ... እንዳወራ ነፍሶበት ነፋስ ሆኖ የሚቀር:: ከቤቢ ህይወት ወጥቻለሁ ብዬ የነፃነትን አየር እንደልቤ እንዳልምግ ለምን ወሬ እሳት ሆኖ እንደሚለበልበኝ ሊገባኝ አልቻለም::

አብነት አካባቢ ተከራይቼ እንደምኖርና ከብዙ ጎረምሶች ጋር የተለየ ግንኙነት እንዳለኝ ተወራ:: ይሄን ማስወራቱን ከቁብ አልቆጠርኩትም:: ንፋስ ባለበት ቦታ ትንሿ እሳት ሰደድ ትሆናለችና:: ለወሬው ግድ እንዲሰጠኝ ያደረገው ምክንያት ግን ዛቻ መሆኑ ነው::

"እገላታለሁ!"

ዛቻውን በንቀት አላየሁትም:: ቤት የተከራዩልኝ ልጆች ግን "እስቲ የሚያደርገውን እናያለን... ህግ ባለበት ሀገር ጫፍሽን ይነካታል" ቢሉኝም ሁኔታው ምቾት ነሳኝ:: *ህግ.. ህም! እኔ ከተደፋሁ በኋላ ህግ ለእኔ ምንድነው?* ደግሞስ ማነው በዚህ ምድር ላይ ከየት አባቷ እንደመጣች፣ የት አባቷ እንደምትሄድና ምናባቷ እንደሆነች ለማትታወቅ ሴት ተጨንቆ ህግ

ቦታ የሚሄደው? "ክሰሸው!" ሲሉኝ እንቢ አልኩ:: ከሱ ጋ ስካሰስ የምኖርበት ምንም ምክንያት አልነበረም:: በቅርቡ ጓደኛ መያዙን ሰምቼ እውነት መሆኑን ካየሁ በኋላ የእኔ ምዕራፍ በሱ ዘንድ የተዘጋ ነበር የመሰለኝ::

ደጋግሞ ወደ አዲስ አበባ በመጣ ቁጥር ዛቻው እኔጋ እንዲደርስ የሚያደርግበት መንገድ ሲበዛ ግን ከአዲሲቱ ጓደኛው ምህረት ጋ የተለያየ መሆኑን እንድጠረጥር ጋበዘኝ::

አንድ ዝዋይ ያለች ጓደኛዬ እኔ ከቤቢ ተለያይቼ እንደመጣሁ ከምቀርባት ምህረት የተባለች ሴት ጋ ግንኙነት መጀመሩንና አብረው ሆነው ዲኤስቲቪ ማሳያ ቤት መክፈቱን ትነግረኛለች:: ከሴት ጋር ግንኙነት መጀመሩ ሳይሆን ከጓደኛዬ መሆኑን አምኜ ለመቀበል ሳመነታ "አንድ ቀን ብቻ መስዋት ብታደርጊ ምንም አይደል... ተደብቀሽ ነይና እኔ ቤት ታድሪያለሽ... ያኔም በማታ ቀስ ብለን እናያቸዋለን" አለችኝ:: ነገሩን ማወቅ ስላጓጓኝም ሄጄ ተመለከትኩ:: በጓሮ በር ስገባ የቤቢ ቤት ባዶ ሆኗል:: እቃውን ሁሉ ወስዶ ለካ ምህረት ቤት አድርጎት ኖሯል:: ዲኤስቲቪ የሚያሳዩበት ቦታ ሄጄ ካየሁም በኋላ የራሱን አዲስ ህይወት ጀምሯል ብዬ ስላሰብኩ አይደለም ለዛቻ ቀርቶ አይኔን ለማየት እንኳ ፍላጎት እንደማይኖረው ነበር ያመንኩት::

በሩቅ፣ በመልዕክተኛ የሚደርሰኝን ዛቻ እየተለማመድኩት እያለ አንድ ቀን እኔንም፣ እሱንም የሚቀርቡን ሰዎች ቤት ተጠርቼ ስሄድ ቤቢን

አገኘሁት:: ፊፅሞ ቤቢን አልጠበቅኩም ነበር:: ያም ሆኖ የተጠራሁበትን ምክንያት ማወቅ ስለነበረብኝ ተቀመጥኩ::

"ሰኒ ዛሬ እንድትመጪ ያደረግነው በአንዳንድ ነገሮች ላይ መወያየት ስላለብን ነው" ተብሎ የይቅርታ ጥያቄ ሲነሳ ደነገጥኩ:: ያለቀ፣ የደቀቀ ነገር ነው የተባለለት መልሶ ነፍስ ሲዘራ ምን ይባላል?

"ለምን?" ስል ተገርሜ ጠየቅኩ::

"መስማማት አለባችሁ:: ተራርቆ ትዳር ጥሩ አይደለም"

"እንዴት? ተለያይተን... ነገሩ ሁሉ አክትሟል አይደል እንዴ? አሁን ምን ተገኘ?" ግራ ተጋባሁ::

"ሰማንያ ሳይቀደድ መለያየት የትዳር ፍቺ ሳይሆን ጊዜያዊ ፀብ ነው" አለኝ ከሚዜዎቻችን አንዱ::

"ቢሆንም!"

"አሁን ምን እየሰራሽ ነው?" ሲል ሌላኛው ሚዜ ጠየቀኝ::

የሙዚቃ ሥራ እየተለማመድኩ መሆኑን ነገርኩት:: እውነትም ከታዬ ጋር በመሆን ትንሽም ቢሆን የኪቦርድ ጥናት ጀምረን ነበር:: ከተለያዩ ሙዚቀኞች ጋር መተዋወቅ ችዬ ሰማኸኝ በለውም የዘመድ ያህል ቀርቦኝ ነበር::

ጥሩ ነው። በሉ አሁን ያለውን ፀብ ሻሩና ተስማምታችሁ ትዳራችሁን አስተካክሉ ተባለ። ረዥም ሰዓት ስንነታረክ ከቆየንም በኋላ ነገራችን ሁሉ ጉንጭ አልፋ ክርክር ሆነ። "መሸ። መሄድ አለብኝ" ስል ተነጋግረን ስላልጨረስን ነገ ለመምጣት ቃል መግባት አለብሽ ብለው ቃል አስገቡኝ።

በበነጋው ስሄድ ግን ውስጤ ላስቀምጠው የሚገባ ምንም ነገር መኖር እንደሌለበት አምኜ ነበር ያቀናሁት።

"በል ይቅርታ ጠይቃት" ተባለና ይቅርታ ጠየቀኝ። ያኔ ነው ይቅርታውን ልቀበል ብችልም አብሬው ልኖር የማልችልበት ምክንያቶች እንዳሉኝ የተናገርኩት። "ምንድነው እሱ ሰናይት? ንገሪን እንስማው" አለችኝ የዐምባ ልጅ የሆነች ጓደኛችን። እንዲያ ስትለኝም ፊቴን ወደ ቤቢ አዙሬ "ቤቢ አብዝተህ እንደበደልከኝ ታውቃለህ?" ስል ጠየቅኩት። ምንም መልስ ሳይሰጠኝ ዝም አለ። "ለመሆኑ እኔ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣሁ ቤትህ ውስጥ ያገኘሁት ጥቅም ላይ የዋለ ኮንዶም ከየት መጣ? እ? እኔ ፈጥሬ ነው የማወራው እንዳይባል እንኳ ለአባ ሚካኤል ጠርቼ አሳይቻቸዋለሁ።"

"እንዴ? እኔና እሷን እኮ ለማለያየት ሬት ለፊት ሊያስቀምጡትም ይችላሉ።" አለ ቤቢ ወደ ሽምጋዮቹ ዞሮ።

"እሺ ይሁንልህ። እህቶችህም ሆኑ ማንም ያስቀመጠው እኛን ለማጣላት ነው ብለህ ማሰብ ትችላለህ። ዋናው ነገር እኔ ትዳራችን እንዲቀጥል

የማልፈልግ መሆኑ ነው:: ከፈለግክ አሁኑኑ የጋብቻችንን ካርድ ልቀድልህ ዝግጁ ነኝ:: የታለ ለመሆኑ?" ስል ጠየቅኩት::

"አለ እኔጋ" ሲል እርግጠኛ ሆኖ መለሰልኝ::

"እሺ አምጣ... ይኸው ጓደኞቻችንና ሚዜዎቻችን በተሰበሰቡበት ልቅደድልህ" ስለው "ቤት ነው ያለው" አለኝ እርግጠኝነት በጎደለው ስሜት ራሱን ወደ መሬት በመድፋት::

"እርግጠኛ ነህ?" ንግግራችን የጣማቸው አይመስሉም- ሽምጋዮቹ::

"ምን የሚሉት ድርቅና ነው?" ጮኸ::

"በእኔ ወጪ እንሂድና የጋብቻ ካርዳችንን ታሳየኛለህ?"

"ምን ጥያቄ አለው? ማለቴ... ይሄን ያህል..."

"ቤት የት ነው ያስቀመጥከው?"

"ሳጥን ውስጥ"

"እርግጠኛ ነህ?"

"እንዴ?" ስለቸኸኝ አይነት ይመስላል አነጋገሩ:: ሽማግሌዎቹም በጣም ተበሳጩ::

"እሺ ይሄ ከየት መጣ?" ከቦርሳዬ ውስጥ አውጥቼ የጋብቻ ካርዳችንን አሳየሁት::

"እ?"

"ከየት መጣ?" ጠየቅኩት::

"ከየት አመጣሽው?" ማረጋገጫ ፈልጎ ጠየቀኝ::

"ልንገርህ አይደል?!" ሁሉም የዚህን ምስጢር ማወቅ የፈለጉ መሰለኝ:: "ይሄን ካርድ ለፌሩዝ ለምን ሰጠሃት? ያገኘሁት እሷ ጋ ነው" ደነገጠ::

"ልታየው ወስዳው ይሆናላ" አለኝ:: ጥፋቱን ለማመን ቢያንስ እንኳን ወኔ ያለው አልሆነም:: *ሰኒ እንዴት ነው እዚህ ጋ ተከራክረሽ ማሳመን የምትችይው?*

"ልታየው ከሆነ ደብተሯ ውስጥ እንዴት ይገኛል? እሷ ልጅ ምንህ ናት? ምን ጥልቅ አድርጓትስ የኔና ያንተን የጋብቻ ሰርተፍኬት ታያለች? ንገረኛ... ንገረኝ! የድሮ ጓደኛህ እንደሆነች ሰምቼ ችዬሀለሁ... ስጠይቅህም ክደህኛል:: ለእህቶችህ እያጎበደድክ ትዳሬን ሲኦል አድርገኸዋል... ህመሜ ግድ ሳይሰጥህ እኩለ ሌሊት እየገባህ.... አባ ሚካኤል ቤት ተከራይና ውጣ ቢሉህ ንብረቴን ጥዬ አልወጣም ስትል..." መናገር ያለብኝን ሁሉ ተናገርኩ:: ሽማግሌዎቹ ቃሌን ከሰሙ በኋላ "በቃ ያለፈው አልፏል ይቅር ተባባሉ" አሉን:: *ይሄ ያለፈው አልፏል የሚሉት ነገር ግን ምንድነው? እንዴት ያልፋል?* ትናንትና የዛሬና ሲልም የነገ መሠረት መሆኑ ልብ

የማይባለው ለምንድነው? እንዴት ያለፈው አልፏል ብዬ ዛሬና ነገ እንደማይደገመው እርግጠኛ መሆን እችላለሁ? ሰው ለውጥ ከሌለው ጊዜያቶቹስ ምን ለውጥ ይኖራቸዋል? ዛሬ ትናንት ሆኖ ያለፈው አልፏል መባሉ እንደሆነ አይቀር "ይቅርታ አድርጊልኝ" አለ ብርድ ከገደለኝ በኋላ እለብሰው ዘንድ ይዞልኝ የመጣውን ብርድ ልብስ እየሰጠኝ::

"አመሰግናለሁ" ስል ፈገግ አልኩ- የፌዝ ፈገግታ:: "ምንድነው ይሄ? እንዳይበርደኝ አስበህልኝ ነው? ልክ ነህ ትናንትና አንተ ቤት እያለሁ ይበርደኝ ነበር:: እርግጥ ዛሬም ይበርደኛል:: ይሁንና ግን ነፃነት አሙቆኛል:: አንተ ቤት አንድ እንጀራ በልቼ አልጋ ላይ እተኛ ነበር:: ዛሬ ግን ባዶ ሆዴን መሬት ላይ እተኛለሁ:: በጣም ነፃነት ያለኝ ዛሬ ነው:: ደስ ብሎኝ ነው የምኖረው... ቤትህ ውስጥ ሆኜ ግን ላብድ ደርሼ ነበር:: ይቺ ልጅ ያማታል ቤት ተከራይና ከቤተሰብ ነጥላት ስትባል ንብረቱ በልጦብህ አፍህን ሞልተህ የንብረትህ ያህል ተራ እቃ እንኳ ክብር እንደሌለኝ ነግረኸኛል:: ያው የተስገበገብክበትን ንብረትም ምህረት ለምትባለው... ካንተ ጋር አራት ወር ያህል ለቆየች ሴት ሰጥተሀታል... አየህ ቤቢ..." ውስጤ ሀይል እየተቀጣጠለ ሲሄድና ምላሴ በደንብ ሲሾል ይታወቀኛል::

"...አየህ ቤቢ... ትዳርህን ያፈረስከው አንተ እንጂ እኔ አይደለሁም:: ከሴት ጋር የተኛኸው አንተ እንጂ እኔ ወንድ ጋር ደርሼ አላውቅም:: ልታምን ባትችልም ከምህረት ጋር ስለመተኛትህ ማስረጃው አለኝ:: እንዴ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም:: እኔን በይቅርታ አለሳልሰህ ዳግመኛ

ልትጎዳኝ አትዘጋጅ:: ቤቢ! አንተ ለሀብት ንብረትህ እንደሳሳኸው እኔም ሰርቼ ሐብት ንብረት ማፍራት እፈልጋለሁ:: አታደናቅፈኝ... ወደኋላ እየጎተትክ የመኖር ትልሜን አታበላሸው:: ይቅርታህ ይጎትተኛል እንጂ ምንም አይጠቅመኝም:: ቆሎም ነገድኩ፣ መቃብርም ቆፈርኩ ወይ ስጋዬን ሸጥኩ ብቻ መኖር... ሕይወቴን መለወጥ እፈልጋለሁ:: ሁሌም ወፍ ዘራሽ... ዘረ ቢስ ሆኜ መቅረት አልፈልግም:: ዘረ-ቢስ ብለኸኛል:: እከካም ሸርሙጣና መቼም የማያልፍልኝ መሆኔን ነግረኸኛል:: ስለዚህ ይቅርታ አላደርግልህም:: ባደርግልህ ግን ያልከኝን እረሳውና ብኩን ሆኜ እቀራለሁ:: ስለዚህ ይቅር አልልህም::" አልኩት::

ሁሉም እኔን ጥፋተኛ አድርገው ቢንጫጩም ግድ አልነበረኝም:: ቁስሌን ማን ታመመልኝና? ቤቢ ደጋግሞ የራሱን መከላከያ ነጥብ እያቀረበ ይቅር አለማለት የበደሎች ሁሉ በደል መሆኑን በማንሣት ነተረከኝ:: *ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ* እንደሚባለው በውሣኔዬ ፀናሁ:: *ትዳር የገሀነም ስሳት ነው!* ይዞት ከመጣው ሲዲ ውስጥ የታምራትን ዘፈን ከፍቶ አሰማኝ:: ዘፈኑን እየሰማሁት አለቀስኩ:: ዘፈኑ የፈጠረብኝ ትዝታ ኖሮ ሳይሆን እንዳው ሆዴን ባር ባር የሚያስብል ስሜት አስለቀሰኝ::

*የማደ ስንቄን ጣልኩት የሰፋፋን*

*ስርሜን ስያየሁ ስድፍ ስድፋን*

ለቅሶዬን ሲመለከት የመጨረሻ ርህራሄ ላይ የደረስኩ መሰለው:: እናም



Scanned by CamScanner

"ይቅርታ አደረግሽልኝ ማለት ነው? ቂምሽን ረሳሽ ማለት ነው?" አለ ተጠግቶ እጄን በመያዝ:: ትኩር ብዬ ህፀፅ የመፈለግ ያህል አየሁት:: አይኖቹ ውስጥ ያነበባቸው ነገሮች ፍርሀት ለቀውበት አቀረቀረ::

"ቂም ያለበቀል ሐይል ነው" አልኩት:: "ለእኔ ቂም ትዝታ ነው:: የመስራት ኃይልን የሚፈጥር:: እናም ይቅር ያለማለት ብለህ አስበው እንጂ ቂም ብለህ አትጥራው::"

"እንዴ? ምን ሆነሽ ነው ሰኒ እንዲህ ነገር የምታከርሪው?" አለኝ ከሚዜዎቹ አንዱ::

"ማንም የኔን ቁስል አያውቅም:: አሁንም ታርቄ እንደገና ራሴን ችግር ውስጥ መጣል... እዚህ ሆኜ ልሰራ የምፈልገውን ትቼ ዘላለሜን በስቃይ መኖር አልፈልግም::"

"እና ተለያይቼ ልኑር ነው የምትይው?" ወንድይፍራው የሚባል የዐምባ ልጅ::

"አዎ"

"እኔ ሚስቴ ብትሆኚ ሐሣብሽን አልቀበለውም:: የኔ ሚስት በቃ እኔ ካልፈቀድኩላት በቀር አጠገቤ እንድትቀመጥ ብቻ ነው የምፈልገው:: እዚህ ሌላ ስራ እየሰራሽ ትዳር ሌላ ቦታ ይሁን የምትይ ከሆነ መለያየታችሁን ነው የምመርጠው::" አለኝ::



Scanned by CamScanner

"እግዜር ያክብርህ::" ብዬ ጥያቸው ወጣሁ::

ቤቴን ለማየትና በሚመቻቸው ጊዜ ሊጠይቁኝ እንደሚፈልጉ ቢነግሩኝም ፈቃደኛ አልሆንኩም:: ቤቱን ጥዬ ስወጣ ምንም እንኳን የጋብቻ ወረቀታችን ባይቀደድም በአለም ላይ ካሉ አስጨናቂ እስሮች አንደኛ ደረጃ ከተሰጠው ጥፍነጋ ነፃ የወጣሁ ያህል ተሰምቶኝ ዘና ብዬ ወደቤቴ አመራሁ::

*ስንኳን ደስ ያለሽ ሰኒ!*

ቤት ስገባ ጓደኞቼ ቁልፍ ስለነበራቸው ገብተው ቤቱን ሞቅ፣ ሞቅ አድርገውት ጫት እየቃሙ አገኘኋቸው:: በፈገግታ ተሞልቼ ሰላም ብያቸው ቁጭ እንዳልኩ የቤቱ በር ተንኳኳ:: መጀመሪያ ላይ ቀስ ያለ ቁርቁራ ነበር:: እርግጠኛ ለመሆን ፀጥ ባልንበት ሁኔታ ውስጥ በሐይል ተንኳኳ:: ልክ ነው በር ተንኳኩቷል ማለት ነው ብዬ ልነሳ ስል ገርበብ ያለው በር ተከፈተ:: ሙሉ በሙሉ ሳልቆም መብረቅ የመታኝ ያህል ደንግጬ በአየር ላይ ቀረሁ::

ቤቢ ነው::

ጨርሶም እንደሚከተለኝ አልጠረጠርኩም::

መምጣቱ ምናለ ባላስደነቀኝ?

ሲገባ ጓደኞቼ ተሰብስበው ተቀምጠው እንደሚቅሙ ተመለከተና ፊቱን

ቋጥሮ ሰላም አላቸው:: ሁሉም ታሪኩን ያውቁ ስለነበር "ቤቢ ይባላል" ስላቸው በቀላሉ ለዩትና በደንብ ሰላም አሉት:: አልጋው ጫፍ ፍራሽ ላይ ተቀመጠ:: የሞት ሞቴን ከድንጋጤዬ ለማገገም እየሞከርኩ "ተጫወት" አልኩት:: "አልጫወትም:: ሸኚኝ" አለኝ:: ተነስቶ ሲወጣ ልከተለው ፈራሁ:: ቤት ውስጥ ያሉት ሁሉ "አይዞሽ ሸኚው... ምን ችግር አለው?" አሉኝ ስፈራ ስቸር ተከተልኩት:: *ምን ሊያደርግ ተከተሉኝ መጣ?* ስወጣ ቤቴ አጠገብ ያለ አንድ ጋራዥ አለ እዛ አጠገብ ያለ ውሃ ልክ ላይ ቆሞ ጠበቀኝ:: ስደርስ አሁንም ይቅርታ እንዳደርግለት ጠይቆኝ አለቀሰ:: እንቢታዬ ሲፀናበት ግን ያደረገው በቁሜ ሽንቴን ሊያስለቅቀኝ ምንም አልቀረውም ነበር::

ሽጉጥ!

ሽጉጥ ደገነብኝ::

# -32-

ትዳር ለእኔ ጥሩ መሆኑን አጥቼው አይደለም:: ስገባበትም የተደሰትኩት ሕይወቴ ጥሩ ቅርፅ እንደሚይዝ ፅኑ እምነት ስለነበረኝ ነው:: ያ ግን አልሆነም:: የእኔ ጥፋት ይሁን ወይ የቤቢ አለበለዛም የሁለታችን ተዋፅኦ የፈጠረው ብቻ ለይቼ ላስቀምጠው ቢቸግረኝም እኔጋ ካለው ድክመት በላይ የሌላውን ለማየት ነው የቻልኩት:: ሕይወት ደግሞ ውስጣችንን ገልፃ ከምታስነብበን ይልቅ ሌሎች ሰዎች ውስጣቸው ሞልቶ የተረፈውንና በግብር የሚገለጡበትን እንድንመለከት ነው የምትጋብዘን:: ኢየሱስ እንዳለው *የቤቷውን ጉድፍ ለማየት ስሁቶች ነን::* እንዳው በነገሩ ላይ ሚዛናዊ ለመሆን ያህል አልኩት እንጂ ለትዳራችን መፍረስ ግንባር ቀድም ተጠያቂዋ እኔ አይደለሁም:: ስለዚህም ሌላው ወገን ያጠፋውን ማወቁ ጥሩ ቢሆንም እንኳን የበለጠ ጥሩ የሚሆነው ዳግመኛ ላያጠፋ የሚችል መሆኑን ማወቁ ላይ ነው:: ቤቢ ደግሞ የሚያውቅ እንጂ የሚለወጥ አለመሆኑን አውቂያለሁ::

ያም ሆኖ ነው እንዳለሁ ተቀበይኝ በሚል መንፈስ ሽጉጥ የደገነብኝ::

"እባክህ ቤቢ... እሱን ነገር ዞር አድርገው?" ሸሸሁት::

"አላደርገውም" እየተከተለኝ መጣ "ለምን እንደማላደርገው ታውቂያለሽ? ይቅርታ የማይገባሽ ደደብ ስለሆንሽ ነው" ጥርሶቹ በእልህ ሲፋጩ እሳት የሚፈጥሩ መሰሉ::

"እ...ና... ልትገለኝ ነው?"

"አልገልሽም:: አንቺን መግደል የሚያስችል ጭካኔ የለኝም:: እዚህ ከተሰበሰቡ ቅምጦችሽ አንዱን በርሽ ላይ ደፍቼ ዘላለምሽን ስትማቅቂያት ትኖሪያለሽ:: ከፈለግሽ አሁኑኑ አሳይሻለሁ" ብሎ እየተወናጨፈ ሲሄድ ሮጬ ያዝኩት::

"ቤቢ... አንተ'ኮ ፀባይህን ብታሳምር ይቅርታ ባደርግልህ ደስ ባለኝ::"

"ምን ልሁን እሺ? ንገሪኝ!"

"በቃ ተረጋጋ እግዜር እህል ውሀችን አላለቀም ካለ የት ይቀራል ብለህ ነው? በቃ ና ልሸኝህ..." ውስጤ ያለው ድንጋጤ እያንዘረዘረኝ ነበር:: ምንም እንኳን እኔን ሲገልበት ያወጣው ባይሆንም ለሴት ልጅ እንዲያ ሽጉጥ ማሳየት ራሱ ምን ያህል ውስጧን ሊረብሽው እንደሚችል የተገነዘብኩት ያን ዕለት ነው:: እንደምንም እየተነታረክን አብነት ደረስን::

"እባክሽ ሰኒ ከኔ አትለይ:: እባክሽ ከልብሽ ይቅርታ አድርጊልኝ" ለቅሶ ጀመረ::

"ደጋግመህ በድለህኛል'ኮ ቤቢ..."

"እናታቸውን... እነዚያ ጫት ቃሚ ሸርሙጦች ናቸው አይደል የልብ ልብ የሰጡሽ?"

"ስርዓት ያዝ"

"እባክሽ በቃ ለመጨረሻ ጊዜ ይቅር በይኝ..." ምን እንዳጀገነኝ ባላውቅም መሀል አብነት ላይ ተገትሮ እያለቀሰ ልመናውን በሚያዥጎደጉድበት ቅፅበት ጥዬው ሄድኩ::

***

ወዲያው ለጓደኞቼ "እሷማ ጫት ቃሚ፣ ሲጋራ አጫሽ ሆና የለ እንዴ?" በማለት ነግሯቸው እንደተበላሸሁ ቆጠረውኝ ቁጭ አሉ:: እኔ ግን ሲጋራ ባጨስ፣ ጫት ብቅም፣ ብሸረሙጥ፣ ሰው እያረድኩ ብበላ፣ ሕይወቴን ብገፋ... ጨርሶም የማንም ሰው ጉዳይ እንዳልሆነ ነገርኳቸው:: ነገሮች ግን እንዲህ እንደዘበት ባሉበት አልቆሙም:: ሽጉጡን ደጋግሜ እንዳየው ከማድረጉም በላይ ዛቻው እየጠነከረ ቁም ስቅሌን አሳየኝ:: አልፎ ተርፎም የሽማግሌዎች መንጋጋት እረፍት እየነሣኝ፣ የእኔም ልብ እየተሸረሸረ ሄደ::

የሰው ሕይወት እንዲጠፋም ሆነ ሌላ መዘዝ ውስጥ ገብቼ መከራ ስመዝ መኖረን አልፈለኩትምና... ሽጉጥ እየተደገነ በየዕለቱ የሚቀርብብኝ ዛቻና ማስፈራሪያ መንፈሴን ረበሸውና... ደጋግመው የተላኩት ሽማግሌዎች በእኔ ላይ ፈረዱና አንድ ግዴታ ሊቀበል ተስማምቶ



Scanned by CamScanner

በመከራ ታረቅን::

ግጼታውም የሙዚቃ ፍላጎቴን ከግብ ለማድረስ እንድችል አዲስ አበባ ሆኜ እንድሰራና ይህንንም እስካሳካ ድረስ ሩቅ ለሩቅ ሆነንም ቢሆን ግንኙነታችን እንዲቀጥል ነበርና...

ስንደግና... ፍቅር ስንደግና... ተባለ::

# -33-

በፍቅር ታንኳ መቅዘፍ፣ በወሲብ ምች መመታት ጀመርን:: ጥቂት ጊዜ እርቁን ተቀብዬ አብሬው ልቃኝ አስቸግሮኝ ነበር:: የለመደ ገላ መናፈቁ፣ የተዳፈነ ፍቅር መቀስቀሱ አይቀርምና እንደገና ተንቧቸሁበት:: ኦሳ ሄደን ከተመረመርን በኋላ ነፃ መሆናችንን ስናውቅ ነው ወሲብ የጀመርነው::

"ቀስ በል ቤቢ!" አልኩት አንድ ቀን ፍቅር እየሰራን እያለ::

"ምነው?" እንቅስቃሴውን አቁሞ በግርምት አየኝ::

"ማህፀኔን እያመመኝ ነው:: ግፊት ሲኖር ደሞ ባሰብኝ" አቃሰትኩ::

"ታውቃለህ አይደል ጥንቃቄ ካላደረግኩ መውለድ የማልችልበት ደረጃ ላይ ልደርስ እንደምችል?"

"ተያቸው... ዶክተሮች መአተኞች ናቸው"

"ተው ቤቢ... እንዲህ አትበል::"

"ግን ስኒ... ለምን ጤነኛ ማህፀን እንዳለሽ አትሞክሪውም?"



Scanned by CamScanner

"ምን ማለት ነው እሱ?"

"ማህፀንሽ ፍሬ መቋጠር መቻሉን ቼክ እናድርግ:: ማለቴ የመውለዱ ፍላጎት ከሌለሽ ታስወርጂዋለሽ::"

"ሀጢያት ነው'ኮ" አመነታሁ::

"ስለሀጢያት ካወራንማ ማብቂያ ምዕራፍ የለንም:: ግድ የለሽም ሞክሪውና የሚሆነውን እንየው" ሳስበው ነገሩ ሊጥመኝ ባይችልም መውለድ መቻል አለመቻሌን የማወቅ ጉጉቱ ግን አየለብኝ::

"አይሆንም"

"ይሆናል"

"አይሆንም!"

"ስኒ ሙች ይሆናል:: ልጅ መውለድ መቻልሽን አወቅኩ ማለት ለዘላለም የፍቅር እስረኛሽ... ምርኮኛሽ ሆንኩ ማለት ነው:: እኔ'ኮ ለማወቅ እንጂ አሁን ይወለድ አላልኩ::" ዝምታ በመሀላችን ነገሰ::

"መውለድ አልፈልግም"

"ታስወርጂዋለሽ... ለሱ ደ'ሞ ከጎንሽ ነኝ"

"ትምላለህ?"



Scanned by CamScanner

ብዙም ትኩረት አልሰጠሁትም እንጂ ቤቢ ጋ እያለሁ ማህፀኔን ታምሜ ህክምና ስወስድ "ቁስሉ ሲድን ጠብቀሽ ግንኙነት ማድረግና ማርገዝ መቻል አለመቻልሽን ማረጋገጥ አለብሽ" ተብዬ ነበር:: ውሳኔዬን ጥበቃ አይን አይኔን እያየኝ ላለው ቤቢ:-

"እና ምን እየጠበቅክ ነው?" አልኩት::

ከአስራ አምስት ቀን በኋላ የስንደልና የጋዝ ሽታ እያስጠላኝ ራሴን መቆጣጠር አቃተኝ:: ትንሽ ቆይቶም የወር አበባዬ መቅረቱን አወቅኩ:: ለነገሩ ሦስትና አራት ወራት ያህል እየቆየ ይመጣ ስለነበር ብዙም አላሳሰበኝም:: ያለሁበትን ሁኔታ ለማወቅ አርሾ ሄጄ 3 ብር በመክፈል ስመረመር ማርገዜን ነገሩኝ:: ወዲያውም በደስታ ተውጬ "በቃ ማርገዜን ካረጋገጥኩ አሁኑኑ ማስወጣት አለብኝ" አልኩትና ሐሣቤን እንደሚቀበለው ነግሮኝ ጥቂት ቀናት ተቆጠሩ::

ሜሪ ስቶፕስ ሄጄ ለማስወጣት እንደምፈልግ ስነግራቸው መረመሩኝና ከባድ የሆነ የጨጓራ በሽታ እንዳለብኝና ደም የሚረጭ ሐሞቴም መስተካከል ስላለበት የተሻለ ሆስፒታል ብሄድ ጥሩ እንደሆነ ነገሩኝ:: በተለይ ሜሪ ስቶፕስ ያለማደንዘዣ በብረት ነው የሚያወጡት የሚል ሀሜት ስለሰማሁና ደርሶ ፍርሃቱም ስለነበረኝ በምክንያቱ ወደ ሌላ ቦታ እንድሄድ ሲመክሩኝ ደስ አለኝ:: ባልቻ ሆስፒታል ሄጄም አልትራ ሳውንድ ታየሁና ወር ከምናምን እንደሆነው ነገሩኝ:: ወዲያው ለቤቢ ደውዬ ቶሎ ማስወጣት እንዳለብኝ ስነግረው "ስንት ብር ጠየቁሽ?"



Scanned by CamScanner

አለኝ:: "አልጠየቅኳቸውም... ሲባል የሰማሁት ግን አምስት መቶ ብር ነው" ብዬ ነገርኩት:: "በቃ እልክልሻለሁ" አለኝ:: እጄ ላይ ሳንቲም ሳላልነበረ እንደላከልኝ በፍጥነት ማስወረድ እንዳለብኝ እያሰብኩ ጠበቅኩት::

*የውሃ ሽታ!*

ከዛሬ ነገ ይደውላል፣ ወይም ብሩን ልኮ ይደርሰኛል ብዬ ብጠብቅም ምንም የተፈጠረ ነገር አልነበረም:: ነገሩ ምንድነው? ሲብስብኝ እኔ ደወልኩለት:: በስልክ ለማግኘት ብቸገረም አንዴ ያገኘሁት እለት ምክንያቱን ማወቅ አጓጉቶኝ ነበር:: በስልኩ ላይ የተሰየመው ቤቢ እኔ መሆኔን ሲያውቅ ግን ስልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጋብኝ::

* * *

ቀኑ እየገፋ ሄደ:: የቤቢም ዝምታ እንዲሁ ገፋ:: ነገሩ ሁሉ ተፋፋመ:: የውሃ ሽታ!

*ምንድነው ምርጫዬ?* በምንም ተዐምር እንዲህ ያለው ቅሌት ይከሰታል ብዬ በእውኔም ይሁን በሕልሜ አልጠበቅኩትም:: እንዲያ እግሬ ላይ እየወደቀ ሲለምን የነበረው... እንዲያ እንደሴት ልጅ ተንሰቅስቆ ያለቀሰው... እንዲያ ያላንቺ መኖር አልቻልኩም ያለው... ራሱን ለማጥፋት እስከመድረስ... ሽማግሌዎች እስከማንጋጋት የበረታው ቤቢ እንዴት እንዲህ ያለውን የዓለም ቁጥር አንድ ሀጢያት ይቀዳጃል ብዬ ማሰብ እችላለሁ? *ለቤቱ ጌታ ሆዩ ወይ ለውቅበት ዘንድ ጥበብን ለሰበገስከኝ፣ ወይ*

*እነቃበተ ዘንድ ብስሐትን ለሳስተማርከኝ... እንደ እርግብ ሆኜ የዕባብ ብልህነት ሲጠፋኝ እንዴት ዝም ብለህ ታያለህ? ወደፊተና ለታገባኝ ማለት ምንድነው? ዝፈቀኝ... ድፈቀኝ... የስቃይ ሲሶል ውስጥ ዱለኝ ማለት ነው እንዴ? በስጋዩ ተቃጥዩ በነፍስም ለቃጠል ታዘጋጀኛለህ?* እግዚአብሔርን አምርሬ ብወቅሰውም ያዘጋጀው ተውኔት የተዋጣለት እንደሆነ በማመኑ ይመስለኛል ምላሽ አልነበረውም - እኔ የምፈልገው አይነት ምላሽ!

ዝምታው ሲያናድደኝና ምሬቱ ሲገነፍልብኝ ምሽቱን ተገን አድርጌ ጉዳዩን ሁሉ ልቋጨው በመወሰን ሱቅ ሄጄ በረኪና ገዛሁ- ጊዮን በረኪና:: *እንዲህ እንደራበኝማ ለልሞትም:: ለማን ለባቱ ይድባው ብዩ እየከፋኝ እሞታለሁ?* ብዬ ቆንጆ ምግብ ሰራሁና ራቴን ግጥም አድርጌ በላሁ:: ፍርሀቱ ይሁን ወይም ምግቡ ተስማምቶኝ አስር ጊዜ አገሳሁ:: ወዲያውም በረኪናውን ከፍቼ ብርጭቆ ላይ ስቀዳው እንደ ምርጥ መጠጥ አረፋ አወጣ:: *ውስኪ!*

ብርጭቆዬን አነሳሁና ወደሰማይ ከፍ አድርጌ "ቺርስ!" አልኩት እግዚአያብሄርን:: ውስኪ የመጠጣት ፍቅር ይኑረው አይኑረው አላውቅም:: "ቺርስ!" ያለኝ ያህል ጎንጨት አልኩት:: *ቆንጆ ውስኪ... ብሳክ ሲብሰ ወይም ዋይት ሆርስ ብቻ...* ውስኪ ሁለተኛ ጊዜ ወስጄ ተጎነጨሁ:: አጣጣምኩት::

"አንተ ቤቢ!"

"ወይ"

"ያውልህ ይድላህ... ተንፈላሰስበት"

"የት ልትሄጂ ነው?"

"ምን አገባህ? እኔና ያ-ዲቃላ ልጅህ የምንዝናናበት ቦታ አለ"

*ይህን ብሽቅ ሰበም ስመሰናበተ ብቸኛው መንገድ ይሄ ነው!*

"አንተ ውሻ! ያው ምድሩ ይስፋህ!" በድጋሚ ብርጭቆው ላይ የቀዳሁትን በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጌ ጠጣሁትና በእርካታ አጣጥሜው ሞትን በተስፋ እየተጠባበቅኩ ከትከት ብዬ ሳቅሁ::

*ሞት ሆዴ...ና እስቲ እቀፈኝ:: ድብን አድርገህ እቀፈኝና ወደሰማየ ሰማያት እንምጠቅ:: መሳዕክቶቹ እያሸበሸቡና እየዘመሩ ባይቀበሉንም ፍቅራችን ሙዚቃ ይሁንና ሰበምህ ውስጥ ሰዳክረኝ... እንደቤተሆቨን ሲምፎኒ ቁር እያሰክ ገብተህ አስደስተኝ:: በቃሽ የሰበም ነገር በቃሽ... የዚህች በሰባሳ ሰበም መከራ በቃሽ በሰኝ:: ና በሞቴ... ና ሆድዬ!*

ቀስ እያለ እንደመሞቅ... እንደማቃጠል አለኝ:: እየቆየ ሆዴ ተነፋ:: *ውስጤ ያለው ሽሰ እየሞተ ይሆናስ::* ወዲያው በአፍንጫዬና በአፌ አረፋ ይመጣ ጀመር:: *ሰኒ ስተሞቺ ነው:: ስረፋ መድፈቅ ከጀመርሽ ስተሞቺ ነው::* የተነፋ ሆዴ ተጣበቀና አንጀት እስኪርቀኝ ያለማቋረጥ አስመለሰኝ:: አረፋ መድፈቅ ማስመለስ:: ሆድና ጀርባዬ በተጣበቁበት ሁኔታ የሚወጣ ነገር ጠፍቶ የማስመለስ ስሜት ተከታትሎ እየመጣ ሲኦል መግባቴን ሲያሳውቀኝ ልቋቋመው እንኳን ተሳነኝ:: ድክም ሲለኝ አምስት ደቂቃ ያህል አሸልብና ተመልሼ እነቃለሁ:: ስነቃ ማስመለሱና አረፋ መድፈቁ ጠብቀው ለጉድ እያሰቃዩኝ ወደቀጣዩ ደረጃ አሸጋገሩኝ::



Scanned by CamScanner

ደም አስመልስ ጀመር::

ያም ሆኖ ሞት እንደናፈቅኩት መጥቶ አልወሰድ ሲለኝ *ኦ ጌታ ሆይ እባክህ ለለምንህ... የሰው ችግር ለይገባህም?* ስል በአፍና በአፍንጫዬ ደም ቡልቅ ቡልቅ እያለ ወጣ::

***

ከሰማኸኝ በለው ጋር የተዋወቅነው ኮፒ ራይት ቢሮ በሚመጣበት ወቅት ነው:: ቤተሰቦቼን እንደማላውቃቸውና የመጣሁበትን የህይወት ውጣ ውረድ ከነገርኩት በኋላ ከልቡ አዝኖ እንደቤተሰብ ስለሚያየኝ፣ ለቤት ኪራይና ለአንዳንድ ነገሮች ገንዘብ ስለሚረዳኝ በጣም እቀርበዋለሁ:: በእውነቱ ሰማኸኝ ለእኔ የደግ መጨረሻ የሆነ ሰው ነው:: ቤት ድረስ እየመጣ ይጠይቀኝ ስለነበር ካከራዩኝ ሰዎች ጋ የሌለኝን ቅርበት እንድፈጥር እንኳ ያደረገኝ እሱ ነው::

ከአከራዩኝ ሰዎች ጋር በደንብ በመቀራረቡ ምክንያት "ምንም ችግር ቢፈጠርባት ያለኋት ዘመድ እኔ ነኝና ደውላችሁ መንገር ያለባችሁ ለእኔ ነው" ብሎ ስልኩን የሰጣቸው ጊዜ "ለምን እንዲህ አልክ?" ስል ጠየቅኩት:: እዛ ግቢ ውስጥ ከሰው ጋር ለመቀራረብ ፍላጎቱ አልነበረኝም:: የዛሬ ሰው ገበና ካወቀ ነገ የከፋው እለት የሰው ቁስል መነካካት እንደሚወድ አውቃለሁ:: ስለዛም ልቀራረባቸው አልፈልግም ነበር:: "ምን ችግር አለው ብለሽ ነው ሰኒ... ያከራዩሽ ሰውዬ እንደሆነ ጥሩ ሰው ናቸው:: ትልቅ ሰው" አለኝ:: ከሳቸው ጋር አውርቶ ስለነበር:: ምንም እንኳን የደረሰብኝ ችግር ኖሮ ባይደውሉለትም ዘመዴ ሰማኸኝ በለው



Scanned by CamScanner

ነው እየተባለ ይወራ ነበር::

የጠጣሁት በረኪና ስቃዬን እያበዛው ከሞት አፋፍ እየመለሰ አይነጋ የለ ነጋልኝ:: ሳልሞት ስማይና ምድር መላቀቃቸው አበሳጨኝ:: መንቀሳቀስ በማልችልበት ሁኔታ ብሆንም ቤቱ በትውከት፣ ደምና አረፋ ተጨመላልቆ ስለነበር እንደምንም በጨርቅ ወለወልኩትና እንቅልፍ ሲወስደኝ በዛው ሞት ጥርግ አድርጎ ቢወስደኝ ተመኝቼ አይኖቼን በመጨፈን ጋደም እንዳልኩ ያከራዩኝ ቤት ስልክ ተደወለና "ሰናይት... ስልክ" ሲሉ ጮኸው ተጣሩ:: "ማነው?" ለማለት እንኳ አቅም አጥሮኝ ነበር:: ጥሪያቸው እንዳልተሰማኝ ገምተው በሬን ሲያንኳኩ ግን "ማነው የደወለው?" አልኳቸው:: "ሰማኸኝ ነው" ሲሉኝ ላቀርብ የምችለው አንዳችም ምክንያት ስላልነበር "አሟት ተኝታለች በሉት" አልኩ::

ስልኩ መዘጋቱን እንዳወቅኩ የሚተፈትፈኝ ወገቤን በልብስ ጥፍንግ አድርጌ አስሬው ለማሸለብ ስታገል በሬ ተንኳኳና ገፋ ተደርጎ ተከፈተ:: ያስመለሰኝን ለመድፋት በሩን እንደከፈትኩት መልሼ ያለመቀርቀሬ ታወሰኝ:: "ምን ሆነሽ ነው አንቺ?" ሲል ሰማኸኝ ሊተርበኝ በተዘጋጀ መንፈስ ወደ ቤት ዘለቀ::

ሰማኸኝ ግጥሞቼን ይመለከት፣ ነጠላ ዜማ ለማዘጋጀት ስፍጨረጭር ያይና ዜማ ሳወጣም ይሰማ ስለነበር ሁሌ በርትቼ ውጤታማ እንድሆን አጥብቆ ይመክረኛል "ወደፊት መድረክ ላይ ስትወጪ አንድ ሺ እናቶች ይሰለፋሉ... እኛ ነን እናቶቿ ይላሉ" እያለ ያስቀኝ ነበር:: እንደምንም ተነስቼ ሰላም ልለው ስሞክር ወገቤ አልችል ብሎ ሽብረክ ብዬ ስወድቅ

"ወይኔ እህቴን!" ሲል ጮኸ:: ወዲያውም የወሳንሳ ተሸክሞ ወደ መኪናው አስገባና ባልቻ ይዞኝ ሄደ:: እዛ ስመረመርም ጨጓራዋን ኦኘ ራሲዮን መሆን አለባት አሉ:: "ሰው ሳላማክር አልሆንም" ብዬ እንቢ አልኩ:: ያም ሆኖ ግን ትተኛ ተብሎ አልጋ ተያዘለኝ:: ብር ሰጥቶኝም "ላንቺ የሚያስፈልግሽ ነገር ካለ ተጠቀሚበት... እኔ ዱባይ ስለምሄድ ህክምናውን ወስደሽ ስትጨርሺ ውጪ ካሉሽም ትወጫለሽ... የሆስፒታሉን ወጪ ስለከፈልኩልሽ አታስቢ" አለኝ::

ባልቻ ተኝቼ ህክምና ቢደረግልኝም የእኔ ችግር ሌላ ስለነበር ውስጤ መረጋጋት አልቻለም:: በቀን አንድ ለስላሳ እንኳ መጠጣት አልችልም ነበር:: አንዲት ራሽያዊት ዶክተር በአስተርጓሚ እያወራች ስለችግሬ ብትጠይቀኝም ባለሁበት ሁኔታ ለማስወገድ የምችለው ስላልመሰለኝ ዝም ብዬ ቆየሁ:: ዐምባ ስራ በተቀጠርኩበት ወቅት የነበረ አንድ ጓደኛዬ አዲስ አበባ መጥቶ ደጋግሞ ቤት ቢደውልም ሊያገኘኝ አልቻለም ነበር:: ትንሽ ሻል ሲለኝ ግን በህዝብ ስልክ ደወልኩለት:: "አንቺ የት ሆነሽ ነው?" አለኝ:: ባልቻ ሆስፒታል እንደተኛሁ ስነግረው መጥቶ አየኝ:: እልም ብዬ መክሳቴን ሲመለከት አለቀሰ:: "ምን ሆነሽ ነው... አሁንም ጭንቀት ነው ያመመሽ?" አለኝ:: በሽታዬ ጭንቀት እንዳልሆነና ያለብኝን ችግር ሁሉ ዘርዝሬ ስነግረው "አያርምሽም መቼም በእጅ አዙር ሲገድልሽ ዝም አልሽው?" ብሎ ጮኸብኝ:: ከዚያም "ምን አሉሽ ታዲያ?" ሲለኝ ደግሜ እንዳልታየሁ ስነግረው "አሁኑኑ መታየት አለብሽ!" አለኝ::

በድጋሚ ስመረመር ጨጓራዬን በጣም ስለታመምኩ፣ ኩላሊትም ስላለብኝ



Scanned by CamScanner

ማስወረድ የምችለው ወይ በመድሀኒት በመታገዝ አልያም ደሜን እንዲረጋ ለማድረግ ከባድ መርፌ በመወጋት ብቻ መሆኑ ተነገረኝ:: መድሀኒት መውሰዱ ከጨጓራ በሽታዬ ጋር የማይሞከር ስለሆነ መርፌውን ተጠቅሜ ለማስወረድ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ብር መክፈል እንዳለብኝ ተነገረኝ:: ይሄንኑ ነገርኩትና "እንዳረጉ ያድርጉኝ እንጂ ሜሪ ስቶኝስ ሄጄ እገላገላለሁ" ስለው "ለምን በራስሽ ላይ አደጋ ትጋብዣለሽ?" ብሎ "እስቲ እፈልጋለሁ" አለኝና አርብ ተመርምሬ ውጤቱን በነገርኩት ሰኞ ጠዋት ብሩን አምጥቶ ሰጠኝ:: ገንዘቡን እየተቀበልኩት ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ::

***

ማደንዘዣ ክፍል ገብቼ መርፌ ተወጋሁና ነገር አለሙን ረሳሁት:: ህክምና እየተደረገልኝ እያለ ሰመመን ውስጥ ገባሁ:: ዶክተሯ ማደንዘዣው እየሰራ መሆኑን ስታውቅ የማስወረድ ሂደቱን ማቀላጠፍ ጀመረች

"እዎ አስወርዳለሁ... ማስወረድ አለብኝ" አልኩ በሰመመን ውስጥ

"እኔ'ኮ የማስወጣው እናቴ ወልዳ ስለጣለችኝ ነው"

"What is she talking about?" ዶክተሯ ግራ ተጋብታ ነርሷን ጠየቀቻት:: ነርሷም እየቀባጠርኩ ያለሁትን ተረጎመችላት::

"እናቴ ወልዳ ስለጣለችኝ እኮ ነው የማስወጣው" አልኩ:: ትንሽ ቆይቼም



Scanned by CamScanner

እየተወራጨሁ "እናቴን አሳዩኝ! እናቴ ወልዳ ጣለችኝ... እናቴን ፈልጉ" እያልኩ እንዳለቀስኩ ነገሩኝ:: እኔ ግን ነፍስ የዘራሁት በሁለተኛው ቀን አመሻሽ ላይ ነበር:: አስተርጓሚ ይዛ የምታናግረኝ ራሽያዊት በሰማችው ነገር በጣም ተደንቃ "ምን አይነት ታሪክ ነው የሰማሁት በጌታ?" ስትል እንደ እናት በተኛሁበት ሞዴስ እያደረገች ተንከባከበችኝ:: ከሆስፒታሉ ስወጣም አድራሻዋን ሰጥታኝ እንድጠይቃት አደራ አለችኝ::

ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ደም እየፈሰሰኝ ተቸገርኩ:: የዐምባ ልጆች ውስጥ ገረመው የሚባል አንድ ጓደኛዬ መታመሜን ሰምቶ "እንዴት ለእኔ አልነገርሽኝም?" ሲል ተቆጣኝና በደንብ እንዳገግም እሱ ቤት ይዞኝ ሄደ:: እዛም ደህና እየተንከባከቡኝ ሰውነቴ መለስ ሲልና መስተካከል ስጀምር በጤናዬ ጊዜ የሰራሁት ነጠላ ዜማ ተለቀቀ::

ያን ሰሞንም ቤቢ ገረመውን ይግባባው ስለነበር ሊጠይቀው ሲመጣ እኔንም አገኘኝ:: ሲያየኝ ገና ድንጋጤ ቀልቡን ቢገፈውም ከሱ በላይ የሆንኩት እኔ ነበርኩ:: ደርሶ ደሜ ፈላ:: የሆነ... ልገልፀው ያልቻልኩት አይነት መጥፎ ስሜት ወረረኝ:: ጣዕረሞት መሰለኝ:: ስላልሞትኩ ድጋሚ ሊገለኝ የመጣ ጣዕረሞት:: ሑሑ ብለሽ ጨኺ አለኝ - ውስጤ:: "ምን ልታደርግ መጣህ? ሬሳዬን ልታይ ነው?" አልኩት:: ገረመው ቤት ከመጣሁም በኋላ ገረመው ደጋግሞ እየደወለ "ታማለች እባክህ ብር ላክላት" ሲለው እሺ እልካለሁ እያለ ድምፁን አጥፍቶ ነበር:: ቤቢ ወደ ቤት ሲገባ ያየውም ገረመው ተበሳጭቶ ክፍሉን እየለቀቀ "ሰው ትመስለኝ ነበር:: ሰናይትን እኮ ይሄንን ልጅ ከካድሽው እግዚአብሄር ይክዳሽ ብያት ነበር" አለውና በሩጋ ሲደርስ በቤቢ በጣም ማዘኑን በሚገልፅ ሁኔታ



Scanned by CamScanner

ራሱን ነቅንቆበት ወጣ:: ገረመው ሲወጣ ብቻችንን ቀረን::

"ምን ልታደርግ ነው የመጣሽው?" አልኩት::

"አንቺን ብዬ አይደለም የመጣሁት... ምህረትን ብዬ ነው በዛው ገረመውን ማየት ፈለግኩ..." አለኝ አፍ አውጥቶ:: ምህረት አብራው ዲኤስቲቪ ያሳዩ የነበረችው ጓደኛው ናት:: መጥፎ ሰው መሆኑን ልኩን ስነግረው ተሰምቶት "እሺ ምን ላድርግልሽ?" አለኝ:: የቤቢን ዕዳ ምንም ያልበላው ነውና የከፈለው "ተበድሬ ነው ያስወጣሁት" አልኩት:: "እሺ በቃ አሁን ስላልያዝኩ የተወሰነ ብር ልስጥሽ" ብሎ ቦርሳውን ከፍቶ ከያዘው በርካታ መቶ፣ መቶ ብር አጠገብ ካሉት መዘዘና ሀያ ብር ሰጠኝ:: ራበኝ ብዬ ብለምን የማገኘውን ብር ሲሰጠኝ ደነገጥኩ:: ብገድለው ደስ ባለኝ:: የዘረጋልኝን ብር ተቀብዬ "ና!" ስል እጁን ይዤ ወደ አንድ ሱቅ ወሰድኩትና በሃያው ብር ጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ ገዝቼ "ይሄውልህ ይሄ ብር የሚጠቅመው ለዚህ ነው:: የቤት ኪራይ አይከፍል፣ እዳዬን አይሸፍን" ብዬ አሳየሁት አያይዤም:-

"ቤቢ... አይንህን ማየት አስጠልቶኛል" በማለት ዞር ብዬም ሳላየው ወደቤት ገባሁ::

* * *

*ስውነትና ንጋት ስያደር ስንዲህ ነው*

*ስደቅርታ መጣ ሚስጥሬን ባኸረው*

ራሱን ነቅንቆበት ወጣ:: ገረመው ሲወጣ ብቻችንን ቀረን::

"ምን ልታደርግ ነው የመጣኸው?" አልኩት::

"አንቺን ብዬ አይደለም የመጣሁት... ምህረትን ብዬ ነው በዛው ገረመውን ማየት ፈለግኩ..." አለኝ አፍ አውጥቶ:: ምህረት አብራው ዲኤስቲቪ ያሳዩ የነበረችው ጓደኛው ናት:: መጥፎ ሰው መሆኑን ልኩን ስነግረው ተሰምቶት "እሺ ምን ላድርግልሽ?" አለኝ:: የቤቢን ዕዳ ምንም ያልበላው ነውና የከፈለው "ተበድሬ ነው ያስወጣሁት" አልኩት:: "እሺ በቃ አሁን ስላልያዝኩ የተወሰነ ብር ልስጥሽ" ብሎ ቦርሳውን ከፍቶ ከያዘው በርካታ መቶ፣ መቶ ብር አጠገብ ካሉት መዘዘና ሀያ ብር ሰጠኝ:: ራበኝ ብዬ ብለምን የማገኘውን ብር ሲሰጠኝ ደነገጥኩ:: ብገድለው ደስ ባለኝ:: የዘረጋልኝን ብር ተቀብዬ "ና!" ስል እጁን ይዤ ወደ አንድ ሱቅ ወሰድኩትና በሃያው ብር ጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ ገዝቼ "ይሄውልህ ይሄ ብር የሚጠቅመው ለዚህ ነው:: የቤት ኪራይ አይከፍል፣ እዳዬን አይሸፍን" ብዬ አሳየሁት አያይዤም:-

"ቤቢ... አይንህን ማየት አስጠልቶኛል" በማለት ዞር ብዬም ሳላየው ወደቤት ገባሁ::

* * *

*እውነትና ንጋት እያደር እንዲህ ነው*

*ለይቅርታ መጣ ሚስጥሬን ሳኮረው*

የሚል ግጥም ጨምሬበት ነጠላ ዜማውን በደንብ አሻሻልኩትና በድጋሚ ተለቀቀ:: ወዲያውም ሀያ ሁለት አካባቢ ያለች ሰርካለም የምትባል ልጅ ቴኒስ ማጫወቻ ቤት ተቀጥራ ስለነበር የቀጠራት ሰው ለረዥም ጊዜ ክፍለ ሀገር ሲሄድ ብቻዋን እያደረች መጠበቅ ስለፈራች እኔ እንዳስተዳድራት ነይ አለችኝና ሻንጣዬን ይዤ እሷ ጋ ሄድኩኝ:: እዛ እንደገባሁም አብነት ተከራይቼው የነበረው ቤት ውስጥ ያለኝ ዕቃ መዘረፉን ሰማሁ:: ለማልከፍልበት ቤት እቃው እንዴትስ ሆኖ ቢጠፋ የምጠይቅበት ምን አፍ አለኝ?

ድንገትም ክፍለ ሀገር የሄደው ሰውዬ በመምጣቱ በጊዜ ማረፊያዬን መፈለግ ነበረብኝ:: ስራ ፍለጋ ብባዝንም ማግኘት ተሳነኝ:: ክፍለ ሀገር የሄደው ሰውዬ ሲመጣም ሰርካለም ስራውን ለቃ በመሄዷ ማረፊያ ቦታ ማግኘት ግዴታዬ ስለነበር ቤት ቢፈለግ ጠፋና ለጊዜው በሚል በሁለት መቶ ብር የተገኘ ቤት ውስጥ አረፍኩ:: ያለችኝን መቶ ብር ቀድሜ ሰጠኋቸውና ሰው አስቸግሬ ቀሪውን ጨመርኩላቸው::

ኑሮዬ ተበላሸ:: ለነገሩ ድሮውንስ መች ደህና ሆኖ ያውቃልና?! ለካ የአንድ ነገር መበላሸት የሚለካው ደህናውን ማጣጣም ሲቻል ነውና:: ከድጡ ወደማጡ... እየባሰበት ሄደ ብል ይሻላል:: የምበላው ተቸገርኩ:: እንደለመድኩት ሳገኝ ስኳር በውሃ እየበጠበጥኩ ሽሮ እንደበሶ እያደረግኩ የቻልኩትን ያህል ተፍጨረጨርኩ:: ከቤት ስወጣ ግን በተቻለኝ መጠን ያለኝን ትንሽ ልብስ በደንብ እየለበስኩ ለሰው ግምት ከአዕምሮ በላይ ነበር የሆንኩት::

ሰው ስቃይ ለመጨመር ትንሽ ነዋ የሚበቃው::

አብነት ተከራይቼ እያለሁ ባለቤቱ ጋሽ ጫኔ አንድ ወቅት ላይ ስልክ ይፈልገኝና ሳይነግሩኝ ይቀራሉ:: ባለቤታቸው ጋብዘውኝ ቤታቸው እንደገባሁ "ምነው ጋሽ ጫኔ ስልክ ሲፈልገኝ ሳይነግሩኝ? አባቴ አይደሉም ወይ ካጠፋሁ..." ለባለቤትየው ሀሳቤን እንኳን ሳልጨርስ "አንቺ... ምንድነው ያልሽው? አባቴ... ጫኔ አባትሽ? ሂጂና አባትሽን ፈልጊ!" ሲሉ ጥንብ እርኩሴን አውጥተውታል:: ለዛ ነው ስወጣ በተቻለ መጠን ሚስጥሬን የሚሸፍን አለባበስ ለብሼ የምወጣው:: ያም ሆኖ ግን በዚህ ሁኔታዬ እንዴት አድርጌ መኖር እንደምችል የማውቀው ነገር አልነበረም::

እናም እግዚአብሔርን እንዲህ አልኩት:-

*እኔ በተፅዛዝህ እንድኖር የምትፈልግ ከሆነ የሀጢያት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ከእጠገቤ አርቅልኝ:: አለበለዚያ ግን በራሴ በምወስደው እርምጃ ታዝናለህ!*



Scanned by CamScanner

ራ

# ክፍል አራት

# ቡና ቤትና ከዚያም



Scanned by CamScanner

ቃ(

## -34-

አንድ ወር፣ ሁለት ወር ሰው እያስቸገርኩ የቤት ኪራይ ብከፍልም ሶስተኛውን ለመድገም ግን ወኔውም አልነበረኝ:: ርሀቡም ሊገለኝ ደረሰ:: መታመም ጀመርኩ:: ግቢው ውስጥ ለአይንም ስጠፋ አንዲት እዛው ግቢ የተከራየች ልጅ ቀርባ ስታጫውተኝ ትልቅ ሆቴል በአስተናጋጅነት እንደምትሰራ ነገረችኝ:: እየቆየ ችግሬ በጣም እየባሰ ሲሄድ ግን "ለማንም ትንፍሽ እንዳትይ" ብላ በአስተናጋጅነት እንደምትሰራ ያወራችልኝ ውሸት እንደሆነና ቡና ቤት ውስጥ እንደምትሰራ ነገረችኝ:: አስከትላም "እንዲህ እየተጨነቅሽ እያየሁ ዝም አልልሽም ብዬ ነው ሚስጥሬን የነገርኩሽ:: ምንም አማራጭ ከሌለሽ እኔ የምሰራው አይነት ስራ ጀምሪ" አለችኝ::

የፈራሁት ደረሰ::

ምርጫ ግን አልነበረኝም:: *ምን መሆን ስችባለሁ?* ምንም! ስለዛም እሺ ብያት ተነስቼ ሄድኩ:: ገና ሳልደርስ እግዚአብሔርን እኔ በትእዛዝህ እንድኖር የምትፈልግ ከሆነ የሀጢያት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ከአጠገቤ አርቅልኝ:: አሰበለዚያ ግን በራሴ በምወስደው እርምጃ ታዝናለህ ያልኩት ታወሰኝ::

ይኸው ወደሚያዝንበት ስራ አመራሁ::

***

ስሄድ ሽሮ መልክ ያለው ጂንስ ሱሪ፣ ሰማያዊ ፓክ አውት ከረኸርም ጥቁር ኮት ጋር በቡትስ ጫማ ነበር የለበስኩት:: ለስራው አዲስ ስለሆንኩ ብዙም አልተቀባባሁ:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ እየመከረችኝ ቦታውን ለማየት እንደጓጓሁ በተለምዶ ቺቺኒያ ተብሎ የሚጠራው ሰፈር ደረስን:: በሚገርም ሁኔታ ተመሳሳይ የሆኑ ከአስር በላይ የሚሆኑ ውስኪ ቤቶች ተደርድረዋል:: ቤቶቹ ወደሚገኙበት አስፓልት ተሻግረን ጓደኛዬ *ሶሲ ባር* የሚባለው ቤት እንደምትሰራ ነግራኝ እኔን *ሳራ ባር* ወስዳ ከሰዎቹ ጋር አስተዋወቀችኝ- ቀድማም ነግራቸው ነበርና::

ፈራሁ:: በጣም ተንቀጠቀጥኩ:: *ስጥብቁ ስሸሸው በነበረው ህይወት ውስጥ ስዘፈቅ ነው?*

"ልብስ መቀየርና መኳኳል ከፈለግሽ እዚህ ገብተሽ ተጠቀሚ" አሉኝ በኮምፖርሳቶ በተከለለ እጅግ አነስተኛ ጓዳ ውስጥ እያስገቡኝ:: ቤቷ ውስጥ የተሰበረ የፊት መስታወት ተሰቅሏል:: በመስታወቱ ራሴን አየሁና ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: ዛሬ በሽተኛ ሆኜ ነገ የምሞት መሰለኝ:: ለቅሶዬን ስጨርስ ቀና ብዬ በመስታወቱ በመመልከት አይኔን ጠራርጌ ወጣሁ:: ሄጄም ባለጌ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ:: ቡና ቤቱ ውስጥ የሚሰሩት ሴቶች ፈጣን ተግባቢዎች በመሆናቸው ወዲያው ከበቡኝና አንዷ እግሬን ተደገፋ... ሌላዋ ወንበር ላይ ተቀምጣ ብቻ ተሰበሰብን ወግ ቀጠለ:: ስለቢዝነሱ መቀነስ፣ የቤት ኪራይ ስለመቸገራቸው... ጓዳ ጎድጓዳቸውን

እንስተው ሲያወሩ ረዥም ጊዜ የማውቃቸው ያህል ተሰማኝ::

ሰዓቱ እየገፋ ስለመጣ ሁሉም እየተኳኳሉ የደረቡትን በማውለቅ ሰውነታቸውን በደንብ ወሲብ ቀስቃሽ እንዲሆን ገለጥለጥ አድርገው በር፣ በር ላይ ቆሙ:: እኔ ብቻ ያቺን ጥቁር ኮት እንደለበስኩ ጭብጥ አድርጌ ይገፔ ወንበሬ ላይ ተቀምጫለሁ:: *ምን ብዬ ተነስቼ እቆማለሁ?*

ፈዝዤ መቀመጤን ያየችው ጓደኛዬ "ሰኒ ተነሽና ዞር፣ ዞር በይ... እዚህ ቁጭ ብለሽማ ስራ አይመጣም" ብላ መደዳ ወዳሉ ቤቶች እያስገባች አስተዋወቀችኝ::

"አፍሪካዊ ትመስላለች"

"ኧረ ሶማሌያዊት ነው የምትመስለው..."

የተለያዩ አስተያየቶች ሰጡኝ:: ለጓደኛዬም "እዚህ ከምታስጀምሪያት ጥቁር ስለሆነች ፈረንጆች ይወዷታልና ሆቴል ውሰጃት" ሲሉ የመከሯትን ነገረችኝ:: "ትንሽ ሳንቲም እንያዝና እንሄዳለን" ስትል ተስፋ ሰጠችኝ:: ተመልሼ ወደ ሳራ ባር ስገባ እስካሁን ልብ ያላልኳቸው ስዕሎች ግድግዳው ላይ ተለጣጥፈዋል:: በየግድግዳዎቹ የተለጠፉት ስዕሎች በጣም ወሲብ ቀስቃሽ ናቸው:: ያልለመድኩትን ስዕል ቀና ብዬ ማየት ስላስፈራኝ በሙሉ አይኔ እንኳን አላየሁትም::

"ከላይ የደረብሽውን አውልቂው!" አለችኝ- የቤቱ ባለቤት:: አንድም ለእሷ ገበያ፣ በሌላም በኩል ወንዶች የተጋለጠ ገላ አይተው ስለሚገቡ



Scanned by CamScanner

ነበር- እንዲያ ማለቷ::

"ስላልለመድኩት ይበርደኛል" አልኳት:: በዚህ መሀል ከደንበኞቻቸው አንዱ የሆነው ግርማ የተባለ ሰው ገባ:: ሁሉም ሴቶች እያቀፉ ሰላም አሉት:: ጓደኛዬ ያለሁበትን ችግር ነግራቸው ስለነበር እየጎተጎቱ ግርማ እኔን እንዲወስደኝ አስጨነቁት:: ልመናቸውን ተቀበለና የሚጠጣ እንድወስድ ጋበዘኝ::

"ቢራ" አልኩ::

"ቀይሪ... ቢራ አይሆንም"

"ሌላ መጠጥ አልጠጣም"

"ነው? እሺ ነይ እንሂድ!"

ቀድሞ ሂሳብ መቀበል የስራው ባህርይ ቢሆንም እኔ ግን "አይከለክልሽም... ጥሩ ሰው ነው" ስለተባልኩ ሳልቀበለው ወደ መኪናው አመራሁ::

*ሰነ ጉድ ሲጀመር ነው!*

ግርማ በጣም የሰከረ ቢሆንም መኪናውን ያለ ስጋት ይነዳው ነበር:: በመንገድ ላይ ኮንዶም እንድንገዛ የሚጨቀጭቁ ጆብሎዎች ነበሩ:: "እንግዛ" ስለው "ምን ያደርጋል?" ሲለኝ ደነገጥኩ:: ስለሱ ጥሩነት ደጋግመው ስለነገሩኝ ያለ ኮንዶም እንፈፅም ካለ እንቢ እለዋለሁ ብዬ ተፅናናሁ:: አዋሬ አካባቢ ባለው አፓርታማ ግቢ ውስጥ ገባን:: እጁን

ወደኋላ ሰጥቶኝ እጄን ወደፊት አድርጌ ይዤው ላለመደናበር እየተጠነቀቅኩ ደረጃውን ወጣን:: መግቢያው ጋ ስንደርስ በረንዳው ላይ ቆሞ አትክልቱ ላይ ሽንቱን ሸና:: ከዚያም እየተንገዳገደ በሩን ከፍቶ መብራት ካበራ በኋላ እንድገባ ጋብዞኝ ወደ ውስጥ ዘለቅኩ::

*ጌታ ሆይ ድፍረተን ስጠኝ!!*

በስተቀኝ ያለውን ቦታ አስፍቶ ትቶልኝ ስለነበር ልብሴን አውልቄ አጠገቤ ያለ ወንበር ላይ አስቀመጥኩት:: መኝታ ክፍሉን ስቃኘው ትልቁ የልብስ ቁምሳጥን አንዱን ግድግዳ ሸፍኖ ይዞታል:: ሱሪዬን ማውለቅ ፈርቼ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አልኩ:: ዓይን፣ ዓይኔን ያየኝ ነበርና "አውልቂና ነይ!" አለኝ:: ሱሪዬን አውልቄ በማላውቀው አንሶላ ውስጥ ወደማላውቀው ገላ ገባሁ:: እጄን በአንገቴ አሳልፎ ሊያቅፈኝ ፈለገ:: የመጠጡ ጠረን ረበሸኝና ተንገፈገፍኩ:: ላለመታቀፍ መሞከሩ ትርጉም አልነበረውምና የግዴን ችዬ ታቀፍኩ:: አሻሸኝ:: እጄን ወደ ብልቴ ሲያስጠጋ ፈቃደኛ አልሆን አልኩት:: ሊስመኝ ታገለ:: ታግዬ ተነሳሁና አልጋው ላይ ቁጭ ብዬ አለቀስኩ::

"ምን ሆነሻል?"

"ኮንዶም አድርግና የምትፈልገውን አድርገህ እንተኛ"

"ገና ሳልነሳሳ? እንዴት ነው ነገሩ ስሜት የለሽም እንዴ?"

ቢያዝንልኝ ብዬ "እባክህ አታስጨንቀኝ... ቤት ኪራይ ተቸግሬ ነው...



Scanned by CamScanner

ለዚህ ቤት አዲስ ነኝ::" አልኩት::

"ወሬኛ!" አለና "ይህች ምክንያት እንኳ የሁሉም ናት" ብሎ አልጋው ላይ እርቃኑን ቆሞ ከቁም ሳጥኑ የላይኛው ተካፋች ውስጥ ኮንዶም አወጣ:: ደስ አለኝ:: ሁኔታው ሳየው እንዲያው ስለሚከፍለኝ ብቻ እንጂ እሱም ስሜት ያለው አልመሰለም:: እንደምንም ብሎ ኮንዶሙን አደረገና ከላይ እንድሆን አዘዘኝ::

"ከላይ አልሆንም እንደዚህ ነው የምሆነው" አልኩት ከስር እንደተኛሁ ከላዬ ላይ ሰፍሮ ይጋልብ ጀመር:: እሱ በስሜት ውስጥ ሆኖ ሲወራጭ እኔ ግን መጥፎ ስሜት መላ ሰውነቴን ረበሸው:: ከዛም የተነሳ አለቅስ፣ ፊቱን አንገቴ ስር ሲሸጉጥ እገፋውና ትንፋሹን ጠልቼ አፍንጫዬን በእጄ እሸፍን ጀመር:: ከብዙ ትግል በኋላ ጉዳዩን ተኩሶ ሲጨርስ ድብን ያለ እንቅልፍ ውስጥ ሲገባ እኔ ግን መተኛት አቅቶኝ አንሶላ ተጠቅልዬ አልጋው ላይ ቁጭ አልኩ::

ፈራሁ::

ከማላውቀው ሰው ጋር አንድ ቤት ውስጥ ነኝ:: ያውም በሱ ቤት:: *ለሁን ቢገድለኝስ? የሚፈልገውን ቢያደርግ ምን ከለካይ ይኖረዋል?* ሀሳቤ ራሱ አስፈራኝ:: ይሁንና ሰዓቱን አየት ሳደርግ ለአስራ ሁለት ሰዓት ምናምን ጉዳይ ሆኗል:: ተነስቼ መጋረጃውን ገለጥ ሳደርገው ሰማዩ ወገግ ማለት ጀምሯል:: ወዲያው ከዛ ቤት ለመውጣት ፈልጌ ነካክቼ ቀሰቀስኩትና "ልሄድ ስለሆነ ብር ስጠኝ" አልኩት::

"የት ነው የምትሄጂው?"

"አውቶቢስ ተራ ሰው ስለምሸኝ ቶሎ መሄድ አለብኝ" ስል የውሸት ምክንያት አቀረብኩ:: ሴቶቹ ሲሉ እንደሰማሁት ከሆነ በጠዋት ሰበብ ፈጥረው ካልወጡ ድጋሚ ወሲብ ስለሚጠየቁ እንደቆዳ ሲለፉ መዋል ነው::

ሲስተሜን ሳያውቀው የቀረ አልመሰለኝም:: "ካልደገምኩ ብሩን አልሰጥሽም" አለኝ:: *ወንዶች የምድር ብካዮች:: ስረመኔ!* እምቢ ብል ብሩን አይሰጠኝም:: ካልሰጠኝ ከየት አባቴ አምጥቼ የቤት ኪራይ እከፍላለሁ? እድሌን እያማረርኩ ቀስ ብዬ ቁጭ አልኩና ሱሪዬን አውልቄ የነበረበት ቦታ መለስኩት:: አንሶላው ውስጥ ሳልገባ ተንጋለልኩለት:: ኮንዶም አደረገና ላዬ ላይ ተሳፈረ:: በዛ ላይ የብልቱ ፅጉር በጣም ስላደገ እየፋቀ አሳመመኝ:: ስሜቱ እርካብ ላይ ተፈናጥጦ የመጨረሻው ጡዘት ላይ መድረስ አቃተው:: ቢል ቢታገል እንቢ አለው:: በታገለ ቁጥር እኔ እየተጎዳሁ እንደሞተ ሰው ምንም እንቅስቃሴ ሳላሳይ እንባዬን እያፈሰስኩ የእዮብን ትዕግስት በመለመን ቻልኩት::

ምንም ውጤት ላይ መድረስ ሲያቅተው እየተልጎመጎመ ከላዬ ላይ ተነስቶ አጠገቡ ያለች ኮመዲኖ ላይ ያስቀመጠውን ሱሪ አንስቶ መቶ ብር አውጥቶ ሰጠኝ:: ብሩን ተቀብዬ ከቤቱ ወጥቼ ታክሲ መጠበቅ የሞት ያህል አስፈራኝ:: ሰው ሁሉ የሚያውቀኝ መሰለኝ:: ቤት ስደርስ ጓደኛዬ ተጨንቃ ነበርና በሰላም መመለሴን አይታ በፈገግታ ተቀበለችኝ::

"ስንት ብር ሰጠሽ?" ጠየቀችኝ::

"መቶ ብር" ደነገጠች::

"ስኒ መቶ ብር እኮ ለሾርት እንጂ የአዳር ዋጋ አይደለም" ብላ አስረዳችኝ::

"በይ ደግሞ ማታ ስራ ቦታ ስንት ሰጠሽ ብለው ከጠየቁሽ ሁለት መቶ ብር ነው በይ" ስትል አስጠነቀቀችኝ:: ያለችኝን ብር ለቤት ኪራይ "እጨምርላችኋለሁ" ብዬ ሰጠሁና እጣ ፈንታዬ ውስጥ ጠልቄ ልሰጥም ከትናንቱ በተሻለ ለዛሬ ምሽት ራሴን ማዘጋጀት ጀመርኩ::

***

ለካ ወንጀል ወንጀል የሚመስለን ሩቅ ሆነን ስናየው ነው:: ህይወቱ ውስጥ ስንገባ ለጥቂት ጊዜ አዕምሯችን ውስጥ ካስቀመጥነው ህግም እንበለው ግብረ ገብነት ጋር ትንሽ እንጋጭና እየቆየን እንለምደዋለን:: ስንለምደው ግን ትክክለኛ ነገር የምናደርግ ያህል ነው የምንቀበለው:: *ሰው መግደል ስንዴት ይቻላል?* እያልኩ የምደነቀው ሴትዮ ለካ ሲለመድ ምንም ማለት ይሆናል:: ታዲያ እኛ የአስተሳሰባችን ውጤት ነን ቢባል እንዴት ትክክል አይሆን?

ሁለተኛ ቀን ማታ ላይ ወደስራ ስገባ ከሁሉም ጋር ሰላምታ ተለዋወጥኩ:: ሰላምታ መለዋወጥ የተለመደ መሆኑ ተነግሮኛል:: አንዴ ተዟዙሮ ሰላምታ መለዋወጥ የተለመደ መሆኑ ተነግሮኛል:: ከገባሁበት ደግሞ ጎበዝ ተማሪ ሆኜ ማሽቃበጡንም መካን ነበረብኝ:: ወዲያው ስለትናንቱ አዳር መጠያየቅ ተጀመረ:: ሁሉም ያጋጠማቸውን ግልጽ ሆነው ያወራሉ:: *ስራችን የተደበቀን ነገር መሸጥ ሆኖ ምን ግልጽ ያስመሆን ይታሰባል?*

ለእኔ ጥሩ ትምህርት ነበር:: አንዷ የቆየ ገጠመኟን እንደዘበት ስታነሳው ሁላችንም ተገርመን ሳቅን:: እኔ ግን ሳቄ ምሬት አዘልና ነገ የሚጠብቀኝን አስቀያሚ ህይወት የሚያሳብቅ ጥልቅ ሀዘን የዋጠው ሳቅ ነው የሳቅኩት::

"አዳር ሶስት መቶ ብር ተስማምተን ይዞኝ ከሄደ በኋላ መኝታ ክፍሉን ዘግቶ ልብሴን አስወለቀኝና ቆዳን በጭቆ በሚያነሳ ችንጋ እየገረፈኝ ነበር ስሜቱን የቀሰቀሰው:: ልክ ስሜቱ ሲነሳሳ ደግሞ አለንጋውን ሰጥቶኝ እርቃኑን ሆኖ መቀመጫውን በማመቻቸት እንድገርፈው አደረገኝና የእልሄን ሁለት ሶስት ጊዜ ስለመጥጠው ከነስሜቱ ተዝለፍልፎ ቁጭ አለ":: *ወንዶች በጠቀባባ ስሡፊዎች ይሆኑ እንዴ?* እኔ ከተዋወቅኳቸው ሀያ የሚደርሱ ሴቶች አስራ አራቱ ባለትዳር ሆነው ነው ቢዝነሱን የሚሰሩት:: ባሎቻቸው ታዲያ በሚኖሩበት ሰፈር ውስጥ የታወቁ ጉልበተኞች፣ ቀማኛና ሌቦች ናቸው:: ከሴቶቹ ሳይቀር ሞባይል፣ ወርቅ፣ ብር ይቀማሉ:: የሚዘርፉት ወይም የሚሰርቁት የጠፋ ቀን ሚስት ተብዬዎቹ ስጋቸውን ሸጠው በሚያመጡት ብር ምግብ፣ ጫት፣ መጠጥ፣ ቤት ኪራይ ይቻልላቸዋል:: የሚገርመኝ ነገር ባሎቹ ሚስቶቻቸውን ዛሬ ማታ ከማን ጋር እንደሄደች ሳይቀር የሚያውቁ መሆኑ ነው:: ሚስቲቱ በዚህ ጉዳይ ላይ መዋሸት የሚባለውን ነገር አታስበውም:: ካደረገችው መከራዋ ማለቂያ አይኖረውም:: የተቀሩት ስድስቱ ሴቶች አግብተው የነበሩና ተለያይተው ከልጆቻቸው ጋር ብቻ ቤት ተከራይተው ስጋቸውን እየቸረቸሩ ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ ናቸው:: ከነሱ ጋር ብዙ ሰዓት መቀመጥ ብዙ ታሪክ ያሰማል::

ሰዓቱ ወደ እኩለ ሌሊት ሲገፋ ሌላ ቦታ ሞቅ ያደረጉ ወንዶች ወደኛ



Scanned by CamScanner

ቤት መግባት ጀመሩ:: እያንዳንዱ ቤት ውስጥ ያሉ ብዙ ሴቶች የራሳቸው ደንበኛ አላቸው:: እንደዚሁ ሁሉ አዲስ የምትገባን ሴት ቶሎ ከእፍታው እንዲደርሳቸው ወጥመድ ዘርግተው የሚጠብቁም ወንዶች አሉ:: ከነዚህ ውስጥ ትናንትና አብሮኝ ያደረው ግርማ አንዱ ነው:: በጣም ደንበኛ የሆኑ ወንዶች ሲመጡ "እዚህ ብርድ ከሚመታኝ ነገ ቢያገኝ ስለሚሰጠኝ ከእሱ ጋር ሄጄ ብለፋ ይሻለኛል" ይላሉ::

የታወቁ ደንበኞች ሲገቡ አዲስ በመሆኔ አይናቸው እኔ ላይ አረፈ:: አንደኛው ጠጋ ብሎ ጎንተል በማድረግ አቀፈኝ:: እጁን በእጄ አንስቼ አስለቀቅኩት:: አሻሸኝ:: ለመሸሽ ሞከርኩ:: የቤቱ ባለቤት መጥፎ ፊት ስታሳየኝ ደነገጥኩ:: ወንዱ እኔ እንደምፈልገው ካልሆንኩለት መጠጡን ሊያቆም ይችላል:: አልፎ ተርፎም የራሴን ገበያ መዝጋት እንደሌለብኝ ተነግሮኝ ነበር:: እኔ ገና ስላለመድኩት መታቀፍና መታሸቱን ተቃወምኩ እንጂ ሴቶቹ አዲስም ሆነ ደንበኛ የሆነው ነካ ካደረጋቸው ራሳቸው ናቸው ፈጥነው የሚጎዳኙት:: መጎዳኘታቸው ሳያንስ ተጠግተው እየነካኩ፣ እያሻሹ፣ ምላሳቸውን ጆሮው ውስጥ እየከተቱት በስሜት ያጦዙታል:: በምላሹም ወንዶቹ ከፓንታቸው ትንሽ ዝቅ የምትል ሚኒስከርታቸው ውስጥ እጃቸውን ይልኩታል:: ፓንት ያልተደረገበት ራቁት ነገር ውስጥ ይውላሉ:: ያኔ ሴቶቹ ብዙ እንዲቆዩ ለወንዶቹ እድል አይሰጧቸውም:: ብዙ ወንዶች በቆሙበት ይሸናሉና:: አንዴ ከረኩ ደግሞ ለአዳር መውጣት አይታሰብም:: እናም ማነቃቂያው ስልቱን የጠበቀ ነው የሚሆነው:: *እንዳያማህ ጥሬው፣ እንዳይበላ ለቅቦው ርሀቡ ደጥናበት ነው መንፈሱ::*

የቤቱ ባለቤት ፊት ሲገላምጠኝ የግዴን ተጠጋሁት:: እንዲህ ዓይነቷ ሴት ሰላቢ ወይም "ቁዝሚ" አላት ነው የሚባለው- ገበያ ታሸሻለች:: ሰውየው "ቀሽም! ደደብ!" ብሎ የያዘውን ቢራ ላዬ ላይ ደፋብኝ:: ጥቃት እንዳየች ሚዳቆ ወደ ጓዳ መሳይዋ ቤት ገብቼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: ትንሽም ቢሆን ያለኝ የህይወት ዕውቀት ደደብ ሊያሰኘኝ እንደማይችል ሳስብ ውስጤ ተነካ:: *ዮት ሰባቱ ያውቀኛል?* የቤቱ ባለቤት ተከተላኝ መጥታ እያዘነች የሷን ታሪክ ምሳሌ በማድረግ መከረችኝ::

"ገና አንድ ሳምንት ሳይሆንሽ እንዲህ ከሆንሽማ ማበድሽ ነው:: ገና ብዙ ነገር ታያለሽ:: ሁሉም እዚህ አምሮበት የምታይው ተመችቶት አይደለም:: እኔ ራሴ..." አለችና ያስገረመኝን ታሪክ ነገረችኝ::

"...እኔ ራሴ ውስኪ ቤት አስከከፈትኩበት ዕለት ድረስ ሀያ ሁለት ዓመታት ሙሉ እዚህ ህይወት ውስጥ ኖሬያለሁ:: ሁለት ልጆች ሲኖሩኝ አንድ እህቴን ጨምሮ አስተምራለሁ:: አንቺ ብቻሽን ሆነሽ እንዲህ በትንሽ በትልቁ የምትከፊ ከሆነ ጥሩ አይደለም:: እዚህ የምትቆም ሴት በሙሉ ለወንዶች ደደብ ናት" በማለት ልታጽናናኝ ሞከረች::

ተመልሼ ስገባ ሰውዬው በድጋሚ ተናግሮኝ የሚጠጣውን ጥሎ ወጣ::

"አንቺ ከማን በልጠሽ ነው? ትላም!" ባለቤቷ የእኔን እንባ በማየቷ ጥሎ መውጣቱ ብዙም አላስጨነቃትም::

"ከዛሬ ጀምሮ ግን ጠጪ ስትባይ እንቢ አትበይ:: እያስቀዳሽ እኔ ከስር እደፋዋለሁ" አለችኝ:: ያን ዕለት አጥንት የሚሰብር ስድብ ተሸከሜ

ያለምንም ገበያ ከለሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ከጓደኛዬ ጋር በመሆን በእግራችን ወደቤታችን ስናመራ እግዚያብሔር ምን ያህል ጨካኝ መሆኑን እያሰላሰልኩ ነበር፡፡

* * *

እያደር ገበያ ሞቅ፣ ሞቅ እስኪል ሴቱ ተሰብስቦ የሚደረገውን ጨዋታ መስማት ይናፍቀኝ ጀምር፡፡ *ውስጤ የኪነ-ጥበብ ስሜቱ ሰባብ ይሆን?* እድሜ ካለኝ እንደምጽፈው እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ቀስ እያልኩ ነገሩን ስማረው የሌላዋን ደንበኛ መያዝ ከሀጢያቶች ሁሉ የላቀ ሀጢያት የወንጀሎች ሁሉ ወንጀል መሆኑን ተረዳሁ፡፡ *ሆሆይ! ድራሽን ሳያጠፉት በፊት ስንቷን ሰወቅኩት፡፡* የአንዷን ደንበኛ አንዷ ይዛ ካደረች ባሌን ቀማሽኝ በሚል በተለይ ጥሩ ሰው እና ጥሩ ቢዝነስ የሚሰጥ ከሆነ ጦርነቱ ሞቅ ብሎ ይቀጣጠላል፡፡ መጀመሪያውኑ ቀሚዋ ሴት ወደሲኦል ከመላኳ በፊት የራሷን ሲኦል ማበጀት አለባት- ወይ ቦታ መቀየር ወይ ከተማውን መልቀቅ፡፡ ያለበለዚያ የመከራ ቀን አይገፋም፡፡ የፈላ ቡና ፊቷ ላይ ሊደፋ ይችላል... በምላጭ ፊቷ ተለይቶ ሊተለተል... ባሏ በጣም የሚፈራ ከሆነም ቤቷን የማዘረፍ ስልት ሊቀየስ... ስውር ሰው ተቀጥሮ እንዳትሞት፣ እንዳትሽር ልትደበደብ ትችላለች፡፡ ተቀሚዋ የተንኮል መረቧን ለመዘርጋት ምንም አይከብዳትም፡፡ ለአንዱ አንድ ሌሊት ሙሉ ስትነጥርለት ማደር ብቻ ነው፡፡

ስራቸው፣ ህይወታቸው፣ አስተሳሰባቸው፣ እነሱ ራሳቸው ሽርሙጣ ናቸው፡፡ እኔም ጭምር፡፡ ልዩነታችን እኔ ጀማሪ ሽርሙጣ ስለሆንኩ

የተንኮል ማጉን ማጠንጠኑ ላይ ገና ነኝ:: ወንዶቹ ደግሞ በሁሉም ነገር እሳት የሆነች ሴት ላይ ነው እንትናቸው ሁሉ የሚሰራው:: ደንበኛ የሚያደርጓት ሴት ብዙ ጊዜ እንደሚፈልጉት የምትሆንላቸውን ነው:: እንደፈለጉት የሚለው ቃል አጓጉል ጨዋነት ተላበሰ አይደል? ሳክ (የአፍ ወሲብ) የምታደርግላቸው፣ ሲፈልጉ በመቀመጫዋ የምትመቻችላቸው፣ ፖዚሽን በመቀየር የልባቸውን ለማድረስ የምትተጋዋንና "የምን ኮንዶም?" ብለው ሲሳለቁ... "እንዳሻህ!" የምትለዋን ነው:: እንዲህ ያለችው ዘላቂ ደንበኛ ከመሆኗም በላይ የፈለገችውን ያህል ገንዘብ ብትጠይቅ ያለማንገራገር የሚከፈላት ናት:: ታዲያ ደንበኛው አንድ ቀን መጥቶ ካጣት "እንደሷ የሚሆንልኝ ካገኘሁ ነው የምወስደው!" ብሎ ሚስጥሯን ካዘረከረከው ጉዷ ይፈላል! ከዛ በኋላ በሴቱ ሁሉ ትጠላና ትገለላለች:: *ይሄ የሰውን ልጅ ድንቅ ለስተሳሰብ የሚያሳይ ነው:: ድንቁም ለቴ!*

ከኮንዶም ውጪ ባልገናኝም ወታደሩ ፍቅሩ እንዳደረገው በመቀመጫዬ የሚገናኙኝ ወንዶች የመጡ እለት ምን እንደምሆን እየዘገነነኝ አንዴ ከገቡ የማይወጡበትን ህይወት አምርሬ ጠላሁት:: *ሰው ለንዴት ለየሞተ ይኖራልና ወደሞተ ይነጉዳል?*

* * *

ከነገሩ ጋር እየተላመድኩ ስሄድ ዘና ማለት ጀመርኩ:: የሙዚቃ ፍቅሬን እያወጣሁ ከሚከፈተው ጋር እኩል አንጎራጉር፣ ነሸጥ ሲያደርገኝም ዳንሱን አቀልጠው ያዝኩ::

አንድ ቀንም አፍሪካ ሙዚቃ ተከፍቶ ስውረገረግ ሁለት ሰዎች ገቡና በግርምት አዩኝ:: ከገቡት ሰዎች አንዱ ለየት ባለ የደስታ ስሜት ውስጥ ሆኖ አይኑን ተክሎብኝ ቀረ:: በመሀልም አስጠራኝና እየተቀባበሉ ከጓደኛው ጋር ልቤ እስኪጠፋ አሞጋገሱኝ::

"ጥርስሽ ሲያምር!"

"አይኗስ ብትል... ውብ አይን!"

"ቁመናሽም የሰጠ ነው"

"ከለሯን ልብ ብለሽዋል?"

"አመሰግናለሁ" ብዬ ወደ ዳንሴ ተመለስኩ:: *ለድናቅት የቤት ኪራይ ለደከፍሰም* ስል:: መልሰው እንደገና አስጠሩኝ::

"ታውቂያለሽ ሚስቴ ሱማሌ መሆኗን?" *የታባክ ለውቃለሁ?* "ተው እንዴ?"

"ሙች ከለራችሁ አንድ!"

"አመሰግናለሁ::"

"ታዲያ የፈለግሽውን ለመጠጣት ማናባቱ ነው የሚከለክልሽ?"

"ማንም አባቱ! ዳሽን ይምጣ::"

"ጠቆር ያልሽ ቸኮሌት:: አሁን አንቺን ስገጥም ባድር ማናባቱ ጥፋተኛ



Scanned by CamScanner

ይለኛል?"

*ደሄ ሰውዩ ሰባቱን ደጠባብ ስንዴ? "ማንስ አባቱ!" ደም ሰባት ሰመጥባት ስኔ ሲበጠጥ ደፈብጋብ ስንዴ?*

"ኢትዮጵያዊ ነሽ?"

ደነገጥኩ:: ለምን እንደ ደነገጥኩ አልገባኝም:: ትንሽ አሰብኩበትና "አይደለሁም!" አልኩት ኢትዮጵያዊ የሚለውን ቃል ቋቅ እስኪለኝ እየጠላሁት::

"አትመስይምኮ... በፍፁም አትመስይም!" አለኝና ከእኔ ጋር ይበልጥ ለመተዋወቅ እንደተስገበገበ በሚያሳውቅበት ሁኔታ የባጥ የቆጡን ቀባጠረ::

"ሚስቴ ውጪ ናት አላልኩሽም?"

"ብለኸኛል"

"ምናባቱንስና ዛሬ ካንቺ ጋር ባድር እግዜር የሚቀስፈኝ ይመስልሻል?"

"ምን ቁርጥ ቢያደርገው?"

"Shall we dance?"

"I'd love to"

ትንሽ ለመደነስ ሞክሮ አቃተው:: ጉንጮቼን አገላብጦ ስሞ ወደ ጓደኛ ው ተመለሰ:: ወደነሱ ስመለስም አጠገቡ የነበረው ጓደኛው "እውነቴን ነው የምልሽ ባርቾ ቺቺኒያ ሰፈር ለረጅም ጊዜ ተዝናንቻለሁ:: የስንቱን እንትን ቀምሻለሁ እንዳንቺ አይኔ ላይ ያጥበረበረች ሴት ገጥሞኝ አያውቅም"

"አመሰግናለሁ" የነዚህ ሰዎች ሙገሳ በየትኛው ክፍለ ዘመን እንደሚያልቅ ማወቅ ቢሳነኝ የአፋሯ ቆንጆ የሚለው ዘፈን ሲከፈት ልደንስ ሄድኩ:: አስጠሩኝና "አፋር ሳትሆኚ አትቀሪም እነሱን ትመስያለሽ" አለኝ ሚስቴ ሱማሌ ናት ያለው:: *ሆሆይ! የዘር ጥናት ባይ ናቸው ስንዴ?*

"እንዳደርግሽ እፈልጋለሁ" በጨዋ ደንብ አስቀመጥኩት:: *ስንኳን ወደ ነጥቡ በደህና መጣህ!*

"ከተስማማን እሺ"

"ይገርምሻል ሴት ይዞ የማደር አላማ አልነበረኝም:: ሳይሽ ግን በጣም ደስ ስላልሽኝ ነው:: ለመሆኑ ስንት ትያለሽ?"

*የሸንኩርት ገበያ* "ሁለት መቶ ብር!" አልኩት መቶ ሃምሳዋ ለቤት ኪራይ እንደምትውል አስልቼ::

"እንዴ! እንዴ! በጣም በዛ:: ሙች ማዕድን ያለበት አስመሰልሽው"

*የበግ ገበያ* "ይሄው ነው እርግጡ!" ምን ላድርግ? እነሱ ለሁለት ሆነው



Scanned by CamScanner

እኔ ብቻየን ቀንሽ በሚል አደረቁኝ ጓደኛውም እሱ ይተኛኝ ይመስል:-
"ሰባ ብር ይበቃሻል!" አለኝ::

"በሰባ ብር አልሄድም!" ስል ጥያቻው ሄድኩ:: *ምን ባደርጋት ነው? ነገ የቤት ኪራዩ መክፈል ስለብኝ::* ትልቁ ችግሬ እስካሁን ስራውን አእምሮዬ አምኖ ሊቀበለው አለመቻሉ ነው:: የቤት ኪራይና ቀለብ የሚሆን ብር እስካለኝ ድረስ ብሞት ወደ ቡና ቤቱ አልሄድም:: አስራ አንደኛው ሰዓት ላይ እንደደረስኩ ራሴን ማጩናነቄን ለመተው ግን ወኔ አጣሁ::

እንደገና አስጠራኝና ድርድሩን ሲቀጥል "ስማ ያንተ ሁለት መቶ ብር ህይወቴን እኮ አይለውጠውም... ቤቱ ገብቼ እንድተኛ ያደርጋል እንጂ!" አልኩት::

"ሌላ ስራ አለሽ?" *ገበሬ! ገበሬ ነህ* መልስ አልሰጠሁትም::

"አትቀንሺም ማለት ነው?"

"ይሁንልህ መቶ ሰባ ብር!" ስለቸኛ ክርክሩ::

"እሺ እንሂድ"

"አልጋ ይዘሀል?"

"ቤት ነው የምንሄደው"

"አይሆንም!" ሁለቱ ወንዶች አብረው እንደሚኖሩ ገባኝና እንቢ አልኩ::

አልጋ ለመያዝ ተስማማና ጓደኛው ወደያዘው ታክሲ ውስጥ ከመግባቴ በፊት "መጀመሪያ ብሩን ስጠኝ" አልኩት:: "እመኚኝ በእህቴ ከማልኩ አልዋሽም:: እቴቴ ትሙት ታክሲ ውስጥ እሰጥሻለሁ::" ጓደኞቼን መልካም እድል ተመኝቼላቸው ሄድኩ::

"በላ ብሩን ስጠኝ"

"አላመንሽኝም?"

"ሳይሆን ደንቡ ነው" ሰጠኝ:: ኮንዶሙን ገዛና ጨርሶ ወደማላውቀው ሰፈር ከመንገድ ገባ ያለ ፔንሲዮን ወሰደኝ:: ጓደኛው "ደስ የምትይ ባሪያ ነሽ ወድጄሻለሁ" ብሎ ተሰናብቶን ሄደ::

ውስጥ እንደገባን የመኝታ ቤቱን በር ከውስጥ ቆለፈና ልብሱን አወለቀ:: እኔም ከውስጥ የለበስኩትን ነጭ ሽሚዝና ፓንቴን አስቀርቼ አወላለቅሁ:: ከዛም "ጥርስሽ ያምራል... ወድጄሻለሁ" እያለ ከንፈሩን እንድስመው ጠየቀኝ:: ፈቃደኛ አልነበርኩም::

"በፍፁም አላደርገውም!" አልኩት:: ወዲያው ጭንቅላቱ ሳይሆን የከፈለኝ ብር እንዲያዝለት የፈለገ መሰለ::

"ከፍዬሻለሁ እኮ"

"ቢሆንስ?"

"የፈለግኩትን የማድረግ መብት አለኝ"



Scanned by CamScanner

ፈገግታው ጠፋ:: ያ - እንዲያ ፍልቅልቅ የነበረ ሰው በአንዴ አውሬ ሆነ::

ባለ በሌለ ሀይሉ ወደ አልጋው ሲገፈትረኝ በጀርባዬ ወደቅኩ:: እላዬ ላይ ወጣ:: ሁሉ ነገሩ አውሬ መሰለኝ:: ከንፈሬን ሲስመኝ በጣም ታገለ:: እኔም የዋዛ አልነበርኩም በቀላሉ አልተረታሁም:: ዱላ ጀመረ:: በጥፊ መታኝ:: ደጋግሞ መታኝ:: አንገቴን ወደጎን መልሼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: ሁለት እጆቼን ወደ ጎን ዘርግቶ ለእያንዳንዱ አንዳንድ ጉልበቱን አዘዘና እጆቼን ተጭኖ ያዘኝ:: ከዛም ብልቱን ከፓንቱ አወጣና ወደአፌ አስጠጋው:: ፊቴን እያወራጨሁ ልመና ጀመርኩ:: "እህት የለህም፣ እናት የለህም፣ በእናትህ ከሴት አልተፈጠርክም?" የእናትን ጣዕም ባላውቀውም ሲባል በምሰማው መሠረት ያለማቋረጥ ለመንኩት:: አፌን በግድ አንቆ ያዘ:: ወደ አፌ ሲያስገባው የግዴን መንጭቁ "ኡ... ኡ..." ብዬ በዚያ ውድቅት ሌሊት የድረሱልኝ ጥሪ አቀረብኩ:: ደንግጦ ከላዬ ላይ ሲወርድ ተነስቼ ስቅስቅ ብዬ ማልቀሴን ተያያዝኩት:: ሱሪዬን እንዳላደርግ ቢከለክለኝም በግድ ታግዬ አደረግኩት:: በዚህ ሰዓት ቦርሳዬን ብድግ አድርጎ እራሴ የነበረኝን 30 ብር ጨምሮ የሰጠኝን 170 ብር በድምሩ 200 ብር ማለት ነው ወሰደው:: ድምጼ እንዲሰማ አድርጌ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: ከጎናችን አልጋ ይዞ የነበረ ሰው ስለተረበሸ ተነስቶ ለባለቤቱ ነግሯቸው ነበርና የታክሲ ሰጥቶኝ እንድሄድ እየለመንኩት ሳለ በር ተንኳኳ::

"ማነው?" አለ ልብሱን እየለበሰ:: ሲጥኜ ከፈትኩት "ችግር አለ?" በእድሜ የገፉ የቤቱ ባለቤት ነበሩ:: እያለቀስኩ ከእሱ ጋር ማደር

አልፈልግም የታክሲ እንዲሰጠኝ ጠይቁልኝና እሄዳለሁ ብዬ ስላቸው "አንቺ ከማታውቂው ሰው ጋር ለምን መጣሽ?" አሉኝ:: በጣም ገረመኝ:: *እዚህ ሀይወት ላይ ሆኜ ስለ እያንዳንዱ ወንድ ማወቅ አለብኝ?*

"እባኮትን እኔ ቢዝነስ ገርል ነኝ:: የከፈለኝን ብር ቀምቶኛል" ስላቸው "ነይ ቆይ ላናግርሽ" ብለው ከክፍሉ ወጣሁና በሩ ተቆለፈ::

"ብሩ ይቅርብሽ እሱን ላስወጣው አንቺ እዚህ እደሪ" አሉኝ:: ነገ ቤት ኪራይ አለብኝ ሰዎቹም የአልጋውን ብር ሊመልሱ አልፈለጉም:: እናም ያለኝ አማራጭ የሆዴን በሆዴ ችዬ በድጋሚ ስራ ቦታ ሄጄ እድሌን መሞከር ሆነ::

"እኔ እዚህ አላድርም እሄዳለሁ" ስል ሰውዬው ከእኔ በላይ ለአልጋ ለተከፈለው ብር አዝነው ነበርና ከትንሽ ቆይታ በኋላ እዛው በር ላይ ቆሜ "ነይ ልሸኝሽ" ብለው ወንድ ልጃቸውን አስከትለው ዱላ ይዘው አስፓልት ድረስ ብዙ ምክር እየመከሩኝ ተጓዝን:: ልክ አስፓልት ስንደርስ "እዚህ ቆመን እናይሻለን በዚህ በኩል ሂጂና ታክሲ ለምኚ ይወስዱሻል" አሉኝ:: የበለጠ ተንሰቅስቄ አለቀስኩ:: ሰፈሩን አላውቀውም::

"መንገዱ የት ነው የሚወስደኝ?"

"ይሄ ሰፈር አዋሬ ነው ካዛንቺስ ያወጣሻል ቀስ እያልሽ ጥግ ጥጉን ሂጂ:: ችግር ካለ ጩኸት አሰሚን" ሲሉኝ ትንሽ ሄድኩና ከአይናቸው ሳልርቅ ቁጢጥ ብዬ አለቀስኩ:: ሞቴን ተመኘሁ:: ከእሳቸው ይልቅ ልጃቸው ያዘነልኝ ይመስላል "እኔ ትንሽ ልሸኛትና ልምጣ" አላቸው::



Scanned by CamScanner

"እባካችሁ የታክሲ አምስት ብር ስጡኝ እኔ እሄዳለሁ" ስላቸው መልስ አልሰጡኝም:: አባት ልጃቸውን ከልክለው ግቢያቸው እንዳይረበሽ ሲሉ እኔን ከግቢው አስወጥተው "እዚህ ጋር ቆመን እናይሻለን" አሉኝ... ከቦርሳዬ ሰዓቴን አውጥቼ ተመለከትኩ:: ሳዘጠኝ አስር ጉዳይ ይላል::

ፍርሀቴ ጨመረ:: እንባዬ ማቋረጫው ጠፋ:: ወደምድር የመጣሁበትን ቀን እየረገምኩ በፍጥነት ስጓዝ አንድ ታክሲ ሲመጣ አየሁና አስቆምኩት:: ከፌትኩና ሹፌሩን ትብብር ስጠይቀው "ግቢ አለኝ" ካዛንቺስ ቶታሉ ጋር ስደርስ "መኪና ውስጥ ካላደረግሁሽ" ሲል ጠየቀኝ:: ደነገጥኩ:: የመጠጡ ሽታ ለጉድ ነው "እባክህ ውስጤ ተረብሿል ለዚህ ነገር ዝግጁ አይደለሁም ላስደስትህ አልችልም" አልኩት::

"ግድ የለም እሺ በይኝ ጊዜ አናቃጥል"

"በርግጥ ጥሩ ሰው ነህ:: ተባብረኸኛል:: ስልክህን ስጠኝና ሌላ ቀን እንገናኝ:: ዛሬን ግን በእግዚአያብሄር ስም ተወኝ" የሚፈልገውን ካላደረገ ከዚህ በላይ እንደማይሸኘኝ ነግሮኝ እንድወርድ አዘዘኝ... ከማላውቀው ሰፈር ስላወጣኝ በልቤ አመስግኜው በአፌ ግን "እህትህ ላይ ይድረስ ጨካኝ!" አልኩና ሌላ ታክሲ ልመና ጀመርኩ... በእዛ ሌሊት በእግሬ ብሔድ የበለጠ የከፋ ነገር ሊያጋጥመኝ እንደማይችል አሰብኩት:: አንድ ታክሲ መጥቶ ነዳጅ ሊቀዳ ሲቆም አየሁ:: ወደ እኔ መጣ:: በትንሹ ችግሬን ነገርኩት:: ሲበዛ ልጅ ነው:: ታክሲ መያዙ ገርሞኝ የማይችል ስለመሰለኝ ፈራሁት:: ልጁ ግን ፍቃደኛ ሆነ:: ቺቺኒያ ስለሚባለው ሰፈር ብዙ ነገር እየነገረ አደረሰኝ::

ቢዝነስ መሄዴን ያዩ ጓደኞቼ "ለምን መጣሽ አልተስማማችሁም?" አሉኝ፡፡

"አልጋ ጠፋ"

ወንዶች ግን ለምንድነው እህት የላችሁም ወይ ሲባሉ የማይራሩት? ከሴት አልተፈጠሩም እንዴ? ነው ወይስ ሁሉም እንደኔ ቤተሰቡን ይጠላል? ይሄን አስቀያሚ ስራ የተውኩ እለት ሰው እንደምሆን ተሰማኝ፡፡ ነገር ግን የምበላውና ለቤት ኪራይ የምከፍለው የለኝም፡፡ ልርቀው ብሻም እንደማገኜት እየሳበ ወደሱ በማጣበቅ ወኔ ቢስ አደረገኝ፡፡

# -35-

ሰሞኑን የቤት ኪራይ ደርሷል:: እጄም ላይ ሳንቲም አጥሮኛል:: *ወደስራ መሄድ ሰለቸኝ* ብዬ ምሽቱን ተገን በማድረግ ለባብሼ ወጣሁ:: እንደተለመደው መደዳ ወዳሉት ቡና ቤቶች እየገባሁ ጓደኞቼን ሰላም ስል ሶሲ ባር ውስጥ በእናቱ ጣሊያናዊ፣ በአባቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ከአንድ ጆማይካዊ ጓደኛው ጋር እየጠጡ ነበር:: ስወጣ አይቶኝ ጆማይካዊው ጓደኛውን "የት እንደምትገባ እይና ና!" ብሎ ይልከዋል:: ትንሽ ቆይተውም እኔ ወዳለሁበት ሳራ ባር መጡ:: አፍሪካዊ ሙዚቃ አስከፍቼ ለጉድ ስውረገረግ አይቶ ወደ ምደንስበት በመምጣት "I wanna dance with you" አለኝ:: ትከሻዬን ናጥ አድርጌ *ሞክረኝ!* አልኩት::

ዳንሳችን አብሮ መሄድ አልቻለም:: እሱ የተለየ ዳንስ ስለነበር የሚችለው እንደነገሩ ትንሽ ሞካከርንና አቆምኩ:: *የምን መወራጨት ነው?* ሕይወት የምታምረው ባላት ቢት እኩል ሲደነስ እንጂ አራምባና ቆቦውማ የኔ እጣ ፈንታ አይደለም እንዴ?

"ነይ!" እጄን ያዘውና የሱን ዳንስ ሊያስተምረኝ ሞከረ:: *በናትህ ስልተመቸኝም!* ተመልሼ ተቀመጥኩ::

"ምን ትጠጫለሽ?" ገና ጥያቄውን ሲያቀርብልኝ ሶሲ ባር ያለች ልጅ ገብታ ጠቀስ አድርጋ ሀብታም መሆኑን ነገረችኝ::

"የፈለግሽውን ማዘዝ ትችያለሽ::"

"አማሩላ!" አንዱ መለኪያ 15 ብር ነው:: ለሴት ተስማሚ መጠጥ:: ከበር መለስ ሁሉም ተጋበዘ:: "የታክሲ በለና?" ሲሉት ለሁሉም ሴቶች ሀምሳ ሀምሳ ብር ሰጣቸው:: *እውነትም ሀብታም!*

"አብረን እንድናድር እፈልጋለሁ" *ጅሉ የእኔ ስራ ምን መሰለህ? ተገኝተህ ነው?*

"ደስ ይለኛል" ለፍቅረኛ የቀረበ ጥያቄ ያህል አመላለሴ ገረመኝ::

"ኦኬ ተዘጋጂ!"

ጓደኞቼ ሁሉ አጉል ገንዘብን የተመለከተ መደራደር ውስጥ እገባና ጉዶ እንዳይፈላ አስጠነቀቁኝ::

*ሰባ መስጠተ ጋር የበግ ገበያ የለም:: ሁሉም የበሬ ዋጋ ነው::*

አቤት ክፋት? አልጋ ቢፈለግ፣ ቢታሰስ የት ይገኝ:: *ሰዳሚ ተጋተ ይሄስ!* ለነገሩ እግዚያብሔር የእኔን ድራማ ሁሌም ልብ አንጠልጣይ ስላደረገው "በይ ደህና እደሪ አንቺ እድለ ጠውላጋ!" ቢለኝም ግድ አይሰጠኝም ነበር::

"ምን ይሻላል?" ጠየቅኩት:: *እንዴ ሰዐጋ በመፈለግ ልብ ሰቀላ ልታመም እንዴ?*

"ወደ ቤት እንሄዳለን::"

"እንዳልክ!" *ስቦ ቢፈልግ ቤቱ ወስዶ ደግደገኝ::* እውነታው ግን ሌላ ነበር አልፈራሁትም:: በትክክል አልጋ መጥፋቱን አይቻለሁና::

"በሩ ሲከፈትልን ወንበሩ ስር ትደበቂያለሽ" አለኝ:: *ለንዴ? ሚስቱ ጎን ቢያስተኛኝ ነው ለንዴ? ከማን ነው የምደበቀው?* እንዳለኝ አደረግኩለት:: ለካ አጅሬው እናቱ ቤት ኖሯል ይዞኝ የመጣው:: *ባፋንኩት!* ቀስ ብሎ ደባብቆ መኝታ ክፍሉ አስገባኝ::

ሻወር እንድወስድ አድርጎ ቢጃማም ሰጠኝ:: *ሸረ ለንክብካቤ! ደህቺ ለንክብካቤ ቲፕ ለማግኘት ነው* አልኩ በሆዴ:: ምንቸገረኝ... ደህና መክፈሉ እንደሁ አይቀር ቲፑን እሰጠዋለሁ::

ግርም እስኪለኝ ድረስ በጨዋ ደንብ አንድ ጊዜ ብቻ ተገናኝቶን እንቅልፉን መለጠጥ ያዘ:: *ሲቲቱን ሊታነቃኝ ነው?* ከእንቅልፌ ስነቃ ከረፋዱ አምስት ሰዓት ሆኗል:: የድፍረቱ ድፍረት እናቱ ሳታይ እህቶቹን አስተዋውቆኝ ያበደ ቁርስ በመጋበዝ ሶስት መቶ ሀምሳ ብር አስጨብጦኝ:- "ደሞ ደውይልኝ እንዳትጠፊ!" ሲል ስልኩን ሰጠኝ::

"ምንሽ እንደተመቸኝ ታውቂያለሽ?"

*በሞቴ ንገረኝ* "ምኔ ተመቸህ?"

"ከለርሽ"

*ደሄ ሱማሲ?፣ ስፋርና ሲኒጋበ የሚያስብበኝ?*

"ትደውይልኛለሽ አይደል?"

"አዎ::"

"ስልክሽን ለማንኛውም ስጪኝ?" ሰጠሁት:: ከሁለት ቀን በኋላ ደውሎ "መነጋገር አለብን" አለኝ:: ሄድኩለት:: ራት እየጋበዘኝ "ከሳምንት በኋላ ጣሊያን እሄዳለሁ" አለኝ::

*እና በዚህ ሳይ ነው የምንነጋገረው?* "ለስራ ነው? ማለቴ"

"እዛው ነው የምሆነው"

"አይ ጥሩ ነው::" *ታዲያ የኔ ጌታ ሳምንቱን ሙሉ ትፈልገኝ ይሆን?*

"አንድ ስጦታ ይገፍልሽ መጥቻለሁ::" ሰጠኝ:: በሚያምር እቃ የታሸገ ነው:: ሪቫኑን አንስቼ ስከፋፍተው የሚያምር ብር ነው::

የጋብቻ ብር::

*ነገሩ ምንድነው?*

የጋብቻ ጣቴ ላይ ሲያደርገው ፈዝዤ ከማየቴም በላይ በእሱም እጅ ላይ



Scanned by CamScanner

ሌላኛውን ቀለበት ማድረጌ ራሴኑ አስገረመኝ::

*ለገበኝ ለንዴ?*

ራቴን አብልቶ ሁለት መቶ ብር ሰጥቶኝ ተለያየን::

የውሀ ሽታ!

*እግዜር ይስጥህ ለቦ!*

***

ቤቴ... ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ ሆኜ የሆነ ሰው የቀሰቀሰኝ ያህል ደንግጬ ተነሳሁ... የወደቅኩበትን አላውቅም ነበር:: ዙሪያዬን ባይ ምንም ነገር የለም:: *ለምን ነቃሁ? ምንስ ለስደነገጠኝ?* መደንገጤ ራሱ መልሶ አስደነገጠኝ:: "በስመአብ ወወልድ..." አማተብኩ:: በራሴ ጊዜ ደንግጬ ነቃሁ እንጂ የቀሰቀሰኝ አልነበረም:: መልኬ ለማሸለብ ብሞክር አቃተኝ::

*ምንድነው ነገሩ?*

ድንገት አዕምሮዬ በሀሳብ ተጨናነቀ:: *ሾረ በዚህ ለኩበ ሴቢቶ ለንዳባብድ!* ቀስ እያለ ህይወቴ እንደሲኒማ እየተንቀሳቀሰ በቤቴ ግድግዳ ላይ የማየው መሰለኝ:: ጓዳ ጎድጓዳዬ ሁሉ ግልጥ ብሎ ተከፈተ::

መጀመሪያ እርቃኔን ስወለድ አየሁት::

ሰነ... ሰው ስርቃኑን ሰደኖርም ውስጤ አቃጨለ:: ራስ ምታት:: ፈጣን... ግን የሚቆራረጥ ራስ ምታት:: ፊልሙ ሰጉድ እየገሰገሰ አሁን ያለሁበት ጠባብ ክፍል ላይ ሲደርስ ቆመ::

"ማነሽ?" አዕምሮዬ::

"ማን... እኔ?"

"ማነሽ?"

የምመልሰው ጠፋኝ::

"ሰ... ሰናይት..."

"መጠሪያ ነው!"

"እና?"

"ታሪክሽን ተናገሪ..."

ምን ልበል? ምን ታሪክ? አሰብኩት::

"የወለዱኝ የማይታወቁ... ከየት እንደመጣሁ የማልታወቅ... የማደጎ ልጅ... ኑሮ ብሽቅ የሆነብኝ ሴት ቡና ቤት ሰራተኛ..." አገላለፄ አልጥም አለኝ::



Scanned by CamScanner

"ማንም ነኝ"

"ንቂ ሰናይት! ንቂ!"

ከእድሜ ልክ ባርነት ወስኖና ቆርጦ ነፃ የመውጣት ፍላጎት ገዘገዘኝ:: በሰው ሰራሽ የውሸት ህግ ተብዬ ቀንበር የሰውን ስብዕና እንደፈለጉ ከሚያሽከረክሩ በዝባዦች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቀንበሩን ሰባብሬ ለመጣል እልህ ወለድኩ::

"የትም መሄድ አልችልም:: ለራሴ ግን የነፃነት ምንጭ ነኝ"

"አግኝተሽዋል:: ራስሽን ከጠፈርሽበት ገመድ ፍቺ!"

እኔ ራሴ ገና ነፃ ሳልወጣ ነፃ ላወጣቸው የሚገቡ ሰዎች እንዳሉ ተሰማኝ:: አዕምሮዬ ሞገተኝ::

* * *

ወገግ ሊል ነው::

"ሰናይት ስንት ጊዜ ትኖሪያለሽ?"

ቀሽም ጥያቄ "አንድ ጊዜ!"

"እንግዲያው ለሌላው ብርሀን ሁኚ!"

***

ሰልችቶኛል... መኖር! ገላዬን እንደሸቀጥ መቸርቸር:: አመት ባይሞላኝም እንኳን ቋቅ ብሎኛል:: ዘላለሜን ተሸንፌ መኖር መሮኛል:: ሞትም እየሸሸ የሚጫወትብኝ ለአላማ ይሆን እንዴ? *ከዚህ በኋላ ሰዎች ሲገሉኝ ካልሞከረ ስኔ ራሴን ሳጠፋ ስልሞከርም!* ውስጤ እርግጠኛ በሆነ ቁጥር ራስ ምታቱ ቀነሰልኝ::

ሰዎች መጠቋቆሚያ አድርገው ሊገሉኝ ቢችሉም የማድነው ህይወት ታየኝ:: *ሰው ሰውን የሚያስተምረው በስሌተ ብቻ ነው ስንዴ?*

"ቀሽም!" አዕምሮዬ ሰደበኝ::

ከእንግዲህ ቀና ብዬ እሄዳለሁ:: ብቻዬን የማደርገው ትግል የጎላ ፋይዳ ባያመጣም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን የጓዳ፣ ጎድጓዳ ሚስጥር ለአደባባይ አወጣዋለሁ:: የነፃነት ቦይ ሲቆፈር፣ የነፃነት ሜዳ ሲደለደል መሳተፍ አለብኝ::

*ዓላማ የሰው ልጅ የሰውጥ መሰባሰ ነው::*

በቃ! ቅርንጫፍነት በቃኝ:: እኔ ራሴ ስር ሰድጄ መብቀልና ጠንካራ ግንድ መሆን አለብኝ:: ከእኔ የሚገኙትን ቅርንጫፎች መሸከምና ነፃ ማውጣት ይኖርብኛል::

የእኔን ታሪክ የሰሙ እና ያዩ ይኖራሉ:: ሁለቱም ሰዎች በተለያየ



Scanned by CamScanner

መንፈስ ቢቀበሉኝም መስጠት አለብኝ:: ፋና ወጊ መሆን አለብኝ:: የሰሙት ከንፈራቸውን የሚያጣምሙብኝ፣ የሚያሽራምሙብኝ ይመስለኛል:: ምክንያቱም ሰሚ ለትችት አንደኛ ነውና:: ያዩት ግን እንደፈልም ህይወቱን እያዩት የራሳቸውን ይጨምሩበታል:: እያለቀሱ ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት ይታትሩ ይሆናል::

መወሰን ነበረብኝ::

ሀሳቤን የምገታበት ልጓም ተበጠሰ::

ጠዋት... በጠዋት ሄጄ ኤችአይቪ ተመረመርኩ:: *ኦ ጌታ ሆይ! ስመሰግንሀለሁ!* ነፃ ነኝ::

ከውስጤ... በጣም ከጥልቅ ውስጤ እርግጠኝነትን ዘላለማዊ ባደረገ ስሜትና መንፈስ «የራሴን አንድ የስኬት መወጣጫ ደረጃ አበጃለሁ!» ስል ጮህኩ:: ግጥም ብሎ በሞላው ሚኒባስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ደንግጠው ዞረው እስኪያዩኝ ድረስ ጮኬ «እንደገና መኖር እጀምራለሁ!» አልኩ:: እብድ ናት ብለው ሳቁብኝ::

እኔ ግን መዳፌ የጨበጠውን እውነት እውን ላደረገው እንባዬ እየተንጠባጠበ "እንደገና እኖራለሁ!" ስል ያለፈ ያደፈ ህይወቴን አውልቄ ጥዬ የራሴን የለውጥ ጎጆ ቤት ልሰራ ወሰንኩ::

ከዛስ?



Scanned by CamScanner

ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ መነሳት ያለበት ጥያቄ ነበር:: የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ ይሁን እንደሚባለው ዳግመኛ ወደ ቡና ቤት ስራ ላልመለስ ከራሴ ተማምዬ እንደ ማንኛውም ሰው ስራ ሳልንቅ ለመስራት ጥቂት ወር ፈጅብኝ:: ውስጤ ያለውን ደባል ስብዕና ሁሉ ጠርጌ ለማውጣት በችግሮቼ ላይ ፍርድ መስጠት ነበረብኝ::

የሚገርመው ደግሞ ዝዋይ የጓደኞቼ ዝግጅት ላይ ለመገኘት እንደሄድኩ መምጣቴን ያወቀው ቤቢ ከጓደኞቹ ጋ በመሆን ጩቤ፣ ሰንሰለት ይዞ መኀቶ ካልገደልኳት ብሎ ነበር:: ፖሊስ ደርሶ፣ ታሪካችንን የሚያውቁ ባለስልጣኖች "እንዴት እንዲህ ታደርጋታለህ?" ሲሉ በማግስቱ አምስት ሰዓት ላይ የጋብቻ ካርዱን ይዞ እዛው ፖሊስ ጣቢያ እንዲመጣና ሁለታችንም ባለንበት እንዲቀደድ ነገሩት:: ይሁንና ድራሹ በመጥፋቱ ፈልገው በቁጥጥር ስር ካዋሉት በኋላ ካርዱ እንዲቀደድ ሲጠየቅ በገዛ ፈቃዱ የቀደደው መሆኑን ምሎ ተገዝቶ በመናገሩ ከዚያን ሰዓት በኋላ ሙሉ ነፃነቴን የተቀዳጀሁና እንቅፋት እንኳ ቢመታኝ ከቶውኑ አንድስ እንኳ ጠላት የለኝምና ሙሉ ሀላፊነቱ የሱ መሆኑ ገልፆ ከፈረመ በኋላ ሰላሜን ተቀዳጅቼያለሁ::

በችግሮቼ ላይ መፍረድ የነበረብኝ ዘላለሜን የጭን ቁስሌን ስንከባከብ መኖር ስለሌለብኝ ነበር:: በቃኝ!

## -36-

ስራ ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ ማለፍ ነበረብኝ:: አስተማማኝ ስራ ካላገኘሁ ነገ ጠዋት ተመልሼ ቡና ቤት ላለመሄዴ ምንም ዋስትና አልነበረኝም:: ስለዛም ያደረግኩት ነገር ቢኖር በማውቃቸው ሰዎች በኩል ስራ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ነበር::

ግን አልተሳካልኝም::

*ምንድነው ያጠኝ ችሎታ?* ስል ራሴን ጠየቅኩ:: ነገሮች በማስባቸው መንገዶች አልሄድ ሲሉኝ ግራ ተጋባሁ:: ህይወቴን መለወጥ ካለብኝ የግድ ባለኝ ችሎታ ወይም ተሰጥኦ ነው መንቀሳቀስ ያለብኝ:: ስራ ሳልንቅ መስራት ብቻ ሳይሆን የምሰራው ስራ ራሱ አስተማማኝ መሆን አለበት ስል አመንኩ:: እናም ሀሳብ ውስጥ ሆኜ ምን መስራት እንዳለብኝ ስዳክር ድንገት አንድ ነገር ተከሰተልኝ::

*ለናደተ* አልኩ ለራሴ:: *ጥሩ ቁመና ለለሽ:: ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ ለለሽ:: ለምንድነው ከዚህ ጋር የተያያዘ ስራ የማትፈልጊው?* ብዙ ጊዜ ማስታወቂያ የሚለጠፍባቸው አራት ኪሎ፣ ለገሀርና ጊዮርጊስ እየሄድኩ ስራ ፍለጋ ማስታወቂያዎችን ባነብም አብዛኞቹ ተስፋ የሚያስቆርጡ ነበሩ::

የአመታት ልምድና በሙያው ላይ በትንሹ ዲፕሎማ ይጠይቃሉ:: እኔ ደግሞ እነዚህ ነገሮች ስለሌሉኝ በጣም ተበሳጨሁ:: *ለ እግዚአብሔር ሆይ ምስኪኗን ልጅህን ለተረዳት ፈቃደኛ አይደለህም ማለት ነው?* ስል ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ገብቼ ተንሰቅስቄ አለቀስኩ:: ዳግመኛ ቡና ቤት ላልሰራ ለራሴ መሀላ ፈፅሜያለሁ:: ህይወቴን ለመለወጥ ቆርጬ ተነስቻለሁ:: ይሁንና ስራ ካላገኘሁ ለእኔ ህይወት አደጋ ስለነበር ነው ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ገብቼ ተንሰቅስቄ ያለቀስኩት::

ከቤተክርስትያኑ ወጥቼ እንደተለመደው ክፍት የሥራ ቦታ የሚል ማስታወቂያ የተለጠፈበት ቦርድ ጋ ተጠግቼ ሳነብ አንድ ማስታወቂ አይኔ ውስጥ ገባ::

ማስታወቂያው የሽያጭ ሰራተኛ እንደሚፈልግ የሚገልፅ ነው:: ልቤ መምታት ጀመረ:: በተለይ ዝቅ ብሎ 0 አመት የስራ ልምድና ቢቻል በማስታወቂያና ሽያጭ ሰራተኝነት የሰለጠነ ይላል:: እኔ ደግሞ ዝዋይ እያለሁ ከአዲስ አበባ በመጣ ድርጅት አማካይነት ለሁለት ወራት የሰለጠንኩበት ሰርተፍኬት አለ:: *እግዚአብሄር ለመናዬን ሰማኝ ይሆን?* ስል እየበረርኩ ቤት ሄጄ ሰርተፍኬቱ ካለበት ፈልፍዬ አወጣሁና በአድራሻው መሰረት ቢሮውን ፈልጌ አገኘሁት::

አጋጣሚ ሆኖ ቢሮው የደረስኩት ሲዘጋ ነበር:: የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ሲወጣ አገኘሁት::

"ለምዝገባ ነበር የኔ ጌታ" አልኩት:: ልጅ እግር ነው::



Scanned by CamScanner

"ምነው ታዲያ ስንወጣ መጣሽ?"

"ገና አሁን ነው ማስታወቂያውን ያነበብኩት::" አልኩት::

"ጠዋት ተመልሰሽ መምጣት አትችይም?"

"እንዴ? ኧረ በደንብ እችላለሁ"

"በቃ ጠዋት 2:30 ላይ ነይ" ሲለኝ አመስግኜው ለመሄድ እጄን ልጨብጠው ስል የያዘውን ቦርሳ ወደ ሌላኛው እጁ አዟዙሮ ሊጨብጠኝ ሲል ከእጁ አመለጠና መሬት ላይ ሲበትን መጨበጡን ትቼ በፍጥነት ቦርሳውን በማንሳት የተበተኑትን ወረቀቶች ሰብስቤ አስተካከልኩለትና ቦርሳውን ስሰጠው በግርምት አይቶኝ:-

"ቀልጣፋ ትመስያለሽ" አለኝ:: እንዲህ ሲለኝ ድንብርብሬ ወጥቶ ሳላመሰግነውም ዝም ብዬ ቆምኩ:: "የታለ ማስረጃሽ?" ሲል እጅ እጄን አየ::

"እ? ይኸው" ብዬ በመፅሄት ውስጥ የያዝኩትን የ10ኛ ክፍል ካርድና በሽያጭ ሰራተኛነትና ማስታወቂያ ሙያ የሰለጠንኩበትን ሰርተፍኬት ሰጠሁት::

"ለምን ኮፒ አላደረግሽውም?"

"ቸኩዬ ስለነበር ነው:: አሁን ላድርገው?"

"ምን ችግር አለው እኔ ጋ ቢያድር?"

"እ? ምንም ችግር የለውም::"

"በቃ ጠዋት ነይ" ብሎኝ ሲሄድ ፈዝገኜ ቀረሁ:: ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞር ነጋ:: *ዋናውን ማስረዳ ሰጥቼው ሰባሆሁም ቢሰኝስ? ቢጥሰውስ?* እያልኩ:: ጠዋት ነጋ አልነጋ ብዬ ቢሮ ስሄድ ገና አልገቡም:: ትንሽ እንደቆየሁ ፀሀፊዋ በመግባቷ ውስጥ ሆኜ ጠበቅኩ::

"ምነው በጠዋት መጣሽ?" አለኝ ቢሮው ከዘለቅኩ በኋላ:: ወዲያው ምን ብዬ እንደምመልስለት እያሰብኩ እያለ:- "ለስራው ጉጉት አለሽ ማለት ነው?" ሲል ጠየቀኝ::

"አዎ" አልኩት:: ከውስጤ ፈንቅሎ የወጣ እውነት ነበር:: ለህይወቴ ነፃነትና ዋስትና አብሳሪ ለሆነ ስራ ያልጓጓሁ ለምን ልጓጓ ኖሯል? አንዲት የሽያጭ ሰራተኛ ማሟላት ያለባት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ጠየቀኝ:: ደንበኞችን በአግባቡ ማስተናገድ፣ ስለምትሰራው ስራ ጥልቅ እውቀት መኖርና ከሰው ጋር ፈጣን መግባባት ሊኖራት እንደሚገባ ነገርኩት::

"አንቺ እነዚህ አሉሽ?"

"አዎ... አሉኝ ብዬ አስባለሁ"

"ምን ማለት ነው አስባለሁ?"

"አይ... ስለራሴ አጓጉል ነገር እንዳልናገር ነው" ስለው ሳቀ::

"ቅልጥፍናሽን ወድጄዋለሁ:: ሀሳብሽን የመግለፅ ጥሩ ችሎታም ያለሽ ትመስያለሽ:: ለማንኛውም ከነገ ጠዋት ጀምሮ ስራውን መጀመር ትችያለሽ" ሲለኝ እንደፌንጣ ዘልዬ ጉልበቱን ልስም ሁሉ ቃጥቶኝ ነበር:: ይሄ የቢሮ ስነ ምግባር አለመሆኑን አስቤ ደስታ እያቁነጠነጠኝ እዛው ቁጭ አልኩ::

"መሄድ ትችያለሽ" ሲለኝ ደነገጥኩ:: *ማስታወቂያው ላይ ደሞዝ በስምምነት ነው የሚለው:: ስለደሞዙ ሳይነግረኝ እንዴት እሄዳለሁ?* ስል ሀሳብ ገባኝ::

"ምነው የቀረ ነገር አለ?" ሲል ጠየቀኝ::

"አይ... ስለደሞዙ አልተነጋገርንም ብዬ ነው" አልኩት ችግሬን በማያሳብቅብኝ ሁኔታ::

"ፀሀፊዋ ስለሁሉም ነገር ታብራራልሻለች:: አሁኑኑ የውል ስምምነት ትፈራረሚያለሽ:: ከኔ መስማት ፈልገሽ ከሆነ በወር የምከፍልሽ ሶስት መቶ ብር ብቻ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የትራንስፖርት ስልሳ ብር ይኖርሻል:: በሽያጭ ስራው ላይ በምታገኚው ውጤት ሁሉ 15% ኮሚሽን እንከፍልሻለን" አለኝ:: እኔ ቶሎ የታየኝ ሶስት መቶ ስልሳ ብር የሚለው ነው:: ኮሚሽኑ በደንብ ስላልገባኝ ፀሀፊዋ እንድታስረዳኝ አደረግኩ:: የገባኝ ነገር ቢኖር የእኔ ጥረት ከታከለበት የወር ደሞዜ በትንሹ ከ5 መቶ ብር ያላነሰ ሊሆን እንደሚችል ነው:: ግን የእኔ ብቃት ነው ነገሩን

የሚወስነው::

በበነጋው ለአለባበሴ ተጠንቅቄ ወደ ቢሮ ሄድኩ:: በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የተስተካከለ ሙሉ ሰው የሆንኩ ያህል ተሰማኝ:: ይሁንና ምን ስራ እንደምታዘዝ ስላላወቅኩት ፍርሀት እያንዘረዘረኝ ነበር:: *ባቃቸሰውስ? ቢከብደኝስ?* ስል:: ቢሮ ስገባ የጠበቀኝ ስራ አልነበረም:: ድርጅቱ ለሚሰራቸው ስራዎች ወደ ተለያዩ ድርጅቶች በመሄድ እንዴት ማሳመን እንዳለብኝ የሚገልፅ መመሪያ ሲሰጠኝ ቆየ:: ለሶስት ቀናት በደንብ ከሞሉኝ በኋላ ስራውን በተለያዩ ቦታዎች መስራት ጀመርኩ:: በሚያሳዝን ሁኔታ ለአንድ ወር ያህል ምንም ውጤት ሳላስመዘግብ ዝም ብሎ ጥረት ብቻ ሆነብኝ::

ወር ላይ ደሞዝ ሲሰጠኝ ስራውን ለመልቀቅ ወስኜ "በቃ ላቆም ነው ስራውን" አልኩት አለቃዬን::

"ለምን?" ሲል ተገርሞ ጠየቀኝ::

"አንድ ወር ሆነኝ ምንም ውጤት አላመጣሁም" አልኩት:: አያይዤም:- "ያለ ውጤት ደሞዝ መቀበል ደሞ ይከብዳል" ስለው ሳቀብኝ::

"ተቀመጭ ሰናይት!" አለኝ በቁሜ የማወራው ያልጣመው መስሎ::

"ጠዋት ከቤትሽ ስትወጪ ምን እያልሽ ነው የምትወጪው?"

"ምንም... አልገባኝም"

"ብዙ ጊዜ በፍርሀት ነው አይደል የምትወጪው? አይሳካልኝ ይሆናል ብለሽ ትጨነቂያለሽ አይደል?"

"አ... ዎ" አልኩት እንዴት እንዳነበበኝ ገርሞኝ::

"እኔ እንዳንቺ አንድ የማስታወቂያ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ አይደለም ስራ የጀመርኩት:: ኮሚሽን 20% ብቻ ነበር የሚከፈለኝ:: ሶስት ወር ሙሉ ሰርቼ ምንም ማስታወቂያ ባለማግኘቴ ተስፋዬ ተሟጦ ነበር..." ሲል ከዛ በኋላ ስላስመዘገበው ስኬት እየነገረኝ ገና ከጅምሩ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብኝ መከረኝ::

"ጠዋት ስትወጪ ስኬታማ እንደምትሆኚ አስበሽ ውጪ:: በፍፁም አልችለውምና አይሳካልኝም አትበይ:: የብዙ ሴቶች ችግር ፍርሀትና አልችለውም የሚል ተስፋ መቁረጥ ነው:: አንቺ ከማንኛውም ሰው አታንሺም:: ይህ ሙያ ደግሞ ጥሩ ማግባባት እንጂ ሌላ ልዩ ችሎታ አይጠይቅም:: ሁለተኛ ተስፋ ስትቆርጪ ማየትም ሆነ መስማት አልፈልግም" አለኝ::

ከቢሮ ከወጣሁ በኋላ ምክሩ ሲያቃጭልብኝ ነበር የቆየው:: በተቻለ መጠን በመከረኝ መሰረት ጠዋት ገና ስወጣ እንደሚሳካልኝ እያሰብኩ መውጣት ጀመርኩ:: ለእኔም በገረመኝ ሁኔታ ሁለተኛው ወር ላይ የሶስት ሺ ብር ስራ አገኘሁ:: ጠቅላላ ሁለተኛው ወር ላይ የተሰጠኝ ሰባት መቶ ምናምን ብር ነበር:: ደስታ አንቆ ሊገለኝ ደረሰ:: ያውም



Scanned by CamScanner

ግማሽ ቀን ብቻ እየሰራሁ ያን ያህል ብር በማግኘቴ ደስታዬ ወደር አልነበረውም:: "አየሽ አይደል ምን ያህል እንደተለወጥሽ?" አለኝ አለቃዬ:: ያኔ አፌን ሞልቼ ምስጋና አቀረብኩ::

የማገኘው ገንዘብ ኑሮን ያለስጋት መምራት እንድችል ቢረዳኝም የእኔ ነፍስ ጥሪ በሙዚቃው ላይ በመሆኑ ከአብዱራህማን ይማም ጋር ተዋውለን የራሴን ሙሉ ግጥምና ዜማ ለመስራት ወደማጥናቱ አዘነበልኩ::

በተለይ የለቀቅኩት ነጠላ ዜማና ከአንድ የኦሮምኛ ድምፃዊ ጋ በአጃቢነት የሰራሁበት ስለ አትሌቶች የተዘፈነ ዘፈን በጥቂቱም ቢሆን ከሰው ጋር አስተዋውቀውኛል ብዬ አምናለሁ::

*♬ በጋ ገመዳን*

*በጋ ሚሰ ከፍተን*

*ገመቹ ኬሳኒ*

*ገመቹ ኬሳ*

*ሰተሌቶተ ኬኛ*

*ሚርጋን በተኒ*

*ሚርጋን ገሰተኒ*

*ስንጂ ፈተኒ*

*ስበበ ገመኒ ♬*

(♫የእናንተ ደስታ የእኛ ደስታ ነው
አትሌቶቻችን ድላቸው ደስታችን ነው
እልል በሉላቸው♫) የሚል ትርጉም ያለው ስራ ላይ ነው አጃቢ ሆኜ የሰራሁት::

ወደፊት የራሴን ህይወት የሚገልፁና በእውነታ ላይ የተመረኮዙ ዘፈኖቼን ለህዝብ ስለቅ ከምታወቀው በላይ የእኔን ህይወት ለብዙ ሴቶች መድህንነት ማቅረብ ትልቅ ስራ ስለመሰለኝ ነው በአደባባይ... ማንም ሴት ደፍራ ልታወጣው የሚከብዳትን ታሪክ ላወጣ የወሰንኩት::

ከስልሳ በላይ የዘፈን ግጥሞች ያሉኝ ሲሆን ለሁለት መፅሐፍ የሚሆኑ ግጥሞችን ስርቼ ጨርሻለሁ:: ይሄ ሁሉ ሆኖም ታሪኬን ለህዝብ ሳቀርብ ነገ ትዳር ለመያዝ ባለኝ ጉጉት ላይ መሰናክል ሊሆንብኝ እንደሚችል፣ የሰው መጠቋቆሚያ ልሆን፣ ብዙ ችግሮች ሊደርሱብኝ እንደሚችሉ ሳላውቀው ቀርቼ አይደለም::

በየጓዳው ብዙ እኔን የመሰሉ ምናልባትም ከኔ የባሰ የመከራና ግፍ ስቃይ ሰለባ የሆኑ ሴቶች አሉ:: እያንዳንዳቸው የሚናገሩት የራሳቸው እውነት እንዳለ ይገባኛል:: ግን ሁሉም በደረሰባቸው ጥቃት መከራና ግፍ ሳቢያ ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ድፍረቱ ያጥራቸዋል:: እውቋ የሴቶች መብት ተሟጋች ጀርሜን ግሪር (Germain Greer) "The fear of freedom is strong in us" ብላለች:: ወደው አይደለም:: ግፍ፣ መከራው፣ ጭቆናውና በደሉ የሚፈጥርባቸው ፍርሃት ነው:: ሁላችንም ፍርሀትን



Scanned by CamScanner

ማሸነፍ መቻል አለብን:: *በአሸናፊነትና በተሸናፊነት መሀከል ያለችው መስመር እንደፀጉር የቀጠነች ከመሆኗ የተነሳ ስናለፍባትም ሆነ ቆም ስንልባት ስናስተውልም* የሚል አባባል አለኝ:: ከህይወት የተማርኩት ይህንኑ ነውና! በሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውም አይነት ጥቃት መቆም ይኖርበታል:: *በባህል፣ በሀይማኖት፣ በኢኮኖሚና በሌሎችም መሰል ሸፍጦች በሴቶች ላይ የሚፈፀም ግፍ ይቁም!* ብለው ለመብታቸው እንዲታገሉ እንደሻማ ልቅለጥና ለሌላው ብርሃን ልሁን ብዬ ነው ውሳኔ ላይ የደረስኩት::

ካልተሳሳትኩ አፌን ሞልቼ መናገር የምችለው... አንዲትም ኢትዮጵያዊ አደባባይ ወጥታ እንዲህ ያለውን ታሪኳን ተናግራ እንደማታውቅ ነው:: ደፍሬ አደባባይ መውጣቴና ያሳለፍኩት መከራና ስቃይ... ባጠቃላይ መራር ውጣ ውረድ የበዛበት ህይወቴ ለሌሎች አርአያ ሆኖ እንደሚያስተምር እምነት አለኝ:: እውነቴን ይፋ ለማድረግ... ይሄን ድፍረት ስለገለሰኝ እግዚያብሄር ምስጋናዬ ጥልቅ ነው::

*ኦ! ለምሳሌ የሴት ልጆችን የግፍ እንባ ለብስ!*



Scanned by CamScanner

# እንደመደምደሚያ

አብነት አካባቢ ቤት ተከራይቼ እያለሁ ከተዋወቅኳቸው ሰዎች አንዷ ስሚራ የምትባለው አንድ ነገር ሹክ ብላኝ ነበር:: የማንነቴን ጥያቄ የምመልስበት፣ ቁርጤን አውቄ የምቀመጥበት ቦታ እንድሄድ:: መጀመሪያ ላይ ነገሩን አልተቀበልኩም ነበር:: እየቆየሁ ግን *ሰውነቴን ማወቅ ስንድችል ከፈዳኝ ብሞክረውስ?* ስል አሰብኩና ጥንቆላ የሌለበት መንፈሳዊ ቦታ እንደሆነ ተሞልቼ ሄድኩ::

ሩፋኤል ሰፈር!

ወደ ግቢው ይዛኝ ገባች:: ፈራጇ ወዳለችበት ቤት ከመግባታችን በፊት ሲዳ የሚባል ቦታ አለ:: ትንሽ ቤት ሆኖ በመጋረጃ የተከለለ ሲሆን ሳር ተጎዝጉዞበታል:: በሩ ላይ የበግ ቀንድ፣ ሞራ ምናምን ተሰጥፏል::

ሄዳ ሲዳው ጋ አጎንብሳ መሬቱን ሳመች:: የፈለገችው የምታደርገውን ተከትዬ እንዳደርገው ነበር::

"አልስምም!" አልኳት::



Scanned by CamScanner

"ግድ የለም… ትችያለሽ" ስትለኝ በመጋረጃ የተከለለውን ስገልጠው መንፈሳዊ ስዕሎች ያሉበት ነው:: የጌታ ስዕል፣ የሚካኤልና የማርያም ስዕል:: ሰው ስለት የሚሳለው እዛ ገብቶ ነው:: እናም ሰዎች እየመጡ ሲዳው ጋ በመሳለም አልቅሰው፣ ተስለው፣ የያዙትን አስቀምጠው ነው የሚሄዱት:: ሴትየዋ ለገብርኤል፣ ለማርያም እያለች የዓመት በዓሎች ሲሆኑ አትሰራም::

ወደ መፍረጃ ቤቱ ለመግባት ወኔ አጥሮኝ እደጅ ቁጭ አልኩ:: ወዲያው ለቅሶዬን ለቀቅኩት:: *እዚህ ቦታ ምን ባደርግ መጣሁ? እግዚአብሄር እስካሁን እኮርኛለ እደደበ እንዴ?*

"መመለስ አለብኝ!" ብዬ ስል ተቆጣችኝ:: ሌሊት መጥተው ወረፋ የያዙት ሁሉ አፅናንተውኝ ፀሎት ተጀመረ:: አባታችን ሆይ ሲባል ደስ አለኝ:: *እደ መንፈሳዊ ቦታ ነው ማለት ነው* አልኩ:: አንዲት ዘፋኝና አንድ አትሌት እዛው ሳያቸው ተገርሜ ነበር:: መንፈሳዊ ቦታ መሆኑን ሳውቅ ግን ግርምቴን አነሳሁት:

ፀሎቱ ሲያልቅ መጀመሪያ ከአወልያ የተላካችሁና የነፍስ ጉዳይ ያለባችሁ ተባለ:: የእኔን መጨነቅ አይተው ስለነበር "የነፍስ ጉዳይ ነው… ቅድሚያ እሷ ትግባ" ሲሉ ገባሁ:: ልጅቱ ቆማ የምትለውን ሰማኋት:: እሷ ባለችኝ መሰረት ማለት ጀመርኩ::

"ገለታ ይግባህ ጌታዬ" ሴት ብትሆንም አንተ ተብሎ በጌታ ስም ነው

የምትገለፀው::

"ምስጋናው ለእግዚአብሔር ይሁን" የሚል ምላሽ ጆሮዬ ላይ ዋለ::

"የኔ ልጅ እንዲህ አይነት ቦታ ሄደሽ አታውቂም? የመጀመሪያሽ ነው?" የሚለው ድምፅ ተሰማኝ::

"የመጀመሪያዬ ነው" ስል አለቀስኩ::

"ምን ሆነሽ ነው የምታለቅሽው የእኔ ልጅ?" ድምፏን ብቻ የምሰማው ፈራጅ ጠየቀችኝ:: መልስ ሳልሰጣት በፊት "ቤት ውስጥ በድንገት ሳይታሰብ የሞተ ሰው አለ አይደለም?" አለችኝ:: ስለየትኛው ቤት እንደምታወራ ሀሳብ ሲገባኝ "የባለቤትሽ አባት ታንቀው አልሞቱም?" ስትለኝ ክው አልኩ:: ይሄ ክስተት እውነት ነው::

"ልክ... ነው" ድምፄ ሞተ::

"አዎ... መፅሀፉን ስገልጠው እንደዛ ይታየኛል:: ለመሆኑ ልጄ ምንድነው የሚያስጨንቅሽ?"

"እኔ... ቤተሰቦቼን አላውቅም... ቤተሰቦቼ እንዳሉና እንደሌሉ ለማወቅ ነው::"

"አይዞሽ የኔ ልጅ..." ድምፏ ጠፋ:: ትንሽ ቆይቶም መጣ:: "የኔ ልጅ...



Scanned by CamScanner

ያሳደገችሽ እናትሽ ላይ አዝነሽባታል:: አልተፋሽላትም:: እና ልጄ በጣም ትፈልግሻለች:: ነገ ጠዋት ሀምሳ ብር ለትራንስፖርት እንዲሆንሽ ይዘሽ ትመጪና ከሰው ጋር አድርጌ ሙት አናጋሪ እልክሻለሁ:: በቃልሽ መያዝ የምትችይ ከሆነ ደግ:: አልያ ግን ደብተርና ስክሪቢቶ ይዘሽ ትመጪና ሙት የምታናግሪበትን አፅፍሻለሁ:: ልጄ በጣም ጠንካራ መሆን አለብሽ:: የምታውቂው ምልክቷን ስታናግሪያት ታያለሽ:: እና ሄደሽ ትተፊላታለሽ:: እንዲህ ካደረግሽ ሚስጥሩን ትነግርሻለች:: እዛ ሆነሽ ብታለቅሺ ግን እንባ ይመልሳታልና ሚስጥሩን ሳታውቂው ነው የምትቀሪው"

"እንዴ? እሷ'ኮ ከመንግስት ላይ ነው የወሰደችኝ:: ምንም የምታውቀው ነገር የላትም!"

"የምልሽን ስሚ... ታውቃለች!"

"ነገ ነይና ትሂጃለሽ::"

እያለቀስኩ ወጣሁ:: *ሙት ለናጋሪ መሄድ ለለብኝ!*

ዙሪያሽወርቅ ስለቤተሰቦቼ ምንም እንደማታውቅ አውቃለሁ:: ሌላው ቀርቶ አለባቸው ተካ ያናገራት ወ/ሮ መሰሉ እንኳ ብትሆን የሚያሳምን ነገር ይመስላል:: መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ ዙሪያሽወርቅ ምንም አታውቅም...

በዛ ላይ ሙት ነጋሪ ቦታ ሄጄ በእነሱ ቋንቋ ፀልየው መንፈስ በማናገር ነው ዙሪያሽወርቅ ጋ የሚያነጋግሩኝ:: በነሱ ቋንቋ ነው ለእናቴ ስም ሰጥተው የሚጠሯት:: ስትመጣ ነጎድጓድ ሁሉ ይሰማል:: መሬቱ ይንቃነቃል:: እናቴ ስትሞት እየሳለች ከሆነ ከነሳሏ፣ ወይም ሳቋን የለመድኩት ከሆነ ከነሳቋ... ብቻ ከነምልክቷ ትመጣና ታናግረኛለች:: ካለቀስኩ ኪሳራ ውስጥ ነው የምወድቀው::

አልመች አለኝ!

"ልጅ እያለሽ እናቴ ትይ ነበር" ትለኝ የነበረችው ዙሪያሽወርቅ ስለቤተሰቦቼ ልታውቅ ትችላለች ብሎ ማሰቡ የማይመስል ነገር ሆነብኝ::

*ከእግዚያብሄር ጋር ድጋሚ መጣላት የለብኝም* ስል በበነጋው ሳልሄድ ቀረሁ::

ከቤተሰቦቼ ጋር እገናኝ ይሆናል የሚል ጭላንጭል ተስፋ ቢኖረኝም:-

*ሰኒ... ከዚህ በኋላ ሰኒ ነሽ:: የኋላ ታሪክሽን እርግፍ አድርገሽ ተተሽ ዛሬን ለነገ ብርሀን መኖር ያለብሽ!* አልኩ ለራሴ:: ወዲያውም የእኔ የዘላለም ምርጫ የሆነው የጂጂ ዘፈን ውስጤ ቁር እያለ ሲፈስ ተሰማኝ::

*♪ አፍሪካዬ እማማ... አፍሪካዬ እናቴ*

*እርስቴ*

*አልጠይቀውም አባቴን*



ሕፃናት [illegible] ውስጥ የደገቱው ጌሾስት [illegible]
ማን [illegible] ከየት እንደተገኘ [illegible]
[illegible] በምባው ወደ ሌላ ቁቋም
[illegible] ሀይወቷ አደጋ ላይ [illegible]...

እናም በ[illegible] አደጋ መራራና
አንገሽጋሽ የሕይወት ትግሏ ለግዜአብሔርን
የምታቀርበው [illegible] ልመና [illegible]
ሊቀ[illegible] [illegible] ሆኖ የሁሉም
ጊዜ እየሰራ [illegible] ማንም ትንፋሽ ሊል
የሚይደናገረው [illegible] ግሳልጠ [illegible]

[illegible] አስተያየቶች

[illegible]

[illegible] ነው። አዋቂ የወጋል። ከዝበ [illegible]
[illegible] ምን ልትሆን [illegible] እያስበ ያስገዛል።
ምኒልክ ጋዜጣ

[illegible] በዘመናዊ መልኩ ተደምሮ በምስጢር መልኩ የሚያልፍ ነው።
የአዲስ አበባ መስተዳድር መገናኛ
ብዙሀን ኤጀንሲ በኤፍ ኤም 97.1

[illegible] 26
PRICE US $9.99
ISBN 978-99944-803-1-